እስኪነጋ ድረስ

ከአሳዬ ደርቤ

መስከረም 2008 ዓ.ም

© በከፊልም ሆነ በሙሉ የማባዛት መብቱ የደራሲው ነው::

መስከረም 2008 ዓ.ም

ስልክ: 0914321846
ኢሜይል: assayederebe@gmail.com
ፌስቡክ: Assaye Derbie/
የፌስቡክ ገጽ: Assaye derbie-ወግና ግጥሞች

የሽፋን ስዕል: በብላታ ግራፊክስ

ማውጫ

1. ባልከፈልነው ሰማይ 8
2. እስኪነጋ ድረስ 9
3. እቃቃ 16
4. የልጅነት ሕልሞች 17
5. ቅጣት 45
6. ሚስቴ "ብሎክ" አደረገችኝ 46
7. እንክርዳድ 51
8. እጥረትና ክፋት 52
9. በትር 58
10. ከአምላኬ ጋር 59
11. ኮንፈረንሱ 66
12. ወደነፈሰበት 71
13. የአዲስ ዓመት እቅድ 72
14. ፍቅርና ፊልም 75
15. ፒፕል ዩ ሜይ ኖው 76
16. ተሰቅለህ ቅር 89
17. ድህነትና ምቀኝነት 90
18. እጦት 94
19. 'አካኪይ አካኪየቪች' 95
20. እንቆቅልሽ 100
21. ሼፍና ሹፈት 101
22. ከሂደት የፀዳ 105
23. ያገረሸብኝ ወቅት 106

24. የምትወደው ልብ ውስጥ 110
25. ድንጉላ 111
26. ቲፎዞ 125
27. አባትነትን በሕግ ስለማውረድ 128
28. አዞን 136
29. ግሎባል ዋርሚንግ 137
30. ጥፍርና ብእር 141
31. ሳቅ 142
32. ማነሽ ባክሽ? 146
33. ወልዳችሁ ቅመሱት 149
34. መታሰቢያ 155
35. ጨረርና ውሃ 157
36. አመድ የሆነው ብር 158

ምስጋና

ከፈጣሪ ቀጥሎ ባለቤቴን ቤተልሄም አያሌውንና ልጄን ኖቬል አሳዬን አመሰግናለሁ።

በመቀጠል መዘርዘር ከጀመርኩ በዚህ ውስን ገጽ ውስጥ ዘርዝሬ ልጨርሳቸው የማልችላቸውን የእኔን እና የባለቤቴን ቤተሰቦች አመሰግናለሁ።

ቀጥሎ ለዚህ መጽሃፍ መታተም ከፍተኛ የሞራል ድጋፍና እገዛ ያደረጉልኝን ሀብታሙ ስዩምን (ጌታ የስደት ህይዎትህን ይባርከልህ) አንተነህ ይግዛውን፣ ግሩም ተበጀን፣ አምሳል ደረበን፣ ደሳለኝ መለሰን፣ ሄኖክ ስጦታውን፣ ቢንያምን፣ ፍቃዱንና ሀሚዶን አመሰግናለሁ።

በመጨረሻ ከጅምሩ ጀምሮ ስታበረታቱኝና መጽሃፍ አሳትም ዘንድ ግፊት ስታደርጉልኝ የነበራችሁትን በአካልና በፌስቡክ የማውቃችሁን ጓደኞቼን ከወገቤ ጎንበስ ብዬ ምስጋናዬን እገልፃለሁ።

እኔንስ ማን ይሆን የሚያመሰግነኝ?

መግቢያ

"እስኪነጋ ድረስ" በምወዳቸውና ከዩኒቨርሲቲ ተማሪነቴ ጀምሮ ብዙ ዓመታትን በለፋሁባቸው ግጥሞቼ የታጀበ የአጫጭር ታሪኮች ስብስብ መጽሃፍ ሲሆን ግጥሞቹ በራሳቸው ጥሩ የግጥም መጽሃፍ መሆን ይችላሉ ብዬ አስባለሁ።አጫጭር ታሪኮቹም እንደዚያው።

እውነት ለመናገር ለእንጀራ ብዬ የምሰራው ስራ ፀሐፊ ለመሆን የሚያስችል አልነበረም። ውስጤ ያለ የኪነ-ጥበብ ፍቅር ባይኖር ኖሮ እንደምኖርበት ቦታና እንደምስራው ስራ ባህሪ በዚያው ጠፍቼ ልቀር እችል ነበር።

ሆኖም ግን አምላክ ለኔ የፈቀደው የህይዎት መስመር አለና ሲከፋኝም ሆነ ሲደላኝ ብሶቴንም ደስታዬንም የምገልጸው በጽሁፍ ነው።

ብዙዎቹን በተለያዩ ድህረ ገጾች የጻፍኳቸው ቢሆንም እንደገና አፍርሼና አስፍቼ ለመጽሃፍ እንዲሆኑ አድርጌ ሰፍቻቼዋለሁ።

ይሄን ለማድረግ ሰፊ ጊዜና ብዙ ልፋት ጠይቆኛል።

በኛ ሀገር ተጨባጭ ሁኔታ መጽሐፍ ማሳተም ቀርቶ መጽሐፍ መግዛት በራሱ ቀላል ነገር እንዳልሆነ ይታዎቃል። እኔም ይሄን ስራዬን ይዤ ስቀርብ በርካታ ውጣ ውረዶችን አሳልፌያለሁ። በመጨረሻ ግን የለፋሁበትን የመጀመሪያ ምጤን ተገላግዬ አቅርቤላችኋለሁ።

መልካም ንባብ

ባልከፈልነው ሰማይ

"ሰፈሬ፣አገሬ" እያልክ - ጦርነት አትቀሰቅስ፣
ኮከብህን ቁጠር - ፀሐይ ሙቅ ይልቅስ፣
"የኔ፣ያንተ" ብለን - ባልከፈልነው ሰማይ፣
የግልህን ኮከብ - የጋራህን ፀሐይ፣
አይከልክሉህ እንጂ - በዚች ቁሳዊ አለም
የግል ቤት ባለበት - የጋራ አገር የለም።

እስኪነጋ ድረስ

አብዱ ዲዮጋን ሆይ...
ከእስተሳሰብ ሁሉ
ከንቱ ምርማሬ ብላሽ ፍልስፍና፣
"ሰው አጣሁኝ" ማለት ከሰዎች ጎዳና፣
መንፈስ ቢሆን እንጂ...
አንተ በኩራዝ ዐይን የምትፈልገው፣
እስከ'ን ተንከሱ ፥ እስከ'ን ተሰጠው፣
እስከ'ን ከፋቱ ፥ እስከ'ን ድከመቱ፣
ሰውማ በሽ ነው ምልቷል በየቤቱ፣
ይልቅ ዲዮጋን ሆይ መናኛው ፈላሰፋ፣
እኛን ያሰቸገረን...
ሰው ባለበት አገር መብራት አየጠፋ።

የገንዘብ እንጂ የሃሳብ ችግር አለብኝ ብዬ አላምንም። ሃሳቤን ወደ ገንዘብ ለመቀየር ሳስብ ግን ቁልቁለቱ አቀበት እየሆነ ያዳግተኛል። ጽሑፍ ሕይወቴ ነው። ሰው ጋር ስጣላ እንኳን ጩቤ ከመምዘዝ ይልቅ ብእር ማንሳት ይቀናኛል። ሆኖም ግን መጻፍ ሳስብ ሃሳቤን የሚሰልብ ክስተት አሁንም፣ አሁንም ይፈጠራል።

ብእር ሳነሳ ባለሱቁ ሽምሱ "ዱቤህን ክፈል" ብሎ ወደ ቤቴ ይመጣል። ደሞዝ እንዳልወጣ ብነግረው እንኳን "እንግዲያውስ ሂሳቡን እንተሳሰብ" ማለት ያመጣል። እኔ ልጽፍ ስል አለቃዬ ስልክ ደውሎ የቃል ማስጠንቀቂያ ይሰጠኛል...እኔ ልጽፍ ስል መንግስት ኮረንቲውን ያጠፋል...እኔ ልጽፍ ስል ሚስቴ ድራማ የምታዳምጥበት

ሬድዮን ኳርቱ ይዛባል።

"ጫማ የለኝም ብለህ አትዘን እግር የሌላቸው አሉና" በሚል ፍልስፍና ስመራ የኖርኩ ሰው ነኝ። እግሬን ያጣሁ ቀን ደግሞ "እግር የለኝም ብለህ አትዘን እጅም እግርም የሌላቸው አሉና" እያልኩኝ በስሬ አንድ አካል እና አንድ ሰው እስኪቀር ድረስ ከመጽናናት ወጥቼ አላውቅም ነበር።

"ይሄን ፍልስፍና መከተሌን፣ የበታቾቼን መመልከቴን ያቆምኩ ዕለት ህይወቴ የሚያበቃላት ይመስለኛል" የሚል ስጋትም ነበረኝ። ሆኖም ግን ይሄ አስተሳሰብ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ እግሬ ላይ ከባድ የቁርጥማት በሽታ ከማምጣት ውጭ የተከረልኝ ነገር የለም። ለካ "የበታቾችህን ሁሌ ስትመለከት የበታችነትን አትራከት ታደርገዋለህ" የሚለው አመለካከት እውነታነት አለው።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተለይ መፃፍን ሳስብ ምቾትን የመፈለግ፣ ህብታም የመሆን ምኞት ያናውዘኝ ጀምሯል። ጩኸት ሲረብሸኝ፣ ድህነት ሲረብሸኝ፣ ቁንጫ ሲረብሸኝ፣ ጥገኝነት ሲረብሸኝ አይምሮዬ በንደት ከነበረበት ውድማ ተመንጥሮ ይወጣና እንደ ችቦ እየተንቀለቀለ መሆን የሚሻውን ለቅጽበትም ቢሆን ጠቁሞኝ ወደ ስርቻው ይወርዳል። ጭራ መቁላት ሲቸከኝ፣ በድህነት ውስጥ ራስን ማጣት እንጂ ራስን መሆን እንደሌለ ሲገባኝ፣ ህብታም የመሆን ስሜት ልቤን ይናኝበታል።

"ህብታም" ስልህ ሁሌ የበላዮቹን እያዬ ባለው ነገር መደሰትን እንደማያደርገው ማለቴ አይደለም... "ህብታም" ስልህ ቤት የገዛ ቀን መኪና ያላቸውን እያዬ፣ መኪና የገዛ ቀን ሌላ መኪና ያላቸውን እያዬ፣ ደሴት የገዛ ቀን አህጉር ያላቸውን እያዬ፣ የማይሞላ ልብና የማይሞላ ካዝና ተሸክሞ እንደሚኖረው ማለቴ አይደለም።

"ህብታም ስልህ" መክሊቱን ያወቀ፣ የህይዎት ግቡንና ፍላጎቱን የለየ ማለቴ ነው። እኔ "ህብታም" የምልህ በቃኝን የሚያውቀው አይነት ማለቴ ነው። አለ አይደለ የሚፈልገውን የሚያውቅ የሚፈልገውን የሚጠይቅ ያን ሲያገኝ ደግሞ ደስተኛ የሚሆነው አይነት ህብታም ማለቴ ነው።

ምን ዋጋ አለው! እኔ ግን የምፈልገውን ባውቅም፣ የምፈልገውን ብጠይቅም ፈጽሞ የህልሜን ማግኘት አልቻልኩም። ይሄን ስልህ "የምትፈልገውን ለማግኘት ጠንክረህ አትሰራም አንዴ?" ልትለኝ ትችላለህ። ሞክሬ ነበር። እንደ መንግስት ሰራተኛነቴ በቀን ውስጥ ለስምንት ሰዓታት ያህል አሮጌ ዶሴ ሳገላብጥ ብኖርም ከምስክር ወረቀት ውጭ ጠብ የሚል ነገር ማግኘት አልቻልኩም እንጂ።

ብቻ ምንም ይሁን ምን የምፈልገውን ባላገኝም የማደግ ምኞቴ ግን አልፎ አልፎ መለስ ቀለስ ማለቱን አይተውም። ለምሳሌ ከዚህ መናኛ የኪራይ ቤት ውስጥ ወጥቼ ከከተማ ወጣ ያለና ሀይቅ ዳር ላይ የተገነባ ቪላ እንዲኖረኝ አፈልጋለሁ። ግቢዬ ውስጥ እንደ ኡመር ኻያም ከዋክብትን የምመረምርበት አብዘርቫቶሪም ቢኖረኝ ደስ ይለኛል። የትምህርቱን ጉዳይ በልምድ ስለማመጣው አያሳስበኝም። መቼም የፈለገ ነገር ቢሆን የሰውን ባህሪ ከመመርመር ከዋክብትን መመርመር የሚከብድ አይመስለኝም።

ህብታም ብሆን የሙዚቃ መሳሪያ ገዝቼ ህዘኔንም ደስታዬንም ጢያኖ በመጫዎት፣ ሳከስፎን በመንፋት መግለጽ አፈልግ ነበር። አለ አይደለ በጊታር ድምፅና በበገና ድምፅ መጠዝም መስከንም እሻ ነበረ። በእድሜዬ ሙሉ እንደ ዘለሰኛና እንደ ዝናብ ድምፅ ልቤን የሚያረጋጋው ነገር አላገኘሁም። ማታ ላይ ዝናቡ የቤቴ ቆርቆሮ ላይ ሲያርፍ እንዴት እንደሚያለዝበኝ! ዝናብ ሲጥል መብራቱን አጠፋውና ሻማ ለኩሼ እየጮሁ መዝፈን እንዴት ደስ እንደሚለኝ!

ዝናብ ሲጥል ለንቅልፌ ይመጣል።
ዝናብ ሲጥል ልጅነቴ ይመጣል።
ዝናብ ሲጥል ሜንቀቴ ጎርፉ ጋር ተጠራርጎ ይሄዳል።

ህብታም ብሆን የዝናቡ ድምጽ እንድርቀኝ ስለማልሻ የሸከላ ከዳን ያለው ቪላ እንዲኖረኝ አልፈልግም። ህብታም ብሆን የቤቴ ጣሪያ ከዳኑ ቆርቆሮ ይሆንና ዝናብ ከሌለ እንኳን በምተኛበት ሰዓት ጣራዬ ላይ ውሃ የሚያፈስ "ስፕሪየር" እንዲኖረኝ አደርጋለሁ። ከዛማ በኋላ ጊታሬን ከተሰቀለበት አወርድና የ"Bob Dylan" ዘፈን እንዲህ እያልኩ እቀልጽላችሁ ነበር።

How many roads most a man walk down
before you call him a man?
how many seas must a white dove sail
before she sleeps in the sand?
yes,n' how many must the cannon balls fly
before they 're fore ever banned?
the answer my friend is blowin 'in the wind
the answer is blowin 'in the wind
yes how many years can a mountain exist
before it is washed to the sea?
yes,how many years can some people exist

before they're allowed to be free?
yes,'n how many times can a man turn his head
pretend that he just doesn't see?
the answer my friend is blowin 'in the wind
the answer is blowin 'in the wind.....

ቅንጦትንና ምቾትን አላውቃቸውም። ቤት ስከራይም ቤት ስመታም እጦቴ በግልጽ ይወጣል። ምቾትን በዋጋው እንጂ በጥራቱ መዝኜው አላውቅም።

በህይዎቴ አንድ ጊዜ የሆነ ድርጅት የሚገርም ሆቴል ውስጥ ለአንድ ቀን እስከ ድህነቴ የሚገርም አልጋ ይዘ አሳድሮኝ ነበር። ጸአዳ አልጋ ላይ ተኝቼ እዳዬን ስቀንስና ስደምር፣ "ይሄን ብር ለአልጋ ከሚከፍሉ ምናለ ለኛ ቢሰጡንና ለሁለት ሰው የመቶ ብር አልጋ ይዘን ባደርን" እያልኩ በአሰልጣኞቹ እንዝላልነት ስበሳጭ የአራት መቶ ብር አልጋ ላይ እንቅልፍ ሳይወስደኝ ሌሊቱ ነጋ። እንዲህ የሚያደርገኝ ድህነቴ እንጂ ምቾትን ጠልቼው አይደለም።

እያሰብኩ እተኛለሁ። እያሰብኩ እነቃለሁ።

ሀብታም ብሆን "ፀሐይ" የምትባል የሰማይ ማድያት ገደል ስትገባ ከቤቴ እወጣና ሰብ ባለው አሸዋ ላይ በባዶ እግሬ እየተራመድኩ፣ የሃይቁ ሞገድ ጥቁሩ አለት ጋር ሲጋጭ እያየሁ፣ ሰማያዊው ሰማይ ላይ ያንጣበበው ደመና ዝናብ በመሆንና ምንም በመሆን መሃከል በንፋስ ሲዋትት እያየሁ፣ የሃይቁ ዳርቻ ላይ ተቅበዝባዥ አንገት ያላቸው ነጫጭ ዳክዬዎች በመንጋ ሆነው እንደ አንድ ሲያስቡ እያየሁ፣ ውዷ ባለቤቴ ከልጇ ጋር ሀይቁ ዳርቻ ላይ ሆና ከርቀት በመንጠቆ አሣ ሲያጠምዱ እያየሁ....

ሀብታም ብሆን በነጭ ቀለም ያጌጠው የጽሁፍ ክፍሌ ውስጥ ዘና ብዬ፣ ከጀርባዬ ስርቅርቅ ያለ ሲምፎኒ እየሰማሁ፣ ሰፊውን የመስኮቴን መጋረጃ እገልጠውና የምወዳት ፍቅሬ ግቢያችን ውስጥ ባለው ፍጹም አረንጓዴ ሜዳ ላይ የምወደውን ልጇን ዥዋዥዌ ስታጫውተው፣ ከሀይቁ የሚነፍሰው ንፋስ የሚስቴን ጸጉርና ስስ ቀሚስ ቀምቼ ካልወሰድኩ እያለ ሲታገላት እያየሁ፣ አዳፋ ልቤን በፍቅሯ የምታጸዳልኝ አማልክቴን በሚዝ የታጀበ መወድስ እጽፍላትና ወደ መስኩ ጋር በመሄድ ፍጹም ሰላማዊ በሆነ የተረጋጋ ድምጽ፡-

በፍቅርሽ ጽድቅን ያገኘች ይቺ አድለኛ ውብ ነፍሴ፣
ነጭ ደመና ተሳፍራ "ቼ" ብላ ነበር ፈረሴ።
ታውቂያለሽ ካንች ጋር ስሆን
የልቤን ግዝፈት መጠኑን፣
እኔን ያዬ ቀን በርግኑ...
የፀሐይ አምላክ አፖሎ
ከሰረገላው መውደቁን።
ታዊቂያለሽ አይደልም ውዴ?
"ኦሊያድ" የሚሉት ደካማ፣
እናቱ ቀሚስ መግባቱን
ከሩቅ መምጣቴን ሲሰማ፣
ታሲታውሻለሽ ልአልቴ?
ደመና ጋልበን ስንጓዝ
ከከብ ከሰማይ ሰናረግፍ፣
ዜዬስ መብረቁን ታቅፎ
"እግሬ አውጭኝ" ብሎ ሲከንፍ፣
አቤት የልቤ ከፍታ
ምድሪቱን "ጦር አምጭ" ማለቱ!
አቤት የአስከንድር መረበሽ
የሔሪኩለስ ፍርሃቱ!
እኔን መፋለም ያማረው
ሻምላ መዞ 'ሚያወጣ፣
ተጠንቀቂልኝ ብርታቴ
አንቺን ገድሎ ነው ሚመጣ!
እግዜር ለሳምሶን ብርታቱን
ጸጉሩ ላይ ዘግኖ ሲሰጠው፣
ለኮልታፋው ሰው ለሙሴ
ሀይሉን በዱላው ሲያድለው፣
የኔን ጅግንነት አምላኬ
ባንች ውስጥ ነው ያኖረው።
አደራ ተጠንቀቂልኝ "ካሰዮጵያ"
ብርታቴ፣ ሀይሌ፣ ግዝፈቴ
አንቺን ሲገሉሽ ብቻ ነው
የሚቀነጠስ አንገቴ።
አደራ ተጠንቀቂልኝ...

... በማለት ላንዲት ቀን እንኳን በችግርና በጩኸት ምክንያት ፋታ በማጣት አድናቆትን ለማሻት የማላውቀውን ሚስቴን በመወዲስ አስፈነጥዛት ነበር።

ሰማዩ ቀለሙን ሲለውጥ፣ ምድሩ ላይ የሌሊት ወፍ ሲራወጥ፣ እንደ ቢራ ሆድን የማይቆዝር በስስና ሾጣጣ ብርጭቆ የተሞላ ቀይ ወይን እየተጎነጨሁ፣ ጭስ አልባ እሳት ደጇ ላይ ለኩሼ፣ ፎጣዬን ትከሻዬ ላይ ጣል አድርጌ፣ ሺላ ቤቴን ለልጇ ለቅቄ በከዋክብት መሃከል የነገሰችውን ሙሉ ጨረቃ እያየሁ፣ እቅፌ ውስጥ ሆና የምትናፍቀኝ ፍቅሬ ከፊቴ ሆና በረዣዥም ጣቶቿ የጢያኖውን ቁልፍ ስትነካካው ከጀርባዋ አንገቷ አካባቢ ያሉትን ስስና ላዛ ጸጉሮች በከንፈሬ እየዳበስኩኝ፣ በእንዲህ አይነት ሙድ ውስጥ ገብቼማ የጥበብ አድባር ተሳፍራኝ "አባቭ ዘ ከላውድ" በሚል አርዕስት ኦስካር የሚያሸልም የፊልም ስክሪፕት፣ የኖቬል ሽልማት የሚያስገኝ የድርሰት ሀሳብ ማፍለቅ ካቃተኝማ ይሄው በአስር ብር መወራረድ እንችላለን።

በመንደር ዙረት ከታጠረው ከብ ህይወቴ መውጣት ችዬ የሌላውን አለምና ማህበረሰብ ባህልና ቅርስ የማጠናበትን፣ በካርታ ብቻ የማውቃቸውን አገሮችን የመጎብኘቱን እድል፣ ከፈረንሳዩ ሎቭሪ ሙዚየም እስከ ፊርኦኖቹ መዲና፣ ከአክሱም እስከ ጎለጎታ፣ ከቲቤት እስከ ሀቫና፣ ከማውንት ኤቨረስት እስከ አፋር ስምጥ ሸለቆ የመቃኘት እድሉን ላግኝና እንደ ግርሃም ሃንኩክ ያለ ጥናት እንደ ዳን ብራውን አይነት ድርሰት መድረስ ካቃተኝማ ይሄው እንደ ልጅነታችን በጥብሻ እንወራረድ።

ይህ ሁሉ ዝባዝንኬ ለኪነ-ጥበብ ምቹ ሁኔታን ሳጣ የምቃዣው ቅዠት ነው።

ግን ለማሰብ እንጂ ለመሆን አልታደልኩም።

በእጦት በታጀበው ህይዎቴ ውስጥ አከራዬ በረንዳዬ ላይ እንጨት እየፈለጠብኝ፣ መንግስት ለዚሁም ሃሳቤ ማዕቀብ እየጣለብኝ፣ ሰላቢ ንፋስ የቤቴን ቆርቆሮ በባህርዛፍ ቅርንጫፍ እየደበደበው፣ የሚስቴን ጎስቋላ ፊት ባየሁ ቁጥር ከፍቅሯ ይልቅ እርጅናዋ ትዝ እያለኝ፣ በአንዲት ክፍል ቤት ውስጥ ታጥሬ.... እዛው ውስጥ ቡና እየተወቀጠ፣ እዛው ውስጥ ወጥ እየተሰራ፣ እዛው ውስጥ ልጇ እየተጫዎተ፣ እዛው ውስጥ ጥበብ የጠራው አባዋራ ሊድፍ እየታገለ፣ እዛው ውስጥ ሬድዬን እየተንሿሿ ስለማላውቀው ብርሃን ቀርቶ እንደ ፊዮዶር ደስቶቭስኪ ጨለምተኛውንም ጽሑፍ ለመጻፍ ሀብቱን ቀርቶ ጸጥታውንም ባላገኝም በዚሁ ሁኔታም ውስጥ ሆኜ ከመጻፍ አልቦዝንምና አስኪነጋ ድረስ የምከትበውን ብሶቴን ጀባ ብያችሁ ምናቤን እቋጫለሁ።

አላሳዝንም?
እኔ እኮ ሰገጥም እንደ አናንተ አይደለም፣
ሃሳብ ላብሰለሰል ሀይቅ ዳር አልሄድም፣
በአዕዋፍ ቅላጼ በአፀድ ሺቶ ትንፋሽ፣
ቤት መትቼ አላውቅም በጭራሽ...በጭራሽ፣
እኔ ልገጥም ሰል....
ሚስቴ ሽንኩርት ልስትፍ ቢላ ትሰላለች፣
የሻፈደች ድመት ፊቴ ተቀምጣ ጸጉሯን ታበናለች፣
እንቅልፍ ያጣ ልጇ ጎኔ ያላዝናል፣
የጠዘ አሳት አራት ሻማው ላይ ይጨሳል።
ይሄን ሁሉ ንቄ ይሄን ሁሉ ችዬ፣
ድመቷን አብርሬ ልጇን አባብዬ፣
ብእሬን አንስቼ እንደዚህ አላለሁ፣
የጨሰ አሳት አራት አሻግሬ አያየሁ።
አሳት አ-ራ-ት-ማ
አሳት አ-ራ-ት-ማ ሰርከ ሚቃጠሉ፣
ጠልተውት ይሆን ወይ?
እንደኔ መኖሩን አሳት አየበሉ።

እቃቃ

"እቃቃው ፈረሰ አባይ ደፈረሰ"
የኛ ልጅነትስ ወደ የት ፈሰሰ?
ወደ የት ደረሰ?
አሲዮ ቤሌማ የቤሌማ ጥጃ
ለምን እንዳስረጀን አላምቅንም እንጃ
አባይ ቢደፈረስ እኛ ብንነረምስ፣
መጃጃል ነው እንጂ
አ-ቃ-ቃ እንደሁ አይፈርስ፣
ሚስት ብናገባ ቪላ ብንገነባ
ልጆች ብንወልድ ኮሌጅ ብንገባ
ፖሊስ ሌባ ብንሆን አሸከርና አለቃ
ይሄ ሁሉ ብላሽ ይሄ ሁሉ አ-ቃ-ቃ
ውሸት... ውሸት... ውሸት...
"እቃቃው ፈረሰ!"
"ዳበው ተቆረሰ!" ብሎ መለያየት
ሰው ካፈር ታንጾ ለአፈሩ ካልበቃ
ልጅነት ቀረ እንጂ አይፈርስም አ ቃ ቃ።

የልጅነት ሕልሞች

ከእለታት አንድ ቀን እናቴም ተኝታ ነበር። በእንቅልፍ ልብም ውስጥ ሳለች የሆነ መንፈስ ወደ እሷ የቀረበ መሰላት። እንዲህም አላት። "ልጅ ትወልጃለሽ መጠሪያውንም አሳዬኸኝ ትይዋለሽ... እሱም ሲያድግ ባንድ ሚስት እና ባንድ መንግስት ተወስኖ የሚኖር ጭቁን ይሆናል" አላት።

እናቴ ይሄን ስትሰማ በርግጋ ተነሳች። ስትነቃም አባቴን ከጓኗ ተጋድሞ አገኘችው። በራዕይ የሰማችውን ነገር የተናገረው አባቴ ይሁን መንፈስ ማረጋገጥም ተሳናት።

ትንቢቱም ተፈጸመና ቀኑ በታሪክ ባልተመዘገበ ዓመተ ምህረት ግራ እጇን አስቀድሜ ከማህጸን በማውጣት "ኢትዮጵያ ትቅደም" የሚል መፈክር አሰምቼ ወደዚች መሬት ዱብ አልኩኝ። ከእኔም መወለድ ጋር ተያይዞ ከተከሰቱት ተአምራቶች አንዱ የአባቴ አሮጌ ጋቢ ለሽንት ጨርቅ አገልግሎት ይውል ዘንድ ለሰባት መሸርከቱ ነው።

*****

ሰዎች ስለ ልጅነታቸው ሲያወሩኝ ስልቹ አይምሮዬ ነቃ ነቃ፣ ጥርሴ ፈገግ ፈገግ ማለት ይጀምራል። እኔም ብሆን ስለ ነገ ተስፋ፣ ስለ ዛሬ ኑሮ ከማሰብ ይልቅ ወደ ኋላ ተመልሼ ያለፈ ልጅነቴን እያሰቡ በትዝታ መከንፍ ደስ ይለኛል።

ብዙም በምኞት ውስጥ ሆኜ አላደኩም። ልጅነቴ "ማርና ወተቴ" የምለው አይነት ባይሆንም ከነቁንጫውና ከነፎረፎሩ እወደው ነበር።

አንደ እኔ አይነት የገጠር ልጅ ልጅነቱን የሚያስታውስ አእምሮ እንጂ ልጅነቱን የሚያስታውስ ፎቶ የለውም። ምክንያቱም የተፈጠርኩበት አገር በወቅቱ ከርስትና እንጂ ፎቶ የሚያነሳ ሰው አልነበረም። ለሚኒስትሪ እንኳን ፎቶ ለመነሳት ከሃምሳ ኪሎሜትር በላይ በእግር መጓዝን ይጠይቀን ነበር። እንደዚያም ተጉዘህ እድለኛ ካልሆንክ የተነሳኸው ፎቶ "ተቃጠለ" ልትባል ትችላለህ።

በእኔ የልጅነት ዘመን ሁሉ ነገር ከብር ነበረው። የቴክኖሎጅውማ ባይነሳ ይሻላል። ወደ ኋላ መለስ ብዬ ስለ ቴክኖሎጂ ሳስብ ከአጎቴ ቴፕ ውጭ የሚመጣልኝ ነገር የለም። ገጠሩን ተውትና ከተማም ቢሆን ቴክኖሎጂ የሚባለው ነገር በተናጠል እንጂ እንዲህ እንደ ዛሬው ባንድ ሞባይል ውስጥ ፎቶ ካሜራው፣ ቴፑ፣ ቴሌቪዥኑ፣ ጌሙ፣ ቪዲዮ ካሜራው፣ ኢንተርኔቱ፣ ስልኩ፣ ካልኩሌተሩ፣ መጽሃፉ ታጭቆ አይገኝም ነበር። ዛሬ ህጻናቱ ሁሉ ላፕቶፓቸውን አዝለው ተች ስክሪን ሞባይላቸውን እያንሸራተቱ ሳያቸው ይገርመኛል። በኛ ጊዜ እኮ ሌላውን ተውትና የጨርቅ ኳስ እንጂ የላስቲክ ኳስ እንኳን ከትምህርት ቤታችን ውጭ አልነበረም።

እንደዚያም ሆኖ ደስተኛ ነበርን። በአካል መኪና አይተን ባናውቅም ከጫማ ቀለም ቆርቆሮና ከሽቦ መኪና ሰርተን ከመዝናናት ቦዝነን አናውቅም። ፎቶ ካሜራ ባይኖርም ከጭቃ የተሰራ ካሜራ አዘጋጅተን እቃቃ ስንጫዎት ጓደኞቻችንን አጋብተን ፎቶ ስናነሳ እንውል ነበረ። ዛሬ በቴክኖሎጅ ዘመን ከተፈጠረው ልጂ ይልቅ እኔ ደስተኛ ነበርኩኝ። እሱ የኮምፒውተር ጌም ሲጫወት፣ ኢንተርኔት ሲጎረጉር እንቅልፍ የሚያጣውን ያህል በኔ የልጅነት ዘመን የነበረው ቁንጫ እንቅልፌን የመንሳት አቅም አልነበረውም።

*****

ወደ ኋላ ተጉዤ አስተዳደጌን በትዝታ ስጎበኘው ሁለት የቂጠቹን ጉንጮች ገልጦ የሚያሳይ የፑሊስተር ቁምጣ የለበሰ፣ በባዶ እግሩ የሚጣደፍ፣ ጭንቅላቱ በፎረፎረ የቦለሰ፣ ጨዋታ የሚወድ ልጅ ፊቴ መጥቶ ድቅን ይላል።

ጫማ ስለሌለኝ እንቅፋት በሚባል መብረቅ ከአስሩ የእግር ጣቶቼ ቢያንስ ሶስቱ አደጋ ደርሶባቸው እንደ አብድ ዱላ በጨርቅ እና በክር የተተበተቡ ነበሩ። አቤት እንቅፋት ሲወደኝ! ስሄድ የመታኝ ድንጋይ ስመለስም ይደግመኛል።

ለምሳሌ በሰማይ ላይ የሚሄድ አውሮፕላን እንጋጥጬ እያየሁና እሱ ወደ ሚሄድበት አቅጣጫ እየከነፍኩ ሸሚዜን አውጥቼ በመዘርጋት፡-

"አውሮፕላን ጤና ይስጥልኝ፣

ልብሴ ላይ ብር ጣልልኝ!" እያልኩ ስለፈልፍ ድንጋዩ የእግሮቼን ጣቶች እንደ መዶሻ ያነግለኝና የአህያ አይነት የስቃይ ድምጽ አወጣለሁ። እናቴ ችግሩን ስለምታውቀው "ምን ሆንክ?" ብላ አትጠይቀኝም።

"የትናንቱን ጣትህን ነው ሌለኛውን?" ትለኛለች አንጀራዋን እያሰፋች።

"የትናንቱን ነው!" እላታለሁ በለቅሶየ መሃል አንጋጥጬ ፈጣሪዬን እየፈለኩ።

እንጀራ ከምታስበት ጨርቅ ቆርጣ የሚደማውን ጣቴን በመተኮስ.... እንኩሮ ካለ እንኩሮ... ከሌለ ደግሞ እንሳቻ አንጉታ በበርበሬ ትሰጠኝና እሷን ስቀማምስ ህመሙን እዘነጋውና፣ አፍታ ሳልቆይ የቆሰለ ጣቴን በጨርቅ አስርና ወደ ጨዋታዬ እመለሳለሁ።

*****

ያልተጫወትኩት የጨዋታ አይነት የለም። አድናመንቲ፣ ሰኞ ማክሰኞ፣ ድመት አይጤን ትብላ፣ እቃቃ፣ ቴምቦ፣ አኩኩሉ፣ ቢጥምህ፣ አሊቡም፣ ዲሞ-ሰመረ፣ መሀረቤን አያችሁ ወይ .....

ከሁሉም ግን ለድብብቆሽና ለእቃቃ ትልቅ ክብር አለኝ። እኒህ ጨዋታዎች ሳቢን በቁጥሬ ስር ለማዋል መልካም እድልን ስለሚፈጥሩልኝ በጣም እወዳቸዋለሁ። ከወንዶች ይልቅ ሴቶች ጋር ያለኝ ቀረቤታ ያይላል። በተለይ ሳቢ ጋር። በየጨዋታው መሃል ተፈጥሮ ያደለቻትን "ሪሶርስ" ሳትሰስት ትለግሰኛለች።

በጣም የምወደው ጓደኛዬ "ማሙሸት" ይባላል። እንደ ሴት ጸጉሩን ቅቤ መቀባትና እንደ አይጥ ሊጥ መብላት ይወድ ነበር። በተለይ የሰንዴ ሊጥ ነፍሱ ነው። ማሙሸት ጋር በጣም የምንዋደድ ጓደኛሞች ብንሆንም በሳሪ ጉዳይ ግን ብዙ ጊዜ ግጭት ይፈጠር ነበር። ሳቢን እሱም አብዝቶ ይወዳታል። በዚህም ምክንያት እሷ ጋር ገዝፎ ለመታየት ያላሳለሰ ጥረት ያደርጋል።

ከማሙሸት ቀጥሎ ያለኝ ጓደኛ "ምትኩ" ይባላል። ምትኩ የአናፂ ልጅ ሲሆን አባቱ እሱ እንደተወለደ አካባቢ ቤት ሲሰራ ከጣራ ላይ ወድቆ ሙቶበታል። ምትኩ ዝፍዝፍ ያለ አልጫ ፊት ያለው ሲሆን አይነ-ግቡ ያልሆነ ልጅ ነው። ይህ ልጅ ከጨዋታ ይልቅ አባቱ ትቶለት ያለፈውን መዶሻ በመጠቀም ጎባጣ ሚስማር በማቃናት ቁርጥራጭ ጣውላዎችን በማፈላለግ ቅሮጻ ቅርጽ መስራት ይወዳል። ከባድ

ዝናብ ጥሎ ያደረ እለት የጎርፍ መፋሰሻ ቦዮች ውስጥ እየዞረ ጎርፍ ያልወሰዳውን ሚስማሮች መልቀም ታላቅ ደስታ ይሰጠዋል። ብዙ ጊዜ መዶሻውን ይዞ ውሻ ያፈረሰውን የሰፈራችንን አጥር በራሱ ሚስማር ሲያድስ ነው የሚውለው።

ምትኩ ጨዋታ የሚችል ልጅ አይደለም። ጅልነትም ያጠቃዋል። ብዙ ጊዜ የበታችነት ስለሚሰማው እኛ ስናወራ ማድመጥ እንጂ ብዙም ማውራት አይፈልግም። እኔ ጋር አንስማማም። የተወሰነ አብረን ከተጫዎትን ሳንጣላ አንለያይም ነበር። ምትኩ በማያስቀናው ነገር ሁሉ የሚቀና አስተሳሰቡ ሁሉ ግራ የሚያጋባ ልጅ ነው። ለምሳሌ እንቅፋት እንኳን እግሬን አንግሎኝ በጣም ሲታዘንልኝ ካዬ እሱም ጤነኛ ጣቱን በጨርቅ አስሮ "እንቅፋት መታኝ" እያለ ያወራል።

*****

የሆነ ጊዜ ሳቢ እስኪብርቶዋን ጥላ እያባበልኳት እያለ ድንገት ምትኩ መጣና "ምን ሁናችሁ ነው?" አለን።

"የቤተሰብ ጉዳይ ነው አያገባህም!" አልኩት የጎሪጥ እያየሁት።

"አወቅኩብህ" በሚል አስተያየት ጉዳዩን ወደ ጾታዊ ትንኮሳ ሊያዞርብኝ ሲሞክር "የሳቢ እስኪብርቶ ጠፍቶ ነው" አልኩት የተለመደ የጅል ስራውን እንደሚያከናውን እርግጠኛ ሆኜ።

"ታድያ ለዚህ ለቀላሉ ነው እንዴ የምታለቅሽው? ባይሆን እስኪብርቶው ሲገኝ ቀፎውን ትሰጭኛለሽ" አለና አንዳች የሚያክል ምራቅ መዳፉ ላይ ተፋ። "አባጨጓሬ እስኪብርቶዬን ያገኘህልኝ እንደሆነ በቅቤ ለቅልቁ በለስ ቂጣ አመጣልሃለሁ" አለና ምራቁን በቡጢ ጠለዘው። ይሄ እንግዲህ ኮምፓስ መሆኑ ነው። ምራቁ ወደ ሰማይ ተፈናጠረ። ሳቁ መጣብኝ። ወደ ጎን ቢሆን ኑሮ የተፈናጠረው ምራቁ በተረጨበት አቅጣጫ ፈልጉ ሊለን ነበር።

"ሰይጣን ወስዶታል አይገኝም" አለና ትፋቱን ልብሴ ላይ ጠርጎብኝ ሸመጠጠ። ምትኩ ማለት እንዲህ ነው። ብልጠትም፣ ጨዋታም፣ ዝምታም የማያምርበት ልጅ ነው።

*****

ሳቢ የናፈቀችኝ እለት ድብብቆሽ እንድንጫዎት ግፊት አደርጋለሁ። ያኔ እንግዲህ የኔና የማሙሽት ፉክክር ይጀምራል። ይሄንንም ስለማውቅ አስቀድሜ

የቤት ስራዬን እሰራለሁ። ጨዋታው ከመጀመሩ በፊት ሳቢን "ሜንታ እንድትሆን" እነግራትና ተቧድና ትመጣለች።

"አባት፣ አባት"

"አቤት፣ አቤት"

"ከሜንታ ከረሜላና ከደስታ ከረሜላ"

"ሜንታ ከረሜላ" እላለሁ ማሙሽት ሳይቀድመኝ በፊት።

የኔ ውብ ሳቢቲ ፈገግ ብላ ወደ እኔ ትመጣና ከንዶቼ ስር ትገባለች። ማሙሽት ሁል ጊዜ ሳቢ ተቧድና በመጣች ቁጥር ለእኔ መድረሷ ጥርጣሬ እየፈጠረበት አንድ አይኑን አጥብቦ አርቆ ለማሰብ ሲሞክር ፊቱ ላይ ይታየኛል።

የራሱ ጉዳይ አልሰማውም።

ከዛ በኋላ ፍቅሬን ይዣ አንዱ ዛፍ ስር የካሽመሪ ሱሪዬን ማንገቻ አወርድና ሸንፈላዬን በእጄ ይዤ "ቶሎ በይ ሳይመጡ" እላታለሁ።

ማሙሽት ከርቀት ሁኖ "ኩኩ አትሉም እንዴ" እያለ ይጓጉራል።

ስራዬን እየሰራሁ"አልነጋም" እለዋለሁ።

"ምነው ዘላለም እንደመሸ በቀረ" ብዬ ያኔ የተመኘሁት ሳይሆን አይቀርም እንዲህ አገሪቱን አጨልሞ ያስቀራት።

"ይጣፍጣል!" ትለኛለች ሳቢዬ አይኖቿን እያርገበገበች።

"ያንቺም ማር ነው" እላታለሁ በሸንፈላዬ አየሩን እየቀዘፍኩ።

ትንሽ እፈገፍጋትና ማንገቻዬን ታጥቄ "ኩኩሉሉሉሉ" ብዬ እንደ ዶሮ እጮሃለሁ።

*****

ማሙሽት ጋር በሳቢ ጉዳይ ካልሆነ በቀር ልዩነት የለንም። ምትኩ ጋር ግን ከምንስማማበት የምንጣላበት ቀን ይበዛ ነበር። ለምሳሌ የሆነ ቀን መንገድ ላይ ከኮባ ጠመንጃ ሰርቼ በማንገት እየተንጎባለልኩ እንዳለ ምትኩ መጣና "እኛ ቤት እንሂድና ከጣውላ ጠመንጃ እንሰራ" አለኝ።

"ጣውላ የት እናገኛለን?" አልኩት የምወደውን የጣውላ ጠመንጃ ለመስራት እየጓጓሁኝ።

"እኔ ጋር አለ" ብሎኝ ወደ ቤቱ ሄደና ቁርጥራጭ ጣውላና ሚስማር ከመዶሻ ጋር ይዞ ተመለሰ። በርካታ የዛጉ ሚስማሮችን በከንፈሩ ነክሶ በመያዝ አንዱን ጣውላው ላይ ሰከና "ግጥም አድርገህ ያዝ" አለኝ።

እንደተባልኩት አድርጌ ያዝኩለት።

ሆኖም ግን የተባለው ጠመንጃ ቅርጹ ወንበር እየመሰለ ሲመጣ ተናድጄ "ለምን ትዋሻለህ?" አልኩት።

"ጠመንጃ ከወንበር ይበልጣል እንዴ?" አለኝ ጣውላውን እያስተካከለ።

"ተናደድኩ። ጠመንጃ ትሰራ እንደሁ ስራ! አለበለዚያ እንጣላለን!" አልኩት።

"የራስህ ጉዳይ ብትጣላኝስ ማን ያስብልሃል?" አለኝ።

"ና ግጠመኝ!" አልኩት ለጠብ እየተዘጋጀሁ።

"ፈሪ አደረከኝ ቤቴ በር ላይ የሰው ሰው የምገድል" አለኝና ከኪሱ ተጨማሪ ሚስማር አውጥቶ በከንፈሩ ነከሰ።

ዘልዬ ላዩ ላይ ጉብ ስልበት እሱም ኮሌታዬን ጨምድዶ በመያዝ እየተላፋን እንዳለ በአጠገባችን እያለፈ የነበረ ሰውዬ "አትላቀቁም እናንተ ባለጌዎች" በማለት እንደሚገላግል ሰው ካነቀን በኋላ እኔን በጉቶ እጁ በኩርኩም ሲቆጋኝ "ሃሃሃሃ" የሚል ድምጽ አሰምቼ ፈንጂ የወረደበትን ጭንቅላቴን በመዳፌ ሸፍኜ ቁጭ አልኩኝ። ቀጥሎ የምትኩን ፊት በሰፊ መዳፉ ከድን ሲያደርግበት "የሜዳው ሚካኤል ያለህ!" ብሎ ወደቀ።

"እናንተ የተረገማችሁ እርጉሞች! ደግሞ የእናንተ ጠብ ምንድን ነው? በሚስት ነው የተጣላችሁት በርስት?" እያለ በወደቅንበት ሲጨቀጭቀን ምትኩ ፊቱን የሸፈነው ጨለማ አለፍ አለለት መሰል ፈትለክ ብሎ ተነሳና ከሰውዬው ራቅ በማለት "እንዴ.ው የአባቴ አምላክ የሜዳው ሚካኤል እንዳለ እንዲህ እንዳጮልከኝ በጥፊ የሚያጮል ይላክብህ! ምን የተረገምክ ሰውዬ ነህ! እኛ ብንደባደብስ አንተ የመታኸንን ያህል መቼ እንጎዳ ነበር!" እያለ ሲያጨሰው እኔም ከወደኩበት ተነሳሁና "ልጅ ቢኖርህ እንዲህ አድርገህ አትማታም ነበር! ደግሞ አንተን ብሎ ገላጋይ!" በማለት ሰደብኩትና ወደ ምትኩ አቅጣጫ ሸሸሁኝ። ሰውዬው የወረወረው አንዳች የሚያክል ድንጋይ የእኛን

ያህል ፍጥነት አልነበረውም።

"ፊቴን እሳት አነደደበት አለኝ" ምትኩ መጣላታችንን ረስቶ። ፊቱ ከማበጡም በላይ ፍም መስሏል። የምትኩ አሪፍ ባህሪ ይሄ ነው። ቂም የሚባል ነገር አይዝም።

"አንተስ ጭንቅላትህ እንዴት ነው?" አለኝ ብብቱ መሃከል አንገቴን አስገብቶ ጭንቅላቴን እየዳበሰ።

"የጭንቅላቴ ህመም እንኳን ስለደነዘዘኝ ብዙም አይሰማኝም! ጆሮዬ ውስጥ ግን የሆነ ነገር እየጮኸብኝ ነው" በማለት መለስኩለት።

ከፍ ብዬ ሳስበው ምትኩን የተጣላሁት ያላግባብ እንደሆነ ገብቶኛል። እውነትም እሱ እንዳለው ከጠመንጃ በፊት ወንበር ይቀድማል። ከዛ በኋላ ነው ወይ "ወንበር ልቀቁ!" ወይ "ወንበር አለቅም!" ብለህ ጠብመንጃ ልታነሳ የምትችለው።

*****

ጥር ወር ሲደርስ አገሬ ታሸበርቃለች።

ህጻናቶች ረዣዥም ዘንጎችን ቆርጠን በማሸለምለም (በእሳት በመተኮስ) እናዘጋጃለን። አዝመራውም ተሰብስቦ ወደ ጎተራ ስለሚገባ ገባያውም ስለሚትረፈረፍ ሰው ሁሉ "እንቧ" ማለት ይጀምራል። ለአቅመ ትዳር የደረሱ ጉብላሊቶችና ወጣቶች መተጫጨት እና መጋባት ይጀምራሉ።

ከጥምቀት ዋዜማ ጀምሮ የፈረስ ግልቢያው፣ ሆታው፣ ጭፈራው፣ ገና ጨዋታው፣ ሁሉ ነገር ይደራል። የጥምቀት እለት ደግሞ የሜዳው ሚካኤል ታቦት ስለሚወጣ የአጎቴ ቴፕም ከበዓሉ ቀደም ብሎ መወልወል ይጀመራል።

በዚያን ጊዜ እኛ አገር አለቅጥ ጥበቃና እንክብካቤ ከሚደረግላቸው ነገሮች አንደኛው የሜዳው ሚካኤል ታቦት ሲሆን ሁለተኛው አጎቴ ቤት የሚገኘው ባለ ቢጫ መርገጫ ቴፕ ነው። የዚህን ቴፕ ያህል አገሪቱ አሉኝ የምትላቸው ቅርሶች እንኳን በቂ ጥበቃ የሚደረግላቸው አይመስለኝም።

ቴፑ ከሰር ሙሉ በሙሉ በላስቲክ ተሸፍኖ ከላይ ደግሞ ነጭ ዳንቴል ተደርቦለት ጠረጴዛ ላይ ይቀመጣል።

ዝነኛው አጎቴ "መቶ አለቃ ነኝ" ይላል። አንዳንዴ እንዲያውም መቶ አለቃ የሚለው ማእረጉ በሰዎች ዘንድ እየተዘነጋ መምጣቱን ያስተዋለ ጊዜ አንድ አጥር

ምጥን ያለች የፈጠራ ታሪክ ያዘጋጃል። "ይገርምሃል ሶማሌ ጋር ስንዋጋ ግራ ክንዴን በክላሽ ተመትቼ ወድቄ ሳለ ኮሌኔል ዳርጌ በሩጫ መጥቶ 'መቶ አለቃ' ብሎ የሚንዠቀዠቅ ደሜን በሽሚዙ ባያስርልኝ ኖሮ ይሄኔ የለሁም ነበር!" ብሎ ድንገት ሊያወራህ ይችላል። የዚህ ወሬ ፍሬ ሀሳብ መቶ አለቅነቱን ላንተ ማስታወስ ነው።

ነገሩን በልጅ አይምሮዬ ለማጣራት ሞከሬ ነበር። ግራ እጁ ላይ አንዲት እንኳን ጭረት ላገኝ አልቻልኩም። እንደ እኔ እምነት የአንቴ መቶ አለቅነት እና የዳርጌ ኮለኔልነት አጠራጣሪ ነው።

ስለ ቴፑ እናውራ።

የአንቴ ቴፕና የሚካኤል ታቦት እርስ በእርስ ይረዳዳሉ። ቴፑ እንዳይበላሽ ሚካኤል ይጠብቀዋል። የአመቱ ሚካኤል ሲከብር ደግሞ የአንቴ ቴፕ በዓሉን ውብ ያደርግለታል። እና ከጥምቀት ዋዜማ ጀምሮ እስከ ሚካኤል ድረስ ባሉት ሁለት ቀናት ግማሹ ሰው መምሬ አበራ የተሸከሙትን ታቦት፣ ግማሹ ሰው የኔ አጎት በማንገቻ ያንጠለጠለውን ቴፕ ተከትሎ ለሁለት ተከፍሎ ሲሄድ ያየ ሰው "ሁለት ታቦት ነው እንዴ ህዝቡ የሚያስገባው?" ብሎ ቢያስብ አይፈርድበትም።

አሁን ላይ ሆኜ ያን ጊዜ ሳስበው ጥላሁን ገሰሰ ራሱ የአንቴን ያህል ደማቅ ኮንሰርት ማዘጋጀቱ ያጠራጥረኛል። አንቴ በድንገት ካሴት ሊቀይር ሲቆም ህዝቡም አብሮ ይቆማል። በኩፍስ መንፈስ ውስጥ ሆኖ ካሴቱን እያገላበጠ መዳፉ ላይ መታ መታ ያደርግና የቴፑን አልማዝ በጋቢው ጠረግ፣ ጠረግ አድርጎ ያስገባዋል። የአንቴን ኩራት ስታየው የሰው ሳይሆን የራሱን ዘፈን የሚጋብዝ ሊመስልህ ይችላል።

ቤት ውስጥ ደግሞ በፓኮ ታሽገው ከቴፑ ጎን የሚቀመጡ ካሴቶች አሉ። በንጽህና ከነ ፖስተራቸው ተደርድረው ሲታዩ ውበታቸው ልዩ ነው። እንዲህ እንደፈለግነው ሙዚቃ ማድመጥ የለም። ባለ ድመቱና ስምንት ቁጥር ምልክት ያለው ላምባዲና ሳጥን ውስጥ ይቆለፍበታል። ሙዚቃ ለማዳመጥ ግደታ ወይ አመትባል መሆን አለበት ወይም ደግሞ የተከበረ እንግዳ መምጣት ይኖርበታል። ከዚህ ውጭ ግን አልማዙና ላምባድናው ስለሚያልቅ መጠቀም አንችልም።

ከፍ ብዬ ሳስበው መቶ አለቃው አንቴ ለአገሩ ካለው ፍቅር ይልቅ ለቴፑ ያለው ፍቅር ያይልበት እንደነበር ይገባኛል። ካሉትም ክቡር ካሴቶች አንዱ ከሚደመሰስ ደርግ አለኝ ብሎ የሚኮራበት "ሃያ አንደኛ ከፍለ ጦር" ቢደመሰስ ይመርጣል።

ይሄን ያልኩት ዝም ብዬ አይደለም። ኢሃአደግ ድል እያደረገች ስትመጣ አንቴ

ገጠር ሄዶ ዘመዶቹ ጋር ተደብቆ ነበር። በአዲስ አበባ በኩል የገባው የወያኔ ጦር ሬድዮ ጣቢያውን ሲቆጣጠር በበጌምድር በኩል የመጣው ጦር ደግሞ የአንቴን ቴፕ ከነ ካሴቱ ተቆጣጠረ።

ይህ ዜና ለአንቴ የደረሰው በየተራ ነበር። መጀመሪያ የደርግ ወታደር ሙሉ ለሙሉ መደምሰሱን ሰማ። "የራሳቸው ጉዳይ" ብሎ ተወው። ቀጥሎ በበጌ ምድር በኩል የመጣው ጦር ቴፑን ከቤት መውሰዳቸውንና የጥላሁን ገሰሰን ካሴት የሚያውቁበትን እናጫውታለን ብለው እንደደመሰሱት ሲሰማ "ደመሰሱት" የምትል ቃል አውጥቶ ሽጉጡን ሊጠጣ ሲል አባቴ ደርሶ ነው ያተረፈው እየተባለ ይወራል። ሆኖም ግን ከስንት አቤቱታና ምልልስ በኋላ የሜዳው ሚካኤል ረድቶት ቴፑን ማስመለስ ችሏል። እናም የጥር ሚካኤል ሲከበር ይሄ ቴፕ ለበዓሉ ድምቀት ከፍተኛ አስተዋጽ ያደርጋል።

እኔም ለበዓል በሚሰጠኝ ሺልንግ...የአስር ሳንቲም ሰባት ፍሬ የሚሸጠውን ጠጠር ከረሜላና የተለያየ ቀለም ያላቸውን ድቡልቡል ማስቲካዎች እገዛና ባንድ ጉንጬ ከረሚላውን፣ በሌላኛው ጉንጬ ማስቲካውን አስገባና ሳቢን "ፈረስ እንዳይድጥሽ ከኔ አትለይ" እያልኩኝ እጇን በመያዝ ስፈልግ ወደ ፈረስ ግልቢያው፣ ሲያሻኝ ወደ ሆታና ጭፈራው፣ አሊያም ደግሞ በህዝብ ወደ ተከበበው አንቴ ይዣት ስዞር ደስታዬ ወደር አልነበረውም።

*****

ማሙሸት ጋር ብንጣላ እንኳን ግፋ ቢል ብንኳረፍ እንጂ እስከ መደባደብ ደርሰን አናውቅም። ብዙ ጊዜ እንዲያውም አንዳችን ሌላ ልጅ ጋር ከተጣላን እንተጋገዝ ነበር። ከጓደኝነት አልፈን እንደ ወንድም ነው የምንተያየው። ሆኖም ግን በሳቢቲ ጉዳይ ስንጣላ በስውርም ቢሆን መጎዳዳታችን አይቀርም ነበር።

ለምሳሌ ከእለታት አንድ ቀን የምሰራውን ሴራ ማሙሸት እንደባነነብኝ ሳላውቅ የምወደውን "ድብብቆሽ" ጨዋታ ከመጀመሩ በፊት ሳቢን ጠራሁና "ከሙዝና ከብርቱካን ብለሽ ተቧደኝና ብርቱካን ሁነሽ ነይ!" አልኳት።

እንዳልኳትም ከሰዓዳ ጋር ተቧድና መጣችና "ከሙዝና፣ከቡርቱካን" አለች።

"ብርቱካን!" አልኩኝ ተሸቀዳድሜ። ማሙሸት "ሰራሁልህ" የሚል መልእክት ያለው በተንኮል የተመረዘ የትልቅ ሰው ፈገግታ አሳየኝ። ለካስ የኔን ሴራ እሱም ሰርቶት ኑሯል። ከርፈፍ እያለች ሰዷዳ ወደ እኔ ስትመጣ ሳቢ በፍራቻ እኔን እኔን

እያየች ወደ ማሙሸት ጋር ሄደች።

"ምን ትንከረፈፊያለሽ ነይ እንጂ!" አለ ማሙሸት በድል አድራጊነት ስሜት።

አይኔን ማመን አልቻልኩም። ከኔ ይልቅ ማሙሸትን መርጣ የሄደች ስለመሰለኝ ንደት ተሰማኝ።

"እኔ ብርቱካን አልፈልግም ጨጓራዬን ያመኛል!" ብዬ ለማፈር ሞከርኩኝ።

"ጨጓራህን ካመመህ እንደ እኔ አባት ሻሜታ ጠጣበት" በማለት ማሙሸት ሊያሾፍብኝ ሞከረ።

ትኩር ብዬ ሳቢን በንደት ሳያት "ታድያ ብርቱካን ነው የምሆነው ብላ ችክ አለችብኛ! እኔ ምን ላድርግ?" አለች ማልቀስ እያማራት።

"ደግሞ አንቺን ብሎ ብርቱካን" አልኩኝና ሰዓዳን በጥፊ ደረገምኳት።

ማሙሸት "አንተ ሳባ ጋር መሆን የፈለከው ለምንድን ነው?" ብሎ ደጋን እስኪሰራ ድረስ ከወገቡ ተቀልብሶ ሳቀብኝ። ይሄ ሰላቢ ሳቢን ከወሰዳት በሰላም እንደማይመልሳት ስለገባኝ ጨዋታው እንዳይካሄድ ቀውጢ አፍልቼ አፈራረስኩት።

እንዲህ አይነቱ ሰው ዛሬ ላይ ስልጣን ብጨብጥ ምን ሊከሰት እንደሚችል ሳስበው ራሴን ከፖለቲካው አሸሻለሁ።

*****

የዛን ቀን በሳቢቲ ምክንያት ጨዋታው ፈርሶ ስንለያይ ማሙሸትን ከባድ ቂም ቋጥሬበት ስለነበር አንዴት በስውር እንደማጠቃው ሳስብ ከርሜ በሳምንቱ "እንጫዎት" ብዬ ልጠራው ቤቱ ስሄድ ጸጉሩን እየተላጨ አገኘሁት።

"ጸጉርህን እየተላጨህ ሰው ከቆመብህ ምላጩ ቆዳህን ይቆርጥህና ደምህ ይፈሳል" የሚል አስማት ማሙሸት ራሱ አስተምሮኝ ነበር።

ጭንቅላቱ ላይ ቆምኩበት።

"እረ ቁጭ በል አንተ ሰው! ታስቆርጠኛለህ!" አለኝ

የተቀመጥኩ መስዬ ከጀርባው ቆምኩኝ።

"ቁጭ ብሏል እማዬ!" አላት ዞሮ ማየት ስላልቻለ።

"አቦ ዝም ብለህ ተላጭ! ምን አይነት መተተኛ የሆነ ልጅ አጋጠመኝ እባካችሁ!" ብላ እናቱ ተቆጣችው።

"እረ ሊያስቆርጠኝ!" ብሎ መቀመጤን ሊያረጋግጥ ዙሮ አያለሁ ሲል ጆሮው ላይ ሸረከተችው።

የት አባቱ! ሳቢ ጋር በተንኮል እንደነጠለኝ ራሱ ባስተማረኝ አስማት ድባቅ አድርጌው ሹልክ ብየ ከግቢያቸው ወጣሁ።

*****

በሳቢቲ ጉዳይ ላይ ምንም ድርድር የለኝም። በልጅነታችን "እከሌ ሚስትህ ናት" ስንባል መበሳጨትም ማልቀስም የተለመደ ነገር ነው። ምክንያቱም እንዲህ አይነት ነገር እንደ ብልግና ይቆጠር ነበር።

ይሄን ባህል ለመጀመሪያ ጊዜ ውድቅ ያደረኩት እኔ ነኝ።

"ሳቢን እወዳታለሁ! ሳድግም እንደ ሜዳው ሚካኤል ቤተክርስቲያን ሰፊ ቤት ሰርቼ አገባታለሁ" ብዬ አዋጅ አስነገርኩኝ።

ይሄን አዋጄን ለሰፈሩ ልጅ በሙሉ ምትኩ "ጉድ" እያለ ሲያወራቸው አላምን ሲሉት "ካላመናችሁ ሄደን እንጠይቀው" በማለት ምድረ ኩታራን ሰብስቦ ያስጠራኛል። እውነት ለመናገር ሀይሌ ገብረ ስላሴ እንኳን ያን ያህል ጋዜጠኛ ኢንተርቪው አድርጎት የሚያውቅ አይመስለኝም።

ሁሉም ባንድ አፍ "ሳባን ስለምወዳት ሳድግ አገባታለሁ ብለኻል አንዴ?" ይሉኛል።

"እዎ ብያለሁ" ስላቸው ሁሉም "የሜዳው ሚካኤል ያለህ! እረ ምኑ ባለጌ ነው!" በማለት ሲሳደቡና ሲስቁ ምትኩ ፊት ላይ የሚታይ እርካታ ለየት ያለ ነበረ። እኔ ግን ጭራሽ በሳቢ የሚመጣ ስድብ አያመኝም።

ከተወሰነ ጊዜ በኋላ እንዲያውም ህጻኑ ሁሉ አይኑን በኔ ገለጠና ሁልም የየራሱን ሚስት እየመረጠ አሳወቀ። እቃቃም ስንጫዎት ያንዱን ሚስት አንዱ ማግባቱ ቀረ።

*****

ሌላው ልጅነቴን ሳስታውስ በጣም ቀልቤን የሚነሳኝ ነገር የእንቅልፌ ጉዳይ ነው። አባቴ ከንዶች ላይ አንገቴን አሳርፌ፣ አባቴ ጭኖች መሃከል እግሮቼን አስገብቼ፣

ግንባሬ ላይ እየተነፈሰብኝ፣ የጀመርነውን ጸለት ሳልጨርሰው በፊት የሚወሰደኝ እንቅልፍ ከሞት የከፋ ነበረ።

ትልቅ እስከሆን ድረስ ሁሌ የምተኛው አባቴ ጋር ነበር። አባዬም የመጀመሪያ ወንድ ልጁ ስለሆንኩም በጣም ይወደኛል። አንዳንዴ እንቅልፉ ሳይመጣ "እንተኛ" ብዬ ወስውሼ በጊዜ ወደ አልጋችን እወስደዋለሁ።

ሳይንቲስቶች የማህጸንን ያህል ተስማሚ ቦታ ለሰው ልጅ አለማግኘታቸውን ይናገራሉ። ይሄን የሚሉት አባቴ ከንድ ላይ ስላለው እረፍትና ምቾት ኢንፎርሜሽን ሳይደርሳቸው ቀርቶ መሆን አለበት።

ፕ!!
አቤት! አባቴ ጭኖች መሃከል ያለ ተመጣጣኝ ሙቀት!
አቤት! አባቴ ከንዶች ላይ ያለ ምቾት!
አቤት! አባቴ ሰውነት ላይ የሚፈልቅ የአልባጥሮስ ሽቶ!
ሰወደው። እንደ አባብ ሰውነቱ ላይ ልጥፍ አልበታለሁ።

ከማንቀላፋቴ በፊት"አባታችን ሆይ" የሚለውን ጸለት ከአፉ እየተቀበልኩኝ በጋራ ማለት እንጀምራለን።

"አባታችን ሆይ"
አባታችን ሆይ
"በሰማያት የምትኖር"
በሰማያት የምትኖር
"ስምህ ይቀደስ"
ስምህ ይቀደስ
"መንግስትህ ትምጣ"
"እንቅልፌ መጣ" አለዋለሁ።
"መንግስትህ ትምጣ በል አይዬል የምልህ!"
"ኧረ እንቅልፌ እየመጣ!" አለዋለሁ ደረቱን መንከስ እያማረኝ።
"ታድያ እንጨርሰው እንጂ"
"ነገ እንጨርሰዋለን"

በሰላም የተጀመረው ጸለት በጸብ ሳይጠናቀቅ በፊት እንቅልፍ ስርቻው ውስጥ ወስዶ ይሸረኩተኛል። ማታ የወደኩ የምነቃው ጧት ደመኔወቹ ሲጮሁ ነው። አንዳንዴ እንቅልፌ ጥልቀት ስለነበረው አባቴ ጭኖች መሃከል ልሸናበት ሁሉ

እችላለሁ።

የሆነ ሊሊት ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ ከእንቅልፌ ነቃሁ። የቀሰቀሰኝ የከባድ መሳሪያ ተኩስ ነበረ። በተደናገጠ ሁኔታ ውስጥ ሆኜ "ምንድን ነው አልኩት?" አባቴን አጥብቄ እያቀፍኩት። የሆነ ጦር አሸንፎ አገሪቱን እንደተቆጣጠረ ነገረኝ። ከዛን ጊዜ ጀምሮ [illegible]ቹ አገሪቱን ብቻ ሳይሆን እንቅልፌንም ተቆጣጥረውት ቀሩ።

****

ልጅነቴን ሳስታውስ ከትምህርት ቤት ቅጥር ውጭ ያለውን ህይዎት ነው የማ[illegible]ደው። ትምህርት ቤት አንድ ወንበር ላይ ተለጥፎ ስድስት ክፍለ ጊዜ ማሳለፌ [illegible]ም ምቾት አይሰጠኝም ነበር። አልፎ አልፎማ የሚያስተምሩት ትምህርት [illegible]ናግረኝም ነበር። ለምሳሌ ሳይንስ አስተማሪያችን "እትዬ ሙሉ" ወደ ከፍላችን [illegible]ገባና የጅል ጥያቄዋን ትጠይቃለች።

"ተማሪዎች ጎመን ከየትኛው የምግብ ዘርፍ ይመደባል?"

"እኔ፣ እኔ ቲቸር" እላታለሁ እጇን ቅንድቧ ላይ ሰክቼ።

"እስኪ አንተ መልስ"

"ከሀይልና ሙቀት ሰጭ ነዋ!"

"ለዚህ ነው የቸኮልከው ሰነፍ!" ትለኝና ለሌላ ተማሪ እድሉን ትሰጣለች።

"እኔ እኔ ቲቸር"

"እሺ አንተ!"

"በሽታ ተከላካይ"

"በትክክል ተመልሷል! እስኪ አንዴ ሞቅ አድርጋችሁ አጨብጭቡለት" ስትል ግር ይለኝና "ታድያ ጎመን ሀይል ሰጭ ካልሆነ ማሙሸትና ምትኩ ጋር ትግል ስንጋጠም እንዴት ልዘርራቸው ቻልኩ?" በማለት አስባለሁ። ደግሞ የሚገርመው እኮ ጎመን በሽታ ተከላካይ ከሆነ አባዬ ጎመን በበላ ቁጥር 'አሜባዬ ተነሳ፣ ሆዴ ተነፋ' እያለ ሽንት ቤት የሚመላለሰው ለምንድን ነው?" የሚል ግርታ በውስጤ ይፈጠርብኛል።

*****

ከረምት ሁኖ ትምህርት ተዘግቶ ሰፈር ውስጥ አድናመንቲ የተባለ መተዛዘል

ያለበት ጨዋታ እየተጫወትን እንዳለ ማሙሸት በሩጫ ወደ እኛ መጣ።

"ምን ሆንክ ነው?" አልነው ልክ አጠገባችን እንደደረሰ።

"ቴሌቪዥኑ በአህያ ተጭኖ እየመጣ ነው አሉ! እንሂድና እንቀበል" አለን ደረቱን ይዞ እያለከለከ።

"ቴሌቪዥን ምንድን ነው? የትስ ሄደን ነው የምንቀበለው?" አለው ምትኩ ከኪሱ ውስጥ አንዲት የዛገች ሚስማር አውጥቶ እየደባበሰ። ቴሌቪዥን ምን እንደሆነ እሱም እንዳልገባው ነገር ግን የከተማው ህዝብ ንቅል ብሎ በመሄድ መምጣቱን እየተጠባበቀ መሆኑን ነገረንና ተሰብስበን ወደ ስፍራው አመራን።

ቦታው ስንደርስ ህዝቡ ግልብጥ ብሎ ወደ ከተማዋ ጫፍ በመውጣት ቴሌቪዥኑን ይዛ የምትመጣውን አህያ በጉጉት እየጠበቀ ነበር። አባዬንም ከአጎቴ ጎን ቁሞ አየሁት። አጎቴ የእሱ ቴፕ ዝና እንደተረት በሚወራበት አገር የበለጠ ቴክኖሎጂ መምጣቱ ምቾት የሰጠው አይመስልም።

ትርምስምሱን ብታዩት መሲህ እንኳን ቢመጣ ከዚህ በላይ አቀባበል ይደረግለታል ተብሎ አይታሰብም። ነገሩን ልብ ብሎ ለተመለከው "ሆሳእና" ይመስል ነበር። ኢየሱስን የተሸከመችው አህያ እንኳን የዚችን አህያ ያክል ኩራት ተሰምቷታል ብዬ አላስብም። አህያዋ ከመደሰቷ ብዛት "ከመንገዱ ላይ ዘወር በሉልኝ" ብላ ቃል አውጥታ ሳትናገር አትቀርም።

"ጂኒሬተሩና ዲሹስ የት አለ?" በማለት የህብረተሰብ ሳይንስ አስተማሪያችን ጋሼ አሰፋ ጠየቀና ከሁለት ቀን በፊት በበቅሎ ተጭኖ መግባቱን ነገሩት።

ይህ ሁሉ የተከሰተው አንድ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ለወጣቶችና ለሴቶች መዝናኛ ብሎ ቴሌቪዥን ለአውራጃችን በመለገሱ ነው። ጊዜውም የአፍሪካ ዋንጫ የሚካሄድበት ጊዜ ነበረ። ቴሌቪዥኑ ከአህያዋ ላይ ወረደና ወደተዘጋጀለት የክብር ማረፊያ ቤት ሲሄድ ከአህያዋ በቀር ሁሉም ሰው እንደ ታቦት አጅቦት ነበር።

ህዝቡ አንድ አንድ ብር አውጥቶ ለሊቀ መንበራችን በማሳየት "ቴሌቪዥኑን ሳታሳዩን ከዚህ ንቅንቅ አንልም!" ብሎ አመጸ። የቀበሌችን ሊቀ መንበር ጋሽ ጥላሁን "ቴሌቪዥን ለማየት አንደኛ ሰሃኑ መተከል አለበት፣ ሁለተኛ ጂኔሬተሩ መነሳት ስላለበት ዛሬ ምስል ያለው ነገር ማሳየት እንችልም" ብሎ ተናገር።

ያዳመጠው ሰው አልነበረም። "ያለ ምስል እንየው!" ብሎ ህዝቡ ችክ አለ።

አንድ አንድ ብር ከፈልንና ቴሌቪዥኑን ከካርቶኑ አውጥተው ካሳዩን በኋላ "አቧራ ይቦልበታል" ብለው መልሰው አስገቡት።

*****

ሰሃኑ እስኪተከል ድረስ ዞን ሄዶ ቴሌቪዥን የማየት እድሉን ያገኘው ጋሼ አሰፋ ከፍታ ቦታ ላይ ሆኖ ምንም የሚያስቸኩል ነገር አለመኖሩን ከገለጸልን በኋላ በቴሌቪዥን ሊታዩ ይችላሉ ብሎ የጠረጠራቸውን አንዳንድ ትዕይንቶች ገለጸልን። በተለይ "ሴትና ወንድ ግንኙነት ሲፈጽሙ ይታያሉ" ብሎ ሲናገር ህዝቡ በመጉረምረም "ስምንተኛው ሺ" መድረሱን ገለጸ።

ትንሽ ቆይቶ ሰሃኑን የሚተከለው ሳይንቲስት በበቅሎ ተጭኖ ወደ አገራችን መጣ። ሳይንቲስቱ አይኑ ላይ ግብደ ጥቁር መነጽር አድርጎ ነበር። በማግስቱ "ሰሃኑ የሚተከልበት እንጨት አምጡ" ስለተባልን አንድ የደን ማሳ ሙሉ በሙሉ በማውደም ማገርና አውራጅ ተሸክመን ከቦታው ደረስን።

የሰውዬው ሳህን የመትከል ችሎታ ለህብረተሰብ ሳይንስ አስተማሪችን ለጋሼ አሰፋ የሚዋጥለት አልሆነም። ሳይንቲስቱ ያለምንም እረፍት ሲጋራውን እያጨሰ ሰሃኑን እያዟዟረ ቀኑን ሙሉ ቦታውን ቢፈልግም ቴሌቪዥኑ ሊሰራ አልቻለም። "ኡፍፍ በምንም አይነት መንኮራኩሩን ላገኘው አልቻልኩም" አለ ከሁለት ቀናት ልፋት በኋላ።

"ሳተላይቱን ማለትህ ነው?" አለ ጋሼ አሰፋ በሳቅ እየተንከተከተ።

"ሳተላይትና መንኮራኩር ምን ልዩነት አለው? ይሄን ሰውዬ እባካችሁ ወይ ከፊቴ አጥፉልኝ፣ አለበለዚያ እኔ ልተውለትና እሱ ይስራው!" በማለት ሳይንቲስቱ ተቆጣ። ህብረተሰብ ሳይንስ አስተማሪያችን ጋሼ አሰፋ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲገለመጥ በአይናችን ለማየት ቢቃን።

ቀኑን ሙሉ ሳተላይቱን ቢፈልግም ሊያገኘው ስላልቻለ ምንም እንኳን ኳሱን ማየት ባይቻልም "በዴከ" የባህል ሙዚቃ ግን እንደሚያሳየን ሳይንቲስቱ በመናገሩ የቀበሌው ህዝብ ግልብጥ ብሎ አንድ አዳራሽ ውስጥ ሊገባ ይቅበጠበጥ ጀመር። የአዳራሹ በር ሲከፈት አጎቴ "በጅብ አይበላሽ" ጫማው ጎኔን በመርገጥ ጣጥሶኝ ገባ። በዛን ጊዜ የጎን አጥንቶቼ ስለተለመጡ አሁንም ድረስ ቅዝቃዜ ሲሆን ጎኔን ውጋት ይሰማኛል።

"ለወጣቶችና ለሴቶች መዝናኛ" ተብሎ የመጣውን ቴሌቪዥን አባቶቻችን

በቁጥጥር ስር አውለውት በሩን ዘግተው በቲሌቪዥኑ የሚታየውን የባህል ሙዚቃ በጭብጨባ ያጅቡት ጀመር። እኛ ብርድ ላይ ተጥደን ድምጹን ብቻ ስንሰማ አመሸን።

አጎቴ ቤት ያሉ ካሴቶች ሽፋን ላይ መልካቸውን በፎቶ የምናቃቸውን ዘፋኞች አባቶቻችን በቪድዮ ለማየት በቁ። አባዬ ቤት መጥቶ ያየውን ጉድ ሲነግረን በዘጠና አመቷ አይኗ የጠፋው አያታችን "ምነው አምላኬ በለጋ እድሜዬ አይኔን አጥፍተህ ይሄን ጉድ ሳታሳየኝ ትቀር!" ብላ ለማልቀስ ሞከረች። ዕይታዋ ብቻ ሳይሆን እንባዋም ከደረቀ ስለሰነበተ የምትስቅ እንጂ የምታለቅስ አትመስልም።

ሳይንቲስቱ "እዚህ ሀገር ሳተላይት የለም" ብሎ መግለጫ በመስጠቱ ጋሼ አሰፋ "እኔ የሚሰራ ሰው አመጣለሁ" በማለት በቅሎ ጭኖ ወደ ከተማ ተጓዘ። እሱ እስኪመጣ ድረስ ሁላችንም የባህል ሙዚቃውን የመመልከት እድሉን አገኘን። መቸም የተሰማን ደስታ በቃላት የሚገለጽ አልነበረም።

ጋሼ አሰፋ ሌላ ሳይንቲስት ይዞ መጥቶ ዲሹ እስኪሰራ ድረስ የአፍሪካ ዋንጫው ተጠናቆ ነበር።

*****

የሆነ ቀን ቅፍፍ ብሎኝ የቤታችን ካብ ላይ አንደተቀመጥኩ ማሙሸት የሚባል ጎደሎ መርዶ ይዞ መጣ።

"እንዴት ይሆናል" አልኩት ልቤ እየተርገበገበ።

"ሆነ እንጂ! ሳቢን የሚያገባትም ሰውዬ መጥቷል አሉ። ሰርጉም የመጭው እሁድ እንዲሆን ቤተሰቦቿ ተስማተዋል" አለኝ።

"ሰውዬው ምን አይነት ነው?" አልኩት።

""አንዳች የሚያከል ሽበቶ ነው" አለኝ በእጁ ትልቅ ከብ እየሰራ።

"ታዲያ ምን ብናደርግ ይሻላል?"

"ሰውዬውን እንደብድበው" አለኝና ሃሳቡን ተቀበልኩት። ለመጀመሪያ ጊዜ በአንድ ሴት ፍቅር የተለከፍን ሁለት ልጆች ሶስተኛ አፍቃሪን ለመደብደብ ቁርጥ ያለ ውሳኔ ላይ ደረስን።

ሰውዬው አዲስ አበባ የሚኖር ነጋዴ ሲሆን ሳቢን የሚያገባት በማደጎ ነው።

ቀኑን ሙሉ ስንጠብቀው አምሽተን ጀንበር ልትገባ ስትል ወደ እነ ሳቢ ቤት መጣ። ማሙሸት እንዳለው ሰውዬው ሽማግሌ ነው። እነ ሳቢ ቤት አምሽቶ ኒወጣ ይሄን ሽበቶ ጭንቅላቱን በድንጋይ ሰንጥቀን ልንጥለው ተስማምተን ደፍጠን እንጠብቀው ጀመር።

ሰውዬው እስኪወጣ ድረስ እነ ምትኩ አጥር ስር ተደብቀን ስንጠብቀው አመሸንና ከምሽቱ አንድ ሰዓት አካባቢ ባትሪውን እያንቦገቦገ ወጣ። ሁሊታችንም ባንድ ላይ የጨበጥናቸውን ድንጋዮች ወደ እሱ አቅጣጫ ወርውረን ወደ ቤታችን ሹልክ ብለን ገባን።

ይሄ ወሬ ቤተሰቦቻችን ጆሮ እንደ ደረሰ ጉዳዩን ማን እንደፈጸመው ማወቁ ለቤተሰቦቻችን ቀላል ምርምርን የጠየቀ ነበረ። ያኔ እንደ ዛሬው በርበሬ ውድ ማዕድን ስላልነበረ ሁሊታችንንም ቢጋራ አንድ ፈረሱላ በርበሬ አጠኑን። ሳቢንም ከመንጋጋችን ላይ መንጭቆ አይናችን እያዬ ወደ አዲስ አበባ ወሰዳት። ያኔ የተለያየን እስካሁን ድረስ አይቻት አላውቅም።

*****

ከረምት አልፎ መስከረም ሲመጣ ባንድ በኩል የዘመን መለወጫና የመስቀል መድረስ ደስታ ይሰጠኛል። በሌላ በኩል አሰልቺው የሰድስት ሰዓቱ ትምህርት መከፈቻው ስለሆነ ቅር ይለኛል።

ዘመን መለወጫ ከመድረሱ በፊት ከሰፈራችን ራቅ ወዳለ ጫካ በመሄድ ለችቦ የሚሆን "ከሴ" መልቀም እንጀምራለን። ጓጉሜን ወንዝ እየወረድን ገላችንን እንታጠባለን። እንቁጣጣሽ የምንላቸውን ሰዎች ስም ዝርዝር እንለያለን።ሴቶቹ ለአበባየሁሽ ወንዶቹ ለሆያሆዬ ጭፈራ እንዘጋጃለን። ቀለል ቀለል ላሉት የትምህርት አይነቶች ባለ አሰራ ስድስት ሉክ ደብተር ለሌሎቹ ደግሞ ባለ ሰላሳ ሁለት ሉክ ደብተር እንገዛና በስሚንቶ ወረቀትና በላስቲክ ማሸግ እንጀምራለን። ለአዲስ አመት አዲስ ልብስ ይገዛልናል። አቅም ያለው ቤተሰብ ለልጁ የካሽመሪ ቁምጣና ኮት ያሰፋል። የሌለው ደግሞ የፑሊስተር ልብስ ያሰፋል።

ልክ የመጀመሪያው ከፍለጊዜ ላይ የአምናውን ልብሱን የለበሰ፣ የአምናውን ጫማውን ያደረገ፣ የአምናውን መጽሃፍ የያዘ መምህር፣ የአምናውን ዱካክ የያዘ ከፍል ውስጥ ማስተማር ሲጀምር "ብርር" ብሎ መጥፋት ያምረኛል። ያውም ያን ጊዜ አብዛኛዎቹ መምህራኖቻችን ከኛ የተሻለ ልብስ ይለብሱ ነበር። አሁን ግን ከአለባበስ

አንጻር ተማሪዎቹ ሳይበልጡ አይቀሩም።

ስለ ትምህርት ቤት ሳስታውስ ቀድሞ ወደ አንጎሌ የሚመጣው የጋሼ አሰፋ ትዝታ ነው። የህብረተሰብ ሳይንስ አስተማሪያችን ጋሼ አሰፋ በሀያሉ ጥፊው ምክንያት ሁሉም ተማሪ የሚፈራው መምህር ነበረ። አንድ ቀን በዛ ሰፊ መዳፉ ጀሮህ ላይ ከው ካደረገብህ መምህራኑ የሚያስተምሩት ትምህርት ሳይገባህ ብቻ ሳይሆን ሳይሰማህም አሰራ ሁለተኛ ክፍልን ልትጨርስ ትችላለህ።

በምንም መልኩ ቢሆን "የሚዳው ሚካኤል ከበሮ የኛን ፊት ያህል ድብደባ ደርሶበታል" የሚል አመለካከት የለኝም። የድብደባው ምክንያት ከደሞዝ ጥያቄ ጋር የተገናኘ ይመስለኛል። እንዲያውም ፈርተን ተውነው እንጂ የሆነ ጊዜ ማሙሸት "ይሄ ሰውዬ ጨፍጭፎ ከሚገድለን ለምን ተማሪውን አስተባብረን ደሞዝ እንድጨመርለት ለርእሰ መምህሩ አናመለክትለትም" ብሎኝ ነበር። ያኔ ደሞዝ የሚጨምረው ርእሰ መምህር ይመስለን ነበር።

እርግጥ ነው በተቻለን መጠን ኑሮውን ለመደገፍ ጥረት እናደርጋለን። አንድ ወቅት ለተግባር ትምህርት እያንዳንዱ ተማሪ አንድ፣ አንድ እንቁላል ይዘን እንድንመጣ በነገረን መሰረት ያመጣናቸውን ሃምሳ እንቁላሎች ከሰበሰበ በኋላ "በሉል እና በእንቁላል ቅርጽ መሃከል የመጠን እንጂ የቅርጽ ልዩነት አለመኖሩን" ነግሮን እንቁላሎቹን ሲወስዳቸው "የት ደረሱ?" ብለን አለመጠየቃችን ድጋፍ ለማድረጋችን አንዱ መገለጫ ነው።

ጋሼ አሰፋ ህብረተሰብ ሲያስተምረን "ሳይንሱ መሬት ትዞራለች ነው የሚለው፣ ሀይማኖታችን ግን በተገላቢጦሹ ፀሐይ በምስራቅ ወጥታ በምዕራብ ትጠልቃለች ይላል! የሚያዋጣችሁን ግን እናንተ ታውቃላችሁ" በማለት አውላላ ሜዳ ላይ ጥሎን መሄዱ የለመድነው ነገር ነው።

የሆነ ጊዜ ደቡብ አፍሪካ የአፍሪካ ዋንጫ እያዘጋጀች በነበረችበት ሰዓት ስለ አለም አገራት ሉል እያሽከረከረ ሲያስተምረን ቆየና "ጥያቄ ያለው?" ብሎ ጠየቀን። ይህ መምህር ብዙ ጊዜ የምንጠይቀውን ጥያቄ በቃላት ከመመለስ ይልቅ እንደ አድማ በታኝ ፖሊስ በዱላ መመለስ ይቀለው ነበር።

"ከገደለኝም ይግደለኝ" ብዬ እጄን አወጣሁ።

"እሺ ቀጥል አጅሬው" አለኝ።

"ከእኛ አገር ይዞ እስከ ደቡብ አፍሪካ ያለው ምድር መንገዱ ቁልቁለት ነው

እንዴ?" አልኩት ለመሰደት ምቹ ሁኔታ እየፈጠርኩ። ሉል ላይ እንዳየሁት ከሆነ ቁልቁለት ለመሆኑ ጥርጥር አልነበረኝም።

"ለመቶ አምስት ብር ደሞዝ አንተ ጋር ስደርቅ እየዋልኩ መቼ አየሁት ብለህ ነው!" ብሎ ፊቴ ላይ በጥፊ ከድን አደረገብኝ። በጥፊው ሃያልነት የተነሳ የብርሃን ዋና ዋና ቀለማት ሰባት መሆናቸውን ፊቴ ላይ ከተፈጠረው ብልጭታ ቆጥሬ ለማረጋገጥ ቻልኩኝ።

ጋሼ አሰፋ የሚያናድደኝ መደባደቡ ብቻ አልነበረም። ከዱላ በኋላ ያለውን ተፈጥሯዊ የማልቀስና የማንከስ መብትን መንፈጉ ነው። ፊቴን እያሻሻሁ ስወጣ ጓደኛዬ ማሙሸት በር ላይ እየተቁነጠነጠ ሲጠብቀኝ አገኘሁት። ይሄን መምህር ከእኔ በላይ እሱ ይጠላዋል።

"አይንህን አሳበጠህ አይ�ዬል? አይኑ ይፍሰስና ይሄ ሰካራም!" አለኝ እንባ እየተናነቀው።

"አዎ" አልኩት እንባ ያቀረረ አይኔን በኮቴ ኮሌታ እየጠረኩኝ።

"ግን እኮ ዝም ብለህ ነው እንጂ ወደ ደቡብ አፍሪካ ያለው መንገድ ቁልቁለት፣ ወደ አውሮፓ ያለው መንገድ አቀበት፣ ወደ አረብ አገር ያለው ደግሞ አግድመት መሆኑን ጋሼ አሰፋን ሳትጠይቅ ካርታውን ብቻ በማየት ማረጋገጥ ትችል ነበር" አለኝ።

በሀሳቡ መስማማቴን ለመግለጽ ራሴን ወዘወዝኩለት።

"እኔ እኮ የሚያናድደኝ ወደ ደቡብ አፍሪካ መሄድ እንዴት እንደሚቻል የማያውቅ መምህር 'እኛ የምናደንቀው ወደ ጨረቃ የሄዱትን ሳይሆን ጨረቃ ላይ እንዴት መሄድ እንደሚቻል ያስተማሯቸውን መምህራን ነው' ብሎ ጉራውን መንፋቱ ነው" አልኩት ዐይኔን እያሻሸሁ።

"ጋሼ አሰፋ እንኳን ጨረቃ ላይ ቀርቶ ፎቅ ላይ እንዴት እንደሚወጣ አያውቅም" አለኝ ማሙሸት የጨርቅ ኳሱን ኪሱ ውስጥ እየከተተ።

*****

ከእለታት አንድ ቀን ጋሼ አሰፋ ምን እንደነካው አላውቅም "ዛሬ ግምገማ እንጂ ትምህርት የለንም። ከደብተራችሁ ላይ ወረቀት ጊንጥሉና በጽሑፍ ገምግሙኝ!" አለን። መቼም ይሄን ሃሳብ ያመጣው አረቂውን ጠጥቶ መሆን አለበት።

በዚያ ዘመን ከደብተሬ ላይ ወረቀት ስገነጥል አገር የገነጠልኩ ይመስለኝ ነበር። ግን ጋሼ አሰፋን ለመገምገም ስለነበር ከባለ አስራ ስድስት ሉክ ደብተሬ ላይ ያለምንም ርህራሄ አንዱን ሉክ ገነደስኩት። ማሙሸት "እንዳትለቀው" በሚል አኳኋን በእጁ ምልክት ሰጠኝ። እኔ ምን እንደምጽፍ እያሰላሰልኩ እንዳለ ተማሪው ሁሉ "ጋሼ እጅግ በጣም ጎበዝ መምህር ነህ በዚሁ ቀጥልበት!" የምትል የፍራት አስተያየት ጽፈው እጃቸውን ዘረጉ። "ይሄን አስመሳይ ህዝብ እጁን በሰይፍ መቅላት ነበር" ብዬ ተመኘሁ።

"እንደሱ አይደለም። የሚሰማችሁን በሙሉ ዘርዘር አድርጋችሁ ጻፉ። በተለይ ደካማ ጎኖቼ ላይ አተኩሩ። ነጻነት እንዲሰማችሁ ደግሞ እኔ እሄድላችኋለሁ። ስትጨርሱ ለሞኒተራችሁ ላኩ" የሚል በሀገሪቱ ላይ ከዚያ በፊትም ሆነ ከዚያ በኋላ ታይቶ የማይታወቅ ነጻነት ሰጥቶን ሄደ።

"ይችን ይወዳል የደርቤ ልጅ" አልኩኝና ወረቀቴን ገልብጬ ይሄን የማምገማ ናዳ አወረድኩት። "የጥፊህ ጥብቀት እንኳን ትምህርቴን የተመደብኩበትን ከፍሌን እያስጠፋኝ ባለፈው አምስተኛ ሲ ከፍል ገብቼ ነበር! እረ ተው ጋሼ ተው! ወልደህ አትማታም እንዴ እኛን የምትቀጠቅጠን!" ግማሽ ሉክ ሂስ ያለ ምንም ርህራሄ አዘነብኩበት።።

ሞኒተራችን የግምገማ ወረቀቶቹን ሰብስቦ ይዞ በመሄድ ሰጥቶት ተመለሰ።

በማግስቱ ጋሼ አሰፋ ወደ ክላሳችን ሲገባ "ጉድ ይፈላል" ብለን ስንጠብቅ የከፍል ስራ ሰጥቶን ቁጭ አለ።

ገረመኝ። "እውነትም ይሄ መንግስትማ መብታችንን አስከብሮልናል" አልኩኝ።

የተሰጠን የከፍል ስራ "ከመሬትና ከፀሐይ ማን ነው የሚዞረው?" የሚል ነበረ። የሜዳው ሚካኤልን የፈራ "ፀሐይ" ብሎ መለሰ። ኩነኔ የማያስጨንቀው "መሬት" በማለት መልሱን ጻፈ።

የከፍል ስራውን ስራንና ልናሳርም ስንሄድ ደብተራችንን እየተቀበለ ባንድ ላይ ይሰበስበው ጀመር። የሁላችንም ተማሪዎች ደብተር ሰብስቦ ሲጨርስ "ቤቴ ወስጄ ነው የማርመው" በማለት ይዞት ሄደ። እኔና ማሙሸት "አይ የዚች አገር ዲሞክራሲ!" በማለት በፈታችን ተስፋ መቁረጣችንን ተገላለጽን።

ጽሁፋችንን አስተያይቶ የገመገምነውን ተማሪዎች ለመለየት የተሸረበ ሴራ ለመሆኑ አልተጠራጠርንም።

አዳሬን እንቅልፍ አጥቼ አደርኩኝ። "እንዳትቀየመኝ ብዬ ፀሐይ ናት የምትዞረው ያልኩልህ የሜዳው ሚካኤልዬ ከነገው ዱላ ያዳንከኝ እንደሆነ የወላጆች በዓል ከሚሰጠኝ ገንዘብ ላይ ቀንሼ የአስር ሳንቲም አድሩስ አመጣልሃለሁ!" ብዬ ተሳልኩኝ።

በማግስቱ ጋሼ አሰፋ በስማችን እየጠራ ደብተራችንን ሲመልስ የኔና የማሙሸት ደብተር እየተንገዋለለ ወደ ኋላ ይቀር ጀመር። ስለቴን በሁለት አሃዝ ጨምሬ ወደ ስሙኒ አድሩስ አሳደኩት። ምን ዋጋ አለው! የሁሉም ደብተር ተመልሶ የኔና የማሙሸትን ደብተር ለይቶ ሲያስቀረው ጊዜ "እንደው የሜዳው ሚካኤልዬ እንደው ምን አደረኩህ? ያልጠየቅነውን ነጻነት እየሰጡ...." ብዬ ምሬቴን ገልጬ ሳልጨርስ በጥፊ ሲያጋጨኝ ግድግዳው ጋር ተላትሜ ተመለስኩኝ። እኔ ላይ ያረፈውን ጥፊ ማሙሸት ተመለከተና ቀጣይ ተረኛ እሱ መሆኑን ሲረዳ ስቅስቅ ብሎ ያለቅስ ጀመር። ምን አለፋችሁ የአገሪቱ የደን ሀብት አላያችን ላይ ተጨፈጨፈ። እንደ ምድር እንደ ጸሃይ እያዟዟረ ቀጠቀጠን። መሬትና ጸሃይ መዞራቸውን አቁመው ያለ ዛቢያ የሚሽከረከረው የኔ ጭንቅላት ሆነ።

በሰዓቱ ምን ተማርኩ መሰላችሁ? የሜዳው ሚካኤል እራሱ እዝች አገር ጣጣ ውስጥ ከመግባት ይልቅ እሳት ውስጥ ገብቶ ፍጡራንን ማውጣት ሳይቀለው አይቀርም። በተጨማሪም ከእያንዳንዱ የብሶት ትንፋሽ ጀርባ እፎይታ ሳይሆን ሌላ ብሶት እንዳለም ይገባኛል።

*****

እድሜዬም አስራዎቹ አጋማሽ ላይ መድረስ በጀመረ ጊዜ ጎርመስ የማለት ስሜት እየተሰማኝ የምጫዎተውም ጨዋታ ወደ ኳስና ወደ "ዳማ" እየተለወጠ መጣ። ቤትም ውስጥ መገላመጥና ከአባቴም ተለይቼ ማደር ጀመርኩኝ። አለባበሴም ቢሆን እየሰለጠነ መጣና በዘመኑ አለ የተባለውን "ከሬሺን" የተባለ ፋሽን ቱታ አስገዛሁኝ። ጫማዬ ደግሞ ከኮንጎ ጫማ ወደ አንበሳ ጫማ አደገ።

ከሰውነቴም ምንነቱን በውል ያለየሁት ሆርሞን እየመነጨ የምሰራውን ያሳጣኝ ጀመር። በባህሪዬም ላይ ሆነ በሰውነቴ ላይ በርካታ ለውጦች ይታዩ ነበር። ከነዚህ ለውጦች መሃከል ብብቴ አካባቢ በጊዜው ሽታውን የወደድኩት ጠረን ከመከሰቱም በተጨማሪ ብልቴ አካባቢም ቀላ ያለ ላዘ ጸጉር ማቆጥቆጥ ጀምሮ ነበር። ማሙሸትም ቢሆን ከልሙጥ ወረቀት ፖስታ በመስራት፣ በቀይና ቧሰማያዊ እስኪብርቶ በማሸብረቅ ለአንዲት የከፍላችን ተማሪ ደብዳቤ መጻፍ ጀምሮ ነበር።

እኔና ማሙሸት መፈንዳት ስንጀምር የምትኩ ሁኔታ ግን ግራ የሚያጋባ ሁኖ ነበረ። በእርግጥ እናቱ በጣም ድሃ ስለሆነች እንደኛ አይነት ልብስ ልትገዛለት ስላልቻለች በአለባበስ ረገድ መሻሻል አላሳየም። ሁኖም ግን ከአስተሳሰብ ረገድ ተለውጦ ነበር። በጣም ነጭናጫና ትንሽ ነገር ሲያደርጉት ጥቃቱን ከአባቱ መሞትና ከእናቱ ድህነት ጋር በቀጥታ ማያያዝ ጀምሮ ነበር። ያም ሁኖ ግን አሁን ላይ ጥቃቱም ህመሙም ይገባናል እንጂ ያኔ ምትኩ የሚሰማውን ስሜት አንረዳውም ነበር።

መቼም አሁን ላለን ስብእና የትምህርት ቤትን ያህል ተጽእኖ የፈጠረብን ነገር ይኖራል ብዬ አላምንም። የበታችነት ቢሰማህ፣ የበላይነት ስሜት ቢጠናዎትህ ይሄ ስሜት መጠንሰሻው ትምህርት ቤት ነው። አንዳንድ ተማሪዎች አለን ህመማችንን ሰው የማይረዳንና መምህሩም አስተማሪውም "ድንጋይ ራስ" ብሎ የሚሰድበን። ምትኩ ከነዚህ ተማሪዎች ተርታ ይሰለፋል።

ለምሳሌ በስፖርት ከፍለ ጊዜ ኳስ ለመጫወት ስንቧደን የቡድን አባት እንዲሆኑ የምንመርጣቸው ተማሪዎች በስራቸው ቡድን ሲመሰርቱ ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎች ቀድመው ይመርጡና ምትኩን ሳይመርጡት ይቀራሉ። እሱ ደግሞ ሃይለኛ የሆነ የእግር ኳስ ፍቅር ነበረው። "ለምንድን ነው እኔን የማትመርጡኝ?" ብሎ ሲጠይቅ "ችሎታ ስለሌለህ ነዋ!" ተብሎ ይመለስለታል። ለአስተማሪ ሲከስ ከፈለከው ቡድን ጋር ግባ ተብሎ ምርቃት ይሆናል። አንዱ ቡድን ሊገባ ሲል "እኛ አንፈልግህም እዛኛው ቡድን ግባ" ይሉታል። ሲያመላልሱት ይቆዩና "አባት ስለሌለኝ ነው አይደል የምትጫዎቱብኝ" ብሎ ማልቀስ ሲጀምር "በቃ አንተ የፈለከው ጋር ግባና ተጫዎት!" ይባላል።

አንዳንድ መምህራኖቻችንም በልዩ ልዩ ከበባት ምርጫችንን እየለዩ ሲያደራጁን ይቆዩና ምትኩ ላይ ሲደርሱ "እሺ ምትኩ አንተስ የትኛው ከበብ ውስጥ ትመዘገብ? መቼም አንዱም አይሆንልህ!" ይሉትና ተማሪውን ሲያስቁት ልጁን ግን ያሸማቅቁታል። የሆነ ጥያቄ ተጠይቆ የመለሰ እለት "ዛሬስ ከምን መለስከው?" ይሉታል። መልሱ የጠፋው ቀን ደግሞ "ይሄ ድንፈፍ! ሁሌ ገንፎ የጠገበ ጅል መስሎ" ብለው ያስቁበታል። ልክ እኛ እንደምናጠፋው ሁሉ እሱም ሳት ብሎት ጥፋት ያጠፋ እለት የሞኒተሮቻችን ዱላ ምትኩ ላይ ሲሆን ይበረታል።

እነህ ሁሉ የወደፊት ማንነትን የሚያሸመደምዱ ነገሮች በምትኩ ላይ ሲደርሱበት ጥቃቶቹን ከአባቱ ሞትና ከእናቱ ድህነት ጋር ያገናኘው ነበር። በርግጥ አስተማሪዎቻችንም ሆኑ ተማሪዎቹ ምትኩ ላይ ስላቅን ሲፈጥሩበት... ለሆነ ነገርም

ምርጫ ሲካሄድ አንገዋላው ዳር ሲጥሉት... ምትኩ የሚበሳጭ ቀርቶ እንደ ሰው የሚያስብ አይመስላቸውም ነበር።

አንድ ቀን ከትምህርት ቤት ስንመለስ ብሶቱን ሁሉ ከአባቱ ሞት ጋር አገናኝቶ ዝርግፍ አድርጎ ሲነግረኝ አለቀስኩኝ። ከዛ በኋላ እንኳን ልሰድበውና ልጣላው ቀርቶ ሌላ ልጅ ጋራም ሲጣላ ለእሱ ማገዝ ጀመርኩኝ። ያም ሁኖ ግን የምትኩ ብስጭትና ንደት እየባሰ ይመጣ ነበር። ለምሳሌ መምህራን ወደ ክፍላችን ሲመጣ ከሁሉም ተማሪ ቀድሞ ከመምህሩ ዳስተር ተቀብሎ ብላክ ቦርድ ማጽዳት ይፈልጋል። መምህራኖቹ ግን ይሄን አይረዱትም። "ምን ያክለፈልፍሃል አንተ ጅል!" ብለው ይሰድቡትና ዳስተሩን ለሌላ ተማሪ ሲሰጡ የምትኩ ፊት በንደት ቲማቲም ይመስላል።

****

የሽቦ መኪናዬንና የጨርቅ ኳሴን ለታናሽ ወንድሜ ካወረስኩኝ ቆየሁ። እንዳልኳችሁ ይሄ ምንነቱን ለይቼ ያላወኩት ሆርሞን ለአውደ ዓመት የምለብሰውን "ከሬሺን" የተባለ የዘመኑ ምርጥ ሙሉ ቱታ በአንበሳ ጫማዬ ገድግጀው በአዘቦት ቀን እወጣ ዘንድ ያበረታታኝ ነበር። ይሄን ልብስ በምለብስበት ሰዓት ጫማዬ በደንብ እንዲታይ በማሰብ "ከሬሺን" ሱሪዬን ካልሲዬ ውስጥ ስለምከተው አየር መግባትም ሆነ መውጣት ስለማይችል ቀን የፈሳሁት ፈስ የሚሸተኝ ማታ ላይ ሱሪዬን ሳወጣው ነበር። ከዚህ በተጨማሪ ይሄው ሆርሞን ጭኖቼ መሃከል ያለችውን ልሙሽሙሽ ሽንፈላ ወደ ቀንድነት በመቀየር ሴቶቹን "እጃቸውን ጠምዝዘህ ጣላቸው!" እያለ ይወሰውሰኝ ነበር።

****

"ጻደንያ" ማለት እድሜው ገፋ ያለ በስልጣኑ የተከበረ ባል ያላት እኛ ቤት የተከራዬች ቀይ እና የምታምር ልጅ ናት። የዚህን ሰውዬ እና የዚችን ልጅ ትዳር የማይኮንነው አልነበረም። "አሁን ይሄ ሽማግሌ ይችን የመሰለች ቂጣም እንደት አድርጎ ነው ሊያረካት የሚችለው" የሚል ግርታ የነበረባቸው ሰዎች በርካታ ነበሩ።

ሰውዬው ብዙ ጊዜ ፊልድ ስለሚበዛበት ቤቱ አያድርም። ጸዲ ባሏ በሌለበት ሰዓት ስለምትፈራ እየሄድኩ አስተዳድራት ነበር። የሆነ ቀንም "ያስተዳድረኝ" ብላ እናቴን አስፈቅዳ ይዛኝ ሄደች።

እራት መኮረኒ ልትሰጠኝ ስጎ ልታደርግበት ስትል "ተይው ስጎ አታድርጊበት!" አልኳት።

"ለምን?" አለችኝ

ስጎ የሌለው መኮረኒ መብላት እንደምወድ ነገርኳትና ፈገግ ብላ ነጩን መኮረኒ ሰጠችኝ። ከዳቦ እና ሻይ ቀጥሎ ምርጥ ምግብ መኮረኒና ፓስታ ያለ ስጎ ነው። ሽንኩርትና ቲማቲም የሌለው ልሙጥ ሽሮም ነፍሴ ነው።

አልጋ ላይ ሆና እኔ ስበላ ሻማ ሻማውን እያየች ጸጉሯን ታበጥራለች። የጸጉሯ ርዝማኔ በጣም ገርሞኛል። መኮረኒዬን በልቼ እንደለመድኩት ፍራሽ ላይ ልተኛ ብርድ ልብስ እንድትሰጠኝ ሰጠይቃት አልጋ ላይ እንዲተኛ ጋበዘችኝ።

"አልጋ ላይ እንኳን አልተኛም" አልኳት።

ተቆጣች።

****

የቀኑን ልብሴን እንደለበስኩ አንሶላ ውስጥ ገብቼ አያት ጀመር። ምንም አይነት ሰው እንደሌለ ቆጥራ ልብሷን እያወጣች ወረወረችው። ከወገቧ በላይ እርቃኗን፣ ከወገብ በታች ደግሞ ፓንት ብቻ የለበሰች ሴት ጋር ተፋጠጥኩኝ።

ጡቶቿን ሰረቅ አድርጌ ሳያቸው እጅ ከፍንጅ ስለያዘችኝ እፍረት ተሰማኝ። ይሄንን ጉድ መቼም ነግቶ ለማሙሸት እስካወራው ቸኩያለሁ።

ያ ብብቴ ውስጥ የሚመነጨው ሽቶ ፈልቆ ሲሸተኝ ተሰማኝ። ቢጃማውን ለብሳ ከጎኔ መጥታ ስትጋደም የሆነ ነገር ሰውነቴን ስለወረረኝ ፊቴን ዙሬ ተኛሁ። አልጋ ላይ ሳይሆን ፌርሜሎ ላይ የተኛሁ ይመስል በጣም ሞቀኝ።

"ዙርና እቀፈኝ እንጂ" አለችኝ።

እንደምፈራ ነገርኳት።

"እህትህ አይደለሁ እንዴ! ምን ያስፈራሃል!" ስትለኝ ባላቅፋትም ሰውነቴን አዞርኩኝ።

የሰውነቷ ጠረን ልክ እንደ ትኩስ ዳቦ ይጣፍጣል። ብልቴ እንደ በግ ቀንድ እንጨት ሆነች። ለማንም የማልናገር ከሆነ የሆነ ነገር እንደምትሰጠኝ ነገረችኝ። "አልናገርም" ብዬ እጇን መታሁ። ምንም ሳልንቀሳቀስ አይኔን ጨፍኜ የምታደርገውን ነገር እንድከታተል ነገረችኝ።

እንደታዛዝኩት አደረኩ።

ለስላሳ ጣቷቿን ወደ ጭኔ ላከችና ቀንዴን ታሻሽልኝ ጀመር። የኔንም እጅ ስባ ወደ ጭኗ መራችው። ጸጉር የበዛበት አካሏን እንደ በሶ እጨብጠው ጀመር።

"ብልቴን አሳካከኝ" አልኳት።

"አይዞህ የመጀመሪያህ ስለሆነ ነው ይለቅሃል" አለችኝና ጭኖቿ መሃል ከተተችኝ።

ቀንዴ ሸርተት ብላ ሰመጠች።

አንድ ጊዜ ስትጨምቀኝ፣ አንድ ጊዜ ስትስመኝ ሳላስበው አለፈልፍ ጀመር።

"ትንሽ ቆይተን ደግሞ ትሰጭኛለሽ?" አልኳት።

"አዎ እሰጥሃለሁ"

"ነገም ትሰጭኛለሽ?"

"አዎ እሰጥሃለሁ"

"ሁሌ በየቀኑ እስከ ከርሞ ድረስ ትሰጭኛለሽ?"

"እስኪ አትቀባጥር ዝም በል!"

ከሆነ ንዝረት በኋላ ደስ የሚል ፈንጠዝያ ተሰማኝና ዝልፍልፍ ብዬ ጡቶቿ መሃል ተወሸኩኝ። እሷም ከንፈሬን ነክሳ ተርገፈገፈች። ለካ መደፈር ይሄ ነው። ሲገርም።

የወሰደኝ እንቅልፍ ከሞት የከፋ ነበር። ጠዋት ላይ ተጨማሪ አንድ ጊዜ አቀመሰችኝና ልብሴን ለብሼ እየተንቋቋሁ ወጣሁ።

ፍጹም የሆነ ንቃት እና ነጻነት ባንድ ላይ ተሰማኝ። ቁርስ የምወደውን ዳቦ እና ሻይ ባግባቡ መብላት አልቻልኩም ነበር። የማታውን ሳስታውስ ቀንዴ ቀጥ ትልብኝና ህመም ነገር ጠቅ ያደርገኛል።

ይሄን ጉዳይ ለማሙሸትም ለምትኩም ልነግራቸው አልፈለኩም። ብቻ ግን ድካም እየተሰማኝ እንደ ድሮው መላፋትና መታገል አስጠልቶኝ ነበረ። በዛው ላይ የድሮው ሙዴም ጠፍቶብኝ ነበር።

ዛሬም እንደ ትናንቱ ጸዲ መጥታ ትወስደኛለች ብዬ ብጠብቃትም ሳትመጣ ቀረችና በቅሬታ ውስጥ ሆኜ ቤቴ አደርኩኝ። በማግስቱ ምሳዬን ከበላሁ በኋላ ከሬሺን ልብሴን "ኪቶ" በተባለው ታዋቂ ሰንደል ጫማ ገድግጀው ወደ ጸዲ ቤት ሄድኩኝ።

"ምን ሆንክ?" አለችኝ ምሳዋን በልታ እጇን እየታጠበች።

"ስጭኝ" አልኳት ገንዘብ እንዳበደረ ሰው ኮስተር ብዬ።

"ምንድን ነው የምሰጥህ?"

በአገጩ የምፈልገውን አሳየኋት።

ባሏ ከሰማ በሽጉጥ እንደሚገድላት ነግራኝ ሁለተኛ እንዳላስበውና የማታውንም ለማንም ሰው ትንፍሰ እንዳልል አስጠነቀቀችኝ።

አልሰማኋትም።

"ትሰጭኝ እንደሁ ስጭኝ!" አልኳት በሱሪዬ ኪስ በኩል ቀንዴን ጨምድጀ ይዤ።

"ባልሰጥህስ ምን ልትሆን ነው? እንቢ አለችኝ ብለህ ፍርድ ቤት ልትከሰኝ ነው?"

"ባልከስሽም ለጓደኞቼ ሄጀ አወራብሻለሁ!"አልኳት።

"ጉድ ያለው ገንፎ አድሮ ይፋጃል!" የሚል ተረት ተርታ ሰጠችኝ።

ድንግልናዬ ከተወሰደ በኋላ የአስተሳሰብ ደረጃዬ ከፍ ብሎ በትምህርቴም ቢሆን ለውጥ ማምጣት እንደጀመርኩ ባልተዘጋጀሁበት ጊዜና ወቅት የጸድ ባል የሰራ ዝውውር አግኝቶ ጥላኝ ሄደች።

የሄደች ቀን ሰው እንዳያያኝ ራቅ ወዳለ ቦታ ሂጀ እናቱ እንደሞተችበት ሰው እየየየን አቀለጥኩት። እንባዬ ሄርሜላ ካለቀሰሰችው እንባ የከፋ ነበር።

እሷ ከሄደች በኋላ ጓደኝቼ ጋር ልጫወት ሄድኩኝ። የጓደኞቼ ወሬ ምንም ሊመስጠኝ አልቻለም። "ቂጡን ያለጠረገ ውሪ ጋር ስዳረቅ ከምውል" ብዬ ጨዋታውን ተውኩና ነጋዴ አባቴን ማገዝ ጀመርኩኝ። ፀዲ ፍቅሬን ብቻ ሳይሆን ልጅነቴንም እሷ የወሰደችው ይመስለኛል።

*****

እንደኛ አቅድማ
እንደ እኛ ልጅነት፣
ግማሻችን ዶክተር
ግማሻችን ፓይለት፣
"እንሆናለን" ብለን
እንመኝ ነበረ፣
እንኳንም ህልማችን
ልጅነት ጋር ቀረ፣
ጡንቻችን ሲዳብር
ለአቅመ አሳብ ሰንደርስ፣
ግማሻችን ሌባ
ግማሻችን ፖሊስ
.....ሳንሆን ብንቀር፣
ሁሉም ፓይለት ሆኖ
ምን እናበር ነበር።

ስምንተኛ ክፍል እያለን የእንግሊዘኛ አስተማሪያችን ጋሼ ስዩም "ወደ ፊት ምን መሆን ትፈልጋላችሁ?" በማለት ሲጠይቅ ከምትኩ ውጭ ያለነው የከላሱ ተማሪዎች በሙሉ ፓይለትና ዶክተር በማለት መለስን።

ምትኩ ደግሞ "ምን መሆን ትፈልጋለህ?" ሲባል ኢንጅነር የሚል መልስ ሰጠ።

"ኢንጅነር ማለት ምን ማለት ነው?" አለው።

"ህንጣ ቤት የሚሰራ"

"አይ ምትኩ አሁን አንተ ህንጣ ቤት ቀርቶ የመቃብር ቤትስ ትሰራለህ?" በማለት ጋሼ ስዩም ሊያስቀን ሞከረ። በዚህ ቀልድ ግን ከመገልፈጥ ባለፈ የሳቀ ተማሪ አልነበረም። በጋሼ ስዩም ተረብ ተናድጇ ምትኩን አሻግሬ ሳየው አንገቱን አቀርቅሯል።

መቼም በእኛ አስተሳሰብና በኛ አገር ኋላቀርነት በተሰጥዖ ሳይሆን በእጣ ወደፊታችን በሚወሰንበት ሁኔታ የልጅነት ህልማችን እውን ይሆናል ብሎ ማሰብ ሞኝነት ነው። ሲጀመርስ ህልም ነበረን እንዴ?

ጋሼ ስዩምም ቢሆን መገሰፅና ማሾፍ ካለበት በምትኩ ሳይሆን በእኛ ነበረ።

ምትኩ "መሀንድስ" የሚል መልስ የሰጠው ከልጅነቱ ጀምሮ የአባቱ የአናጺነት ሙያ አብሮት ስላደገ ነው። እኛ ግን "ፓይለት" ብለን ስንመልስ ፓይለትም አውሮፕላንም አይተን አናውቅም። በርግጥም ደግሞ ፓይለትነት ዝም ብለን የሸመደድነው ነገር እንጂ ህልማችን አልነበረም።

ጋሼ ስዩምም እንዲህ አይነት መልስ ስንሰጠው "ይሄ ሁሉ ሰው ፓይለት ሁኖ አሞራ ሊያበር ነው አውሮፕላን?" ብሎ ማሰብ ነበረበት። መምህርም የሚያስፈልገው ለዚህ ነው። ፍላጎታችንን ከመጠየቅ ባለፈ መክሊታችንንም መለየትና መናገር ያስፈልጋል። ወሬ የሚዋጣለትን ተማሪ "አንተ ፖለቲከኛ" ብትሆን...."የወላጆች በአል መነባነብ ካላቀረብኩኝ" ብሎ የሚያለቅሰውን ተማሪ ደግሞ "አንተ አርቲስት ብትሆን ያዋጣሃል" እያሉ መምራት ያስፈልግ ነበር። ምን ዋጋ አለው ለዛም ነው አውሮፕላን ለማብረር ስናቅድ ኑረን እኛው በራሪ ሁነን የቀረነው።

ስምተኛ ክፍል ሚኒስትሪ ተፈትነን የውጤት ካርዳችን ሲመጣ የምትኩ ካርድ ላይ "አልተዛወረም!" የሚል ጽሁፍ ሰፍሮበት ነበረ። መውደቁን ለእናቱ ሲነግራት "እንተ ተምረህ ሰው ትሆናለህ ብዬ አሻሮ በመቁላት በእሳት ስቃጠል እየዋልኩ..... አንተ ግን ስትራገጥ እንደ ጓደኞችህ ማለፍ አቃተህ" በማለት በርበሬ አጠነችው።

ምትኩ ሚኒስትሪ ብቻ ሳይሆን ከአሮጌው አመት ወደ አዲሱ አመትም እንዲዛወር ፈጣሪ አልፈቀደለትምና የአይጥ መርዝ ጠጥቶ ሞተ። አዘንኩ። ላንዲት ቀን ስሜቱን ሳንረዳው መሆን የሚፈልገውን መሆን ቀርቶ... መሆን የሚፈልገውን መናገር ከልክልነው በመሞቱ አዘንኩ። የሚዳው ሚካኤል ስዕል ላይ ተደፍቼ አለቀስኩ። ገነት እንደሚገባ እርግጠኛ ስለነበርኩኝ "ነፍሱን በገነት አኑርልኝ ምናምን" ብዬ አልጸለይኩም። እስካሁን ድረስ የሚከነክነኝ ነገር ከሌሎች ተለይቶ የምትኩ መቃብር ብቻ ቤት ሳይሰራለት መቅረቱ ነው።

የማሙሸት እና የእኔ ህልም ፓይለት መሆን ነበረ። ማሙሸት ህልሙ እውን ሆኖ ማብረር ባይችል እንኳን መብረርን አሳክቶ አረብ አገር ፍየል ጠባቂ ሁኗል። እኔ በአየርም በምድርም መሄጃ አጥቼ ይሄው ለመጣ ለሄደው ልጅነቴን ስተርክ እውላለሁ።

ቅጣት

በወንጀል ተከሶ በህግ ፊት ቁም
ንሰሃ የሚሰጥ ዳኛ ተሰይሞ
ጥፋቱን ተናዘ ፍርዱን ያገኘ ሰው
"ነጻ ሆንኩኝ" ብሎ ልቡን ደሰ ይበለው።

አሰርስ-አለመያዝ፣ ቅጣትሰ-ነጻነት
አሻራን ሳይጥሱ ሰው በድሎ መጥፋት።
አራሱ ጠበቃ፣ አሱው ፈራጅ ዳኛ
አራሱ ምስክር፣ አሱው ወንጀለኛ
ሆኖ በሰው መሃል አየተራወጡ
አድሜ ይፍታሽ አስር፣ ብይን አየሰጡ
በራሰ ላይ መቃወስ አብደት አያመጡ
ቅጣትሰ መፀፀት፣ ወህኒሰ ጎዳና
አሰረኛስ ጭንቅላት፣ ከሳሽስ ልቦና
ችሎትሰ በልብ ውሰጥ፣ ፈራጅሰ ህሊና።

ሚስቴ "ብሎክ" አደረገችኝ

አንጨቱ...
አሳትን የሚወልድ
አሳቱ...
አንጨትን የሚያነድ
አመድ መሆንን የሚወድ
ወይ አንጨት...!
አሳትን ወልዶ የሚሞት
ወይ አሳት...!
አንጨት ወላጁን የሚያነድ
አመድ አጥፊውን የሚወልድ።

ሁለተኛ ሚስቴን ካገባሁ አንድ ወር ከአስራ ሰባት ቀን ሆነኝ።

የመጀመሪያ ሚስቴን እወዳት ነበር። ግን ምን ያደርጋል ከዘመኑ እና ከቴክኖሎጅው ጋር አብራ መሄድ ስላልቻለች ፈታኋት። የበፊቷ ሚስቴ ከእንቅልፍ ሰዓቷ ውጭ ያለውን ጊዜ ኮተት በማጠብ ታሳልፈው ነበር። ቤት ስትወለውል፣ እቃ ስታጥብ፣ ልብስ ስታጥብ ታመሽና የምታጥበውን ነገር ሁሉ ስትጨርስ "ገላህን ልጠብህ" ብላ ትለማመጠኛለች።

ስለ እሷ ሳስብ ደሜ ይፈላል። ሻንጣ ሙሉ ልብስ አውጥታ ስታጥብ ትቆይና "ጨረሰች" ብዬ ሳስብ የዶሮ ወይም የቅቅል መረቅ ይመስል "የሳሙናውን መረቅ ከምደፋው" በማለት ሌላ አንድ ሻንጣ ተጨማሪ ልብስ በመረቁ ማጠብ ትጀምራለች።

ብዙ የማንስማማባቸው ነገሮች ቢኖሩም የኔና የሚስቴ ጠብ የተካረረው ፌስቡክ እንዳልጠቀም መጨቃጨቅ ስትጀምር ነው። ጭቅጭቁ ጋብ ቢል ብዬ ምን የመሰለ እሳት የላሰ ተች ስክሪን ሞባይል ገዝቼ... የፌስቡክ አካውንት ከፍቼ... ከሶስት ቀን ስልጠና ጋር ሰጣኋት። ፌስቡክም ላይ ከእኔ ውጭ ጓደኛ ማፍራት አልፈለገችም። እሱም ባልከፋ! የገዛሁላትን ሞባይል ከታሰበለት አላማ ውጭ እንደ "ኤዲዋርድ ስኖውደን" እኔኑ ለመሰለያና ለማሸበሪያ ድርጊት ታውለው ጀመር።

የሆነ ጊዜ "ሃኒ" የተባለች የፌስቡክ ጓደኛዬ ከፊል እርቃን የሆነ ጉደኛ ፎቶ ለጥፋ ነበር። ሞባይሌ እስኪለመጥ ድረስ ላይክ ገጨኋትና ከቢሮ ወጥቼ ወደ ቤቴ ስገባ ሚስቴ "ማን ናት?" አለችኝ የሀኒን ፎቶ ወደ አይኔ አሰጠግታ።

"እኔ ምን አውቃለሁ?" አልኳት።

"እንዴት አታውቅም? የማታውቃት ከሆነ ለምን ላይክ አደረካት?" አለችኝ እንባ እየተናነቃት።

"እንዴ! መቼስ የሀገራችን የሞደሊንግ ኢንዱስትሪ አንድ እርምጃ ወደ ፊት ይሂድ ከተባለ እኒህን ልጆች እኛ ካላበረታታናቸው....." ብዬ ንግግሬን ሳልጨርስ በንደት ከንፈሯን ነክሳ ወደ ጓዳ በመግባት ተች ስክሪን ሞባይሏን ኩበርጭቆ ጋር ቀላቅላ ታጥበው ጀመር።

ከስህተቴ መማር አልፈለኩም። እንደ አብዛኛው ወንድ የምወዳቸውን ሴቶች እንጂ የሚወዱኝን ሴቶች አልመርጥም። የሚያስቀኑኝን እንጂ የሚቀኑብኝን ሴቶች የመናቅ አባዜም አለብኝ።

ለተወሰነ ጊዜ የታጠበው ሞባይል እስኪደርቅ ድረስ የወደድኩትን እንዳደንቅ፣ የጠላሁትን እንዳናንቅ ጊዜ አግኝቼ ነበር።

በሌላ ጊዜ ደግሞ "ሃሌሉያ" የተባለች ልጅ ከአገሯ ይልቅ የምትኮራበትን እግሯን ፎቶ በማንሳት ለጥፋ ነበር። እኔ ደግሞ እንደ አብዛኛው ወንድ ሴትን ከጀርባ ሳይሆን ከግርጌ መመልከት ይቀናኛል። ከእግሯ የተደላደለች ተረከዟ የጠፈጠፈ ሴት ብዙም አልወድም። ለአንድ ውብ እግር ሊሰጥ የሚገባውን አድናቆት ቸርኳት።

ይሄንንም ሚስቴ አይታው ኖሮ ቤት ስገባ ፊቷ ላይ ከባድ ቅሬታ አነበብኩኝ። "ጉዳዩ ምን ይሆን?" ብዬ ሳስብ የእግሩን ሚስጥር ደርሳበት ኑሯል። አንዳንዴ ላይክ ያደረኩበትን ምክንያት ለሚስቴ በመሃላና በማስረጃ ከማስረዳት ይልቅ ያላችሁበት ድረስ መጥቼ አድናቆቴን በአካል ግልጨላችሁ መመለሱ የተሻለ መስሎ ይታየኛል።

ደግሞስ እግር ከፍቼ ስገባ የያዘችኝ ይመስል "አደነቀ" ተብዬ ለምን ይሄን ያህል ሰቆቃ ይደርስብኛል?

"የማነው እግር?" አለችኝ።

"ስሚ ከላይ አለልሽ!" አልኳት።

"ስሚንማ አየሁት ጥያቄዬ ለምን ላይክ አደረከው ነው?"

"ማን? እኔ!"

"አዎ አንተ!" አለችኝ ዐይኗ በንደት እየተንቀለቀለ።

"ኧረ አፈር ልብላ ይሄ "ኦፔራ ሚኒ" የሚባል ብሮውሰር ያላሰብኩት ቦታ ወስዶ ፎቶውን ላይክ አድርጎብኝ እንደሆነ እንጂ እንደዚህ እንደ ውሃ ደሜ ይፍሰስ እኔ ላይክ አላደረኩም" ብዬ ከጀሪካኑ የማፈሰው ውሃ ልቀዳ ጎንበስ እንዳልኩ "ኮሜንቱንስ ኦፔራሚኒ ነው የሰጠው?" ከሚለው ቃሏ በኋላ የሄሮሺማና ናጋሳኪ ፍንዳታ እኔ ጨንቅላት ላይ ተደገመ። ጭንቅላቴ ላይ የፈነዳው ነገር መብረቅ እንጂ መዳፍ አልመሰለኝም።

ሌሊቱን ሙሉ በድንጋጤ ሳማትብ አድሬ በማግስቱ ፈታኟት።

ደግነቱ "አንድ ሚስትና አንድ ጎል አያስተማምንም!" ብሎ ጓደኛዬ በመከረኝ መሰረት ቀደም ብዬ መጠባበቂያ አዘጋጅቼ ስለነበር በፌስቡክ የጠበስኳትን ሁለተኛ ሚስቴን ካገባሁ አንድ ወር ከአስራ ሰባት ቀን ሆነኝ።

ሰው ቀናትን አብዝቶ የሚቆጥረው ሲመቸው ይሆን ሲጨንቀው?

ይችን ልጅ ለመጀመሪያ ጊዜ በአካል ያገኘኋት ቀን እንደ ፎቶዋ "ኤዲት" አልተደረገችም ነበር። እሷም ብትሆን ጀርባዬ ላይ ባለው መላጣ ግር መሰኘቷ አልቀረም። "ችግር የለውም! ፎቶዋን በአዶቤ ፎቶ ሾፕ ማስተካከል ከተቻለ አካሏን ደግሞ በምኞት ማሳመር ይቻላል" ብዬ አገባኋት። ባንድ ቤት መኖር ከጀመርን ሳምንት እንኳን ሳይሞላን የአሁኗን ሚስቴን ከዘችኛዋ ጋር አወዳድራት ጀመር።

የበፊቷ ሚስቴ የባንክ አካውንቷ ላይ ነበር ያገኘቻትን ሳንቲም ጣል የምታደርገው። ይህች ደግሞ የፌስቡክ አካውንቷ ላይ ነው ቀኑን ሙሉ ፎቶዎቿን ጣል ስታደርግ የምትውለው። ደግሞ እኮ የሚገርመኝ የሷ ፎቶ መለጠፍ ሳይሆን ከጓደኞቿ የሚሰጣት አግባብ የሌለው አድናቆት ነው። አንዲት ተላላ ሴት "ፕሮፋይል

ፒክቸር ቀየረች" ተብሎ አለምን የቀየረች ይመስል የኮሜንትና የላይክ መአት ሲላክላት አንጀቴ ትከን ይላል።

ብዙ ጊዜዬን የምገድለው ከሷ እርቃን ፎቶ ሰር የሚሰጡትን አስተያየቶች በማንበብና በጣም ወጣ ያለ ኮሜንት የሰጡትን ሰዎች በሚሴጅ "የእገላችኋለሁ" ዛቻ በመላክ ሆነ። ተቃጠልኩ! በአጭር ጊዜ ውስጥ የአስተሳሰብና የአካል ለውጥ ተከሰተብኝ።

የበፊቷ ሚስቴ ፊልድ በምሄድበት ሰዓት ባገኘችው መኪና ተጠቅማ በምግብ የታጨቁ ሳህኖችን ትልክልኝ ነበረ። የዚችኛዋ ምግብ ግን የሚላከው በዋትስአፕና በፌስቡክ ነው። የተለያዩ በአትክልትና በስጋ የተሞሉ የምግብ ፎቶዎችን ስትልክኝ ትከርምና ከፊልድ ስመለስ ሽሮውም ሳይገነፈል ሞባይሏ ላይ ተጥዳ ትጠብቀኛለች።

ሌላውን ተውትና ታላቅ ቦታ የምሰጠውን የልደት በዓሌን በፊት ሳከብረው ዳቦ ተጋግሮ፣ ፋፎ ፈንድቶ፣ ብርቱካንና ሙዙ ቀርቦ፣ ለስላሳና ቢራው ተገዝቶ ነበር። ይሄን ሁሉ ግን የምታደርገው የገፋኋት ሚስቴ ነበረች።

ለአሁኗም ሚስቴ ቀደም ብላ እንድትዘጋጅ የልደት ቀኔን አስታውሻት ፊልድ ከርሜ በልደቴ ቀን ስመለስ ለሴረሞኒው ያዘጋጀችውን ኬክ ያገኘሁት ቤቴ ውስጥ ሳይሆን ፌስቡክ አካውንቴ ላይ ነበር። ጭራሽ ይሄንንም እንደ ትልቅ ስራ ቆጥራው "በስማም ስንት ቦታ ጎግል አድርጌ ይሄንን ኬክ እንዳገኘሁት አትጠይቀኝ!... እንዴት ነው ግን? ሰርፕራይዝ አደረኩህ አይደል!" እያለች ትቀባጥር ጀመር። እውነት እላችኋለሁ በልደቴ ቀን የተከፋሁት መከፋት በቃላት የሚገለጽ አይደለም።

ቤት ውስጥ ብዙም ንግግር የለንም። ትዕዛዝ ራሱ የምትሰጠኝ በፌስቡክ ነው። አልጋ ላይ ተዘርግታ "መጋረጃውን ጋርደው፣ ሽንኩርቱን አማስለው" እያለች ቻት ታደርግልኛለች።

ከሁሉም ደግሞ በጣም የሚገርመኝ ጉዳይ "ሼር" የምታደርጋቸው ነገሮች የወረዱ መሆናቸው ነው። ለምሳሌ ባለፈው ቁምሳጥን ውስጥ የተከመረውን ቆሻሻ ልብስ ሳጥብ ቆይቼ ፌስቡክ ስከፍት "ፈንድሻ ምንድን ነው እንዲህ አበባ እንድትሆኝ ያደረገሽ ብለው ቢጠይቋት እሳቱን ታግሼው" አለች አሉ የሚል አባባል ከሌላ ሰው ላይ "ሼር" አድርጋ አገኘሁኝ።

ይሄን አባባል "ሼር" ያደረገችው "እሳት ውስጥ ገብቼ ተቃጠልኩ!" ለማለት ፈልጋ መሆኑ ስለገባኝ "አሻሮስ እሳቱን መታገስ አቅቷት ይሆን ወይ እርር ብላ የቀረችው?"

የሚል ኮሜንት ብሰጣት "አንተ ጋር ምን አታገለኝ!" ብላ በብሎክ አሰናበተችኝ።

እናም ወንድሜ... "ቤትህ ያስቀመጥካትን ሚስትህን አስቀምጠህ ፌስቡክ ላይ በምታያቸው አካላቸውን በኮስሞቲክስ፣ ፎቷቸውን በፎቶሾፕ ያሸበረቁ ሴቶችን ስታሳድድ በእጅህ ያለውንም እንዳታጣ!" እያልኩኝ ለእንስቶቻችንም "ሴት ሆይ! ወንድ ልጅን አለቅጥ አትንከባከቢው እናቱ ትመስሊዋለሽና!" የሚለው አባባል በተወሰነ መልኩ እውነታነት አያጣም በማለት ቁጭቴን እቋጫለሁ።

እንክርዳድ

ወዳጄ ሆይ አንተ ምሩቅ የምርጥ ዘር
በፈጣሪም በሰውም ዘንድ ‘ምትፈቀር
አኔ ታድያ...
ባንተ ልሳን "እንክርዳድ ነህ" እንደተባልኩ
ለሰንዴነት ካልተመረጥኩ ፥ እንክርዳድነትን በታደልኩ

ግን አልሆነም....
የማይረባ መገለጫ "እንክርዳድ" እንዳሉት አረም
እንኳን አኔ ግሳንግሱ አንተ ጓዴ ምርጥ-ዘሩ
ቅዱስ ቃሉ አጣጥሎህ ተጠይፎህ እግዜሄሩ
በሰው ወንፊት ተንገዋለህ ከጥራጊ ጋር ተደፍተህ
ሰንዴነትህን ካጣህ
መቼም... መቼም "አይረባም" እንዳሉት አረም
አንተ ረብተህ እንክርዳድ ሆነህ አትበቅልም።

እጥረትና ክፋት

"ይህች መሬት አጫጭር ፍጡራንን ባታፈራ ኑሮ ከጦርነትና ከግጭት የጸዳች ትሆን ነበር!"

ይሄን በጥናት የታገዘ ንግግር የተናገረው የአሜሪካን ፕሬዝዳንት የነበሩት "አብረሃም ሊንከን" ከመሰላችሁ ተሳስታችኋል። ይሄን ያለው ያው የፈረደበት የባለቤት አልባ ጥቅሶች ባለቤት የሆነው "ሶቅራጠስ" ከመሰላችሁም ትክክል አይደላችሁም። ይሄን ታሪካዊ አባባል የተናገርኩት እኔው ራሴ ነኝ። ይሄንንም በሺ ዘጠኝ መቶ ዘጠና ሁለት ዓመተ ምህረት በወርሃ መጋቢት የታተመው ቃልኪዳን መጽሄት ላይ "ከታላላቅ ሰዎች አንደበት" የሚለው አምድ ስር በስሜ ተመዝግቦ ታገኙታላችሁ።

አጭር ሰው ለዚች አለም ጠንቅ ነው። እዚህ መደምደሚያ ላይ ለመድረስ በሚስቴ ላይ፣ በአለቃዬ ላይ፣ በጓደኛዬ ላይ ሰፊ የሆነ ጥናት አድርጌለሁ። ጌታ የፈቀደ እለት ከዚች ድኩማን ሚስቴ ጋር ፍቺ ማድረጉ የተሳካልኝ እንደሆነ ቀጣዮን ፍቅረኛዬን የምመርጣት በአስተሳሰቧ ሳይሆን በቁመቷ ነው።

አሁን ባለፈው አንድ ህጋዊ ያልሆነ ጥናት ተካሂዶ ነበር። "በአለማችን ላይ ካሉ ሴቶች ሃምሳ ፐርሰንቱ ለአጫጭር ወንዶች ከጋብቻ በፊት ድንግልናቸውን ይሰጣሉ" ይላል። እዚህ ላይ "ሃምሳ ፐርሰንቱስ?" የሚል ጥያቄ መነሳቱ አይቀሬ ነው። "ሃምሳ ፐርሰቱማ አጫጭር ሴቶች ስለሆኑ እንዲህ በዋዛ ድንግልናቸውን ከጋብቻ በፊት አይሰጡም" ይለናል። ጥናቱ ሲያጠቃልል ከአጫጭር ሴቶች ይልቅ ረዥም ሴቶች በዚህ ጉዳይ ላይ ተላላ መሆናቸውን ይገልጻል። ያም ሁኖ እንደኔ አጭር አግብቶ ነዶ ከመሞት ከነድከመታቸው ሎጋ ሴቶችን ማግባት ይሻላል ብዬ አስባለሁ።

ዝም ብለህ ብታሰበው አለም የምትመራው በነዚህ አጫጭር ሰዎች ነው። ሀብቱም፣ ስልጣኑም፣ ዝናውም፣ ክብሩም የነሱ ነው። ይሄን ስልህ አንድ ረዥም ፕሬዝዳንት ወይም አንድ ረዥም ባለሀብት በአይምሮህ ብልጭ ካለ አትጠራጠር ከዚያ ሰው ጀርባ አንዲት ድንክዬ ሴት አለች። እኛ አገር እንኳን በተከታታይ የነገሱትን መንግስታት ብትመለከት ስልጣን የአጫጭር ሰዎች ርስት መሆኑን ትረዳለህ።

እንዲህ አይነት በስሜት የተሞላ ጅምላ ጨርስ መደምደሚያ ላይ እንዲደርስ ያደረገኝ ሰሞኑን ከአንድ አጭር ጓደኛዬ ጋር በመጋጨቴ ምክንያት ነው። ይሄ ተንከሲስ ጓደኛዬ (ሰሙን መላዕከ ሞት ይጥራውና) ከስሬ ዲከ ዲከ እያለ የሚያሳየኝ የንቀት ፊት በቃላት የሚገለጽ አይደለም። መቼም በአካል ብታውቁት "እንዲህ ያለ ድንክ ሰውዬ ይሄን ሁሉ ተንኮል፣ ይሄን ሁሉ ጉረኝነት፣ ይሄን ሁሉ ትዕቢት፣ ይሄን ሁሉ ክፋት እንዴት አድርጎ ቻለው?" ትላላችሁ።

ይሄው ልጅ በቅርቡ ጉቦ በልቶ ቴሌቪዥን ገዝቷል። ማታ ማታ ቤቴ ቴሌቪዥን ስለሌለኝ እሱ ቤት እየሄድኩ ፊልም ማየት ጀምሬ ነበር። ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ግን ልክ ሲኒማ ቤት የከፈተ ይመስል ቤቱ ሰሄድ አለቅጥ ይገላምጠኝ ጀመር። መቼም ረዥምነቴ የዋህ ስላደረገኝ ትናንት ባደረገኝ ነገር ቂም መያዝ አይሆንልኝም።

ከሆነ ቀን በኋላ ጭራሽ "ፍራሼን እየገደልከው ስለሆነ ዱካ ላይ ተቀመጥ" ብሎ ሲለኝ ያኔ ነበር ወስኜ ከቤቱ መቅረት የነበረብኝ። የገለባ ፍራሽ ምን ህይወት ኑሮት እንደምገድለው እማዜር ይወቅ? ደሰ ያለው ቀን ደግሞ እሱ ዜና ሰምቶ ሲጨርስ አሪፍ ፊልም እያየሁ ባለሁበት "ልተኛ ነው ድምጹን አጥፋና በምስል ተመልከት!" ይለኝና ስሜቴን ጎድቶት ያንቀላፋል።

ያም ሆኖ አፍ አውጥቶ "እቤቴ አትምጣ" እስኪለኝ ድረስ ቤቱ እየሄድኩ መረጃ የመቃረሙን ጉዳይ ገፍቸበታለሁ። በርግጥ ቻናል የመቀየር መብት የለኝም። ድንገት ሳት ብሎኝ ቻናሉን ከቀየርኩት "ተው እንጂ ከአለም ተጨባጭ ሁኔታ ጋር አብሬ ልጓዝበት" በማለት ቻናሉን ከ"ቢቢሲ" ወደ "ኢቲቪ" ይመልሰዋል።

አቤት ማካበድ ሲወድ! "ቴሌቪዥን ገዛሁ" ብሎ እንዲህ ያካበደ ራሱን የቻለ የቴሌቪዥን ጣቢያ ቢኖረውማ "እንቅልፌ መጣብኝ" ብሎ እንደ ኢቲቪ "በቴክኒክ ብልሽት ምክንያት" ሳይለን እንኳን ስርጭቱን አቋርጦብን መተኛቱ አይቀርም።

አንድ ቀን ሁሌ የማይሰለቸኝን የቤን ስቲለርን "ናይት አት ዘ ሙዚየም" የሚለውን ፊልም እያየሁ እያለ ፊልሙ ሊያበቃ ሲል ዝናብ ማካፋት ጀመረና ድንገት

ከአልጋው ላይ ወርዶ ቲቪውን አጠፋው።

"ምነው!" አልኩት እንባዬ እየመጣ።

"መብረቅ ያቃጥልብኛል" አለኝ።

እግዜር የፈቀደ ቀን ይሄን ድኩማን ሰውዬ ከነቴሌቪዥኑ በእሳት እንደማቃጥለው እርግጠኛ ሁኜ ከቤቱ ወጣሁ።

ይህ ጓደኛዬ በጣም የሚወደው የቴሌቪዥን ፕሮግራም "እስማማለሁ አልስማማም" ይባላል። ፕሮግራሙን የሚወደው ገንዘብ ወዳድ ስለሆነ ነው። እኔ ደግሞ ፕሮግራሙ ላይ ቅሬታ ባይኖረኝም ዝግጅቱ ላይ ሳጥን ይዘው ለአንድ አጭር ተጋባዥ የሚያጨበጭቡትን ረዣዥም ሞደሎች ሳይ ውስጤ ይረበሽብኛል። እነዚያን ሚስት ሊሆኑ የሚችሉ ሎጋ ሎጋ ሴቶችን የፕሮግራሙ አዘጋጅ ሰብስቦ እጃቸው እስኪግል ድረስ "ሞቅ ያለ ጭብጨባ" እያለ ለሰዓታት ሲያስጨበጭባቸው ሳይ የወላድ አንጀቴ ይንሰፈሰፋል። ድኩማኑ ሰውዬ ግን ይሄን መሰሉን ነገር መታዘብ አይፈልግም። ትኩረቱ ያለው "ተጋባዡ እንግዳ ስንት ብር አሸነፈ?" የሚለው ላይ ነው።

አንድ ቀን ፊልድ ላይ ሁኜ ደወልኩለት።

"ሄሎ" አለኝ። በስልኩ ውስጥ አጭሩ የፕሮግራም መሪ ረዣዥም ሞደሎቻችንን "ለዳሽን ቢራ ሞቅ ያለ ጭብጨባ" ሲላቸው ይሰማኛል።

"ፊልድ መሽቶብኝ ስላደርኩ ቤቴ እንዳይሰረቅ ነቅተህ ጠብቅ!" አልኩት።

"አትሰጋ ጥቅስ ማን ይሰርቃል ብለህ ነው!" አለኝ በፌዝ ልሳን።

"የትምህርት ማስረጃዬስ ቢሆን!" አልኩት በቴሌቪዥን ባለቤትነት እንጂ በትምህርት ደረጃዬ ከሱ የተሻልኩ መሆኔን ለማስታወስ።

"አቦ አትጨቅጭቀኝ! ለራሴ እስማማለሁ አልስማማም የሚያጨናንቀኝ አንሶ ምን ያደርቀኛል!" ብሎ ስልኩን ጆሮዬ ላይ ዘጋብኝ።

*****

ከመስከ ከተመለስኩ በኋላ "እስማማለሁ አልስማም" በሚጀምርበት ሰዓት ቴሌቪዥን ለማየት ቤቱ ሄድኩኝና "ዱካው ላይ ተቀመጥ" አለኝ እሱ አልጋ ላይ ሁኖ ቴሌቪዥኑን አሻግሮ እያዬ። ያኔ ወጥቼ ብሄድ ምን ነበረበት? ግን አላደረኩትም።

ጠባቧ ዱካ ላይ ሁኜ ረዥም ወገቤ የሚደገፈው አጥቶ እየተቅለበለበ ድኩማኑንና ቴሌቪዥኑን በየተራ እያፈራረኩ እከታተል ጀመር።

"የምትፈልገውን ቁጥር መጥራት ትችላለህ" አለ የፕሮግራሙ አዘጋጅ።

"አስራ ዘጠኝ ብለህ ገብሬልን ጥራ!" አለ አልጋው ላይ የተቀመጠው ቀትረ ቀላል ጓደኛዬ።

በቲቪው የሚታይ ሰውዬ ሰባት ቁጥርን ጠራ።

"ስላሶችን መጥራት ይሻላል ብለህ ነው?" አለ አልጋውን እያንቋቋ።

ሳጥኑ ሲከፈት ሀያ ሺ ብር ወጣ።

"የት አባክ! ደግ ሆነሃል ገብሬልን ጥራ እያልኩህ" አለና በስሜት ከአልጋው ወርዶ ፍራሹ ላይ ተቀመጠ።

"እሺ ቀጣዩን ቁጥር ጥራ" አለ አዘጋጁ።

"አስራ ሁለት በል! ሚካኤል ጥሎ አይጥልህም!" አለና ምራቁን ጆሮዬ ላይ ለጠፈብኝ።

"አስራ ሶስት" አለ ሰውዬው።

"የራስህ ጉዳይ! የምልህን ካልሰማህ!" ብሎ ተመልሶ አልጋው ላይ ወጣ።

ሳጥኑ ሲከፈት አስር ብር ሆነ።

"አሁን ገና አደረከለት!" አለ በደስታ ተሞልቶ።

የፕሮግራሙ አዘጋጅ በፕሮግራሙ መሃል "ለኮካኮላ ሞቅ ያለ ጭብጨባ!" በማለት አዘዘ።

ጓደኛዬም አብሮ እያጨበጨበ እያለ ቴሌቪዥኑ ጠፋ። በድንጋጤ ተነስቶ ሶኬቱን ነቅሎ መልሶ ቢሰካውም ቲቪው ሊበራ አልቻለም። ፊቱ ላይ የድንጋጤ መስመር ተሰመረ።

"እስኪ አሁን ምን ሆነ ይባላል?" አለኝ እኔን እኔን እያዬ።

"ተቃጥሎ እንዳይሆን" አልኩት።

"ጨጓራህ ይቃጠል" ብሎኝ ብልሹቱን ከጀርባ በኩል ይፈልግ ጀመር። ቢያገላብጠውና ቢያሻሽው አልሰራ ሲለው ቲቪውን ጎኑ ላይ በጥፊ መታው። ድምጹ መጣ። ምስሉ ግን ሊመጣ አልቻለም። እንኳን ባንድ መዳፍ "እስማማለሁ አልስማማም" ላይ የሚያጨበጭቡ መዳፎች ቴሌቪዥኑ ላይ ቢያርፉ እንኳን ምስሉ የሚመጣ አይመስልም።

"እግርህን ወደ ሶኬቱ ልከህ ነበር እንዴ?" አለኝ የብልሹቱ ምክንያት አልገባህ ቢለው።

"ማን እኔ? እረ የልጅነት አበባዬ ይርገፍ" አልኩት በየዋህነት።

"የትኛው አበባህ ነው የሚረግፈው?" አለኝ።

"እንደት አበባ የለኝም?"

"የለህማ! ነው ወይስ በልጅነትህ የወር አበባ ታይ ነበር?" እያለኝ እያለ ጓደኛው ከውጭ መጣና ሊያረጋጋን ሞከረ። ይሄ ድኩማን ግን በቅጽበት ውስጥ ምን እንዳሰበ አላውቅም በነገር ያጣዘኝ ገባ።

"አሳሳች! ሰውን ለማሳሳት እንጂ አቅም ኑሮህ አይደለም" አልኩት በንደት ቦግ ብዬ።

"በረዘመ መሰለህ እንዴ? ዋ! እንዳልገነድስህ!" አለኝ የጓደኛውን መኖር እያረጋገጠ።

"አንተ ነህ እኔን የምትገነድሰኝ? አንተ ድኩማን!" በንደት ብው አልኩላችሁ።

"ዋናው እኮ ልብ ነው! ረዥም ሰው ወይ ሱሪ ወይ ቁመት ያጥረዋል ሲባል አልሰማህም?" አይለኝም።

ሰማይ ልሁን መሬት አላውቀውም ብቻ ሪሞቱን አንስቼ ግንባሩን አልኩትና ሌላ የመማቻ ቁሳቁስ ስፈልግ ጓደኛውን "እማኝ ነህ!" አለውና ተፈትልኮ ወጣ።

በኋላ ነው ለቴሌቪዥኑ ማሰሪያና ለአንዳንድ አስቤዛዎች ማሚያ እንዳመቻቸኝ የገባኝ።

በወረወርኩት ሪሞት ሳቢያ ግንባሩ ላይ የተፈጠረችውን ነጥብ የምታክል ቁስል እስከ አይኑ ድረስ በፋሻ ግጥም አድርጎ አሳሽጋትና ከሰሰኝ። ሁኔታውን ሳዬው ምስክሩም አጭር፣ ዳኛውም አጭር ሲሆኑብኝ ጉዳዩን በሽምግልና መቋጨት

ፈለኩኝ። የአጭሩም ሰው አላማ ይሄው ነው።

እናም በመጨረሻ ሽማግሌዎች የወሰኑብኝን ካሳ ክሼው በኔ ገንዘብ ቴሌቪዥኑን አሰርቶ "ራኒ" ማንነውን እየጠጣ "እስማማለሁ አልስማማምን" ከፍቶ እያዬ "አሰራ ሁለትን ጥራ! ሚካኤል ጥሎ አይጥሉህም" እያለ ሲጮህ "የሚዳው ሚካኤልዬ ይሄንን አጭር ሰውዬ ከነ ቴሌቪዥኑ በመብረቅ ያቃጠልከልኝ እንደሆነ ጃንጥላ አመጣልሃለሁ" እያልኩኝ እሳላለሁ። ይሄው ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የሰውን ስብእና የምለካው በጭንቅላቱ ሳይሆን በቁመቱ ነው።

በትር

ሙሴ ባለ በትር ሙሴ ባለ ገድል
በሰበራ አጣና ባህር የሚከፍል
አየ የኛ ዘመን አየ የኛ ሕይወት
መፈጥፈጥ ነው እንጂ ማረግ የቀረበት
መንፈስ ያልነበኘው የኔ መልፍጥ ዱላ
አንኳን አባብ ሆኖ ሰከና ሊበላ
መሰንጠቁ ቀርቶ ባህርን ለሁለት
በገዛ ዱላዬ አለሁ ሰፈነከት።

ከአምላኬ ጋር

ፈጣሪ ጋር ትግል መግጠም የምፈልግ ሁሉንም ሱሶች የምጠቀም ደባል ነበርኩ። ስጠጣ ወሰን አልነበረኝም። የምጠጣበት ገንዘቤ ወይም የምጠጣበት አቅሜ ካላበቃ በቀር ወደ ቤቴ አልገባም። በዚህም የተነሳ ስካሬ ትዝታ አልባ ነበረ። ከሆነ ቅጽበት በኋላ ያደረኩትን ነገር ማስታወስ አልችልም። ያም ሆኖ ፈጣሪዬ አቅፎና ደግፎ ወደ ድንኳኔ ያስገባኛል።

የተለየ አምላክ ነው ያለኝ። እየፈተንኩት ምድር ላይ ካሉ ፍጥረታት ሁሉ አልቆ ይወደኛል።

ወዳጄ ሆይ እንደ እኔ አምላክህን ማግኘት ከፈለክ የሀይማኖት አባቶች በሚመሩህ ሳይሆን በእራስህ መንገድ ፈልገው። ጾለት ከማድረግህ በፊት አምላክህ እየሰማህ መሆኑን አረጋግጥ። የብቻህ ጾለት የብቻህ ስለት ይኑርህ። ጅምላው ጋር አትክነፍ። እነሱን በመከተል አምላክን ማግኘት ቀርቶ እራስንም ማወቅ አይቻልም። "መሪ ነን" የሚሉት ራሳቸው አምላካቸውን መቼ አገኙ። እነሱን የተከተልክ እለት አምላክህን ማጣት ትጀምራለህ። የሚያወሩት ሌላ፣ የሚሰሩት ሌላ መሆኑን ድርጊታቸውን በማየት ያወክባቸው ቀን "ቃሉን እንጂ እኔን አትመልከት" በማለት ሊሸነግሉህ ቢሞክሩም ከመጠራጠር አትድንም።

እኔ ልንገርህ፤ ሳይኮሎጂስት፣ ሳይንቲስት፣ ቲወሎጂስት፣ ሙህር፣ ፓስተር፣ መምህር፣ ወዘተ የምትላቸው ሰዎች እንዴት ማፍቀር እንዳለብህ፣ እንዴት ማመን እንዳለብህ፣ እንዴት መኖር እንዳለብህ ሊነግሩህ ይፈልጋሉ። "የምትፈልጋትን ሴት፣ የምትፈልገውን ስኬት፣ ያጣኸውን አምላክ ለማግኘት የሚረዱ አስር ወሳኝ ምክሮች" ብለው ይጽፉልሃል። በነሱ ጽሁፍ አንኳን አንተ እነሱም ስኬታማ መሆን አልቻሉም።

በእነሱ ምክር አንኳን አንተ እራሳቸው ጸሃፊዎቹ ፍቅረኛቸውንም አምላካቸውንም ማግኘት አልቻሉም።

ምናልባት የእነሱ ምክር ራሳቸውን ስኬታማ ካደረጋቸው እንኳን ያ መንገድ ለእነሱ ብቻ የተፈቀደ ነውና በነሱ ቦይ አትፍሰስ። ምዕራፉን ሸምድደው፣ ቃሉን ሰብከው ከሚኖሩት ይልቅ ቃሉን ተግብረው፣ ቃሉን ጠብቀው የሚኖሩት ጋር ተወዳጅ።

ወንድሜ ሆይ እራስህንም፣ ተሰጥህንም፣ ፍቅረኛህንም፣ አምላክህንም ስትፈልግ በራስህ መንገድ ይሁን።

"በጾም በጾለት ያጣሁትን አምላኬን በስካር መንፈስ አገኘሁት" ብልህ ታምናለህ? እንዲህ ስልህ ጠጥተህ አምላክህን ፈልገው እያልኩህ አይደለም። እኔ የምልህ በፈለከው ሁኔታ ውስጥ ሆነህ፣ በፈለከው ቦታ ሆነህ፣ በምትፈልገው ቋንቋና ቃል ተጠቅመህ "ጌታ ሆይ" ብለህ ጥራው ነው። ብቻ ግን ፍለጋህም፣ ጾለትህም ከልብህ ይሁን።

እንዳልኩህ ማታ የሰራሁትን ቀን የማስታውስ ሰው አልነበርኩም። እራሴን እስክስት ድረስ ስጋት አመሽና ልወቅሰው ይዳዳኛል። የሚገርመው ግን በዛ ሁኔታ ውስጥም ሁኜ ከሰው ጋር ከማውራት ይልቅ እሱው ጋር ማውራትን እመርጣለሁ።

ቢራን የመሳሰለ ቀላል መጠጥ ውሃ ማቆር ስለሚሆንብኝ አይመቸኝም። የኔ አልኮል ቀመሩ ይሄን ይመስላል። ጅን+አምቦውሃ+በረዶ+ሎሚ= ከሀያሉ ፈጣሪ ጋር የሚያጋጭ ሀያል ስካር።

"ወንድ ከሆንክ ና ግጠመኝ!" አለዋለሁ። ጸጉሬን እያሻሸ ወደ ቤቴ ያስገባኝና አዳም ላይ የጣለበትን አይነት እንቅልፍ ጥሎብኝ "ደህና አደር" ብሎኝ ወደ ከፍታው ያርጋል።

ልክ ከእንቅልፌ እንደነቃሁ መጀመሪያ ራሴን በማወዛወዝ የራስ ምታቴን ልክ እለካለሁ። ቀጥሎ ማታ የጠጣሁትን የመጠጥ ልክ ለማስታወስ ጥረት አደርጋለሁ። እንደተለመደው ስንት ጠጥቼ እንደገባሁ ማስታወስ ያቅተኛል። "እንዴት እንደዚያ ማስታወስ እስኪያቅተኝ ድረስ ጠጥቼ ቤቴ ገብቼ መተኛት ቻልኩ" ብዬ ግን እራሴን ጠይቄ አላውቅም። ምክንያቱም እሱ ከነኔ እንደማይለይ አውቃለሁና። በባዶ ሆዴ ሲጋራዬን አጨስና ሁለት የተለያዩ ካልሲዎችን አድርጌ ወደ ሆቴል ቤት በማምራት ቁርሴን በዱቤ በልቼ እወጣለሁ።

አንድም ቀን በእቅድ ተመርቼ አላውቅም። እኔና አምላኬ የምንጣላው እቅድ ያወጣሁ ቀን ነው።

"ምን አገባህና?" ይለኛል።

"አይ በራሴ እቅድ ነው የምመራው" ብዬ ካልኩት መሰናክል ደርድሮ ይጠብቀኛል። የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅዱን ያቀድኩት እኔ ብሆን ኑሮ ይሄኔ በርሃብ አልቃችሁ ነበር።

አስቤዛዬን የሚሸምተው እሱ፣ ልብስ የሚገዛልኝ እሱ፣ እስከሞት ድረስ ለመስከር ሳስብ ዘደ ፈልጎ ቤቴ የሚያስገባኝ እሱ ነው።

ከእግዚአብሄር ይልቅ የልቤን የማያውቀው መንግስት ያስፈራኛል። አምላኬ የንዴት ማብረጃዬ ነው። መንግስትም ጋር ልጣላ ህዝብ ጋር፣ ግለሰብም ጋር ልጣላ አገሬ ጋር፣ ተንደርድሬ አምላኬን መወረፍ ይቀለኛል። ግጥሜ ሁሉ እሱን በመውቀስ ላይ የተመሰረተ ነው። ቤት መትቼ እንደጨረስኩ "በሰጠሁሽ አቅም ልክ ሞክረሻል" ብሎ ያጨበጭብልኛል።

"ለምን የፈርኦንን ልብ አደነደንክ?"

"ትንቢትህ ይሳካ ዘንድ ይሁዳን ከፈጠርከው በኋላ ለምን ጥፋተኛነት ይሰማው ዘንድ ፈረድከበት?" ወዘተ ወዘተ እለዋለሁ። "ባትደርሽበትም እስኪ ትንሽ ተመራመሪ" ብሎ ፈገግ ይልልኛል። አቤት ..ኝ እኮ! ልክ እንደ ጓደኛው ነው የሚያየኝ።

ጥፋት የሰራሁ ቀን ደግሞ እንዲህ አለዋለሁ።

አትዘን ወዳጄ አይከፋህ ጌታዬ
ሀጥያት ቢሆንብህ
ብላሽ ከንቱ ነገር ምግባሬ ሰራዬ፣
አንተ ፍጹም ጌታ አልፋና ኦሜጋ
አንተን መሰል አምላክ ልፈጥር ሰተጋ
በአምሳልህ ያነጽከው ሲቋጭ የእጅ ሰራህ
አንደ አዬ ሰው አንጂ መቼ አማዜር ሆነልህ? አለዋለሁ።"

ይስቃል። "በርካታ እኔን መሰል ፈጥሬ አለምን በኮሚቴ ብመራት ምን የሚሆን ይመስልሃል?" ብሎ ይጠይቀኛል።

"እኔ እንጃ!"

"ተመራመር እንጂ"

"እትመራመሩ አላልከኽም እንዴ?"

"ተመራመር! ከአቅምህ በላይ የሆነን ነገር ላትደርስበት ነገር ስትጨናነቅ ይህች ስስ አይምሮህ እንዳትበላሽብህ በማለት እንጂ የኔ ቃል ባንተ ምርምር የምታፈርሰውና የምትንደው ህገ-መንግስትህ አይደለም" በማለት ያወራኛል።

"ፖለቲካውን ተወውና ሌላ ጥያቄ ልጠይቅህ?" አለዋለሁ።

የምጠይቀውን ስለሚያውቅ ፈገግ ይልና "እሺ ጠይቀኝ" ይለኛል።

"ቀድመህ የጻፍከውን ነው የምኖረው ወይስ ነጻ አድርገህ ፈጥረኽኛል?"

"እትልፋ አንተን የማስተዳድርበት ራሱን የቻለ ህግ አለኝ"

"ንገረኛ!" አለዋለሁ ጥያቄዬን አድበስብሶ ሊያልፈው ሲል።

"ይሄን ማወቅ አይጠቅምህምና ሌላ ጥያቄ ከሌለህ ማረጌ ነው!" ይለኛል።

"ሲኦል ትከተኝ ይሆን?"

"አንተን?"

"አዎ እኔን"

"እይውልህ ሰማይ ቤት ላይ ፍርድ የምፈርድብህ እኔ ሳልሆን እዚህ ምድር ላይ ገፍተህ የገደልካቸው ሰዎች ናቸው። ጥፋት ካጠፋህ ጉልበቷን በዝብዘህ የገደልካት ሰራተኛህ፣ ደፍረህ የገደልካት ጨቅላ ህጻን፣ ሰው አላየኝም ብለህ ማንጅራቱን ቀልተህ የጣልከው ምስኪን፣ የእለት ጉርሳቸውን ሰብስበህ የተንደላቀቀ ኑሮህን ያሳካህባቸው በእራብ የሞቱ ሰዎች እነሱ ናቸው ፍርድህን የሚሰጡህ! ያም ሆኖ ሲያል የምትለው ነገር ካንተ ኑሮ የከፋ አይደለም" ብሎ ይስቅብኝና ጸጉሬን ዳበስ አድርጎኝ ይሰወራል።።

አንዳንደ ከመጠን በላይ በድግግሞሽ በተሞላው ህይወቴ በጣም ይመረኛል። በጠዋት እነሳና አልኮል አልኮል በሚሸተው ትንፋሼ፣ ሲጋራ ሲጋራ በሚሸተው ገላዬ፣ በስልችት በተሞላው መንፈሴ፣ ለውጥ በሌለው ህይዎቴ እበሳጭና "በአንተ እቅድ እየተመራሁ በቃ ልትገለኝ!" ብዬ አለቅሰበታለሁ።

"አልገልህም! ግን ትንሽ ታገሰኝ"

"የምታገስህ እስከ መቼ ነው?"

"አንተ እስክትበስል ድረስ!"

"ከመብሰልም አልፎ አረርኩልህ እኮ ጌታ ሆይ!"

"እንግዲህ እኔና አንተ የምንጣላው ልትሸውደኝ ስትሞክር ነው። የምትጓዝበትን መንገድ አንተ ራስህ መቼ ጠገብከውና ነው አረርኩ መረርኩ የምትለኝ?" ይለኛል።

እውነቱን ነው ስካር ሳይሆን የሰለቸኝ ህንጎሮር ነው። ሱስ ሳይሆን የሰለቸኝ ለሱስ የማወጣው ወጭ ነው።

ሁኔታው ግርም ይለኝና "እኔው ራሴ የምጠየፈውን ሰው ለምን ወደድከኝ ጌታ ሆይ?" አለዋለሁ።

"ስለማታስመስል ነዋ! በራስህ መንገድ ስለፈለከኝ ነዋ! ስለማትፈራኝ ነዋ! ግልጽ ስለሆንክ ነዋ! አየህ ልጄ ወደ ደጄ ነጠላቸውን አጣጥለው፣ ጀለቢያቸውን ለብሰው፣ መስቀሌን ተሸክመው፣ ቅዱስ ቃሌን ሸምድደው በመምጣት ህዝቤን የሚሸውዱት አንሶ እኔንም ሊሸውዱኝ የሚሞክሩ በርካቶች አሉ።

ወደ ቅጽሬ ሲገቡ አንገታቸውን ደፍተው ጨዋ ሊመስሉኝ ይሞክራሉ። ከደጄ አለፍ ሲሉ ደረታቸውን ገልብጠው ወደ መመዝበራቸውና ወደ አመንዝራነታቸው ይመለሳሉ። እኔው በፈጠርኳት መሬት የድርሻዬን ከፍለው ለኔው ሊሰጡኝ ይሞክራሉ። እነሱ ከከለሉት ቅጽር ውጭ እኔ የሌለሁ ይመስል ያሻቸውን ያደርጋሉ። በሊዝ መሬት ከልለው እንደሚሸጡት ሁሉ ለኔም ሊከልሉልኝ ይጥራሉ። ይሄን የሚያደርጉት እንግዲህ "መሪ ነን" የሚለት ሰዎች ናቸው። ምእመኑ እንዳይጠይቃቸው እኔንም እነሱንም "ለምን" ብሎ የጠየቀ እለት መብረቅ እንደሚዘንብበት ሊያስተምሩት ይሞክራሉ።

"ምዕመናን" የምትለው መንጋ ደግሞ እኔ ባበጀሁት ልብ ውስጥ ሚስጥሩንና ተንኮሉን ደብቆ 'ተመስገን' ብሎ ሊሸውደኝ ይሞክራል። ሰው ብሉቱን፣ መከራውን፣ ግርታውን ለአምላኩ ካተናገረ ለማን ይናገራል። አንድ ቀን ያማረረኝ እንደሆነ በቁጣ የምነድ አድርገው ያስባሉ። በጣም የሚገርመኝ ነገር ደግሞ ምዕመኑም የሚሉትን ነገር ሰምቶ ትንሽ ቅሬታውን ለእኔ የገለጸ እንደሁ ንፍር ውሃ የምደፋ ከአፍሪካ መሪዎች የባሰኩ አምባገነን አድርገው ሲያስቡኝ እንዴት አዝናለሁ መሰለህ!"

"እናም ልጄ ሆይ አንተን የምወድህ ለዚያ ነው። የመረረህ ቀን መረረኝ ትለኛለህ፣ የደላህ ቀን ተመስገን ትለኛለህ፣ የፈጠርኳቸው ፍጡራን ሲረብሹህ እነሱን ከመጋፈጥ ይልቅ፣ በጠለፉህ ልክ ከመጥለፍ ይልቅ፣ በሸረቡልህ ሴራ ልክ ሴራ ከመጎንጎን ይልቅ ለእኔ አሳልፈህ ትሰጣቸዋለህ። በተጨማሪም ደግሞ እንዳንተ አይነት እንደ ጓደኛው የልቡን የሚያጫውተኝ ሰው እወዳለሁ። እኔም እኮ ሰው ይናፍቀኛል። አንድ እንኳን ነቢይ፣ አንድ እንኳን ልበ-ቀና አጥቼ እረኛ እንደሌለው መንጋ ከተውኳችሁ ስንት ዘመን ሞላኝ መሰለህ! ያንተ ስካር የሚጎዳህ ራስህን ነው። እንኳን አንተን ቀርቶ በቃሌ ከሚነግዱት፣ በስሜ ገንዘብ ሰብስበው በስማቸው ከሚከፋፈሉት የሀይማኖት አባቶች ጋራም እኖራለሁ። እንደሌለሁ ቆጥረው ቤቴ ውስጥ ሲዶልቱብኝ እያየሁ አልፋቸዋለሁ። አንዳንዱ ሞኝማ፣ ታቦቴንም ለመስረቅ "አሳካልኝ" ብሎ ስለት የሚሳልልኝም አለ ይልና ይስቃል። እሱ በሳቀ ቁጥር አንዳንድ ቆንጆ ሴቶች ከማህጸን ይወጣሉ።

እኔን አምኖ እኔን ሰው ብሎ፣ እኔን ወዶ ይሄን ሁሉ ነገር ሲነግረኝ ልቤ በፍቅሩ ጥፍት ይልና "እኔም እኮ እወድሃለሁ!" እለዋለሁ

"እሱን አውቃለሁ። ግን ራስህን አትናቅ! ለምን እኔን መረጠኝ ብለህ አትወዛገብ! አንተ ጋር ለመዋል ግልጸኝነትህና ትህትናህ በቂዬ ነው። እስኪ በገንዘቡ እና በዘሩ ብዛት የመረጥኩትን ንገረኝ?" ይለኛል።

አስቤ፣ አስቤ፣ አስቤ ጌታ የመረጣቸው ሁሉ በትህትናቸው፣ በትዕግስታቸው፣ በልብ ቀናነታቸው የተመረጡ ይሆኑብኝና "እሱስ እውነትህን ነው" እለዋለሁ።

"ሌላስ ጥያቄ አለህ?"

"የለኝም ጌታ ሆይ"

በእጆቹ ዳበስ ያደርገኝና ወደ ከፍታው ይዘልቃል።

እሱ ከጎኔ ሲርቅ ወደ ደባልነቴ፣ ወደ ጡዘቴ እመለሳሁ።

ያም ሁኖ የእኔኑ አይምሮ እኔው ማስተዳደር፣ የእኔኑ ልብ እኔው መምራት ሲያቅተኝ "ኧረ ተው ጌታ ሆይ ተው! ያላንተ እገዛ ብርቱ የሆነ፣ ያላንተ ንፍገት ደካማስ የሆነ ማነው?" ብዬ አማርረዋለሁ።

ከእለታት አንድ ቀን ስራና የስራ ቦታ በቀየርኩ ማግስት አምላኬ አለወጥ ዘንድ ፈቀደና በከባድ እንቅልፍ መታኝ። ከእንቅልፌ ስነቃም ሽሙንሙን ያለች

እርቃን ሴት አንሶላዬ መሃከል ከንዴን ተንተርሳ አይን አይኔን ስታየኝ አገኘኋት። ተንጠራርቻ ከጠረጴዛ ላይ የማጨሰው ሲጋራ ላነሳ ስል በሲጋራው ፈንታ ጡቶቿን አስጨበጠችኝ።

እንዴት እንደወደድኳት፣እንዴት እንዳገባኋት፣እንዴት እንዳስረገዝኳት አላውቅም።

በአልኮል ፈንታ ሾርባ ስጠጣ እራሴን አገኘሁት።

በሲጋራ ፈንታ ጥርስ አልባው ልጄ አንገት ውስጥ አፍንጫዬን ወትፌ ልሃጩን ሳሸት ተገኘሁ።

እናም እንላለን፡-

"ወንድሜ ሆይ አምላኩን ያላገኘ ሰውና ትዳር ያልመሰረተ ሰው ደስታን አያውቃትም! ምክንያቱም 'መጽሃፉ ሰው ብቻውን ይኖር ዘንድ መልካም አይደለም!' ይላልና።"

ኮንፈረንሱ

ሰብሰባ ውስጥ ነኝ...
አብድ የሚያህል እንቅልፍ አያንደባለለኝ።
"ሰበሰብኩት" ብሎ ሰብሳቢው ይጮኻል፣
ብኩን ጭንቅላቴ እንኳን ከሰብሳቢ
ከራሴም ቁጥጥር ካመለጠ ከርሟል።

እንኳን አዚህና...
ቤተሰኪያን ደጅ ላይ በሚቆረብበት፣
ቤተሰኪያን ደጅ ላይ በሚፀለይበት፣
ቤተሰኪያን ደጅ ላይ በሚሰገድበት፣
ቤተሰኪያን ደጅ ላይ...
ይቅርታና ምህረት በሚለመንበት፣
መረን አይምሮዬ ያለ ትዕዛዝ ነጉዶ
ያሴረዋል ሴራ ይሰራዋል ሃጢያት፣
አ ቤ ት!
ማሰብ፣ ማሰብ፣ ማሰብ
ማማተብ፣ ማማተብ
/አ ጀ ብ/
እንዲህ አይነቱን ሰው አዳራሽ አጉሮ
እንቅልፍ እንደ አርጅና በገላዬ ሰፍሮ
አሰሬ ሰብሳቢው ድምጹን እየሳለ
"ወትሮም ታጋይ እንጂ ትግል አይሞት" እያለ

.....ሲጮህ አሰማለሁ፣
እኔ በእንቅልፍ ልብ እንደዚህ አላለሁ።

"እውነት ነው...እውነት ነው
'ወትሮም ታጋይ እንጂ ትግል አይሞትም' ያልከው።
ቅድመ አያቴ ታጋይ፣ አያቴም ያው ታጋይ
ለማያቀው ሰላም ለማይወርድ መሲህ በባሩድ የሚጋይ
አንተን መሰል መሪ በምትፈለፍል በዚች ሶስተኛ አለም
ትግልን ከመውረስ ውጭ ሌላ አማራጭ የለም
አያቴ አድሜ ልኩን ታግሎ የሸመውን
አባቴ አድሜ ልኩን ታግሎ አያወረደው
አንተ ታላቁ ሰው አሰቀድሞ እንዳልከው
ወትሮስ ታጋይ እንጂ ምኑን ትግል ሞተው?"

የአዳራሹ ግድግዳ በመፎከርና በአቋም መግለጫ ተሞልቷል።

ፊት ለፊት ያለው ግድግዳ ላይ "ራዕዩን እናሳካለን" የሚል ጥቅስ ተለጥፏል። ራዕዩ የመለስ ይሁን የዮሃንስ የታወቀ ነገር የለም። ዝቅ ብሎ ደግሞ መጭው ጊዜ ከመንግስታችን ጋር ብሩህ መሆኑን የሚያስረዳ ጽሁፍ ሰፍሯል። ይሄን የሚለው የላይኛው መንግስት እንጂ የኔ ሊቀመንበር እንደሆነ መጭውን ጊዜ ቀርቶ ዛሬንም ሊያጨልምብኝ ካሰበ ሰንበትበት ብሏል።

የስብሰባ አዳራሹ ውስጥ ፊት ካለው መቀመጫ ላይ የውሃ ኩዳ በእጃቸው የያዙና መነጽር ያደረጉ "አንዳንድ" የቀበሌችን ነዋሪዎች ታድመዋል። እኒህ "አንዳንዶች" ውሃውን መቼ እንደጠጡት ተሰብሳቢው የሚያውቀው ነገር የለም። "አንዳንዶቹ" መነጽሩን ያደረጉት ጋዜጠኛ ኢንተርቪው በሚያደርጋቸው ሰዓት ከዐይናቸው ላይ የሚፈልቀውን የማይፈለግ ውዝግብ ከካሜራው እይታ ለመደበቅ መሆኑ የተረጋገጠ ነገር ነው።

ዛሬን መኖርን ትቶ፣ መጭውን ጊዜ በተስፋ መጠበቅን ዘንግቶ፣ በትናንት ትዝታ ውስጥ በሚዳክር አይምሮ ውስጥ ተወጥሬ የባጥ የቋጡን እያነሳሁ ስጥል እሳት የላሰ የፕሮግራም መሪ ወደ መድረክ ወጥቶ "ማይክራፎኑ" መስራቱን በትንፋሹ ከፈተሸ በኋላ ማውራት ጀመረ።

ያለምንም ማጋነን ፕሮግራም አስተዋዋቂ የተባለው ሰውዬ ሙሉ ፕሮግራሙን

አውርቶ ጨርሶታል ማለት ይቻላል። ለረዥም ጊዜ ከእያንዳንዷ ድርጅታዊ ጋዜጣና መጽሄት የለቀማትን ፖለቲካ ሲደሰኩርብን ከቆየ በኋላ ወደ መድረክ ጋሽ ውሴንን ጋበዘ።

የቀበሌችን አስተዳዳሪ ጋሽ ውሴን ለረዥም ጊዜ በሰልጣን ስላሳለፈ አዕምሮው ዝጓል። የማይመለሱ ጥያቄወችን ሲመዝገብ፣ የማይተገበሩ መልሶችን ሲመልስ ይሄው የአንድ ወጣት እድሜ ሆነው።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን እርጅና ባመጣበት ጣጣ "መድረክ እያበላሸህ ነው" የሚል ግምገማና ትችት እየቀረበበት ይገኛል። ጋሽ ውሴን መድረክ እየመራ "አንዳንድ" የሚባሉ የወደፊት ተተኪ ባለስልጣኖች "አካሄድ" እያሉ በንግግሩ መሃል ሲያወናብዱት አንዳንዴ ክልብሽ እያለው "እኛ ባቀናነው መድረክ በነጻነት መናገሪያ እንጣ እንዴ?" እያለ ይበሳጫል። በዚህ በኩል ጋሽ ውሴን እውነቱን ነው! አገር አቅንቷል የሚል አቋም ባይኖረኝም መድረክ ሲያቃና ለመኖሩ ግን ጥርጣሬ የለኝም።

ዛሬም በቀበሌችን ምርጫውን መንግስታችን ስላሸነፈ "እንኳን ደስ አላችሁ" ሊለን መድረኩን ከፕሮግራም መሪው ተረከበና በተሰላቸ መንፈስ ውስጥ ሁኖ ከማስተማሪያነት ባለፈ የቤት ግድግዳ ለመለጠፍ በሚጠቅመው ድርጅታዊ ጋዜጣ በመታገዝ ንግግር ያደርግ ጀመር።

"ከቡራንና ከቡራት የቀበሌችን ህዝቦች" በማለት ንግግሩን አሃዱ አለና ባለፉት አመታት ድርጅቱ ያከናወናቸውን ስራዎች ከዘረዘረ በኋላ ወደፊትም ይሄንኑ ለማስቀጠል ቆርጠን ተነስተናል በማለት በቀጣይ ትኩረት የሚሰጥባቸው ተግባራትን ወደ መዘርዘር ተሸጋገረ።

"የውሃ ተቋማትን በሁለት ኪሎ ሜትር ርቀት ለሁሉም ህዝብ ተደራሽ እናደርጋለን" አለና ስለውሃ ሲያነሳ ውሃ ጠማው መሰል አንዱን ተሰብሳቢ ውሃ ቀድቶ እንድያመጣለት ባዶ ኮዳ አቀብሎት ንግግሩን ቀጠለ።

"በመጭው አምስት ዓመታት የመብራት መቆራረጥን ቀርቶ አምፖል የማይበራበት አካባቢ ሊኖር እንደማይችል" ተናግሮ ሳይጨርስ መብራት ጠፋና አዳራሹ ጨለመ። "አላህ ያዳፍናችሁ" የሚል ቃል ከጋሽ ውሴን አፍ በለሆሳስ አመለጠ። እንዲህ አይነት ከአፉ የምታመልጥን ስህተት በማጉላት ስልጣኑን መረከብ የሚፈልጉ አንዳንድ የቀበሌችን ነዋሪዎች ጋሽ ውሴን የተናገራቸውን ቃላቶች በፍጥነት ማስታወሻቸው ላይ አሰፈሩ።

አንዳንድ ጸረ-ልማቶች ደግሞ የተናገሩት በመድረሱ እጃቸውን አወጡ።

"ምን ሆናችሁ?" አለ ጋሽ ውሴን እጃቸውን በሰይፍ መቅላት እየተመኘ።

አንድ ተቀምጦ የቆመ የሚመስል ረዥም ሰው እድል ሳይሰጠው ተነስቶ መናገር ጀመረ። "እንደምታውቁት ከመንግስት ብድር ወስጄና የቤተሰቦቼን ባዶ ቦታ ሸጬ የጣውላ ቤት መክፈቴን የማያውቅ ተሰብሳቢ ያለ አይመስለኝም" አለና የማያውቅ ሰው ካለ በማለት አንገቱን እያዟዟረ ፈለገ። "ታዲያ የሚገርማችሁ ነገር ማሽኑንና እንጨቱን አዋድጄ መስራት ስጀምር መብራቱ ይጠፋል! "ጠፋ" ብዬ ስራውን ትቼው ቤቴ ስሄድ ይመጣል! እንዲህ እንደ ፔንዱለም ዥዋዥዌ እየተጫወተ ሲያስቸግረኝ ልክ ጠፍቶ እንደበራ በብስጭት ኮረንቲውን ጨብጬ መሞት ስለፈለኩኝ የተላጠውን ሽቦ ተንደርድሬ ያዝኩት። ታድያ ምን ይሆናል ደሜን መጦ ሳይጨርሰው ተመልሶ ጠፋ! እናም አሁን ባለው የመብራት ተጨባጭ ሁኔታ ለመስራት ቀርቶ ለመሞትም አስቸጋሪ መሆኑን ለማስረዳት ነው!" ብሎ ተሰብሳቢውን ፈገግ አሰኝቶ ተቀመጠ።

"ምነው በአናትህ ተከሎህ በነበር!" አለ ጋሽ ውሴን ድምጹን ቀነስ አድርጎ።

ሳቁ ሲረጋጋ ሊቀመንበራችን በረጅሙ ተንፍሶ ያለ ማይክራፎን ንግግሩን ቀጠለ።

"እኔ እኮ ስለ መብራት ምን አድርግ እንደምትሉኝ አላህ ይወቅ! ውሴን ነው ቆጣሪውን የሚያጠፋው ብሎ የነገራችሁ ሰው አለ እንዴ? እንደምታዩኝ መብራት ከጠፋ እኔም ብሆን እንደ አናንተው ኩራዝ እንጂ ጄኔሬተር የለኝም" አለና ወደ 'ሚቀጥለው አጀንዳ አለፈ።

"ባሁኑ ሰዓት ኔትወርኩ የተስተካከለ ቢሆንም ከዚህ በላይ ተደራሽነቱንና ጥራቱን የበለጠ ለማሳደግ ድርጅቱ እንደሚጥር" ተናግሮ ወደ ሌላ ሀሳብ ሊሸጋገር ሲል ስልክ ተደወለለት። ስልኩ የክልል ቢሮ ስለሆነ ይቅርታ እንድያደርጉለት ተሰብሳቢውን አሳስቦ "ሃሎ" አለ።

"ኧረ ሃሎ!"

"ሃሎ"

"ሃሎ እያልኩህ አይደለም እንደ!"

"ኔት ወርክ የለም! አይሰማም አልኩህ እኮ! በኋላ ደውል ነው የምልህ!" እያለ ጎረቤት አገሮች እስኪሰማ ድረስ ቢጮህም ደዋዩ ሊሰማው ስላልቻለ "ምን ይሄ

የተረገመ ኔትወርክ" አለና ሞባይሉን ዘግቶ ወደ ኪሱ መለሰ።

"አካሄድ እንጂ! ኧረ አካሄድ!" አሉ አንዳንዶች አሁን የተናገረውን መልሶ ሲሸረው በመታዘብ።

"አካሃዱ ይጥፋችሁ! የማንም ልቃሚ ትናንት እየመጣ የኖርኩበትን መድረክ ሊያስተምረኝ ይፈልጋል እንዴ?" ጋሽ ውሴን በንደት ብው አለ። አንዳንዶች ሴራ ሲጠነስሱ ፊታቸው ላይ በግልጽ ታዬ። እንደምንም ራሱን አረጋግቶ ወደ አቋረጠው ሀሳብ ሊገባ ሲል "ውሃ አምጣ" ተብሎ የተላከው ሰውዬ "ውሃ የለም" ብሎ ባዶውን ኮዳ መለሰ።

"እንዴት ውሃ የለም?"

"የለማ! ውሃ ከመጣ ወር ሆነው አሉ! እንግዲህ እኔ ከሰማይ አላዘንበው!" አለ የተላከው ሰውዬ ተናዶ።

ጋሽ ውሴን ኮዳውን ተቀብሎ ወደ ጀርባው ወረወረና በደረቅ ምላሱ ኑዛዜውን ቀጠለ። "ስለ ስኳርም ቢሆን አርባ ጊዜ እንደ ህጻን ልጅ 'ስኳር፣ ስኳር' አትበሉ! መንግስታችንም ቢሆን በረባ ባረባው ማማረሩ ደግ አይደለም" አለና ንግግሩን አጠቃለለ።

በዚሁ ቅጽበት ፕሮግራም አስተዋዋቂው ወደ መድረክ ወጣና "በጋሽ ውሴን ንግግር ላይ የተወሰነ ሀሳብ ለመጨመር ፈልጌ ነው" በማለት ሊቀጥል ሲል ተሰብሳቢዎቹ "ኧረ በቃን!" በማለት አጉተመተሙ። ሰውዬው ግን ተሰብሳቢው ቢጮህም የመናገር ሱሱን ሳያረካ የሚተው አልሆነም።

"ስለ ስኳር የተባለው ነገር እንዳለ ሁኖ እኛ ሽንኮራ አገዳ በሰፊው እንትከል እንጂ በየበራችንና በየመንደራችን የስኳር ፋብሪካ የሚተከልበት ዘመን ሩቅ አይሆንም! የሚለው ነገር ቢሰመርበት የሚል ሀሳብ አለኝ። በተጨማሪም ስለ መብራት ያነሳችሁት ነገር እንግሊዝም፣ ጀርመንም፣ አሜሪካንም አገር ብትሄዱ" እያለ እንደ ጸረ-ሽብር ህጉ የመብራት መቆራረጥ ተሞክሮውን ከየት ከየት አገሮች እንደተኮረጀ ሊያስረዳ ሲሞክር ሽንቱ እንደመጣበት ሰው አዳራሹን ለቅቄ ወጣሁኝ።

ወደነፈሰበት

የኔ እኮ የጉድ ነው
ህዝብ ጋር የምነግስ ህዝብ ጋር የምነፍስ
"ሃድድ ተነጠፈ፣ ጎዳናች ተቃኑ፣ ሰዓታት አጠሩ
እንግልት ቀነሰ" እያሉ ሲያወሩ
አብሬ ስዘምር "ሃድድ" ስል ከርሜ
ከተጓጉች ጋራ ባቡር ጣቢያ ቁሜ
ባቡርና ሃድድ የተሰናዱ እለት
ተሳፋሪው እኔ ምሄድበት አጥት
/አ ቤ ት/

አሁን በቀደም እለት ግድቡ ሲጀመር
ሃገራዊ ጥቅሙን ፋይዳውን ሰናገር
"ፋብሪካ ብንተክል ጣውላ ቤት ብንከፍት"
"መሰኖ ብናለማ አሳ ብናመረት"
"ዋናው ነገር ግድብ ዋናው ነገር መብራት"
ሊያልኩ እከርምና...
አሁን በቀደም ለት አሁን ትናንትና
ለሰንት የታቀደው መብራት የበራ እለት
አምፖሉን አጥፍቼው አዳፍኔው ትኝት
/አ ቤ ት/

የአዲስ ዓመት እቅድ

ከሁሉም በዓላት ለዘመን መለወጫ ታላቅ ክብር አለኝ። ሁሉ ነገር ለለውጥና ለእቅድ ያነሳሳኛል።

- ገባያው፡- በብርቱካን፣ በትርንጎ፣ በሎሚ፣ በአዴስ፣ በጠጀ ሳር፣ በአትክልት ዘር፣ ተሞልቶ ሳየው...
- ምንጩ፡- ውሃ አቁሮ፣ እንቁራሪቱን፣ አሳኮሪቱን፣ አልቀቱን ፈልፍሎ ሳየው...
- መስኩ፡- በቀጤማ፣ በሰርዶ፣ በበሬጨው፣ በአደይ አበባ፣ በቱልት፣ በሙጃ ተሸፍኖ ሳየው...
- ተራራው፡- በእንቁጣጣሽ፣ በአላሹሚ፣ በከሴ፣ በእንቧጮ፣ በመቅመቆ፣ በፍየለ-ፈጅ በልጽጎ ሳየው...
- ማሳው፡- በአተርና በባቄላ አበባ፣ በብዕርና በአገዳ ሰብሎች ተሸፍኖ አረንጓዴ ሆኖ መንፈሴን ሲያለመልመው...
- ከብቶቹ፡- በጥጋብ ሲጨሁ፣ ጥጆቹ በየመስኩ ሲፈነጩ፣ ጋጡ በሚጣፍጥ የጥጃ ትንፋሽ ሲታወድ...
- ወንዙ፡- የእኛን ሰገራ ተገላግሎ፣ ከወባና ከትንኝ እንቁላል ጸድቶ፣ ከመደፍረስ ወደ መጥለል ተሸጋግሮ፣ በእንቁራሪት ድምጽ ታጅቦ ኩልል እያለ ሲፈስ ሳየው...
- ሽንታችንን ጎርፍ ጠራርጎት፣ ጫማችንን ጨቀጨቅና ቅዝቃዜ ሰልቦት፣

አየሩ ከጫማና ከሽንት ጠረን ተገላግሎ፣ በአደይ አበባና በቀሰም እጽዋት ጠረን ተለውሶ፣ የማር ሽታ አፍንጫዬን ሲሰልበው...

- ሰፈሩ፡- ከዝንብ መንጋ ተገላግሎ፣ ቤቱ ሁሉ ግድግዳው በአመድና በእበት ተለቅልቆ፣ ኮርኒሱ ተቀይሮ፣ ማጀቱ በጠላ ጥንሰስ ሽታ ታውዶ፣ ሳሎኑ በአደይ አበባና በቀጤማ ፈክቶ ስመለከት...
- ሰው፡- በኑሮ ውድነት ምክንያት ሊጠፋ ጫፍ የደረሰውን የበዓል ቀን ልብስ የመቀየር ባህላችንን ላለመተው፣ ጃኬት መግዛት ባይችል ሸሚዙን፣ ጫማ መግዛት ባይችል ካልሱን ሲሸምት ሳይ...
- ሱቁ፡- በአዲስ ሸቀጥና በአዲስ አልባሳት ተሞልቶ፣ ለውጥ ለውጥ በሚሸቱ ሸማቾች ተከቦ፣ ድስካውንት አድርገናል በሚል ጽሁፍ ተወሮ ሳየው...

ይሄን ሁሉ ስመለከት የተስፋ ቀለም አረንጓዴ በመሆኑ ልቤ ተስፋን ያደርግና ከመሬት ተነስቼ እንደ መስቀል ወፍ ሳይታይ የሚጠፋ እቅድ ማቀድ እጀምራለሁ።

የተሻለ ትምህርት ሳልማር፣ የተሻለ ስራ ሳልይዝ ሚስቴ ቀጤማውን ጎዝጉዛ አቦል ቡናውን ልትቀዳ ስትል ውስጤ "ፍንክንክ" ይልብኝና "ልመርቅሽ" የሚል አመል አመጣለሁ። አቦል ቡናውን ጠጥቼ አይምሮዬ ተረከ ሲል ደግሞ ባለ አስራ ስድስት ሉክ ደብተሬን እገልጥና "የቀጣይ አመት እቅዳችንን አብረን እንቀድ!" እያልኩ ሚስቴን በተስፋ ሳጠዛት እከርማለሁ።

ይህ የሚሆነው እስከ ዘመን መለወጫ ድረስ ነው። ከዛ በኋላ በበአሉ ማግስት ያንኑ አመት፣ ያንኑ መንግስት፣ ያንኑ ቤት፣ ያንኑ ህይዎት ቁጭ ብሎ ሳገኘው ወደ ጨለምተኛው ሰብዕናዬ እመለሳለሁ።

የበዓል ቀን በሀገር ባህል ልብስ አሸብርቃ የሀገር ባህል ሽማግሌ መስላ የዋለችው ሚስቴ ገና በጠዋቱ የደረተ ቢጃማዋን አጥልቃ፣ ጸጉሯን አንጨፍርራ ከእንቅልፌ ትቀሰቅሰኝና የተለመደ የአስቤዛ አለቀ ችክችኳን ስትጀምር ከመኝታዬ እነሳና ወደ ሳሎን እመራለሁ።

ሳሎኑ ውስጥ ደግሞ ወለሉ ላይ ያለው ቀጤማ ደርቆ፣ ብርጭቆ ውስጥ የተሰካው አደይ አበባ እንደኔ እራሱን ጥሎ ስመለከተው..... ቴሌቪዥኑን ስከፍተው ማላ ለማላ ሲልከሰከስ ሳየው ፊቴን ልታጠብ ወደ ጓዳ እገባለሁ።

ጓዳውም ውስጥ ስገባ ሀንጎቨር ወሮት አገኘዋለሁ። ጠላ ያትረከረካቸው

ብርጭቆዎች፣ ቡና የገነረበት ስኒ፣ ዝንብ የሚወረው ሰጋ፣ ቅራሬ የያዘ ጆግ፣ የተጋጠ አጥንት የተሸከመ መዘፍዘፊያ... ዝብርቅርቅ ብሎ ስመለከት ፊቴንም መታጠቡን እተወውና ቀይ ወጥና ጠላ የፈሰሰበትን ልብሴን ለብሼ ከቤቴ አወጣለሁ።

በመንገዴ ላይ ደግሞ ሽምሱ የዱቤ መዝገቡን ይዞ የሱቁ በር ላይ ሲጠብቀኝ ሳየው... በሌላ መንገድ አሳብሬ ወደ ስራ ስሄድ ደግሞ... ያው ቢሮ ውስጥ ያው ኃላፊ ተቀምጦ የአሮጌ አመት ፋይል አምጥቶ ጠረጴዛዬ ላይ ከምሮ ስመለከት.... ከአይምሮዬ ውስጥ "ድሊት" ያደረኩት ፋይል "ሪሳይክል ቢን" ውስጥ ታጭቆ ሲጠብቀኝ... የእኛ ለውጥ ከጊዜ ይልቅ በቦታ ተወስኖ ሲታየኝ መስከረም ሁለት ላይ ወደ አሮጌነቱ የሚለወጥ ዘመን ሲቀይሩ ከመኖር ይልቅ ቦታን መቀየር የተሻለ ሆኖ አገኘዋለሁ።

ምንም እንኳን የእኔ እቅድ እንደ አገራችን እቅድ አፈጻጸሙ በሁለት አሃዝ ወደላይ ሳይሆን ወደ ታች ቢሆንም.... እንዲህም ሁኖ ከአድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅዳችን ያልተናነሰ እቅድ ከማዘጋጀት አልቦዝንም።

ፍቅርና ፊልም

በዛብህን አሆን ብለህ ሰለ ፍቅር ብትሰደድ
ብትደቁን፣ ዳዊት ብትደግም፣
ከመዋስለት የዘለለ ቀብር እንጂ ፍቅር የለም።
እነ ሰብለ ካልተነሱ ፈታውራሪ ካልነገሱ
ጋሼ ሀዲሰ በሞተበት በዘመነ ባረጀ አለም፣
የኛ ፍቅር ተለጥጦ ከወሲብ ሜፍ አላለፈም፣
ይልቅ ዘመን ባይመለስ ሰብለን መሰል ፈልግና፣
መሆንህን ትውት አ'ርገህ በዛብህን ምሰልና፣
ሲተውኑ አብረህ ተውን ተመሳሰል ጊዜ ጋራ፣
ዘመኑ ጋር አብረህ ንጎድ ፍቅሩን ትተህ ፊልሙን ስራ።

ፒፕል ዩ ሜይ ኖው

አምሃራ ሳይንት ማለት የበላይ ዘለቀ የትውልድ ቦታ ነው። አይነ ስውሯ እና ባለ ብሩህ ጭንቅላቷ የትነበርሽም የእዛው ሀገር ሴት ነች። የሀገሬን ሰው "ቶዮታ መኪና መቼ ስራ ጀመረ?" ብትለው "የጋሼ አሸብር መኪና ሳይንት የመጣ ዕለት" ብለው ይመልሱልሃል።

ጋሼ አሸብር ከሳይንት ወደ ደሴ ሊሄድ ያሰበ ቀን "አባከህ ጌታዬ በሰላም ያሰገባኸኝ እንደሆነ ጃንጥላ አመጣልሃለሁ" ብሎ ለሜዳው ሚካኤል ይሳላል። አንድም ቀን በሰላም ገብቶ ስለማያውቅ ስለቱን አስገብቶ አያውቅም። በኋላ ላይ መኪናው ከምታስገባው ገቢ ይልቅ የምትገላቸው ሰዎች ቁጥር ሲበዛበት ሊሸጣት ቢሞክርም "የጦር መሳሪያ ማን ይገዛል!" እያሉ ስላሾፉበት ጎማዋን ለልብስ ማጠቢያ አውጥቶ መኪናዋን ለማቆም ተገደደ።

አማራ ሳይንት ሁለት አይነት ሐይማኖቶች አሉ። አንደኛው "ክርስትና" ሲሆን፣ ሁለተኛው "ሙህዬ ጀማል" ነው። "ሙህዬ ጀማል" ማለት የግንቦት ልደታ ቀን "የእመቤቴን ጠበል ቅመሱልኝ" እያለ ህዝቡን የሚጠራ ብቸኛ ሙስሊም ነው። የሀገሬው ሰው ሀይማኖቱን ሲጠየቅ "አማራ" ብሎ መመለሱ የተለመደ ከስተት ነው።

በአንድ ወቅት ወደ ዩኒቨርሲቲ ልሄድ ሳይንት መናሃሪያ ተገኝቻለሁ። መናሃሪያው ውስጥ በጋሼ አሸብር ቲዮታ መኪና ምትክ ቅጥቅጥ አውቶብስ ቁሟል። በአውቶብሱ የፊት በር ገባሁና መሃል ላይ ስደርስ አንዲት የከተማ ልጅ ብቻዋን የሁለት ሰው መቀመጫ ይዛ ተቀምጣለች።

"ሰው አለ?" አልኳት።

"የለም" አለችኝ ቦርሳዋን አንስታ ጭኗ ላይ እያስቀመጠች።

እድለኝነቴ እየገረመኝ ከጎኗ ተቀመጥኩኝ። ተሳፋሪው ሱሪ በመልበሷ ምክንያት በግርምት እየተመለከቱ ይሳሳቁባታል። ከላይ እስከ ታች አየኋት። ጣኦት ነች። የለበሰችው ጅንስ ሱሪ በሚካኤል አንጀሎ የተቀረጸውን የውብ ጭኗን ውበት ሊደብቀው አልቻለም።

ጡቷ "ጡት" በሚባል የጅምላ ስም መጠራት የለበትም። መልኳ! እድሜዋ! መቀመጫዋ.....! የፈጣሪ ያለህ! ከዘር የወረሰኩት ደም ግፊቴ እንደማዞር አደረገኝ። ይቺን የመሰለች ቀዘባ ኑሮ ያጎሳቆላቸው ተሳፋሪዎች መሃከል ምን ታደርጋለች? ብዬ አሰብኩኝ።

ከሰማይ ወርዳ መሆን አለበት። በስሜት ጡዣ በጣም ከመንጠራራቴ የተነሳ የተቀመጥኩበት ወንበር መደገፊያው ከመሰበር ለጥቂት ተረፈ። ወገናቼ ከእንዲህ አይነት መናጢ የሆርሞን ብዛት ፈጣሪ ይሰውራችሁ። ጉዞ ከመጀመራችን በፊት ለሁሉም ተሳፋሪ ፔስታል ታደለ። ለኔም ረዳቱ "እንካ" ሲለኝ እንደማያመኝ ነገርኩት። "ያምሃል ያዝ" በማለት ጥሎልኝ ሄደ። ልጅቱ ጋር በመቀመጤ በጣም ሳይናደድ አልቀረም።

ሀኪም እህቷን ልትጠይቅ የመጣች የአዲስ አበባ ልጅ መሆኗን ነገረችኝ። የአስራ አንደኛ ክፍል ተማሪ ነች። ሁሉ ነገሯ ያምራል። ጥርሷን በበረዶ መመሰል ይቻል ይሆናል። ሳቋንስ?

"አምላኬ ሆይ ይቺን ልጅ የማርኳት እንደሁ አትማረኝ" ብዬ በልቤ ቃል ገባሁኝ።

****

ጉዞው እንደተጀመረ መኪናው ከአውቶብስነት ወደ ሬስቶራንትነት ተቀየረ። እንደ ቅመማ ቅመም ነጋደ "ፔስታል" የሚሉ ድምጾች በረከቱ።

ፈጣሪ ዩኒቨርሲቲ እንዲገባ ያደረገኝ ይህች ልጅ ጋር ሊያገናኘኝ አስቦ እንጂ እውነት ተምሮ ሀገርና ወገኑን ይቀይራል ብሎ አይደለም። ልጂቱ ጋር በቀላሉ ለመግባባት የዩኒቨርሲቲ ተማሪነቴ ልቧ ላይ ግንባር የገባያ ቦታ አሰጠኝ። በመንገዳችን መሃል ብዙ አይነት ስብከት፣ ብዙ አይነት ሽፍደት፣ ብዙ አይነት ከስተት ነበረ።

"መሃሉ አይነገርም" ብዬ ተውኩት።

*****

ደሴ ከጦሳ ተራራ ስር የተሰራ "ካሊበር ሆቴል" የሚባል ባለ አንድ ፎቅ ህንጻ ውስጥ ሁለት የሰው ገላና ላብ ያልነካቸው የኮምቦልቻ ጨርቃ ጨርቅ አንሶላዎች መሃከል ሁለት የተባረኩ አፍላ ወጣቶች ገድመዋል። "እንደ እሳት የሚፋጀው ውብ ጭኗ መሃል፣ ከንፈሯን በከንፈሬ ቁጥጥር ስር አውዬ፣ እንደ ሽንኩርት ያኮረተ ቂጧን እየዳበስኩ፣ ወዘተ" እያልኩ እንደ አጋታ ክርስቲ ድርሰት ልብህን አልረብሸህም።

"ማረኝ" አለችኝ።

አልማርኳትም።

በልሳን ታወራ ጀመር። እኔሳ ምን አወራሁ? አንደበቴን አጥቼ ነበር።

አቤት ከንፈር። ቱፍ! እኔ እኮ የማልረባ ሰው ነኝ። ያንን ከንፈር "ከንፈር" ልበለው?

እንደ ለውዝ... እንደ ኑግ... እንደ ሰሊጥ... ዘይት ከገላችን ላይ ታለበ።

"እንደማገባት" ነግሬያት ተስማምታለች። ይሄን ቃሌን ያጠፍኩ ቀን ምላሴ ትታጠፍ! ይችን ቀን የዘነጋሁ ቀን ትውስታዬን ልነጠቅ! አጋጣሚውን አስበውና ማመን ያቅተኛል። ከንዴ ላይ ጥቁር ነዶ ጸጉሯን ነስንሳ ያንተራስኳትን ጠይም ጣዖት ልብ ብዬ አያትና አምላኬን እንዲህ አልዋለሁ። "ስለምን ለዚህ ሹመት አጨኸኝ? ስለምን አብዝተህ ወደድከኝ? ጌታ ሆይ በትረ ስልጣንህን ካስጨበጥከው፣ ሰፊ ርስትን ካወረስከው ባለሚልህ ይልቅ እኔ የታደልኩ አይደለሁምን?"

በዚህ መሃል "ምነው የኔ ጀግና በሀሳብ ነጎድክብኝ?" ትለኛለች። እንደገና የታመቀ ሃይሌ፣ እንደገና የተገደበ ፍቅሬ መፍሰስ ይጀምራል። በቅጽበት ውስጥ ሳፈቅራት፣ በቅጽበት ውስጥ ሰማንያ ሳስርላት፣ በቅጽበት ውስጥ ቃልኪዳኔን ልቧ ላይ ስፈጽም ይታወቀኝ ነበር። ከማላውቀው የአዕምሮ ክፍሌ የማላውቀው ስብእና ሲፈልቅ ይሰማኛል። እሷም ላይ ይሄ እንደተከሰተ እርግጠኛ ነበርኩኝ።

*****

ሳቅን አላውቀውም ነበረ። ደስታን አላውቀውም ነበረ። እርካታን አላውቀውም ነበረ። ፍቅርን አላውቀውም ነበረ። አለምን አላውቃትም ነበረ። እንደ ህጻን ነው የሆንኩት። ሳቄ ውስጥ ደስታ ብቻ ሳይሆን ቅላጼም፣ ከኔ በላይ ማን አለ? የሚል ጥጋብም ነበረበት።

ሌሊቱን ሙሉ ያለ እንቅልፍ አንግተን ጧት ወደ መናሃሪያ ስንሄድ የድካም ስሜት አልተሰማኝም። ልጅቱ እኮ የምትራብ እንጂ የምትጠገብ አይደለችም። ከደሴ ወደ አዲስ አበባ ያደረግነው ጉዞ በምክር፣ በእቅድ፣ በወደፊት የተሞላ ነበረ። አዲስ አበባ ላይ ሶስት የፍቅር ቀናትን አብረን ለማሳለፍ አቅደናል።

ውዴን ሳያት በአጋጣሚው በጣም ደስተኛ ሆናለች። ሀሜ በረዶ የመሰለው ጥርሷ ፈገግታን ተላብሶ ነበር። እውነት ለመናገር ትምህርትህን ተወውና እዚሁ አዲስ አበባ የቀን ስራ እየሰራህ ሸቅለህ አብላኝ ብትለኝ እንኳን እንደማደርገው እርግጠኛ ነበርኩኝ። ይሄ ባይሆን እንኳን የቀረችኝን የአንድ ዓመት ትምህርት አጠናቅቄ ከዩኒቨርስቲ ተመርቄ ስመለስ የመጀመሪያ ስራዬ ስራ መቀጠር ሳይሆን ውዴ ጋር ትዳር መመስረት መሆኑ ሳይታለም የተፈታ ነው።

አዲስ አበባ ደረስንና ስልክ ቁጥሯን በብጣሽ ወረቀት ላይ ካሰፈርኩኝ በኋላ የሆነ አረንጓዴ መናፈሻ ያለበት አካባቢ ላይ ስንደርስ "ወራጅ" የሚል ድምጽ አሰማች። ከመኪናው ሰትወርድ ልቤ ተረበሸብኝ። በመኪናው መስታዎት አሻግሬ አይኗን አየሁት። አውቶብሱ ከመንቀሳቀሱ በፊት የግራ እጇን ጣቶች እየሳመች የቀኝ እጇን አውለበለበችልኝ።

*****

"ሊነጋ ሲል ይጨልማል"
ሲሉ ሰምተህ፣
አ ት ጽ ና ና
እውነት መስሎህ፣
የኛ ጸሃይ የኛ ቢጋ
ሊጨልም ነው የሚነጋ።

ከነገ ጀምሮ አብረን ለማሳለፍ ብንነጋገርም ባዶ አልጋ ቤት ውስጥ ሁኜ እሷ ጋር ለብሼው ያደርኩትን ቢጃማ ስለብስ ልብሴ ላይ ተጣብቆ የቀረው የገላዋ ጠረንና የጸጉሯ መዓዛ በስርኔ በኩል ሰርጎ ትዝታዬን በቀሰቀሰው ጊዜ ልቤ ሽብርብር፣ ጨጓራዬ ግልብጥብጥ አለብኝ። በአካል ባላገኛት እንኳን በስልክ ድምጿን ሳልሰማ ማደር ስላልፈለኩ ቢጃማዬን ቀይሬ ከክላሴ ወጣሁኝ።

ቴሌ ሴንተር በር ላይ ቁሜ ኪሴን በፈተሸኩት ጊዜ ኪሴ ብቻ ሳይሆን ይህች ጎዶሎ አለምም ባዶ ሆና አገኘኋት። የባህራንን የሞት ደብዳቤ ወደ ሞት የቀየረው

መልአክ የኔን ብጣቂ ወረቀት ወደ የት እንዳደረሳት ሳይታወቅ ቀረ። ስልክ ቁጥር የጻፍኩባት ወረቀት የህይዎት ዘመኔን ደስታ፣ የህይዎት ዘመኔን ራዕይ፣ የህይዎት ዘመኔን ነገዎች እንደያዘች ተሰወረች።

እንደ መቀወስ አደረገኝ። ይህች ወረቀት ካልተገኘች እስከመጨረሻው ድረስ እራሴን ተቀይሜው እንደምኖር እርግጠኛ ነበርኩኝ። ይህች ወረቀት ካልተገኘች ከዚህ በኋላ እራሰን ማዳመጥ፣ እራሰን ማክበር፣ እራሰን መሆን ወዘተ የሚባሉ ነገሮች በህይዎቴ ውስጥ ሊኖሩ እንደማይችሉ ምንም ጥርጥር አልነበረኝም።

ቢጨንቀኝ ወደ ግድግዳ ስልክ አመራሁና እንደ "ፌቦናች ቀመር" ቁጥሮችን እየቀያየርኩ ብደውልም ተሳስተሃል እንጂ አዎ የሮዚ ቤት ነው የሚለኝ ድምፅ ጠፋ።

****

ያሳለፍኩት አዳር በስካር፣ በተስፋ መቁረጥ፣ በእብደት፣ በብስጭት የተሞላ ነበረ። ጥርሴን ሳንቀራጭጨው፣ ግንባሬን ግድግዳ ጋር ሳጋጨው አደርኩኝ። በርካታ አልኮል ብጋፍፍም እንቅልፍ የሚባል ነገር በዐይኔ ዝር ሳይል ሌሊቱ ነጋ።

ማለዳ ተነስቼ ሮዚ የወረደችበት ቦታ ላይ ለመድረስ የቀደመኝ ሰው አልነበረም። እድለ-ቢሱ እኔ አረንጓዴውን መናፈሻ እንጂ አሷን ማግኜት አልቻልኩም።

አዲስ አበባ ላይ ያሳለፍኳቸውን ቀናቶች የመዘርዘር አላማ የለኝም። እንደ ስታስቲክስ ቆጣሪ ቤት ለቤት ስዞር፣ እንደ ሰባኪ መንገደኛውን ሁሉ ሳስቆም.... ከስሟ ውጭ የአባቷን ስም እንኳን የማላውቀውን ፍቅሬን ስፈልግ ነበረ። ሶስት ዘልዛላ ቀናቶችን በፍለጋ ሶስት ዘልዛላ ሌሊቶችን በስካር አሳልፌ በተስፋ መቁረጥ ውስጥ ሁኜ ወደ ሀረር ለመሄድ ትኬት ቆረጥኩኝ።

*****

አለማያ ገብቼ የተነፋፈቀ ጓደኛ ላውንጅ ተሰብስቦ ስለ አከራረሙ ሲወያይ፣ ግሬድ የተበላሸበት ሲበሳጭ፣ ጥሩ ውጤት ያመጡ ልጆች ሲፈነጥዙ፣ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ የተጣበሱ ፍቅረኛሞች ጥንድ ጥንድ ሆነው በሳይቤርያ መንገድ ሲተሙ፣ በሱስ የተለከፉ ጀዝቦች በገንደቦይና በባቲ አረቂ ቤቶች ውስጥ ተሰባስበው ሲፈላሰፉ፣ የማልረባው እኔ ተዘግቶ የከረመ ዶርም ውስጥ እንደ እኔ አይነቱን ነቀዝ የሚገድል "ማንኮዚየም" የተባለ መርዝ በጥብጨ ቁጭ ብዬ ነበረ።

ሁኖም ግን የመርዝ ብልቃጡን ከፍቼ ሳስበው፣ ሳስበው፣ ሳስበው መርዝ

ጠጥቶ በአንዴ ከመሞት አልኳል እየጠጡ ቀስ በቀስ መሞት የተሻለ ቅጣት መሰለኝ። ይሄ ውሳኔዬ የፍርሃት ሀሳብ ከመሰለህ ተሳስተሃል። የፈለገ ነገር ቢሆን የያዝኩት መርዝ ከአማሬሳ አረቂ የበለጠ የመምረርም የማስፈራራትም አቅም የለውም።

****

አለማያ ያሳለፍኳቸው ወራቶች የሚጸፍም የሚኖርም ህይዎት አልነበረባቸውም። ሌሊቶቹ በስካር ቀናቶቹ በሀንጎቨር የታለፉ ናቸው። እንደ ጉድ ጀዝቤ ነበር። በእኔ ሂሳብ አልኮል ሊጠጣ ከግቢ የወጣ ተማሪ የእኔን የፍቅር ታሪክ የማድመጥ ግደታ ነበረበት። በዚህም ምክንያት የእኔን ሂራርና ለቅሶ ላለማየትና ላለመስማት ብዙዎች ጓደኞቼ እኔ ጋር መጠጣት አይፈልጉም ነበር።

ከዩኒቨርሲቲ ተመርቄ ወደ ቤተሰብ ስሄድ ፍቅሬ የወረደችበት መናፈሻ ጋር በመሄድ አጥሩን ደገፍ ብዬ ፡-

ይገርምሻል ውዴ....
አምና እንችን አቅፌ
የዋልኩበትን መስክ- ያንን ለምለም ሜዳ፣
ተፈጥሮን ለማድነቅ
ቃል ከአፌ እንዳልጠፋ- እንዳልሆንኩኝ ዱዳ
ዘንድሮ እዛው ቦታ
ያላንቺ ልምላሜን- ሊይኔ አሻግሮ አያዬ
እከራከራለሁ.....
"መስክ የሚባል-ነገር ሜዳ የለም" ብዬ። የምትል ኑዛዜ ጽፌላት ወደ ሀገሬ ተመለስኩኝ።

*****

የልጃቸው ከሲጋራ እስከ ማሪዋና፣ ከጫት እስከ አልኮል ሱስ መለከፍ ያሳሰባቸው ቤተሰቦቼ ወደ ፀበል ሊወስዱኝ ቢምክሩም አልሄድም በማለቴ ሳይሳካላቸው ቀረ። ይልቅ ያኔ ስራ ማግኘት ቀላል ነገር ነበረና ሌላ ቦታ የመንግስት ስራ አግኝቼ ከፊታቸው ገለል አልኩኝ።

የጀመርኩት ሱስ በአጭር ጊዜ ውስጥ በርካታ የጤና መታዎኩኝን ቢያስከትልብኝም የመተው እቅዱ አልነበረኝም። በርግጥ ይሄን ሱስ በሮዚ ምክንያት ብጀምረውም አሁንም ሱሴን ለመቀጠሌ ምክንያቷ እሷ ነች ማለት አልችልም። ሱሱም ጉልበት እያወጣ እንዳሻው ይነዳኝ ነበር። ለአራት አመታት ያክል በስራ ላይ

ብቆይም የገባሁበት ሱስ ጥልቀት ስለነበረው ሚስት ለማግባት ቀርቶ ፍቅረኛም ለመያዝ አላስቻለኝም።

****

ከዓመታት በኋላ ውዴን በአረቂ ሃይል ዘንግቻት (ረስቻት አላልኩም) ባንድ የተባረከ አሁድ ግሮሰሪ ተቀምጬ ፌስቡክ ስጎረጉር "people you may know" የሚለው አምድ ስር ከነ ፎቶዋ ቁጭ ብላ አገኘኋት።

በድንጋጤ የኡዞው መለኪያ ከእጄ አምልጦኝ ወለሉ ላይ ተከሰከሰ። ኮረንቲ እንደጨበጠ ሰው ሰውነቴ ተርገፈገፈ። ወደ አይምሮየ ከፍተኛ መጠን ያለው ደም ተረጨ። መረጋጋት አልቻልኩም። የሚንቀጠቀጡት ጣቶቼ መለኪውን መጨበጥ አቅቷቸው ተንዘፈዘፉ።

በላብ በጨቀዬው መዳፌ የጓደኝነት ጥያቄ ላኩላትና ፕሮፋይሏን እመረምረው ጀመር። አካውንቷን ከተጠቀመችበት ዓመት ገዳማ ሁኖታል። የስራ ቦታዋ "ባህርዳር" ይላል። የመስሪያ ቤቷም ስም ተጠቅሷል። ማግባት አለማግባቷን የሚገለጸው ስታተስ ግን አልተሞላም። ስልክ ቁጥሯን ብፈልገውም ላገኘው አልቻልኩም።

የሞባይሌ ቁልፎች ተነቃቅለው መውደቅ እስኪቀራቸው ድረስ የሆነውን ነገር ሁሉ በሚሴጅ ልኬላት መልሷን እጠብቅ ጀመር። "ጌታ ሆይ አስራኤላውያንን በበረሃ የመራሃቸው አምላክ ህይዎቴን ወደ አካውንቷ አስገባት" ብዬ ብፀልይም፣ "እን ላይን" ተጥጄ ካሁን አሁን ገባች እያልኩኝ ለሳምንት ያህል ብጠብቃትም አካውንቷን እንጂ ሮዚን ሳላገኛት ቀረሁ።

****

አውቶብስ ውስጥ ነኝ።

ስልሳ እቅድ፣ ስልሳ መልክ፣ ስልሳ አመል ያለን፣ ስልሳ ሰዎች ወደ አንድ አቅጣጫ ለመሄድ አውቶብስ ውስጥ ተቀምጠናል። በእንቅልፍ እጦት ምክንያት በሚቆጠቁጠኝ አይኔ ትርምሱን እየታዘብኩ መኪናው እስኪንቀሳቀስ ድረስ እጠብቃለሁ።

"እዘኑልኝ ጎበዝ አራሩልኝ ለኔ

እንደ አደይ አበባ ለፈሰሰው አይኔ" እያለ የሚለምን አይነ ስውር በኋለኛው በር በኩል ገባ።

በፊት በር በኩል ደግሞ "ለተቃጠለችው ቤተክርስቲያን ማሰሪያ የአቅማችሁን ጣል ጣል አድርጉልን" እያለ ምጽዋት የሚጠይቅ ቄስ መጣ። አብዛኛው ሰው አይነሰውሩን ትቶ ወደ ቄሱ ሳጥን ውስጥ ምጽዋቱን አስገባ። ቄሱ የሰበሰበውን ገንዘብ ይዞ ሳይወጣ በፊት ሁለት ፖሊሶች በፊትና በኋለኛው የአውቶብስ በር በመግባት ያዙትና "መታወቂያ እንዲያሳያቸው" ጠየቁት። ሰውዬው ከመስቀልና እራሱ ካዘጋጃት ፎርጂድ የድጋፍ ወረቀት ውጭ ማንነቱን የሚገልጽ መታወቂያ አልነበረውም። በወረቀት ያሸጋትን ሳጥንም የሚከፍታት እራሱ ሲሆን ምዕመናኑ ሁሉ በምርመራ ሲያፋጥጡት ቄስ የተባለው ሰውዬ መሸታ ቤት ውስጥ የነጋት ወመኔ ሁኖ ተገኘ።

ግማሹ ተሳፋሪ በእርግማን ቀሪው ደግሞ በእርግጫ እና በጥፊ ወረዱበት። ፖሊሶቹም ምጽዋት መመጽወቱ ተገቢ ቢሆንም ከልግስናችን በፊት ግን የሰዎቹን ትክክለኛነት ማጣራቱ ተገቢ መሆኑን በመናገር ግንዛቤ ለመፍጠር ሞከሩ።

ከአውቶብሱ ወደ ልቤ ስመለስ በውስጤ እንዲህ የሚል ሙዚቃ ተከፍቷል።

ወልድያን አልፌ፣መቄትን አልፌ
ጋይንትን አልፌ፣ወረታን አልፌ
ጎጃም ላይ፣ጎጃም ላይ፣ጣና ላይ
አለኝ ጉዳይ፣ አለኝ ጉዳይ።

በጉዞዬ መሃል ወደ ፍቅሬ እየሄድኩ መሆኔን ሳስበው ደም ግፊቱ እንደተነሳበት ሰው እጄን ያልበኖል! የልብ ምቴ እንደ መኪናው ማርሽ ይቀያየራል።

*****

ቀኑ አሁድ ስለሆነ መስሪያ ቤት እንደሚዘጋ ባውቅም እስከ ሰኞ ድረስ ለአስራ አምስት ሰዓታት ያክል መጠበቅ ስላልፈለኩ ሮዚ መስሪያ ቤት የውጭ በር ላይ መለዮ ለብሶ የቆመውን ጥበቃ በሚርበተበት ድምጽ፣ በሚንቀጠቀጥ ከንፈር ታጅቤ "ሰው ፈልጌ ነበር" አልኩት።

"ማን ትባላላች?" አለኝ።

ነገርኩት።

ጥበቃው ዐይኑን ጠበብ አድርጎ አርቆ ለማሰብ ሞከረና "እረግ ሮዛ ያቺ ጨዋ ልጅ! እሷማ ከዚህ መስሪያ ቤት ለቃ ወደ አዲስ አበባ ከሄደች ረዥም ዓመት ሆናት" አለኝ።

ጭንቅላቴን በመዳፌ ይዤ ቁጭ አልኩኝ። ማልቀስም፣ ማሰብም፣ ማዘንም፣ መበሳጨትም፣ መጮህም፣ ዝም ማለትም አልቻልኩም። በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሁኜ ብዙም ሳልቆይ ጥበቃው ነገ መምጣት ከቻልኩኝ ስልክ ቁጥሯን ማግኘት እንደምችል ነገረኝ። ባህርዳር ድረስ መጥቼ ሮዚን ባላገኛትም ስልክ ቁጥሯን ማግኘት እንደምችል ማወቄ ትልቅ እፎይታን ሰጠኝ። ጥበቃውን አመስግኜ ወደ ዶርሜ ተመለስኩኝ።

****

አንደ መሰቀል አዕዋፍ እንዴ አደይ አበባ
የቀጠርኩሽ እንደሁ መስከረም ሲገባ
ሰኬታማ እንዳልሆነ ቀድሞ ተደንግጓል
አንቺ ብትመጭ እንኳን መስከረም ይቀራል።

አምላክ እኔና እሷን ለመነጣጠል የፈለገው ለምን እንደሆነ ባይገባኝም ነገሮችን የበለጠ እንዳያወሳስብብኝ በማሰብ ልወቅሰው አልፈለኩም። በማግስቱ ቀኑ ረፈድ ሲል ባጃጅ ተሳፈርኩኝና ወደ ሮዚ መስሪያ ቤት ነጎድኩኝ። ልቤ ስልክ ቁጥሯን አገኛለሁ የሚል ተስፋ ሰንቋል።

እንዳልኩትም ከሰንት ምርመራ፣ ከሰንት ውይይት፣ ከሰንት ጥርጣሬ በኋላ የአፈጣጠሬን ሚስጥር እና የህይወቴን የስኬታማነት ፎርሙላ የያዘችውን ስልክ ቁጥር አገኘሁ። ስልክ ቁጥሯን በሞባይሌ "ሴቭ" ከማድረግ ባለፈ በአይምሮዬም ሸመደድኩት።

*****

የያዝኩት ፔንሲዮን ውስጥ ከትሜ ስልኳ በጠራ ጊዜ የልቤን መረበሽ ሳስተውለው በር እያንኳኳሁ እንጂ ስልክ እየደወልኩ አልመሰለኝም። ከሶስት ጥሪ በኋላ አላአዛርን ከሞት ያስነሳ ድምጽ፣ ሙሴን በበረሃ ሲያነጋግር የነበረ ድምጽ "ሄሎ" አለኝ።

አነባሁ።

"ሄሌ ማን ልበል?" አለች መልስ ስታጣ ጊዜ።

ስሜን ነገርኳት።

"ማን አልከኝ?"

ደገምኩላት።

"ይቅርታ በተሳሳተ ቁጥር ሳትደውል አልቀረህም!"

"ሮዚ አይደለሽ እንዴ?"

"አዎ ነኝ። የት ነው የምታውቀኝ?"

በቅሬታ ውስጥ ሁኜ ለማስታወስ ጣርኩኝ።

በሷ በኩል ረዥም ዝምታ ሲሰፍን "የት ነው ያለሺው?" አልኳት ቤርሙዳ እንኳን ብትለኝ ሄጄ እንደማገኛት እርግጠኛ በመሆን።

"ምን ያደርግልሃል?" አለችኝ።

"ነገ ልመጣ አስቤ ነበር"

"ለምንድን ነው ነገ የምትመጣው?"

"ዛሬ የሚመጣ መኪና ስለማላገኝ ነዋ!"

ፈዘኛ ሳቅ ሳቀችና "በል አትጃጃል ወንድሜ!" በማለት ስልኩን ዘጋችው።

የተዘጋውን ስልክ ከጆሮዬ ላይ ለማውረድ ረዥም ጊዜ ፈጀብኝ። እውነትም አላውቃትም! ተሳስቼ መሆን አለበት። ወደ ቀልቤ ስመለስ ሲጋራ ለኮስኩኝና በረዥሙ ስቤ መልሼ ደወልኩላት። ስልኳ አይነሳም።

****

እኔ አምልሽ ውዴ...
በእኔና አንቺ ጉዳይ ቀን ተጎዥ ነው እንዴ?
አይደለም!... አይደለም!
አንቺን ካጣሁ ወዲህ
መምሸቱን መንጋቱን ልብ ብዬ አላውቅም።
"ከተውኩት ጀምሮ "አትበይ" ዘመን ምላኝ"
እኔ እንደሁ አትልፊ አዛቹ ቀን ላይ ነኝ።
አይውልሽማ...
እኔ ካንች ጋ እንጂ ከጊዜ ምን አለኝ ?
ንጋት የምናፍቅ...
ከአስማት አካላሽ ላይ ጥላሽ እንድያደርገኝ።

በፀሐይ ብርሃን መፈንጠቅ መንጫረር
አካል በሌለበት ጥላው እኔ ልኖር?
አመብርሃንን አቡዬን የኔ አናት
ትዝ ብሎኝ አያውቅም መምሸትና መንጋት
ያጣሁሽ ቦታ ላይ ያጣሁሽ ሰዓት ላይ
ትናንት፣ ዛሬ፣ ነገ ሻግተዋል ባንድ ላይ።

የሽንፈቴን ጽዋ ስንነጭ አደርኩኝ። ብዙ ነገር አወጣሁኝ። ብዙ ነገር አወረድኩኝ። አንዳንዶች አለን ራሳችን በፈጠርነው አለም ውስጥ ሰምጠን የቀረን። የዚች አለም እድሜያችንን ለአንዲት ቀን ክስተት አሳልፈን በመስጠት ምርኮኛ የምንሆን። እኔ እንደዛ ነው የሆንኩት።

በማግስቱ ጧት በሌላ ስልክ ደወልኩላት። ማንነቴን ስታውቅ ስልኩን ልትዘጋው ብትራወጥም "በፈጣሪ ይዠሻለሁ ስልኩን አትዝጊው" አልኳት። አልዘጋችውም። በጸጥታ ውስጥ ሁና ታዳምጠኝ ነበር። የሆነውን ሁሉ ስዘረዝርላት እብድ ሰው ጋር እንጂ ጤነኛ ሰው ጋር የምታወራ አልመሰላትም።

መሃል ላይ አቋረጠችኝና "እየውልህ የኔ ወንድም የምታወራው ሁሉ አንተ ጭንቅላት ላይ የተፈጠረ ነገር ነው። ምናልባት አንተ በአይምሮህ አዝለኸው የኖርከው ነገር እኔ ጭንቅላት ውስጥ ሳምንትም ሳይቆይ ጠፍቶ ሊሆን ይችላል። እናም እኔ አሁን እንደ ነፍሱ የሚሳሳልኝ ባል አግብቼ፣ ልጆች ወልጄ፣ ደስተኛ ኑሮ እየኖርኩ ነው አንተም ያንን እንዲታደርግ እመክርሃለሁ" አለችኝ።

"ቢቃ እሽ ሮዝዬ አንድ ጥያቄ ብቻ ልጠይቅሽ?"

"እሺ ጠይቀኝ"

"እደውልልሻለሁ ብዬ ሳልደውል ከቀረሁበት ጊዜ ጀምሮ ለምን ያህል ጊዜ ስለ እኔ ስታስቢ ነበር?"

"ሳምንት አካባቢ ሊሆን ይችላል ከዛ በኋላ ግን ከነመፈጠርህም ዘንግቼህ ነበር"

ከሷ በፊት ስልኩን ቀድሜ የዘጋሁት እኔ ነበርኩኝ።

*****

ጣይቱ መናፈሻ ተቀምጬ ያሳለፍኩትን ሁሉ ባሰብኩት ጊዜ ምኝነቴ አለቅጥ

ገረመኝ። ራሴ በቆፈርኩት ጉዳጓድ ውስጥ ራሴን ቀብሬ መኖሬ ቆጨኝ። ላንዳችን ገጠመኝ ለመሆን የማትበቃ ነገር ላንዳችን የዘላለም ትዝታ ሁና ትኖራለች። ላንዳችን ሀዘን የምንለው ነገር ላንዳችን የረሽም ጊዜ ደስታ ሆኖ ይገኛል። ላንዳችን ለወሬ የማይበቃ ነገር ላንዳችን ታሪክ ሆኖ ቁጭ ይላል። አንዳችን ከቁብ የማንቆጥረው ነገር ላንዳችን የነፍሳችን መሃላ ሆኖ ይገኛል። ምን አይነት ሰው መሆኔን ሳስበው ራሴን አለቅጥ ናቅሁት።

"ጆን ባር፣ ቱሪስት፣ ኤክሲዶስ፣ ዲአፍሪክ..." የሚሉ ጭፈራ ቤቶች ውስጥ ስዳከር አመሸሁኝ።

ሕይወት እንደ ሆሊውድ ፊልም ፍትሃዊ እንደ ልቦለድ ሚዛናዊ አይደለችም።

ሕይወት ከፍቅር እስከ መቃብር የባሰች ጨካኝ ናት። ስትበድልህ፣ ስታሰከፋህ በዋይታ እንጂ እንደ ፊልሙ በዋሽንት አታጅብህም።

ሕይወት የተጠናቀረ፣ ስርአት ያለው፣ በአግባቡ የተዋቀረ ሴራ የላትም። በዛብህን ስትገድል ፊታውራሪን ከፈረሰ ላይ አትፈጠፍጥልህም። ሕይወት ለበዳይ እንጂ ለተበዳይ አትወግንም። ተሸናፊዎች እየወደቁ ብልጦች ግን እየለመለሙ ይሄዳሉ። በሕይወት ውስጥ ሲበደል ኑሮ መጨረሻ ላይ በደሉን በድል የሚወጣ አከተር አይታይም።

*****

እንደ ወትሮው ሁሉ የጠጣሁት አልኳል ስራውን ሲያቆም በሌሊቱ ከእንቅፌ ነቃሁኝ። ከርቀት የሚመጣ የቅዳሴ ድምጽ ኩልል ብሎ ይሰማኛል። ትንፋሼ አልኮል አልኮል፣ ገላዬ ጭስ ጭስ ይሸታል።

ስካር የተለመደ ተግባሬ ቢሆንም የዛሬው ስካሬ ከእስከዛሬዎቹ ለየት የሚያደርገው ነገር በሴት የታጀበ መሆኑ ነው። ወደ ጓኔ ስገላበጥ በከሬም የላሸቀ ገላ ጋር ተላተምኩኝ። ትኩር ብዬ ሳያት ግንባሯ ላይ የደበዘዘ ንቅሳት አየሁኝ። የመቅፈፍ ስሜት ተሰማኝ። "ከአጠገቤ ተነሽና ውጭ!" ማለትም አማረኝ። አፍታም ሳልቆይ ግን እሷም ባንድ ቀን ክስተት እንደ እኔ ወደ አሮንቃ የገባች ሴት ልትሆን እንደምትችል ሳስብ በሀዘኔታ ስሜት የተመሳቀለ ጸጉሯን ዳበስ አደረኩት።

ቅዳሴው እየተሰማኝ ነው። ጎኔ ያለ ጠረጴዛ ላይ ፓኮ ሲጋራና ክብሪት ተቀምጧል። ከአልጋዬ ላይ ተነሳሁና መስኮቱን ከፈትኩት። ከጊዮርጊስ ቤተክርስትያን የሚመጣው ድምጽ ወደ ክፍሌ፣ ወደ ጆሮዬ፣ ወደ ልቤ ገባ።

በቅዳሴው ድምጽ ታጅቤ ወደ ውስጤ ሰርጎ ሮዚን ዙፋኗ ላይ አጣኋት።

በራሴ ላይ ቅጣት ወስኜ እራሴን ዘቅዝቄ ስገርፈው ኑሬለሁ። ፀጉሬ እስኪረግፍ ድረስ፣ ደም እስከተፋ ድረስ በጭስና በአረቂ ስንገበገብ ኑሬለሁ። አሁን ግን ፍጹም የሆነ ነፃ የመሆን ስሜት ተሰማኝ።

ልብሴን አወጣሁና ወደ ሻወር ቤት ገባሁ። በአልኮል በተቃጠለ ገላዬ ላይ ቀዝቃዛው ውሃ ሲያርፍ ጭስ ተፈጠረ። ውሃው የሲጋራውን ሽታ፣ የሴተኛ አዳሪዋን ከሬምና ሎሽን፣ የሮዚን ትዝታ፣ የአልኮሉን ጠረን፣ ትናንትና የሚባልን ቀን እጥብጥብ አድርጎ ይዞት ወደ ቱቦው ሰረገ። ገላዬን ብቻ ሳይሆን በአልኮልና በሲጋራ የወየበውን አፈጌንም ከፍቼ ለሚንፎለፎለው ውሃ ጋበዝኩት።

ነጭ ፎጣ አሸርጌ፣ ነጭ ገዋን ለብሼ ከሻወር ቤቱ ወጣሁኝ።

መስኮቱ አሁንም እንደተከፈተ ነው። ጠረጴዛው ላይ ያለውን ባኮ ሲጋራ አነሳሁና ጨባብጬ በመስኮት ወረወርኩት። ከዚህ በኋላ ለኔ ሱስ ማለት እንደዚች ሴተኛ አዳሪ ነው። መቼም ተመልሼ አላየውም። ከዚች ልጅ ጋር እንደፈጸምኩት ወሲብ ምንም ትዝታ አይኖረውም። መቶ ብር አውጥቼ ጠረጴዛውን ላይ አስቀመጥኩላት። ሻንጣዬን አነሳሁና ወደ መናሃሪያ ከመሄደ በፊት ወደ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን በመሄድ ቀዝቃዛውን ግንብ ሳምኩት። እጣን እጣን፣ አድሩስ አድሩስ፣ ከርቤ ከርቤ ሽተተኝ። ከሮዚ ብቻ ሳይሆን ከሱሰም ነጻ ለመሆን በመቁረጤ ውስጤ ንጹህ ሆኖ ነበር።

ስወስን እንደዚህ ነኝ። በዋዛ ፈዛዛ የምፈጽመው ነገር የለም። ሮዚ የውሳኔዬ አካል ነበረች። ሱሴ የውሳኔዬ አካል ነበረ። በውሳኔው ወደ እብደት ጎዳና መሄድ የቻለ ሰው በውሳኔ ወደ ደህንነት መመለስ አይቸግረውም። በውሳኔው ከሲጋራ ጭስ ጋር፣ ከአረቂ ቃጠሎ ጋር የተዛመደ ሰው በራሱ ውሳኔ ንጹህ አየር መሳብና ከኢታናል የጸዳ ሕይወትን መጀመር አያቅተውም።

አሁን ሮዚም፣ ሱሴም የሕይወቴ አካል ሊሆኑ ቀርቶ የትዝታዬም ምዕራፎች የመሆን አቅም የላቸውም። መናሃሪያ ስሄድ "አንድ ሰው፣ አንድ ሰው ብቻ!" የሚል የወያላ ድምፅ ተሰማኝ።

"አንድ ሙሉ ሰው ነኝ" ብዬ ወደ ሚኒባሱ ውስጥ ገባሁኝ።

"ሰው እንደምሆንም" እርግጠኛ ነበርኩኝ።

ተሰቅለህ ቅር

ወንድሜ ሆይ....
አንተ ሃብታም ባለጸጋ፣
ከአናት ሰፍረህ ፣
ቁልቁል ልትወርድ የምተጋ፣
እኔ ድሃ ባለተሰፋ፣
አንተን ልሆን
ዳገት ልዘልቅ የምለፋ፣
ምኞት ሀልሜ መሆንህን እያወከው፣
አቀበቴን ቁልቁለትህ ሊታድርገው፣
ሀልሜ እንዳይከሸፍ ካንተ ተርታ እንድሰፍር፣
...ከረምኩ እንጂ
አልፈለህም "ተሰቅለህ ቅር"፣
መውረድ ውረድ መውደቅ ውደቅ፣
ግን ምናለ ሰንበት ብትል እኔ እስክዘልቅ።

ድህነትና ምቀኝነት

ባለንጣ ጎረቤቴ አባተ ጾሙ ከተጋመሰ ጊዜ ጀምሮ ባሉ የገባያ ቀናቶች የበግ ዋጋ እንዴት እንደዋለ ሲጠይቅ የተመለከተው ሰው "በበግ ንግድ ሰራ ውሰጥ የተሰማራ ነጋዴ ይሆን እንዴ?" በማለት ቢጠይቅ የሚያስገርም አይደለም።

ብቻ በግ እየገተትክ ስትመጣ ከአገኘህ ይወቅህም አይወቅህም "ገባያው እንዴት ነው ወንድሜ?" ብሎ ይጠይቅሃል። ከሆሳዕና ጀምሮ ቤቱ ውሰጥም በየቀኑ "ለፋሲካ በግ ብንገዛ ይሻላል ፍየል?" የሚል መጠነኛ ሰብሰባ ሲያካሄድ ከርሞ "ቆዳው ውድ ሰለሆነ በግ ቢገዛ ይሻላል" ተብሎ ቢቃለ-ጉባኤ መወሰኑን ሰምተናል።

የእኔ እና የእሱ ቤት ጎን ለጎን ሲሆን የቢታቸን ግድግዳ ድምጽ ሰለሚያሳልፍ የሚያወሩትም ሆነ የምናወራው ይሰማል።

ሀሙስ አለት ወደ ገባያ ሄድኩኝና በመጀመሪያ ወደ በግ ተራ በማምራት ይሄው ጎረቤቴ አሰኪመጣ ድረስ መጠበቅ ጀመርኩኝ። ትንሽ እንደቆየሁኝ አባተ በሬ የሚገዛ ይመስል የመኪና ካቦ ያህል ውፍረት ያለው ገመድ ይዞ እንደ ቁልፍ እየወዘወዘ ሲመጣ በያዘው ገመድ አንገቱን ባንቀው ደስታዬ ነበረ። መቼም ይሄን የሚያክል ገመድ የያዘው የሚቆረጥ ዛፍ ሊገትትበት እንጂ በግ ሊያስርበት ነው ብሎ የሚያስብ ሰው አይኖርም።

የእሱ መምጣት ጋር ተያይዞ ገባያው ውሰጥ ካሉ በጎች በግዝፈቱ እንደኛ ወደሆነው በግ አመራሁኝና ፍርንባውን ጨብጨ ባለ በጉን "ይሄ በግ ሰንት ነው?" አልኩት አባተ እንዲሰማኝ ድምጼን ከፍ አድርጌ።

"አትሸው! ኧረ አትሸው!" አለኝ ባለ በጉ እጇን ከበጉ ላይ መንቄቆ እያነሳ። ለበግ እንዲህ የሆነ የሚሰቱን ጡት ብጨብጥበት ምን ሊሆን ነው?

"መቼ አሸሁት? ይልቅ ዋጋውን ቁርጥ አድርገህ ተናገር!"

"አርባ ሁለት ነው" አለኝ ባለ በጉ ጥርሱን በመፋቂያው እየፈገፈገ።

"አርባ ሁለት ማለት ምን ማለት ነው? የበጉን ዋጋ እንጂ የጫማህን ቁጥር አልጠየኩህም አኮ"

"አራት ሺ ሁለት መቶ ብር ማለቴ ነው"

አባተ በመዳፉ አፉን አፍኖ ሲፍነከነክ ሰረቅ አድርጌ አየሁት።

"መሄጃውን ተናገር!" አልኩት የበጉን ግዳንግድ ላት በሁለት እጇ እያነሳሁ።

"በቃ በአራት ሺ ውሰደው!"

"ኧረ አትቀልድ ባግባቡ ንገረኝ?" በማለት ራቅ ብዬ በጉን አሰተዋልኩት።

"እኔማ ነገርኩህ"

"አልነገርከኝም" አልኩት ወደ ሱሪ ኪሴ እጇን ከትቼ የያዝኳትን አራት መቶ ብር እያፍለተልኩ።

"በቃ አንተ ንገረኝ!" ባለ በጉ መለሰ።

"ሰስት ሺ ልውሰደው?" አልኩት አባተ እንድሰማኝ ጮህ ብዬ።

ባለ በጉ አማዜር ይሰጠውና "አይሸጥም!" ብሎ በቁጣ መለሰለኝ። አባተ አየሳቀ ከአጠገቤ ሲሄድልኝ ጠብቄ ፈሰቡክ ላይ ፖስት የማደርገው ፎቶ ከዚህ በግ ጋር ተነስቼ ከበግ ተራ ስወጣ በር አካባቢ ላይ ጠብቆ "ባለ በጉ ጋር ሳትስማሙ ቀራችሁ እንዴ?" አለኝ።

"አዎ አልተሰማማንም በሰስት ሺ ልውሰደው ብለው እንቢ አለኝ!" አልኩት።

"ታድያ ሌላ በግ አትገዛም ነበር?"

"ገመድ ልግዝ ብዬ ነው እንጂ አሱማ መች ይቀራል!" አልኩትና እየወጣሁኝ እንዳለ ከኋላዬ "ገመድ ምን ያደርግልሃል በምባይልህ ይዘኸው ሄድክ አይደል!" ብሎ ሲሰቅብኝ ሰማሁት።

እንዳልሰማ ሰው ችላ ብዬው ወደ ዶሮ ተራ አመራሁኝና ባለ ሁለት እግር ባይሆን ኑሮ "በግ ነኝ" ብሎ ቢፎክር የሚያምርበት አውራ ዶሮ ገዝቼ ቤቴ በር ላይ ቁሜ እንዳልኩኝ ምንነቱን በውል ለመለየት ያልቻልኩትን እንሰሳ ገዝቶ መጣና ለልጇ እያቀበለ "እንካ አንተ

ይሄ በግ ገመዱን እንዳይበጥሰው ግጥም አድርገህ አሰረው!" አለው አኔን አኔን እየተመለከተ።

"ኡኡቴ ከገመዱ ይልቅ አንገቱ እንዳይበጠስ ፍራ!" አልኩኝ በልቤ። ለይ በግ አቴ! ልብ ብላችሁ ብታዩት እኮ ያለ ምንም አረፍት እስከ ዳግማይ ትንሳኤ መሳቅ ትችላላችሁ። ፎቶውን ፌስቡክ ላይ ፖስት ላደርገው አስቤ ከማነሱ የተነሳ በአጉሊ መነጸር ካልታገዘ በቀር ምባይሌ ካሜራ ውስጥ ሊገባልኝ አልቻለም። የሚገርማችሁ ነገር ይሄን ሙትቻ በግ ለመግዛት ያደረገው ክርክር አሰብን ለማስመለስ የሚያስችል መሆኑን ሳስብ ሳቄ ያፍነኖል።

ይሄ ተንከሲስ የሆነ ሰውዬ እኔም በህማማቱ ተረጋግቼ ሱባዔ እንዳልገባ ሊረብሸኝ አሰቦ ይሄው አርብ ቀን የጀመረ በደጄ ላይ እየተመላለሰ ቢለዋ መሳሉን እና መሞረዱን ቀጥሎበታል። የሞተን በግ ለመግደል ምንድን ነው እንዲህ አለቅጥ መዘጋጀት? ያቺ ጉፋያ ሚስቱ ደግሞ ሚስቴን ሲታናድዳት "ቆዳውን ሸጠን ተጨማሪ አንድ ዶሮ እንገዛለን" እያለች አፏን ስትከፍት ነው የዋለችው።

ባንተዋወቅ ይገርመኝ ነበር። እኛ ቤት አመቱን ሙሉ ቋንጣ ሲሰቀል እነሱ ቤት አለንጋ ነበር የሚሰቀለው። እውነት እላችኋለሁ በኔ ዶሮና በሱ በግ መሀከል ያለው ብቸኛ ልዩነት የመጠን ሳይሆን የድምጽ ብቻ ነው። እስከ ሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት ድረስ የሱ በግ እየጮኸ አላስተኛኝ ብሎ ነበር። ከዘጠኝ ሰዓት በኋላ ግን የኔ አንበሳ ጩኸቱን ጀመረ።

ኩ.....ኩ.....ኩ...ኡኡኡኡኡ

ኩ.....ኩ.....ኩ...ኡኡኡኡኡ

የአባተ በግ "ጅብ መጣብኝ" ብሎ መግቢያ ቀዳዳ አጣ ነው የምላችሁ።

ሌሊቱ ነጋና ማለዳ ይሄ በግ ተገፎ ምን እንደሚቀረው ለማየት እንደጓጓሁ "የሰው አይን መጥፎ ነው" በሚል ተልካሻ ምክንያት ቤት ውስጥ አረዱት። የዚህ ጠላቴ ዋና መለያ ምን እንደማስብ ቀድሞ ማወቁ ነው።

ሸር ጉዱን ብታዩት የህዳሴው ግድብ መሰረት ድንጋይ የተጣለ ቀን እንኳን እንዲህ ሴረሞኒው መድመቁ ያጠራጥረኛል።

በግድግዳው አልፎ የሚያወሩት ነገር ይሰማናል። ህጻኑ ልጅ "አባዬ ጠብሼ የምበላው የበጉን ቆለጥ ሰጠኝ" ሲለው "ቆለጥ የለውም ማለት አማረኛ አይደለም እንዴ?" በማለት አባተ ተቆጣው።

"ትንሽ ከቆየ ከቆዳው ውጭ ፍርንባና ቅልጥምም እንደሌለው ይገባዋል!" ብዬ በራሴ ንግግር ንፍር ብየ ሳቅኩኝ።

በጉ ተገፎ አለቀና ትንሹ ልጅ ቆዳውን አርባ ብር ሸጦ ግማሽ ሊትር ዘይት ገዝቶ እንዲመጣ ተላከ። ልጁ አስኪመለስ ድረስ ልጄንና ሚስቴን ይዤ ደጅ ላይ ቁጭ አልኩኝ። ከአፍታ ቆይታ በኋላ ልጁ ቆዳውን ይዞ ተመለሰ።

"ምን ሆነህ መለስከው?" አለ አባተ በሲጋት ውስጥ ሆኖ።

"አባባ የግልገል ቆዳ አንገዛም አሉኝ!"

መጀመሪያ ብቻዬን ከት ብየ ሳቅኩኝ። ቀጥሎ ዞር ብዬ ቤተሰቤን በየተራ እያየሁ ሳቄን ለከሰኩባቸው። ሃሳቤ ገባቸው መሰል ሁሉም በጅምላ ፍንትው ብለው ሳቁ። አባተ ቆዳውን ከልጁ እጅ ላይ መንጭቆ ወደ ቤት ይዞት ገባ።

የት አባቱ ሲፈልግ አንዛ ያድርገው አሁን ተረጋግቶ ፈረሰኛዬን መጋጥ እና የእንኳን አደረሳችሁ መልእክቴን ማድረስ እችላለሁ።

እጦት

በረዶ ንጣቱን አይቼ
ቅዝቃዜውን ዘንግቼ
ለብታውን ውብ ጥርስሽን ፥ "በረድ ይመስላል" አልኩ እኔ
እኔን ብሎ ውበት ገላሜ ፥ እኔን ብሎ ባለቅኔ

ሀር መሰል ጉድ ጸጉርሽን ፥ ተፈጥሮውን ላድንቅ ብዬ
"የባህር ጥግ ቀጤማ" አልኩት ፥ ባራሙጃ ሳር ወከዬ
አልጠውላኒ ጉንጉንሽን ፥ ከድርቆ አረም የምመድብ
ደግሞ እኔን ብሎ ገጣሚ ፥ እኔን ብሎ ደግሞ ጠቢብ

ውብ መአዛን የታደለን ፥ የጎመራ ያንቺን ገላ
ከፍናፍንት ወገን ባለች ፥ ምጣድ ያከል ደረት አዝላ
የጣፈ አንጓ በሰለተ ፥ ባልገባችኝ የሰው ምስል
"ሞናሊዛ" በሚሏት ሴት ፥ ሀላፊሽን የምመስል
ባለዜማ ልሳንሽን ፥ ከዱዳ ጋር የምመድብ
እኔን ብሎ ደግሞ አድናቂ ፥ እኔን ብሎ ደግሞ ጠቢብ።

'አካኪይ አካኪየሺች'

ጫኔ ማለት መስሪያ ቤት ውስጥ የተዋወኩት በጣም ከፍተኛ የገንዘብ ችግር ያለበት የስራ ባልደረባዬ ነው። ፈጣሪ ይሄን ሰውዬ የሰራው የሩስያ ልብ-ወለዶችን አንብቦ ይመስለኛል። ቃሉም ይሳካ ዘንድ በደርግ ጊዜ ተምሮ እንዲመጣ የተላከው ወደ ሞስኮቭ ነበረ።

የእኛ ርእዮተ-ዓለም ብዙም አይመቸውም። የሶሻሊዝም አቀንቃኝ ነው። በዚያ ዘመን ሩስያ ሄደው የተማሩትን ዜጎቻችንን ስንመለከት በአንዳንዶቹ ላይ የሆነ ለውጥ ይታይባቸዋል። ከባህልና ከማህበረሰቡ የማፈንገጥ አይነት አዝማሚያ አላቸው። ጫኔም ላይ ይሄው ነገር ስለሚታይ "ወፈፌ" የሚል ቅጽል ተሰጥቶታል። መቼም ያም ሁኖ ከአረብ አገሩ አብደትና ከእኛ አገሩ ቀውስነት የራሽያው ወፈፌነት ሳይሻል አይቀርም።

የጫኔ የአብደት አይነት ልብስ የሚያስጥል ሳይሆን ቅልጥ ባለ ጠራራ ፀሐይ ሁለት ገበር አልባ ኮት አስደርቦ "በረደኝ" የሚያስብል ነው። አንዱን ኮት ኮሌታውን ዘርግቶ አንዱን አጥፎ ይለብሰዋል። ልብስ አለቅጥ ይደራርባል። እንዲያውም ለሆነ ነገር ሲቀጥርህ "ቤቴ ልብስ እየደረብኩ አጠብቅሃለሁ" በማለት ነው።

እንደዚያም ሆኖ አንድ ቁምሳጥን የማይበቃው ልብስ ደርቦ እየዋለ መስሪያ ቤት ይመጣና "አሞኛል" ይላል። "ምንህን?" ተብሎ ሲጠየቅ "ብርድ መቶኝ" በማለት ይመልሳል። "አይ ጫኔ አሁን አንተ ይሄን ሁሉ ልብስ ለብሰህ እየዋልክ እንኳን ብርድ ጥይትስ ይመታሃል!" በማለት ሃላፊያችን ሊያሾፍበት ይሞክራል።

ጫኔ ያለበት የገንዘብ ችግር "ካቦርቱ" ላይ ከምናውቀው ካራክተር ከአካኪይ

አካኪየቪች በሆነ መልኩ ይመሳሰላል። በጫኔ ቤት ልብስ "አልቋል" ተብሎ የሚጣል አይደለም። አዲስ ልብስም ሲገዛ አይታይም። ለምሳሌ ጌሾ አይነት ሴደርያውን ብንወስድ ሴደርያ ከመሆኑ በፊት እጅጌ ጉርድ ሸሚዝ ነበረ! ሸሚዝ ከመሆኑ በፊት ደግሞ እጅጌ ሙሉ ኮት ሆኖ አገልግሏል።

ደሞዙ ያን ያህል ዝቅተኛ የሚባል ባይሆንም ካቲካላ በመጠጣት ነው የሚጨርሰው። እንዲያውም በጣም የሰከረ ቀን ኮማሪቶቹ ከኪሱ ሁሉ አውጥተው ሊወስዱበት ይችላሉ።

ቢሮ ውስጥ ያለው ባህሪ የሚገርም ነው። የመረጃ አያያዙ በጣም ዘመናዊና ጥንቃቄ የተሞላበት ሲሆን ባለጉዳይም ሲያስተናግድ በቅንነት ነው። አንዳንዴ ቢሮ ውስጥ ስንወያይ ቁምነገር ብሎ የሚያወራቸው ነገሮች ለሌላው ሰው አስቂኝ ሆነው ይታያሉ። ባንድ ወቅት "የሆነ ጫማ ቤት ጫማ ልገዛ ሄጄ 'ሁለት ሺ አምስት መቶ ብር' አሉኝ" እያልኩ ሳወራ ጫኔ ሰማኝና "አምስት መቶ ብር ጨምረህ በሶስት ሺ ብር እንዴት ያለ ሰጋር ፈረስ ገዝተህ በባዶ እግርህ አትጋልብም እንዴ?" የሚል ሃሳብ አፈለቀ። ይሄን ነገር ያለኝ ለቀልድ ብሎ አለመሆኑ ደግሞ ነገሩን አስገራሚ ያደርገዋል።

የወሲብ ፍላጎት የለውም። ሴቶችንም አይወድም። አዳምን ባበሉት እፀ-በለስ ዛሬም ቂም እንደያዘባቸው ነው። "ከእያንዳንዱ ስኬታማ ወንድ በስተጀርባ አንዲት ጠንካራ ሴት አለች" በሚለው አባባል አይስማማም! "ከእያንዳንዱ ወፈፌና ሱሰኛ ወንድ ጀርባም እነሱው ናቸው ያሉት!" በማለት ይሞግትሃል።

ጫኔ አዳና ዱቤ ነፍሱ ነው።

በአዳ ብዛት ከኢትዮጵያ ቀጥሎ በሁለተኛነት ደረጃ ስሙ መጠራት ያለበት ሰው ነው። ያለበት አዳ ብዛቱ በአገር ደረጃ እንጂ በግለሰብ ደረጃ ሊመዘገብ የሚችል አይደለም። የእሱ አዳ ከአገራችን አዳ ለየት የሚያደርገው የማይከፈል መሆኑ ነው። አበዳሪው ካልሰረዘለት እራሱ ይሰርዘዋል። ፍርድ ቤቶችም ቢሆኑ ከሶቹ ከመብዛታቸው የተነሳ የእሱን ፋይል ላለማየት የወሰኑ ይመስለኛል።

የሆነ ጊዜ እማማ ጀንበሬ ከመንግስት ብድር አውጥተው "ህዳሴ ምግብ ቤት" የሚል ታፔላ ለጠፉ። ለእጅ መታጠቢያ አጃክስና የዘይት ጀሪካን አስቀመጡ። ከተዋቂ ሬስቶራንት የሚስተካከል የምግብ "ሜኑ" አዘጋጁ። ከዚህ በፊት በምግብ ስራ ላይ ተሰማርተው ያውቁ ይመስል "ለከቡራን ደንበኞቻችን በቅርብ ቀን ስራ እንጀምራለን" ብለው ለጠፉ። ከዛሬ ነገ እማማ ጀምበሬ ቀይ ወጥ መስራት ጀምረው

"አቅልተን፣ አቅልተን እንጥለዋለን" እያልን ስናወራ... በቅርብ ቀን የተባለው ቀጠሮ እንደ እለተ ምፅዓት ረዘመ። ይሄም አልበቃ ብሏቸው "ከሰርኩ!" የምትል የእርጥባን ወረቀት ይዘው መዞር ጀመሩ።

"እንዴት ስራ ሳይጀምሩ ይከስራሉ?" በማለት ጠየቅናቸው።

"አይ መጀመሩንስ ጀምሬ ነበር። አቅሜ ካንድ ሰው በላይ መያዝ ስላላስቻለኝ ጫኔን ስቀልብ ከርሜ 'አላውቅልሽም!' ብሎ ካደኝ" በማለት ተከዙ። ብር አሰባስበን ሰጠናቸውና ወደ ጫኔ ዘንድ ሄደን "ለምንድን ነው የማትከፍላቸው?" ብለን ጠየቅነው።

"እሰጣቸዋለሁ እንጂ! ያን ሁሉ ጨው ስበላ ከርሜ ምን ብዬ እቀማቸዋለሁ" በማለት አሾፈብን። ይሄን ስታስብ ደግሞ ፊዮደር ደስቶዮቪስኪ "crime & punishment" የሚለው መጽሃፉ ላይ ዋና ገጸ-ባህሪ ካደረገው "ራስኮልኒኮቭ"ጋር ይመሳሰልብሃል። መቼም የእማማ ጀንበሬን ገንዘብ መቀማት አሮጊቷን ከመግደል አይተናነስም።

"እንዴት ህሊና እያለህ ይሄን ታደርጋለህ?" ስትለው ድርጊቱን ከሚከተለው ፍልስፍና አንጻር አገናኝቶ ሊያወራህ ይፈልጋል። "የማርክሲስት ፍልስፍና ዳይሌቲካዊም ቁስ አካላዊም በመሆኑ ከህሊና በፊት ህልውናን ማስቀደም አለብህ!" ይልሃል።

የእዳውን ጉዳይ እንተወውና ስለ ኮቱ እናውራ።

የኮቱ ሁኔታ አሳሳቢ ደረጃ ላይ ቢደርስም ጫኔ ሊቀይረው አልፈለገም። ሁሉም ኮቶቹ ዋና አካላቸውን ጨርሰው በገበር ብቻ የቆሙ ናቸው። የሆነ ቀን ኮት የሚገዛ ከሆነ የተወሰነ ብር እኔ እንደምጨምርለት ነገርኩት። እሱን ኮት ማልበስ ማለት ለአካኪይ አካኪየቪች ካፖርት መግዛት መሆኑን ተገንዝቤለሁ። በስንት ልመናና ምልጃ "እሺ" ብሎኝ ወደ ቡቲክ አመራን።

እግራችን እስኪቀጥን ብንዞርም እንደ አካኪይ አካኪየቪች የአውሬ ጸጉር ወይም ኮሌታው ላይ የድመት ቆዳ ያለው ካፖርት የሚፈልግ ይመስል አይኑ የሚገባ ኮት ማግኘት አልቻለም ነበር። ከብዙ ልፋት በኋላ አንድ ነጫጭባ አሻንጉሊት የለበሰው የታይዋን ኮት ላይ አይኑ አረፈ። እሱ የሚፈልገውን ኮት ለማግኘት የተጓዝነው ርቀት "ታይዋን" ሂዶ ገዝቶ ለመምጣት ያስችል ነበር።

"ይሄ ኮት ስንት ነው?" አለ ክአሻንጉሊቱ ላይ ልብሱን እየገፈፈ።

"አንድ ሺህ ብር"

"መሄጃውን" አለ ኮቱን እየለካ! ሁኔታውን ሳየው ኮቱ ልኩ ባይሆንም ሊገዛው ወስኗል።

"ከአንድ ሺህ ብር አይቀንስም!" የተሰላቸው ባለ ቡቲኩ መለሰ።

"በል መጨረሻውን ቁርጥ አድርገህ ንገረኝ!"

"ዘጠኝ መቶ አምሳ ብር ይሁንልህ!"

"ከዘጠኝ መቶው ብር የምቀንሰውን ተናገር?"

"በቃ በዘጠኝ መቶው ብር ውሰደው"

"መሄጃውን ተናገር ነው የምልህ!"

ክርክሩ እንደ ጉድ ጦፈ።ኢትዮጵና ኤርትራ እንኳን በድንበር ጉዳይ ይሄን ያህል የተከራከሩ አይመስለኝም።

"በቃ አንተ ተናገር?" አለው ባለ ሱቁ።

"ሰባት መቶ ልውሰደው?"

ባለ ሱቁ ተንኮል ባዘለ ሁኔታ "በቃ ውሰደው" አለው። በመስማማታቸው ትልቅ እፎይታ ነው የተሰማኝ። እነሱን ከማስማማት ደቡብ ሱዳኖችን ማስማማት ሳይቀል አይቀርም።

ሁለት መቶ ብር አወጣሁኝና "እዚህ ላይ አምስት መቶ ብር ጨምርና ክፈል" አልኩት።

"እስኪ ደግሜ ልሞክረው" አለ ጫኔ አፍንጫው ላይ ላቡ ችፍ ችፍ እያለ።

"ለካሽው እኮ?" አለው ባለ ቡቲኩ በቁጣ።

"እሺ በቃ የዚሁ አይነት አድስ ኮት አምጣ!" አለው። እንደዚህ አይነት ኮት ባሁኑ ሰዓት እንኳን እዚህ ቡቲክ ታይዋን አገር ራሱ እንደማይር እርግጠኛ ነበርኩኝ።

"እሱ ሳልባጅ ነው እንዴ?" አለ ባለ ቡቲኩ እየተናደደ።

"ታድያ ምንድን ነው?"

"ተጎሳቁሎ ነው እንጂ ሳልባጅ አይደለም!"

"እንዴ! ሰልባጅ ነው እንጂ! ይሄ አሻንጉሊት ከለበሰው ስድስት ወር ሞላው አይደለ?"

ባለ ቡቲኩ ደሙ ፈላ።

"ላትገዛ ነገር ምን ያስቀባጥርሃል አንተ ዝትቻ" አለ የልብስ መስቀያ ዘንጉን እየጨበጠ።

"ተው አንተ ሰው በህግ አምላክ! ደምበኛ ከቡር ነው አይሰደብም!" አለ ጫኔ ሲገዛው የኖረ ይመስል።

"ኧረ ዱላም ይከተልሃል" አለ ባለቡቲኩ የልብስ መስቀያው ዘንጉን እያነሳ!

ከዱላው በፊት እኛ እየወጣን በር ላይ እንደደረስን ጫኔ "የዛሬ ዘመንን ልብስ አሻንጉሊት ይልበሰው" አለ፣ ከላይ እስከ ታች ዝንጥ ብሎ ያማረባት አሻንጉሊት ፊቱን አዙሮ እያየ።

እንቆቅልሽ

"እንቆቅልሽ" ብለናቸው__ቢጠፋባቸው መልሱ
"አገር ሰጡን" ሰንላቸው__አህጉር ሰጥተውን እነሱ
አውነት ሁኖ ተቀያይረን__እኛ ብንሄድ አሜሪካ
ሰንካሰስ ይግባኝ ሰንል__ድንበር ወሰን ሰናስለካ
ኮሚቴችን አስኪዋቀር__የጤፉ ሊጥ አስኪቦካ
በዛች ከፍተት
ያኔ አፍሪካ ተለውጣ__አሸብርቃ ሆና ገነት
ዲቪ መሙላት ጀምረናል__ወደ ሄጮች ለመሰደት።

ሼፍና ሹፈት

የድሮ ድሃ ሀልም ቅቤ 'ሚጠጣበት
ያለ እቅድ ያለ አሳብ የሚታለምበት
የወትሮ ሰው እንቅልፍ አልፏል እንደ ዘበት!
የአሁን ዘመን ድሃ ያለ ፕሮግራሙ
እንኳን ቅቤ ቀርቶ ጠላ እንኳን ለጥሙ
ከበጀት አቅድ ውጭ አይጠጣም በህልሙ።

በሀገራችን የሚተላለፉ የቴሌቪዥን ሾዎችና ፕሮግራሞች አብዛኛውን የህብረተሰባችንን ከፍል የማይወክሉ እየሆኑ መምጣት ከጀመሩ ሰነባብተዋል። ምንም እንኳን ፕሮግራሞቹ አይተላለፉ የማለት አቅሙ ባይኖረንም አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ምግብ ዋስትናውን ያላረጋገጠ ነውና ልክ ፊልሞቻቸውን "ከዚህ ዓመት በታች ላሉ የተከለከሉ" እንደሚሉት ሁሉ የቴሌቪዥን ሾዎችንም "ከዚህ ገቢ በታች ላለው ሰው ያልተፈቀዱ" እያሉ ክልል ቢያበጁልን የሚል አስተያየት አለኝ።

ለምሳሌ አንዳንድ የህክምና ባለሙያዎቻችንን ብንወስድ በቴሌቪዥን መስኮት ውስጥ አንዳች የሚያክል ቦርጫቸውን ጭናቸው ላይ አስቀምጠው፣ አገጫቸው ላይ ስም ያልተሰጠው ሲጋ አንጠልጥለው "ኮሌስትሮል የበዛበት ጮማ እና ምግብ እንዳንመገብ፣ ውፍረታችንን እንድንቀንስ፣ ገላችንን በየእለቱ እንድንታጠብ" በሰፈው ምክር ሲለግሱን በላተኞቹም እነሱ... መካሪዎቹም እነሱ ሆነው ሳይ ግርምታ ይፈጠርብኛል።

ኑሯችን በስጋት እንጂ በሰጋ ላይ የተመሰረተ አለመሆኑ እየታወቀ፣

የምንታጠብበት ቀርቶ የምንጠጣው ውሃ እስኪፈልቅልን ድረስ ጀሪካችንን ደርድረን ስንጠብቅ እያዩ፣ በኮሌስትሮል የበለጸገውን ዘይት ማቅረብ ለመንግስታችን አዳጋች ሁኖበት ከዛሬ ነገ "ያለ ዘይት መብላትን ተለማመዱ" የሚል የአቋም መግለጫ እስኪያወጣ እየጠበቅን ባለንበት ሁኔታ ከብደትን ስለመቀነስ፣ የአበላል ባህልን ስለማስተካከልና የግልና የአካባቢን ንጽህናን ስለመጠበቅ በማስተማር የአየር ሰዓትን መፍጀት አግባብነት የለውም።

"መማር" ማለት የተማሩትን ማስተጋባት አይደለም። "መማር" ማለት አካባቢን፣ ህብረተሰብን የመታዘብንና የመረዳት ከህሎትን ማዳበር ነው። በቆሎ አስፈጭቶና ወደ ገንፎነት ቀይሮ በዘይትና በቅቤ የመብላት አቅሙን አጥተን.... በቆሎን ከእሳት ጋር በማዋሃድ አስጠብሰን መንገድ ላይ ስንግጥ እያዩን.... ሰጋ ቤት መግባት ቀርቶ በሰጋ ቤት በኩል ማለፍ ሰቆቃ ሁኖብን.... ስለ ኮሌስትሮልና ስለ ጮማ አላስፈላጊነት ማስረዳት ከንቱ ድካም ነው ብዬ አሰባለሁ። ይልቅ ውፍረትን ሳይሆን ሃሳብንና ጭንቀትን እንዴት መቀነስ እንደሚቻል ግንዛቤውን ብትፈጥሩልን መልካም ነው።

አልተረዳችሁንም እንጂ የምንፈልገውን ትተን የምናገኘውን መብላት ከጀመርን ቆየን እኮ። ድሮ ለዓመት በአል የምንዘለዝለው ስጋ ዛሬ ተረት ሁኖብን ለበግ መግዣ ያዘጋጀነው ገንዘብ ዶሮ አልገዛ እያለን፣ የምንገዛውን ፍየል ከገባያ አስረን ልናመጣበት ይዘነው የሄድነው ገመድ እየወዘወዘነው ወደ ቤታችን ስንመለስ "ታነቁብኝ" እያለ እየወሰወሰን.... ቤታችን ገብተን ደግሞ በዓሉን እናንተ ስትበሉና ስትጠጡ እያየን ልናሳልፍ ቴሌቪዥናችንን ስንከፍተው ያልበላንን ማከክ ትጀምራላችሁ።

በዚህ በስጨት ብለን ቻናሉን ስንቀይረው ደግሞ "ሼፍ" የሚባሉ የምግብ ሊቃውንት ቢላዋቸውን ይዘው እያሻመዱ ይጠብቁናል። ባማረ ኪችናቸው ውስጥ እየተሞናደሉ፣ ያማራቸውን ሁሉ ከሞላ ፍሪጃቸው ውስጥ እየመዘዙ አሰራሩንና አበላሉን ሊያስተምሩን ሲሞክሩ ሽንኩርት የሚከትፉበትን ቢለዋ ቀምቼ እጃቸውን ብቆርጠው ደስታውን የምችለው አይመስለኝም።

ስሙን ሰምተነው የማናውቀውን የቅመም፣ የቅባት፣ የአትክልት ዘር ሲዘረዝሩ ሳይ "እኒህ ሰዎች የሚያስተምሩን ስለ ምግብ አበላል ነው ስለ ሙስና አበላል" የሚል ጥያቄ አነሳለሁ። ምክንያቱም የነሱን ምግብ አዘጋጅተህ ለመብላት አስቀድመህ ሙስናውን መብላት አለብህ።

በዚህ ሃሳቤ ግን ሚስቴ መስማማት አትፈልግም።

ጨውና በርበሬ የጎደለበት ማጀት ታቅፋ፣ ፈንገስ ያበቀለ ባዶ ሞሰብ አስቀምጣ የምግብ አዘገጃጀት ፕሮግራሙን ግን ለመከታተተል ወደ ኋላ ብላ አታውቅም። እንዲያውም እንደ ኤለመንታሪ ተማሪ ባለ አስራ ስድስት ሉክ ደብተር ታስይዘኝና "የምነግርህን ቶሎ ቶሎ ጻፍልኝ" በማለት ትእዛዝ ትሰጠኛለች።

እንደ አባዋራነቴ የምትነግረኝን ሁሉ "ገዝተህ አምጣልኝ" ካላለችኝ ለመመዝገቡስ ችግር የለውም በማለት "እሺ ንገሪኝ" አላታለሁ አስኪብርቶውን ደብተሩ ላይ እየሰካሁ!

"ጎመኑን ለብ አድርጎ መቀቀል ብለህ ጻፍ"

"ጎመኑን ለብ አድርጎ መቀቀል" እላለሁ እያንዳንዷን ፊደል ረገጥ አድርጌ።

"ግማሽ ኪሎ የሚሆን የተፈጨ ቀይ የጥጃ ስጋ በል!"

"ብያለሁ ቀጥይ!"

"የተጠበሰ አሣ ብለህ ጻፍ!"

"አልጽፍም!"

"ለምንድን ነው የማትጽፈው?"

"አሣ የሌለበት ሀገር እየኖርኩ ምን ብዬ ስለ አሣ እጽፋለሁ?"

"ለወደፊቱ አሣ ያለበት ሀገር ልንሄድ ስለምንችል ጻፈው!"

"እሺ ይሁን" ብዬ እጽፋለሁ።

ከዛ በኋላ ሚስቴ የማታውቃቸውንና የማትፈልጋቸውን መዝለል ትጀምራለች

"ዝንጅብሉንስ ልጻፈው?" እላታለሁ እንዳልሰማ ስታልፈው ጊዜ ሳቄ እየመጣ ።

"እሱን ዝለለው! ኪሎ ስልሳ ብር ገብቷል"

"ካቻፕ እያለችሽ እኮ ነው እሱንም ልዝለለው እንዴ?"

"አዎ ዝለለው"

"ምንድነው ዝለለው ማለት ጠቅላላ አጥር አደረግሽው እኮ"

" እህ! እስኪ መቀባጠሩን ትተህ የገብስ ዳቦግል!"

"የገብስ ዳቦ"

"ማርጋሪንና እና የለውዝ ቅቤ ብለህ ጻፍ"

"ጽፌዋለሁ ቀጥይ"

"ቀይ ወይን ወይም ኮካ ኮላ መጥበሻው ላይ መጨመር በል!"

"ኧረ ተይ ማሬ ተይ! ይሄን ምግብ ለማዘጋጀት እኮ የሁለታችንም ደሞዝ ተደምሮ አይበቃንም"

"ባንሰራውም እውቀቱ ጥሩ ነው ጻፈው!"

"እሺ" ብዬ እጽፈዋለሁ።

በመጨረሻ አዘጋጁ ጉዷን ታመጣለች። "ይሄን ምግብ ለማዘጋጀት ዋናውና አስፈላጊው ነገር "Oliva oil" ሲሆን አሪፍ ጥራት ያለው ዘይት ከፈለጋችሁ ከጣሊያን አገር ማስመጣት ትችላላችሁ" ብላ ወደ ሌላ ቅመማ ቅመም ልትገባ ስትል አላስጨርሳትም።

"ምግቡ ሳይኖር አዘገጃጀቱን ማወቅ ምን ያደርግልናል?" ብዬ ቻናሉን ወደ ኢቲቪ አዞረዋለሁ።

"ተው እንጅ! ቀየርከው እኮ" ትላለች ሚስቴ ተስፋ በቆረጠ ስሜት ውስጥ ሆና።

"ባክሽ ተይ! የጭነት መኪና ይመስል የወይራ ዘይት ከጣሊያን አገር ላስመጣ እንዴ?" ብዬ እቆጣትና ተነስታ ወደ ባዶ ማጀቷ ትገባለች።

ኢቲቪ ላይ እንደተለመደው "የእርሻ ማሳ አዘገጃጀት" እየታየ መሆኑን ሳስተውል ደግሞ ግብርና ለመማር ዩኒቨርሲቲ ከመግባት ይልቅ ሰርቲፊኬቱ እንጂ የሚቀረው ትምህርቱን በፕላዝማ በታገዘ የርቀት ትምህርት ኢቲቪን ብቻ በመከታተል መማር እንደሚቻል አስባለሁ።

ከሂደት የፀዳ

ከተፈጨ ሸክላ ከተበላ ሜቃ
እኛ እንደሰራነው ማሰሮ ቡሃቃ
በእግዜር ጥበብ መሃል እንዴ እንስራ ምንችት
ለአንዲት ቀን ረግቶ ቁሜ ያለ በማቶት
ከአፈር የተገኘ የት አለ ሰውነት?
ሰው ሆኖ መረጋትን መች ታደለን ለኛ
እድሜዎችን ድልድይ ነው አፈር የመሆኛ።

ያገረሸብኝ ወቅት

እብደቴ ተነስቶብኛል።

እብደቴ ሲነሳ ገመናዬ ያበቃለታል። ወቅት እየጠበቀ ሰኔ ግም ሲል የሚነሳ እብደት አለብኝ። ያኔ ሰዎች ከንፈራቸውን ሲመጡልኝ እታዘባቸዋለሁ። እኔ ግን የሚሰማኝን እፎይታ አምላክ ይወቀው።

እብድነቴን የሚያረጋግጥ ከአማኑኤል ሆስፒታል የተገኘ ሰርቲፊኬት አለኝ። ይሄ ሰርቲፊኬት አንዳንድ ቦታወች ላይ ከታዋቂ ዩኒቨርሲቲ ከተገኘ የሁለተኛ ድግሪ ወረቀት በላይ ጥቅም አለው። ለምሳሌ ግንባርህን ፈርክሽህ ላልታሰር እችላለሁ።

በአማኑ ቀን አሰራ ሁለቱን የስነምግባር፣ ስምንቱን የመልካም አስተዳደር መርሆች ከፊትና ከኋላዬ ለጥፌ ቢሮክራሲዬን ስደረድር እና ፍትህን ሳጓድል የምውል ሰው ነኝ።

ከቢሮ ውጭ ደግሞ አቤት የሰላምታዬን ቁጥብነት ብታዩት፣ አቤት ስነስርአት፣ አቤት ለራሴ ያለኝ አመለካከት "አቶ" የሚለውን ማእረግ ሳልጨምር ስሜን እጠራዋለሁ ማለት ዘበት ነው።

በህዝብ ዘንድ ተቀባይነት አለኝ ማለት አልችልም። ሰዎች "የሳር ውስጥ እባብ፣ ቀይ እባብ፣ ሙሰኛ ወዘተ" እንደሚሉኝ አውቃለሁ። እነሱ የሚሉትን ነገር እኔ ውስጥ ስለማይታየኝ እና ለሚሉት ነገርም ማሰረጃ ስለሌላቸው ያን ያህል ቦታ አልሰጣቸውም።

ጉረኛ ነኝ። በሰዎች ፊት ልጄን እጁን እየሳብኩ እሄድና "ወደ የት ነው?" ሲሉኝ

"ለዚህ ጎረምሳ በስሙ አካውንት ከፍቼ እስኪ ትንሽ ብር ጣል ላድርግለት ብዬ ነው" እላቸዋለሁ።

ሰዎች ከማይወዱት ባህሪየ አንዱ አስመሳይነቴን ነው። አለቃዬ ጋር፣ መንግስት ጋር፣ ሊቃውንቱ ጋር፣ ቀሳውስቱ ጋር ሁሉም ጋር እንደ እስስት አለዋወጣለሁ። በግብዝነት የተሞላ በጎ አድራጎትም ላይ እሳተፋለሁ። መንግስትማ "መዋጮ" ብሎ ይጠይቅ እንጂ ማንም ሳይቀድመኝ በፊት እጄን አወጣለሁ። ሰዎች ምን እንደምናገር ስለሚገባቸው ያጉረመርማሉ።

ስለማወራው ነገር እንጂ ስለሚያወሩት ነገር ስለማላስብ ከቁብ አልቆጥራቸውም። "ምን ልበል እንጂ ምን ይላሉ" ብዬ ተጨንቄ አላውቅም። "ደግሞ ለእንዲህ አይነት ልማት የወር ደምዎዝ ቀርቶ የአመቱንስ ብንሰጥ ምን አለበት? እንዲያውም ይሄ መዋጮ የመሰበብሰቡ ጉዳይ በየወሩ እንደ ጡረታ ቢቆረጥና ተጠናክሮ ቢቀጥል! የሚል ሀሳብ አለኝ" እልና ጨጓራቸውን እልጠዋለሁ። እብደቴ የተነሳ ጊዜ ደግሞ "ለአባይ የከፈልኩትን ብር መልሱልኝ!" ብዬ አቧራ ሳስነሳ እውላለሁ።

መንግስት ሰራተኛው ጋር ያለኝ መጠማመድ የከፋ ነው። ያለምንም ማሰረጃ "ሙሰና በልቷል" ብለው ጸረ-ሙሰናዎችን ጠርተውብኝ ነበር። እነሱ ሊመጡ አካባቢ "እብደቴ ተነሳ" ብዬ አማኑኤል ሄድኩ እንጂ።

"ሙሰኛ ይሉኛል" ብዬ አልሳቀቅም።እንዲያውም መድረክ ካለ "የስራ ሰዓት መሸራረፋችን፣ የመንግስት ወረቀትና እስኪብርቶ ማባከናችን ኪራይ ሰብሳቢነት ነው" እያልኩ የተሰብሳቢውን ጆሮ ሳገማው እውላለሁ። አንዳንድ ሰዎች ንግግሬን ላለመስማት በብስጭት ስብሰባውን ረግጠው ይወጣሉ።

ቤተክርስቲያንም አካባቢ አልጠፋም። ምጽዋቴ በሰዎች ፊት ይሆን ዘንድ ተግቼ እሰራለሁ። ለነፍስ አባቴ ብዙ ጊዜ ሀጢያቴን ልነግራቸው እየፈለኩ ምንም አይነት የፈጸምኩት ሐጢያት አጣና ለይስሙላ ብቻ "ሃሰት ተናግሬለሁ" በማለት እናዘዝላቸውና "አስር ጊዜ ስገድ" ብለው ያሰናብቱኛል። እየሰገድኩ እንኳን ጭንቅላቴ ሐጢያት መስራቱን አይተውም።

እግዚአብሄር እኒህን ነገሮች ሲሰበስብ ይከርምና ገመናዬ ይጋለጥ ዘንድ በየሆነ አመቱ ሰኔ ላይ ያሳብደኛል። ከዛ በኋላ ልከበው ስታትር የነበረውን ክብር እንደ ፌስቡክ ዝና በአንድ ጀምበር ድምጥማጡን አጠፋዋለሁ። ማንኛውም ሰው ከቀወሰ በኋላ የሚለፈልፈው ነገር ያበደበትን ምክንያት ነው ብዬ አምናለሁ። በሴት እጥረት

የወፈፈ ሰው ብልቱን ዘርግቶ ሴት ከማባረር የዘለለ ተግባር አይፈጽምም። እኔም ህመሜ ሲነሳ ስደብቃቸው የነበሩ ነገሮችን መቀባጠር እጀምራለሁ። ሆኖም ግን ሰዎች ሊሰሙኝ አይፈልጉም።

ሙጫ ልጄን እጁን አንጠልጥዬ እሄድና "የልጄ አካውንት ውስጥ ያስቀመጥኩትን ብር የከረምት ማገዶ ልገዛበት ስለሆነ አሁኑኑ ስጡኝ!" ብዬ አንባጓሮ እፈጥራለሁ።

ጸረ-ሙስናዎች የመጡ እለት አብጃለሁ ብዬ ወደ አማኑኤል የሄድኩት ሀሰት መሆኑን፣ ትክክለኛው አብደቴ ይሄ መሆኑንም ጭምር ባስረዳቸውም የሚሰማኝ አላገኘንም። ከዚያ በንደት የሆነ ጊዜ "ይሄን ያህል ብር ሙስና እሰጥሃለሁ" ብሎኝ ጉዳዩን ካስፈጸመ በኋላ ቃል ከገባልኝ ብር ላይ አጉድሎ የሰጠኝን ባለሃብት ከአጥሩ ውጭ ሆኘ ያስቀረብኝን ብር ይሰጠኝ ዘንድ መውጫ መግቢያ አሳጣዋለሁ።

ለነፍስ አባቴ ንዋየ ቅዱሳንን መመዝብሬን፣ የብዙ ሰው ሕይወት ማበላሸቴን እነግራቸዋለሁ። እሳቸውም ሲጠየቁኝ ሳይ ደግሞ ወደ ሚስቴ ጋር እሄድና ከሌላ ሴት ስለደቀልኩት ልጄ ማብራሪያ እሰጣታለሁ። በጤነኝነቴ ዘመን ከሰዎች እይታ ደብቄ የሰራሁትን ነገር ሁሉ አንድ ባንድ እየዘረዘርኩ ላባለጉዳዩ ባስረዳም ከመጤፍ የሚጥፈኝ ሰው አላገኘንም።

መጨረሻ ላይ ወደ አማኑኤል ይዘውኝ ይሄዱና ዶክተሮቹ "እሺ ጌታው አሁንስ ለምን እንደመጣህ ልትነግረን ትችላለህ?" ይሉኛል።

"ድፕሎማዬን ትሰጡኝ እንደሁ ለመጠየቅ ነበር!" እላቸዋለሁ።

"የምን ድፕሎማ?"

"በህይወት ዘመኑ አንዴ ታሞ የዳነ አብድ ጋር እኩል ሰርቲፊኬት የሚሰጠኝ ለምንድን ነው? ለኔ ለየት ያለ ድፕሎማ ለምን አይዘጋጅልኝም?"ብዬ ቀውጢ አፈላለሁ። ያንኑ አስቀያሚ ከኒን ከመስጠት ባለፈ የምላቸውን ማዳመጥ አይፈልጉም።

ይሄን ሁሉ እየለፈለፍኩ የሚያዳምጠኝ ሳጣ ራሴን ማጥፋት እፈልጋለሁ።

በነገራችን ላይ የሰው ልጅ ከሌሎች እንስሳት ለየት የሚያደርገው በፈለገው ጊዜ ራሱን ማጥፋት መቻሉ ነው። ራሳችንን በፈለግነው ቦታና ጊዜ የመፍጠር እንጂ የማጥፋት ስልጣኑ ተሰጥቶናል።

"ሰው እንደ ቲማቲምና ቃሪያ አይደለም። ጓሮህ የበቀለን ቲማቲም ይሄ ጥሬ

ነው ለመቀጠፍ አልደረሰም፣ ይሄ ብስል ነው መቀጠፍ አለበት እያልክ ትለየዋለህ። ሰው ግን እንደዚያ አይደለም። የሰው ልጅ ከተፈጠረ ጊዜ ጀምሮ ለመቀጠፍ የደረሰ ነው?" ያለው ፈላስፋ ማን ነበር? ፍልስፍናው እንጂ ፈላስፋው ስለማያስፈልገኝ መልሱን ባትመልሱትም ችግር የለውም።

ራሴን ላጠፋ ውሳኔ ላይ እደርስና ግን ከመሞቴ በፊት ያሉኝን ሚስጢሮች መደበቅ እንዳለብኝ በማሰብ የብልቴን ጸጉር እላጫላሁ፣ ፌስቡክ አካውንቴን "ድአክቲቬት" አደርጋለሁ፣ ገላዬን እታጠባለሁ፣ ከዛ በኋላ መዳን እጀምራለሁ ማለት ነው። ከሞት በኋላ ስለሚገለጥ ሚስጥር ማሰብ፣ ሰው እንዲህ ይለኛል ብሎ መጨነቅ የጤነኝነት ምልክት መሰለኝ።

አሳብዶኝ ሀጢያቴን ተናዝዣ፣ ራሴን ሂስ አድርጌና ሱባዔ ገብቼ ወደ ሞት ልሄድ ስጣደፍ ፈጣሪ ከህመሜ ይፈውሰኝና ሌላ ሰው የመሆኛ እድልን ይሰጠኛል።

ጤናዬ ሲመለስ የወትሮው አስመሳይነቴ፣ ቀጣፊነቴ፣ ጉረኝነቴ፣ ተንኮለኝነቴ፣ ኩፍሰነቴ... አብሮ ይመለሳል።

የምትወደው ልብ ውስጥ

ሲያዝብኝ.....
ዐይንሽን በኮከብ መሰልኩኝ፣
ሰተዊኝ...
ከዋክብቱንም ጠላሁኝ።
አግዚኦ.....
ጸጉርሽን ቀጤማ ከንፈርሽን አበባ፣
ጥርስሽን በረዶ አካልሽን ዘንባባ፣
የማየው በሙሉ ባንች ተመስሎ ሆዬን አያባባ፣
አሁን አንቺን ሳጣ የት አባቴ ልግባ?

ባለፈው እንደ ቀልድ መድብሌን አየሁት፣
ግጥሙ በሙሉ አንቺን ነው የሚያትት፣
"መንግስት" በሚል አርስት የጀመርኩት ግጥም፣
ዘብዝቦ፣ ዘብዝቦ መጨረሻው ግድም፣
"መንግስቴም አንችው ነሽ
ንጉሴም አንችው ነሽ" ብሎ አሳቡን ድምድም።

ይሄን የዋህ ልቤን....
የምትወደው ልብ ውስጥ መሞትክን ከምታውቅ፣
"አልሞቱኩም" በልና ከአካባቢው ራቅ፣
...ብዬ እነግረዋሁ
ልርቅሽ አያልኩኝ
በሸሸቴ መሃል -ምናለፋሽ ውዴ፣
ልረሳሽ አልቻልኩም የማየው በሙሉ ልቤን አያራዴ።

ድንጉላ

ለሴት "ድንግል" ካልን ለወንድ "ድንጉላ" እንላለን።

ፍስሃ ድንጉላ ነው።

ስለጡት ሲያስብ ወተቱን እንጂ ስሜቱን አያውቀውም። ድንጉላ የሆነው ፈልጎት አይደለም። በህልሙ ካልሆነ በቀር በእውኑ ሴት ጭን ውስጥ ገብቶ አያውቅም። መቼም በህልሙ የበላን "ጠግቧል" እንደማንለው ሁሉ በህልሙ የወሰበንም "አመንዝሯል" ለማለት ያስቸግራል።

ከራሱ ብሶት ጋር የቤተሰቦቹ "ለምን አታገባም?" የሚል ጭቅጭቅና ንትርክ ተጨምሮ ማግባትን ካሰበ ከረምረም ብሏል። ምን ዋጋ አለው ከድንጉላቱና ከሽንኩርት ከተፋ የምታወጣው ሴት በአግር በፈረስ ፈልጎ አጣ እንጂ።

ሽንኩርት ሲልጥ ዐይኑን ስለሚቆጠቁጠው እንባው እንደ ወንዝ ነው የሚፈሰው። ሰዎች "በምትከትፍበት ሰዓት ሽንኩርቱ እንዳይከነክንህ ልጫውን ጆሮህ ላይ አድርገው" ብለውት ነበር። ዐይኑ ማልቀሱን አልተወም እንጂ ቅንድቡም ላይ አድርጎ ሞክሮታል። ይሄን ሲያስብ የተከተፈ ሽንኩርት የሚሸጡ ሴቶችን መንግስት በጥቃቅንና አነስተኛ ቢያደራጅ ውጤታማ እንደሚሆኑ ሃባ ታክል ጥርጣሬ አይሰማውም።

በመንግስት ሰራተኛነቱና በወንደላጤነቱ አንድም ቀን ተደስቶ አያውቅም። ኑሮው በስልችት የተሞላ ነው። አንዳንዴ የእድሜ ልክ እስራት ተፈርዶበት በወህኒ ቤት ውስጥ ሕይወትን የሚገፋ ሰው አይነት ስልቹነትና ጎደሎነት ይሰማዋል። በተለይ ሁል ጊዜ እቤቱ ይገባና እንደ በረዶ የሚቀዘቅዘውን ያልተነጠፈ አንሶላ ገልጦ ሊተኛ

ሲል የሚሰማው ባዶነት ከአንታርቲካ አህጉር የከፋ ነው።

"ሕይወቱን እንደ ፖለቲከኛ ንግግር በድግግሞሽ የተሞላ ነው" ብሎ መግለጽ ይቻላል። ሽንኩርት መከተፍ፣ አልጋ ማንጠፍ፣ ሪፖርት መጻፍ፣ ፓስታ ማጠንፈፍ፣ ከዛ በኋላ መተኛት፣ መንጋት፣ ትናንት ያደረገውን ዛሬም መድገም...። ይሄን ሲያስብ "ኤጭ" የሚል ቃል ከአፉ ያመልጠዋል።

ነፍሱን ጎደሎና ስልቹ አድርጎ ያስቀራት ነገር ለረዥም ዘመን ተሸክሞት የኖረው ድንጉላነቱ እንደሆነ ያምናል።

ልጆች በመውለጃው ዘመን ላይ ቢሆንም እስካሁን ድረስ የሴት ጭን ውስጥ ገብቶ አያውቅም። ባንድ ወቅት እንደ ጥንካሬ ሲቆጥረው የነበረው ድንጉላነቱ ህመም ከሆነበትም ሰንብቷል። ከዚህ ጉዳይ ጋር ተያያዥነት ያለው ነገር ሲያነብ ባዮሎጂካል ፍላጎቱ ያልተሟላላት ሰው ደስታን ከማጣት ባለፈ ወደ አብደት ጎዳና ሊሸጋገር እንደሚችልም ከተረዳ በኋላ ይህ ነገር እኔም ላይ ሊከሰት ይችላል የሚል እምነት እያደረበት መጥቷል።

ከሴት ጋር ቀርቶ ከወንድም ጋር ቢሆን ብዙም ተግባቢ ሰው አይደለም። አንዳንድ ሰዎችን ሊቀርባቸው ይፈልግና የአካል ድንጉላነቱን አስተሳሰቡም ላይ ሲንጸባረቅ ይታዘቡታል መሰል በቀላሉ ይርቁታል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ አይምሮው ከሴት ጭንና ከሴት ቂጥ ውስጥ አልወጣ እያለው መቸገር ጀምሯል። ግን ደግሞ የሚኖርበት ሰፈር ላይ በሱ ፍራቻ በሴቶቹ ተግደርዳሪነት እንዲህ በቀላሉ አይነ-ጥላውን ማስገፈፍ አልቻለም። ሴት መጥበስን ሲያስብ ከሰድስተኛ የሰሜት ህዋሱ (ከብልቱ) ውጭ ያሉት ህዋሳቶቹ አልታዘዝህ ይሉታል።

****

ቤተሰቦቹ በሴት ጉዳይ ላይ ጨዋ መሆኑን ሲያደንቁለት ቢኖሩም አሁን አሁን ግን ወንድነቱን ከመጠራጠርም አልፈው እስከ መናገርም ደርሰዋል። ለምሳሌ የልደታ ቀን ደጅ ላይ ቡና ተፈልቶ ንፍሮ እየተበላ እንዳለ አባቱ ቆጣ ብለው "ለምንድን ነው ሚስት አግብተህ አይንህን በአይንህ የማታየው?" አሉት።

"ለትዳር የሚሆን ሴት መች አለና" ብሎ መለሰላቸው።

"እንዴት የለም?" አሉት

"የለማ! እኔ መቼም እስካሁን ፈልጌ ማግኘት አልቻልኩም" አላቸው።

"እንግዲያውስ ሴት የለም እያልክ አንተው ሴት ሆነህ እረፈዋ! እንዴት ሰው በዚህ እድሜው ሚስት ማግባትና ልጅ ማፍራት ቢያቅተው እንኳን የሴት ገላ መሞከር ያቅተዋል?" ብለው የሹፈት ሳቅ ሳቁበት።

በብስጭት የተፈላውን ቡና ሳይጠጣ ወደ ቤቱ ተመለሰ።

*****

ኮከቡ "ቪርጎ" ነው። ቪርጎ ሲተነተን ድንግልናን ይወክላል። "ምናልባት ችግሩ ያለው ከኮከቤ ይሆን?" ብሎ ማሰብ ጀምሯል። ይሄ ጥርጣሬው ተገቢነት አለው። እንደዚያ ባይሆን ኑሮ በወንድምነት የሚቀራረቡት ሴቶች ወደ ወንድነት ሲቀየር ለምን ተቆጥተው ይርቁታል?

አንድ ወቅት የኤች አይቪ ክበብ ውስጥ በሊቀመንበርነት የተመረጠች የመሰናዶ ተማሪ ወላጆቻቸውን በኤድስ ላጡ ህጻናት የልብስ መግዣ ለመጠየቅ ወደ መሰሪያ ቤታቸው መጥታ ነበር። እሱም በግሉ ሃምሳ ብር አውጥቶ ሰጣትና መግባባት ቻሉ። እውነት ለመናገር ብሩን የሰጠው ከጉዳዩ ይልቅ ጉዳዩን ይዛው የመጣችውን ልጅ እንቢ ላለማለት ብሎ ነው።

በዚያው ተግባቡና ጓደኛሞች ሆኑ። በዚያው ቢጋቡ መልካም ነበረ። ግን አልሆነም። መግባባት፣ መጋባት፣ መራባት፣ መፋታት አልፎ አልፎ ቢዘበራረቁም ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮች ናቸው። ግንኙነታቸው ጠንከሮ ቤቱ እስከ መምጣት ደረሰች። የሆነ ቀን ቤቱ ስትመጣ ወሲብ ለመፈጸም ቆርጦ ተነስቶ ነበር።

"ማነው?" አለችው ቤቱ የተለጠፈውን ፎቶ አሻግራ እያየች።

"ኔልሰን ማንደላ ይባላል። በቅርቡ ነው ያረፈው" አላት።

"በኤችአይቪ ነው?" አለችው።

ከዚህ በላይ ካወራችው ልታስጠላው ስለምትችል አጀንዳውን መቀየር ፈለገ። ሆኖም የሚናገረውን ከማሰብ ባለፈ ቃላትን ከአፉ ማውጣት አልሳካልህ ሲለው ጊዜ ባላበው መዳፉ እጇን ጨበጣት። እሷም ስሜቱ ገባት መሰል "ምነው?" አለችው አሳት እንደበላው ላስቲክ ሰውነቷ እየተጨራመተ።

"ለምን አረፍ አንልም?" አላት ወደ አልጋው እያሳያት።

"በስማም! በዚህ እሳት በሆነ የመቅሰፍት ዘመን! ወገን እንደ ቅጠል በሚረግፍበት ዘመን፣ ህጻናት ያለ አሳዳጊ፣ አረጋውያን ያለ ጧሪ በሚቀሩበት ዘመን፣ ኤችአይቪ ስለት ቢጋራ በመጠቀምና በግብረ ስጋ እንደሚተላለፍ እያወቅህ፣ በቫይረሱ አንዴ ከተያዙ መድሃኒት እንደሌለው ሲነገር እየሰማህ፣ ምንም እንኳን አሁን በጤና ተቋም በመውለድ ችግሩን ማስቀረት ቢቻልም ከእናት ወደ ልጅ እንደሚተላለፍ እያወክ..." እያለች ቫይረሱ ከተከሰተበት ጊዜ ጀምሮ በበሽታው ዙሪያ የታተሙትን መጽሄቶች ሃሳብ ልትዘረዝርለት ስትሞክር "በኮንዶም እኮ ነው የምናደርገው" አላት ባኮውን ከኪሱ እያወጣ።

ሽጉጥ ያወጣ ይመስል ሶስት ጊዜ አማትባበት ጥላው ሄደች።

****

ምሽት ላይ ቤቱ ውስጥ ተጋድሞ ጣራ ጣራውን እያዬ መናጢ እድሉን እያሰበ ሲተክዝ አመሸ። ሲያቀብጠው ደግሞ ሰው የራቀውን ቤቱን የሙጥኝ ብለው ብቅ ጥልቅ እያሉ ሊያዋሩት የሚፈልጉትን አይጦች ጓደኝነታቸውን አጠንክረው ጸጥታውን በገፈፉለት፣ ቤቱን ባደመቁለት "ንብረቴን አወደሙብኝ" በሚል ተልካሻ ምክንያት የሚወድም ንብረት ቀርቶ ጥራጥሬ በሌለበት ሁኔታ በመርዝና በወጥመድ ጨፍጭፎ ጨረሳቸው። ወጥመዱማ ተሰፈንጥሮ ሲይዝ ደስታውን ያዬ ሰው አንበሳ እንጂ አይጥ የገደለ አይመስለውም። እውነት ለመናገር እነዚያ አይጦች አብረውት ሲኖሩ የነበረው "ተዋወቅነው" ብለው እንጂ ከሱ ቤት ውስጥ የሚያገኙት ሃባ ታክል ጥቅም አልነበረም። ወደ ኋላ መለስ ብሎ የአይጦቹን አስተሳሰብ በግልጽ ሲረዳ ከቤቱ ጭርታ ጋር ተዳምሮ "አልቅስ አልቅስ" የሚል ስሜት ልቡን ወረረው።

ለረኽም ወራት ሰፈሩ ውስጥ አይኑ የገቡትን ሴቶች ሁሉ ከመመኘት ባለፈ አንዳቸውም ጋር መግባባት አቃተው። ይሄን የተረዳው አይምሮው ከእለታት አንድ ቀን ከልብስ አጣቢው "መዓዛ" ጋር የመራከብ ሀሳብን አፈለቀለት። ሀሳቡን ባይወደውም አልጠላውም ነበር። ሁኖም ግን "ወሬው የተሰማ እንደሆነ የሰፈር ሰውና ቤተሰቦቼ ምን ይሉኛል?" ብሎ ተወው። በመጨረሻ ይሄን የተረገመ ድንጉላነቱን ለሴተኛ አዳሪ ሰጥቶ አይኑን መግለጥ እንዳለበት ቁርጥ ውሳኔ ላይ ደረሰና የደሞዝ ቀኑ እስኪደርስ ድረስ ይሄን አቋሙን እያጠናከረ ከረመ።

****

ለጨጓራው የከበደውን ዱለት በልቶ ደሞዙን ሊቀበል ወደ ፋይናንስ ሄደ።

መንግስት ሰራተኛ መሆኑ ይቆጨዋል። በዚች አገር ላይ መንግስትነት እንጂ መንግስት ሰራተኝነት ባባዶ ዋሌት ሸሚዝ ኪስ ላይ እስኪብርቶ ደርድሮ... ጥቅም አልባ ቁልፎችን ባንድ ላይ አስሮ ከማንኳኳት ውጭ ጥቅም እንደሌለው ብዙ አመት አገልግሎ አይቶታል። በነዚህ አመታት ውስጥ ለዚች ለማትረባ ደሞዙ ስንት ሂስና ስንት ክስ ሲያስተናግድ ዘመኑን ፈጅቶ በየአመቱ ከሰራ ልምዱ ውጭ የሚያድግም የሚለወጥም ነገር አላገኘም። በፊት በፊት ቢያንስ መንግስት ሰራተኛ መሆን ገንዘብ ባይኖረው እንኳን ክብር ነበረው። አሁን ግን ክብሩም ብሩም ተረስቷል። ይሄን በማስረጃ ለማረጋገጥ ፍስሃን እራሱን መመልከት በቂ ነው። ከደሞዝ ከፋዩ ደባልቄ ጀምሮ እስከ ኃላፊው ድረስ፣ ከቤት አከራዩ ጀማል አንስቶ እስከ ልብስ አጣቢው መዓዛ ድረስ ደጅ ሲያስጠኑት ይውላሉ።

ቁልፉን እየወዘወዘ ፋይናንስ ቢሮ ደረሰና ደሞዝ የሚከፍለው "ደባልቄ" መሆኑን ሲነግሩት ተበሳጨ። ይሄ ደደብ የሆነ ሰውዬ ከዚህ ቢሮ መቼ በጡረታ እንደሚገለል አይገባውም።

****

"ምን ፈለክ አለው?" ደባልቄ ከብርጭቆ ቂጥ የተሰሩ ሌንሶች የተገጠሙለት የሚመስለውን መነጽሩን ማዲያታም አፍንጫው ላይ እየሰካ።

"ደምወዝ መውሰድ ፈልጌ ነው" ብሎ መለሰለት።

ቁልፉን ከቀበቶው ላይ አላቆ፣ የዛገ ካዝናውን ከፍቶ፣ ፔሮልና ብር እስኪያወጣ ድረስ ረኽም ሰዓት ፈጀበት።

"ማነው ስምህ?" አለው።

ይሄን ያለው ስሙ ጠፍቶት እንዳልሆነ ቢያውቅም ጭቅጭቅ ስላልፈለገ "ፍስሃ" ብሎ መለሰለት።

"ፍስሃ...ፍስሃ...ፍስሃ" እያለ ስሙን መፈልግ ጀመረ። በሃሜት የጠፋ ስምን እንኳን ለማስመለስ ይሄን ያህል ጊዜ አያስፈልግም። በመጨረሻ ፈልጎ አገኘውና ቆጠራ ጀመረ። ቆጠራውን የሚያከናውነው በዝግታና በተመስጦ ነው። ኮከብ እንጂ ብር የሚቆጥር አይመስልም።

ሁለት ባለ መቶ ጥቅል የአስር ብር ኖቶችን በስንት ትግል ቆጥሮ ጨረሰ። ሶስተኛውን ጥቅል ግን "ሰማንያ" ካለ በኋላ "ሰማንያ አንድ" ይላል ብሎ ሲጠብቅ

የተቆጠረውንና ያልተቆጠረውን ድብልቅ አደርጎ ከአንድ ጀመረ።

"ስምን መልዓክ ያወጣዋል አሉ! እውነትም ደባልቄ!" ብሎ በውስጡ ሰደበው።

አሁንም የዚህ ጥቅል ጣጣ በቃላሉ የሚፈታ አልሆነም። ጥቅሉን ሁለት ጊዜ ቢቆጠርም ዘጠና ዘጠኝ እንጂ መቶ መሙላት አልቻለም። ደባልቄ ኬንያ ድረስ የሚፈናጠር ምራቅ አውራ ጣቱ ላይ ተፋና ብሩን መዳፉ ላይ ቸብ ቸብ አድርጎ ሶስተኛ ሊቆጥር ሲል "ባይሞላም አትጨነቅ! ዝም ብለህ አምጣው" አለው።

"አይ አይ! ያንተስ ሃቅ ለምን ይቀርብሃል" በማለት መለሰለት።

"እና በቆጠራ መዋል አለብኝ እንዴ! ብሩን ለማጥፋት እንኳን ለቆጠራ ያባከንከውን ያህል ጊዜ አያስፈልገኝም" አለው።

"እኔ ደሞዝህን መክፈል እንጂ ስትፈልግ አጥፋው ስትፈልግ ቀደህ ጣለው" አለውና ዘጠና ዘጠኝ የሚባል ቁጥር በቆጠራ ብዛት ወደ መቶ ያድግ ይመስል እንደገና ከአንድ ተነስቶ ሊቆጥር ሲል "መቶ ነው አልኩህ እኮ!" ብሎ ከእጁ ነጠቆት ወጣ።

****

ወሰኝ የሚላቸውን እዳዎች ከፋፈለና የተረፈው ብር ከደባልቄ ንግነጋ ጋር ተቀላቅሎ አበሳጨው። ደሞዝ ያወጣ ቀን ሁሌም ይበሳጫል። ደሞዙን ከተቀበለው ሰዓታት እንኳን ሣይሞላው ከእጁ ላይ ብን ማለት ሲጀምር ያበግነዋል። "እ ፎ ይ" የሚለው ያሉበትን እዳዎቹን ከፋፍሎ ሁሉንም ብሩን ጨርሶ ሲገላገል ነው።

ቀኑን ሙሉ እዳዎቹን ሲከፍል ውሎ ወደ ቤቱ በመሄድ የቀረውን ብር ቆጠረና አይነ-ጥላውን ለምትገላግለው ሴተኛ አዳሪ የተወሰነ ብር መደበ። አራቱንም ሆቴል በልቶ በዚያው ወደ ጭፈራ ቤት ለመሄድ እቅድ ነደፈና አራት እሽግ ኮንዶም በኪሱ አጭቆ ከቤቱ ወጣ።

ይሄን ሁሉ ኮንዶም ሊሸጠው ይሁን ሊጠቀምበት ግልጽ አይደለም።

****

ጭፈራ ቤቱ ውስጥ ካሉ የጠጭዎች ቁጥር ይልቅ የሴተኛ አዳሪዎቹ ቁጥር በልጦ ሲመለከት አገሪቱ በዚህ ዘርፍ ያስመዘገበችውን የሁለት አሃዝ እድገት ለመጀመሪያ ጊዜ አመነ። ብዙ ጊዜ መንግስትን መንቀፍ ያበዛል። የሚነቅፍበት ምክንያቱ የሀገሪቱን ድንግልና ወስደው ብቻውን ስላስቀሩት ሊሆን ይችላል።

የሴቶቹ ቁንጅና አንድ አይነት ሆነበት። በአካላቸው ላይ የሚሸከረከረው "ላይት" ገላቸውን ብልጭ ድርግም እያደረገበት ልቡ ኖሁልሎ ባለበት እንደቆመ አንዲት ለግላጋ ሰውነቷን እርቃኑን ያስቀረች ቆንጆ የሚቀመጥበት ቦታ እየመራች ወሰደችውና "ምን ልታዘዝ?" አለችው።

ወሲብ ቢላት ደስተኛ ነበረ። "ቢራ አምጭልኝ" አላት።

ከጀርባዋ ያዘለችውን ያበጠ መቀመጫዋን እያዬ የሚሰራውን አሳጣው! ሽፍደትና ቅንዝር አይምሮውን ጋለበው። ቢራውን ይዛለት ስትመጣ "ለእንችም ታዘዥ" ስላላት ጉርደን ይዛ ተመለሰች።

"ሳሚኛ ድግሚኛ" የሚለው ሙዚቃ ዘፍኖ ጨረሰና "ትብላው ብሬን" የሚለው ዘፈን ተለቀቀ። ይሄ ሙዚቃ ሲከፈት ለሴት የሚተርፍ ቀርቶ ለራሱም መጠጫ የሌለው በባዶ ሆዱ ሲጋራ የሚነፋ ሰካራም ሁሉ ለጭፈራ ተነሳ።

ባንኩኔውን እንደ መደገፍ ብላ ረዥሙ ባለጌ ወንበሩ ላይ ስትቀመጥ "ቀሚስ ነኝ" የሚለው ሹራቧ ተገለጠና አገልግሏን የሸፈነው ነጭ ፒኪኒ ፓንቷ ወለል ብሎ ታየው። "ደስ ይበለው" ብላ ነው መሰል እግሯቿን ከፈት ዘጋ ስታደርጋቸው ፒኪኒዋ መሃሉ ላይ የመታጠፍ እና የመነከስ አደጋ ሲደርስበት አስተዋለ። ከብልቱ የሚፈልቅ ፈሳሽ በየትኛው ባቡር እንደመጣ ሳይታወቅ ጭኑን ሲያርሰው ተሰማው። ሊያዋራት ፈለገና ምራቁ ደርቆ ምላሱ ከስጋነት ወደ እንጨትነት ተለወጠበት። ቢራውን አንስቶ ባንድ ትንፋሽ አጋመሰው።

አብሯት መጨፈር ቢፈልግም ዘመን አመጣሽ እንኩቶ ዘፈኖች አስኪያልፉ ድረስ "ተጫዎች" እያሉት ሲጠብቅ አመሸ። ለረዥም ሰዓት ከአሁን አሁን አሪፍ ሙዚቃ ይመጣል ብሎ ቢያስብም ያሰበው አልሆነም። እኒህ "ዲጄ" የሚባሉ ጸጉራም ፍጡሮች ሙዚቃ እንደ ማጫወቱ ማዳመጡንስ መቼ እንደሚጀምሩ አይገባውም። የድሮ ሙዚቃ ያጫወቱ እንደሆነ "ትባረራላችሁ" የተባሉ ይመስል ሳምንት ሳይሰሙ ከቢልቦርድ ላይ የሚወርዱ የዘመኑ ሙዚቃዎች ላይ ያተኩራሉ። "ቅንቡላ" የሚለው ዘፈን አበቃ ብሎ ሲጀምር "ኢቦንጎ" የሚለው ተተካ። ይሄ ዲጄ መቼም ከፈደሬሽን ጽህፈት ቤት ተልኮ የመጣ መሆን አለበት ብሎ ደመደመ።

ሙዚቃ ሲያማርጥ የማይገኝ አድል እያለፈው ስለሆነ "ኪሌ...ኪሌ.....ኪሌ" ብሎ እጁን ይዟት ለዳንስ ተነሳ። ፊቷን አዙራ ቂጧን ብልቱ ላይ ስታስጠጋለት ረዥም ወገቧን በሁለት እጁ አቅፎ ለመወዛወዝ ሞከረ። እውነት ለመናገር መሰረር እንጂ

መጨፈር ይችላል።

ሙዚቃው ሲያበቃ በአልኮል ብዛት በመጣ ፍጹም ጀግንነት ውስጥ ሆኖ "ስንት ይመችሻል" አላት። እዳውን ሳይከፍል በፊት ከደሞዝ ከፋዩ ከደባልቄ የተቀበለውን የደሞዙን ልክ ነገረችው። ከድንጉላነቱ ነጻ ለመውጣት የጠየቀችው ብር ላይ ትንሽ ጨመር ቢያደርግበት ወደ አረብ አገር ለመውጣት የሚያስችለው ነበረ። ወር ሙሉ ሰርቶ የሚያገኘው ደሞዙ ለአንዲት አዳር ሴተኛ አዳሪ ይዞ ለማደር እንደማይበቃው ተረዳ። የደሞዝ ጭማሬ ጥናት በሚካድበት ጊዜ ጥናቱ የሴተኛ አዳሪዎችን ዋጋ ግምት ውስጥ ቢያስገባ አሪፍ ነው ብሎ አሰበ።

ነገሩ እንደከሸፈ ሲገባው "ፒኤችዲ" የሚል መልስ ከአፏ እየጠበቀ የትምህርት ደረጃዋን ጠየቃት ።

ገላምጣው ሄደች።

*****

ሴቶቻችንን ሴተኛ አዳሪ እንዲሆኑ ከሚያደርጓቸው ነገሮች አንዱ የቢዝነሱ ማደግ ነው ብሎ አመነ። ሂሳቡን ከፈለና የጀመረውን ቢራ እስኪጨርስ ድረስ እነዚህን ገንዘብ አምላኪ እንስቶች ላለማየት አይኑን ወደ ቡና ቤቱ "ጋርድ" ላከው።

የጋርዱን አቋቋም ልብ ብሎ ሲመለከተው ለአፍሪካ ህብረት ስብሰባ የመጡ ልኡካንን የሚጠብቅ እንጂ ኑሮና ስካር ያናወዛቸውን ሰካራሞች ደህንነት ለመጠበቅ የቆመ አይመስልም። የቡና ቤት ጋርዶች ባሉበት ቤት መጣላት በራስ ላይ መፍረድ መሆኑን ያውቃል። እግዜር ፈርዶብህ ጠብ ካነሳህ የተጣላኸው ሰካራም እንኳን የጋርዱን ያህል አይደበድብህም።

ይሄንንም ጋርድ ልብ ብሎ ሲመለከተው የመደባደብ ሱሱ እያቅበጠበው መሆኑን ተረዳ። አይኑን ከጋርዱ ላይ ነቀለና ዝም ብሎ ቁጭ ማለት ስለደበረው ለጭፈራ ተነሳ። የጠጭው ሰላማዊነትና አለመጋበዝ ያበሳጨው ጋርድ ጠብ ፍለጋ ወደ ፍስሃ ጋር ሄደ።

እንደ ተራራ ላዩ ላይ ተከመረና "በአግባቡ ጨፍር እንጂ!" አለው ወደ ጆሮው ጠጋ ብሎ እየጮኸ።

"በአግባቡ ሲጨፈር እንዴት ነው?" ብሎ መለሰለት ውዝዋዜውን አለቅጥ እያፈጠነ።

ስውዬው ከጋርድነት ወደ ኪሮግራፈርነት መሸጋገሩ ጠብ ፍለጋ መሆኑ ገብቶታል።

ጋርዱ የካፖርቱን እጅጌ እየሰቀሰቀ "ምን ያንቀባርርሃል!" በማለት አፈጠጠበት።

"እረ እኔ አልተንቀባረርኩም" አለው ሰርሰሮ እያስተዋለው። ፊቱን ትኩር ብሎ ሲመለከተው ይሄን የቡና ቤት ጋርድ ጥበብ በሃይለኛው እንደጠራችው ተረዳ። ጋርድ ደግሞ ጥበብ የጠራው ቀን አፍንጫ እንጂ ወረቀትና እስኪብርቶ አያስፈልገውም። ሊመታው መሰናዳቱን ባስተዋለ ጊዜ ሳይቀድመው በፊት ቢራ የያዘ ብርጭቆውን አይኑ ላይ ደፍቶበት ሲጨናበስ በዚያች ቅፅበት "ብን" ብሎ ከአካባቢው ጠፋ።

አበበ ቢቂላ በሮም አደባባይ መንገድ በስሙ እንደተሰየመለት ሁሉ እሱም የሮጠበት ጎዳና በስሙ መሰየሙንና አለመሰየሙን ዳግም በዛ መንገድ ተመልሶ አላረጋገጠም እንጂ የዩሴን ቦልትን ሪከርድ እንደሰበረው እርግጠኛ ነበር።

*****

"ከድንጉላነት ነጻ ከመውጣት ከድህነት አረንቋ ነጻ መውጣት ይቀላል" ብሎ ደምድሞ ትኩረቱን ወደ መጸሃፍ ባዞረበት ሰአት አንዲት አንባቢ ነኝ የምትል ብዙ ጊዜ በአይኑ ሲመኛት የነበረች የኮሌጅ ተማሪ አንድ ቀን ሰፈራቸው ያለ ጣብቂያ መንገድ ላይ አስቆመችው።(እዚህ ላይ "ጣብቂያ" የሚለው ቃል ጣሊያነኛ መሆኑን ልብ ይሏል)

"ወንድሜ አንድ ጊዜ ላናግርህ እችላለሁ?" ብላ አረፍተ ነገሩን ሳትጨርሰው በፊት "በደስታ!" ብሎ መለሰላት።

"መጽሃፍ ብታውሰኝ ብዬ ነበር" አለችው።

"በቅድሚያ ማን ልበል?" አላት እጁን ለትውውቅ እየዘረጋ።

"ዳግማዊት እባላለሁ"

"ፍስሃ" ብሎ ስሙን ከነገራት በኋላ "የምትፈልጊውን መጽሃፍ ንገሪኝና ቤትሽ ድረስ አመጣልሻለሁ" አላት።

"እረ እራሴው መጥቼ እወስደዋለሁ አለችው" መዳፏን እያሸች።

"እንደሱም ይቻላል! በቃ ከምሳ ሰዓት በኋላ ነይና ውሰጂ! ካልሆነ ደግሞ የሚመችሽን ሰዓት ንገሪኝና ቤቴ ጋደም ብዬ እጠብቅሻለሁ" እያለ "መጥቼ

እወስደዋለሁ" ያለችው መጽሃፉን እንጂ ድንጉላነቱን ይመስል ያዘበዝብ ጀመር።

"አይ በቃ ቤትህ መጥቼ እወስዳለሁ" አለችውና በዛው ተሰማምተው ተለያዩ።

****

ልጅቱን ሲያጠናት ፍቅር ከመስራት ይልቅ ፍቅርን መተዎን የምትፈልግ አይነት ሴት ሁና አገኛት። አለ አይደለ ሰብለን ሁና በዛብህን የሚሆን ወንድ የምትፈልግ አይነት፣ ወይም ደግሞ ትእግስትን ሁና አቤልን የሚሆንላት ሰው የምትፈልግ አይነት።

ብቻ ዝም ብሎ ሲገመግማት ወደ ገደለው ከመግባት ይልቅ ሂደቱ ላይ የምታተኩር፣ በገጸ-ባህሪያት ፍቅር የተለከፈች ነበረች። በፍቅር ከመጥገብ ይልቅ በፍቅር መቃጠልን የምትሻ ሆነችበት። በዚህና በራሱ ፍራቻ ምክንያት በተደጋጋሚ ቤቱ እየመጣች መጽሃፍ ስትወስድና ስላነበበችው መጽሃፍ ይዘት ማብራሪያ እየሰጠች ጥልቅ አሳቢነቷን ስትገልጽለት ከመስማት ባለፈ የሚፈልገውን አጀንዳ ማንሳት አልቻለም።

"ዛሬ እነግራታለሁ" ይልና ልክ ቤቱ ስትመጣ ልቡ ይርበደበድበታል። በርግጥ በሱ መፍረድ አይቻልም። ለረዥም ጊዜ ታምቆ የቆየ የወሲብ ስሜት ፈሪ ያደርጋል። ሁሉ ነገር በጊዜውና በወቅቱ መካሄድ አለበት! ወሲብም ቢሆን። መቼም የልጅ አባት በመሆኛው ሰዓት ስለ ድንጉላነቱ የሚያስብ ሰው በምንም መልኩ ቢሆን ሊደገፍ አይችልም።

****

እንደ ሁል ጊዜው ዛሬም እመጣለሁ ብላ ስለቀጠረችው ጉዳዩን አፍረጥርጦ ሊነግራት ቁርጥ ውሳኔ አሳለፈ። ለዚህም ሲል ገና ከጠዋቱ ጀምሮ በአይምሮው የሚያብሰለሰለውና የሚዘጋጀው ይሄንኑ ሁኗል። ባዶ ቤት ውስጥ ተዘግቶ ምን ብሎ እንደሚጠይቃት ሲለማመድ ላየው ሰው የሼክስፒርን ተውኔት የሚያጠና ሊመስለው ይችላል።

ሲጽፍ፣ ሲሸመድድ፣ አልጥምህ ሲለው፣ ሲቀድ ዋለና በመጨረሻ ቃላትን መርጦ ዓረፍተ ነገር መመስረት ቻለ። ከፍራሹ ላይ ተነሳና አልጋውን አነጣጠፈ። ይህ አልጋ ከደቂቃወች በኋላ ሮማንቲክ ፊልም የሚሰራበት መድረክ እንደሚሆን ሲያስበው ላቡ ግጥም አለ። የቆሸሹ ካልሶቹን በፔስታል ቋጥሮ አልጋው ስር አስገባና ሰንደል ለኮሰ።

ልቡ ያለቅጥ ይመታል። መሸበሩ ፊቱ ላይ ይነበባል።

በሩ ተንኳኳ። ዳግማዊት መሆን አለባት። ተጣድፎ ሲከፍተው ልብስ አጣቢውን መዓዛን ተገትራ አገኛት።"ልብሰህን አጥቤ ጨርሻለሁ" አለችው።

"ብሩን በኋላ መጥተሽ ትወስጃለሽ" አላት በዳግማዊት መምጫ ሰዓት ግቢው ውስጥ በመኖሯ ተበሳጭቶ።

*****

እስከትመጣ ድረስ ጎረቤቱ ያለው ተከራይ ቤት ጋር በመሄድ ቴሌቪዥን ማየት ጀመረ። መንግስታችን አንዱን የቴሌቪዥን ጣቢያ ከፋፍሎ ወደ ሶስት ለማሳደግ እቅድ ሲነድፍ እሱም ቴሌቪዥን ለመግዛት አቅዶ ነበር። በኋላ ግን አልሳካ ሲለው ጊዜ "ኢቲቪ እንደሆነ አዲስ ፕሮብሌም እንጂ አዲስ ፕሮግራም ላያመጣ ነገር ምን አታከተኝ" ብሎ ተወው።

እንደተለመደው በቴሌቪዥኑ ውስጥ ዛሬም የሚተላለፈው ስብሰባ ነው። ጠቅላይ ሚኒስቴሩ ፓርላማውን ሰብስበው በቀጣዩ የአድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ውስጥ ከድህነት ጋር ከሚካሄደው ጦርነት ባለፈ ከሻእቢም ጋር ጦርነት ሊኖር እንደሚችል ጠቁመው አለፉ።

"እኛን ወክለው እንዲበሉ መርጠን ወደ ፓርላማ የምንላክቸው የፓርላማ አባላት ጦርነቱንስ ለምን እኛን ወክለው አያካሂዱትም" የሚል አሳብ አፈለቀ። ጎረቤቱ በእዚህ ጉዳይ ላይ ሀሳብ መስጠት ባይፈልግም "እውነቴን እኮ ነው መከላከልን መሰረት ባደረገው የጤና ፖሊሲ አማካኝነት አጎበር አልብሰውን ከርመው.....የክትባት መዓት ሲወጉን ከርመው..... ኮንዶም በኪሳችን አሽከመው ሲያስዞሩን ከርመው.....ዝሆኖቹ ወፈፍ ያደረጋቸው እለት ዋጋ ስንሰጣት የከረምናትን ህይዎት ዋጋዋን ሊነፍጓት አይገባም" እያለ ባልተረጋጋ አይምሮው ይቀባዥር ጀመር።

"መስሎህ ነው እንጂ ወጣቱ እንደሆነ በጦርነት ባይሞትም በሱስ ከመሞት መች ዳነ ብለህ ነው" ብሎ ጎረቤቱ ሲመልስለት አላዳመጠውም ነበር።

ከሻእቢያ ጋር ስለሚካሄደው ጦርነት ማሰቡን ትቶ ከዳግማዊት ጋር ስለሚያካሂደው ፍልሚያ ትዝ ሲለው በደመነፍስ ቤቱን ለቆ ወጣ። ቤቱ ሆኖ የቆለጡ ጎፈሬ ትዝ ሲለው ሰፊ ጋዜጣ ወለሉ ላይ አንጥፎ ላዩ ላይ ተቀመጠና ጭኅሩን መቁረጥ ጀመር። ስራውን ሲጨርስ ብልቱን ጫፉ ላይ ያዝ አደረገውና "በለስ ይቅናህ" ብሎ ወደ ሱሪው ከተተው።

ብዙም ሳይቆይ ዳግማዊት በሩን ሳታንኳኳ ዘው ብላ ገባች። ቤቱ ውስጥ የገባው መብረቅ እንጂ እሷ ናት ብሎ አላሰበም።

"በስማም አስደነገጥሽኝ" አላት በቅጽበት ውስጥ ያላበውን ቅንድቡን እየጠረገ።

"ደነገጥክ?" አለችው በሀረፊዎች ቢጃማ ሽክ ብላ።

"እንዴት አልደነግጥ" አላት ትኩር ብሎ ሲያያት ደግሞ ውበቷ የበለጠ እያስደነገጠው።

ከጎኑ ስትቀመጥ የተቀባችው ሽቶ የህያዋንን ቀርቶ የግኡዛንንም ብልት ሊቀሰቅስ እንደሚችል ተረዳ። ኮካውን ከፍቶ ሲያቀብላት ገነፈለ።ቀጥሎ ደግሞ የሚገነፍለው ነባዘሩ መሆኑ ገብቶታል።

****

በመጨረሻ "ዛሬ ለምን አናደርገውም?" አላት

"ምኑን" አለችው እየተቅለሰለሰች።

"ግብረስጋውን" አላት ቃላት ሳይመርጥ።

"እንዴ! ከጋብቻ በፊት?"

በእቅድና በፕሮግራም የሚደረጉ ነገሮች አይመስጡትም። "ምን ችግር አለው" አላት ትዕግስቱ እያለቀ።

"በቃ ከተጋባን በኋላ እናደርጋለና" አለችው።

"እሱማ ከወለድን በሆላም ማድረግ ይቻላል"

"ምኑን?"

"ሴክሱን"

"ሴክስ ሳያደርጉ መውለድ አለ እንዴ?" አለችው ሃሳቡ አደናግሯት።

"እንግዳውስ ሴክስ ሳያደርጉም መጋባትም የለም" አለና ጎተታት።

"ስርዓት ያዝ እንጂ!" አለችው የጨመደዳትን እጁን ለማስለቀቅ እየታገለች።

"ስርአት ሲያዝ እንዴት ነው?" አላት ዚፑን እየፈታ። ከአፉ የሚያመልጡት

ቃላት ታስበው የሚወጡ አይደሉም።

"እንዲህ አይነት ጅል አትመስለኝም ነበር" ብላ አራስ ነብር ሆነችበት። በልጅቱ ሁኔታ ብልቱ ብቻ ሳይሆን አእምሮውም ሲጠነዛ ተሰማው።

ጥላው ስትሄድ የማሰቢያም ሆነ የመናገሪያ ጊዜ አላገኘም ነበር። የጠነዛ ብልቱን ሳያስበው በእጁ ሲጨብጠው ስሜቱ ጫፍ ላይ መድረሱን አረጋገጠ። መቼም በዛ ሁኔታ ውስጥ ሁኖ የረገማት ርግማን ቤቷ እንኳን ሳትደርስ ጠልፎ ሊጥላት ይገባ ነበረ።

ብዙም ሳይቆይ በሩ ተንኳኳ።

ምን ልታደርግ እንደተመለሰች ባያውቅም ተነስቶ ከፈተላት።

በሩን ያንኳኳችው ልብስ አጣቢዋ መዓዛ ነበረች።

****

ከሶስት ወር በኋላ "ፍስሃ ልብስ አጣቢውን መዓዛን አስረገዘ" የሚለው ወሬ ከሰፈር ተነስቶ ቤተሰቦቹ ጆሮ ሲደርስ አባቱ "ይሄን ካደረገ ገድዬው እጁን ለመንግስት እሰጣለሁ" ብለው ዛቱ። ታናሽ ወንድሙ ጉዳዩን "ከሳይኮሎጂካል ክራይስ" አንጻር አይቶ "ለረዥም ጊዜ አፍኖት የቆየው ባዮሎጂካል ፍላጎቱ አእምሮውን ተቆጣጥሮት ያደረገው ነገር ነው። እንዲህ አይነት ነገር ሲቆይ የስነ-ልቦና መሰበር ያስከትልና ያልተገባ ነገር ለማድረግ ያነሳሳል" እያለ ሊያስረዳ ሲሞክር "ምን ስነ-ልቦናው ይሰበራል የኛን ቅስም ሰባበረው እንጂ!" ብለው አባቱ ተቆጡ።

እህቶቹ ደግሞ የፍስሃን ተግባር በፍቅር እና በፍላጎት የተደረገ ሳይሆን መተት አስነክታው፣ መስተፋቅር አሰርታበት ነው እንጂ የኛ ወንድም ይሄን አያደርግም ብለው ጉዳዩን ለማስተባበል ሞከሩ።

ይሄ ሁሉ ሲሆን ፍስሃ ሊሰማቸው አልሞከረም።በሆነው ነገር ሁሉ ከመደሰቱም በላይ ሙሉ ወንድ የመሆንና ሰው የመሆን ስሜት በልቡ እየተጸነሰ ነበር።በዛ ላይ ደግሞ መዓዛ ለሱ ሰዎች እንደሚያወሩት ሳይሆን በደብዛዛና አሮጌ ጨርቅ የተጋረደች ድንቅ ፍጥረት ነበረች።

እንዳሻው ቢመረምራትም ከድህነቷ ውጭ ምንም የሚናቅ ነገር አላገኘም።

*****

ቢሮ ቆይቶ ወደ ቤቱ ሲገባ መዓዛ ሻንጣዋንና ጓዟን ከእናቷ ቤት አምጥታ ቤቱ ገብታ ለምሳ የሚሆን ወጥ እየሰራች አገኛት።

"መጣህ እንዴ?" አለችው አዲስ የገዛላትን ውብ ቀሚስ ለብሳ እየተሞናደለች።

"አይ አልመጣሁም" አላት ከንፈሯን በስሱ ስሞ ኩቱን አውልቆ እያቀበላት።

"ምሳ አልደረሰም?" አላት የሚንተከተከውን ወጥ እያዬ።

"ትንሽ ይቀረዋል። እስከዛ ግን የደረሰውን ላቅርብ" አለችና ከረባቱን ይዛ ወደ አልጋ ሳበችው።

"ልጁ ላይ ግን ጉዳት የለውም" አላት ቀሚሷን አውልቆ ላዮ ላይ እየተሳፈረ።

"እኔ ምን አውቃለሁ ልጁን ጠይቀው እንጂ" አለችው በረሸሙ እየሳቀች።

በሳቀች ቁጥር፣ ባወራች ቁጥር፣ በአወቃት ቁጥር የበለጠ እየፈካች፣ የበለጠ እያማረችው ስትሄድ ተሰማው።

ቲፎዞ

አንዳንዴ....
ውሰጤ ውጭ ሆኖ ሲታይ
ገበሩ ብቻ ሲለበስ፣
እርቃን ማንነት ሲታሰስ፣
እኔስ? አኮ እኔስ?
ከምኑም የማላምላ
ከምኑም የማላጎድል፣
እንደው ምን ይሆን የኔ እጣ?
እንደው ምን ይሆን የኔ እድል?

ቲፎዞ ታውቃለህ አይደል?
ቲፎዞ ማለት እኔ ነኝ፣
ራሱን ካጣ ሞዛቂ
ፊርማ ስለቅም የምገኝ።
"ጉድ" ሲባል ሰምተህ ታውቃህ?
የማይፈለግ ትርፍ ዕጢ
እዚህም እዚያም የሚገኝ
ልብ የማይሉት መናጢ
አትሌት ሪከርድ ሲሰብር
በደስታ አናቴ የሚዘር፣
ለእናት አገሬ ደስታ
የአረቂ ጠርሙስ የምሰብር፣

በለቅሶ በእንባ 'ማጅበው
አትሌቱ ከብሮ ሲመጣ፣
ለእሱ ኢንቨስትመንት መሳካት
ካርቶን ጎጇቼን የማጣ፣

ቲፎዞ ታውቃለህ አይደል?
ቲፎዞ ማለት እኔ ነኝ፣
ከማይጽፍልኝ ጸሃፌ
ፊርማ ሰለቅም የምገኝ።
"ጉድ" ሲባል ሰምተህ ታውቃለህ
የማይፈለግ ከፉ እንቅርት፣
ፈንቅለው የጣሉት ሊታ
መሄዱን ልብ 'ማይሉት፣
ቲፎዞ ታውቃለህ አይደል?
እንትና አሰካር ላነሳ፣
የሰው ማንነት ሳደምቅ
የኔን ማንነት 'ምረሳ፣
የግል ታሪክ የሌለኝ
በጋራ ህዝብ የምትለው፣
እንደ ፈርኦን ሰራዊት
ባህር ውስጥ ሰጥሞ እንደቀረው፣
እንደ ነነዌ አህዛብ
አርባናን አጥቶ እንደኖረው፣
ማእበል የላሰው ሊታ
በጅምላ "ሞታ" ምትለው፣
ያ ፍጡር ማለት እኔ ነኝ
ሲሸሙ የማጨበጭብ፣
ሲወርዱ የምደበድብ፣
"አጢ" ታውቃለህ አይደል?

"ቲፎዞ" ሚባል ግለሰብ፣
የራሱን ማንነት ዘንግቶ
የሰው ማንነት የሚከብ፣

ቲፎዞ ታውቃለህ አይደል?
ቲፎዞ ማለት እኔ ነኝ፣
በጭብጨባዬ ሰቅየው
አንገቴን ሰቅሎኝ የምገኝ፣
ቲፎዞ ማለት እንግዲህ
አጢ ታውቃለህ አይደል?
እንቅርት ታውቃለህ አይደል?
ፈንቅለው የጣሉት ሊታ
ከአለም ላይ የማያንድል፣
ያ ማለት እንግዲህ እኔ ነኝ።

አባትነትን በሕግ ስለማውረድ

አባዬ ባንድ ወቅት "ልጄ አለመሆኑ ይታወቅልኝ" ብሎ ለፍርድ ቤት ማመልከቻ ያስገባበት ታላቅ ወንድም አለኝ።

ቅልጥ ያለ ወመኔ ነው። ወመኔነቱን የሚያረጋጋጥ ድግሪ ከአንዱ የግል ኮሌጅ ተሰጥቶታል። ምድር ላይ ያሉት ሱስ አስያዥ ንጥረ ነገሮች በአንድ አካባቢ ተወስነው አለመገኘታቸው የሚያበሳጨው ይመስለኛል። ከሴት ውጭ ሁሉንም ሱሶች ይጠቀማል።

የአርሴናል ደጋፊ ነው።

በዚህ ወንድሜ አባቴ ተስፋ የቆረጠበት ሊያስመርቀው ሂዶ የምረቃ መጽሄቱ ላይ ከፎቶው ስር የተጻፈውን "ተልኮዬን ጨርሻለሁ" የሚል ኑዛዜ (Last word) በተመለከተ ሰዓት ነው። ከተመረቀ አመታት ያለፉት ቢሆንም ስራ የመፈለግ አንዳች ፍላጎት አለማሳየቱ በቤተሰቡ ላይ አግራሞትን መፍጠሩ አልቀረም። ያስተማረው ቤተሰብ ስራውንም እንዲፈልግለት ቃል አውጥቶ ባይናገርም አዝማሚያው እንደዚያ ይመስላል።

በርግጥ በሱስ እንጂ በምግብ ስለማይኖር "ሞሰባችንን አራቁቷል" የሚል ስሞታ አልቀረበበትም።

አባዬ በወጣ በገባ ቁጥር "እዚህ ተዘፍዝፈህ ከምትውል ስራ ብታፈላልግ ምናለበት!" ሳይለው ውሎ አያውቅም። እሱ ግን ስራ ተቀምጦ ቀርቶ ተፈልጎ በማይገኝበት ዘመን የተንጨባረረ ጸጉሩን እየገመደ የማንንም ምክር ሊሰማ አልፈለገም።

ይሄው ወንድሜ ከአለታት አንድ ቀን ከመሬት ተነስቶ "ሰዓሊ ልሆን ነው" አለ።

"ሰዓሊ ለመሆን ጸጉርን ማሳደግ እንጂ አእምሮን ማሳደግ አያስፈልግም ብሎ የነገረህ ማነው?" አለው አባዬ የተጠቀለለ ጸጉሩን በብርጭቆ መላጨት እየፈለገ።

"ሰዓሊነቱስ ሳይሳካልህ አይቀርም! ሌሎችንም ሰዓሊዎች ልብ ብዬ ሳያቸው ጸጉራቸውም፣ አቋማቸውም እንዳንተ ነው" አለች እማዬ ጸጉሩን እየነካካች።

"በአቋም መመሳሰል ማለት በአቅም መመሳሰል ማለት አይደለም!" አለ አባታችን ተነስቶ እየወጣ።

"እማዬ አንቺ ብቻ ነሽ 'አንደር ስታንድ' የምታደርጊኝ! አባዬ እንደሆነ የኔ ነገር አይጥመውም አላት" በሚያባብል ሁኔታ።

"ፈጣሪ ልሆን ነው ካላልክ በቀር ለሰአሊነቱስ ችግር የለውም! እንዲውም ስዕልህን እኔን በመሳል ትጀምራለህ!" አለችው እናታችን።

እሱ እቴ ምን አንዳጨሰ እንጃለት ከእማዬ የተወሰነ ገንዘብ ወስዶ "ሊጠጣበት ነው" ብለን ስናስብ ለአንድ ሰዓሊ የሚያስፈልጉትን ነገሮች ሸምቶ መጣ።ከእነዚህም ውስጥ ቀለም፣ ብሩሽ፣ አቡጊድና እፀ-ፋርስ ይገኙበታል።

ስዕሉን ሊጀምር ሲል እናታችን በክብር ሰቅላ ያስቀመጠችውን የሞኣ አንበሳ ምስል ያለበትን ትሪ እንድትሰጠው ጠየቃት።

"ደግሞ ትሪዬን ምን ልታደርገው ነው አለችው?" እማዬ ታሪካዊ ትሪዋን የቀለም ማስቀመጫ እንዳያደርገው ፈርታ።

"አንበሳውን መሳል ፈልጌ ነው" አላት።

"ስዕሉንም ስሪልኝ ካላልክ ይሄስ ቀላል ነው" ብላ ሠጠችው።

"አንበሳውን ከመሳል ይልቅ ትሪውን ለመሳል ቢሞክር ይቀለው ነበር" አለች እህቴ እንዳይሰማት ድምጿን ቀነስ አድርጋ።

*****

በሳምንቱ ሁለት ስእል ሰርቶ ጨርሶ ሶስተኛ ለመጀመር ቀለም እንዳለቀበት ለእማዬ ሲነግራት "የሳልካቸውን ስዕሎች ለቤተሰቡ ብታሳይና ቢገመገሙ" የሚል ሃሳብ ስለሰጠችው የእኛንና የጎረቤታችንን የአቶ ታደሰ ቤተሰቦች ያቀፈ መለስተኛ

"ኤግዚቭሺን" ግቢያችን ውስጥ አዘጋጀ።

አባዬ ስእሉን ቀርቶ ሰዓሊውንም ማየት ስለማይፈልግ አልተገኘም።

መጀመሪያ የፈረደባት አንበሳ ሽምቅቅ ብላ ቀረበች። በምስል የሚሸሸችውን አንበሳ በቃላት ሊያገዝፋት ሞከረ። እኔ የሱን ማብራሪያ ትቼ በፈገግታ ውስጥ ሆኜ አንበሳውን እታዘብ ጀመር። እውነት ለመናገር ይሄን አንበሳ "አንበሳ" ከማለት ይልቅ "እንቦሳ" ማለት ይቀላል። የአንበሳው የፊት እግሮች አራስ የተወለደ የህጻን ልጅ እጅ መስለዋል። አፉ ከመሾሉ የተነሳ የአንበጣ እንጅ የአንበሳ አይመስልም። በተጨማሪም እንስሳው ሳር በመጋጥ እንጂ አደን በማደን የሚተዳደር አይመስልም። ቂጡን አየሁት ቂጥ አይመስልም።

ሳላስበው ሳቄ አመለጠኝ። የኔን ሳቅ ተከትሎ እህታችን "መቼም በምድር ላይ የሚያስፈራራ አንበሳ እንጂ የሚያስቅ አንበሳ አይቼም ሰምቼም አላውቅም" በማለት ልታናድደው ሞከረች።

በሷ ንግግር ሁሉም ሰው በሳቅ ሲፈርስ እማዬ ጣልቃ ገባችና "ይሄ ልጅ ገና ጀማሪ እንደመሆኑ መጠን የሳለው ስዕል አንበሳ ባይመስል እንኳን ባግባቡ ስህተቱን ማስረዳት እንጂ አላግባብ በመሳቅ እእምሮን ማቁሰል ተገቢ አይደለም። እኔ መቼም ትንሽ አንገቱ ላይ ያለውን ጸጉር ብታነሳው ስዕልህ አንበሳ ባትሆን እንኳን የምታምር በግ ትሆንልሃለች" ብላ የየዋህ ሀሳቧን ስትሰነዝር ሁሉም ታዳሚ አፉን በጋቢውና በኮቱ ሸፍኖ ይስቅ ጀመር።

"እስኪ ደግሞ ሁለተኛውን ስዕል እንየው" አሉ ጎረቤታችን ጋሽ ታደሰ።

ቀጣዩ ስእል ተሰቅሎ ወንድማችን ማብራሪያ እስኪሰጥ ድረስ የስዕሉን ሰውነት እንጂ የስዕሉን ማንነት አብዛኛው ታዳሚ አልገባውም ነበር።

ወንድማችን ግን በድፍረት "ይሄ ስዕል እንግዲህ አጼ ቴዎድሮስ ነው" በማለት ተከብረው ኑረው፣ ተከብረው ያረፉትን ንጉስ አዋረዳቸው። ጭራሽ ይሄም አልበቃው ብሎ ስእሉ ልብ ተብሎ ሲታይ በአጼ ቴዎድሮስ አካል ውስጥ ገብርዬም አብስትራክት ሁኖ እንደሚታይ አብራራ። ወንድሜ እንዳለው ገብርዬን ለማየት ልብ ከማድረግ ባለፈም እንደሱ አሺሽ ማጨስ ያስፈልግ ነበረ።

ጎረቤታችን ጋሽ ታደሰ ከአጼ ቴዎድሮስ በተጨማሪ አጼ ዮሃንስንም እንደሚያውቁ ለመግለጽ "እኔ ግን ይሄ ስዕል አጼ ዮሃንስን ነው የመሰለኝ" በማለት ሃሳብ ሰነዘሩ።

"ምኑ ነው አጼ ዮሃንስን የሚመስለው?" በማለት የወንድሜ ጓደኛ ጠየቀ።

"ደም ግባቱ ብትል ጂስሙ! ቁጭ እሱን አይደለ እንዴ! ሹርባስ ብትል! ይሄ ሹርባ የትግራይ እንጂ የጎንደር መቼ ነው?" አሉ።

ወንድማችን በሱ ስዕል የተነሳ የጦፈውን ክርክር ሲመለከት ከባድ ፈገግታ ፊቱ ላይ ነገሰ። ግን ደግሞ ይሄ አጼ ዮሃንስ የሚባል ንጉስ ሙቶም አጼ ቴዎድሮስን መቀናቀን አለማቆሙ ገረመው። በክርክሩ መሃል ጓደኛው "አቦ ይሄ ልጅ ሙድ ሲይዝብን እንጂ ይሄ ስዕል ሁለቱንም አይመስልም!" በማለት ተናገረ።

"እንዴት?" ተባለ።

"እስከማስታውሰው ድረስ ሁለቱም ንጉሶች በልጅነት ልምሻ በሽታ ስለመጠቃታቸው የሰማሁት ነገር የለም። ደግሞ ስዕሉን እንደምታዩት ነው። በዚህ እጅ ነው እንዴ አጼ ቴዎድሮስ መድፍ የገተቱት? እስኪ እዩት ይሄ እጅ መድፍ ቀርቶ ዱላስ መያዝ ይችላል? እኔ መቼም በምንም ታምር ይሄ ስዕል ከሹሩባው ውጭ እነዚህን ንጉሶች ቀርቶ ሰብአዊ ፍጡርን ይመስላል ብዬ አላስብም" በማለት የውስጡን ዘርግፎ ተናገረ።

ከሱ ቀጥለው የተናገረው አያታችን ነበረ። "መቼስ ይሄ ልጅ ይሄን ስዕል አጤ ቴዎድሮስ ነው ካለ ምን ይደረጋል? እጁ ቢቀጥን፣ እግሩ ቢንሻፈፍ ንጉስ አይከሰስ! አይወቀስ! ደግሞስ አንድ የተቀባን ንጉስ ስልጣኑን እንጂ አካሉን ማየት ምን ይረባል ብላችሁ ነው ልጁን የምታደናግሩት!" በማለት የረገፈ ጥርሱን በጋቢያቸው ሸፍነው ተፍነከነኩ።

በመቀጠል ሃሳብ የሰጠው ጋሽ ታደሰ ሲሆን "ቢታ ስዕሉ አጼ ቴዎድሮስን እንዲመስል መድፉን ከፍቱ ቦታ ላይ ብትስለው ሰውዬውን አይቶ ማወቅ የተሳነው ሰው ቢያንስ መድፉን አይቶ ሊለየው ይችላል" በማለት ቴክኒካል አስተያየት ሰጠና ኤግዚቪሽኑ በዚሁ ተጠናቀቀ።

ሀሳቡን ተቀብሎ መድፉን ሲሰራው የሙቀጫ ቅርጽ እየያዘ አስቸገረው። መጨረሻ ላይ "እንግሊዞች ባግባቡ ያልሰሩት መድፍ እኔ እሰራለሁ ብዬ ምን አታገለኝ?" ብሎ ነው መሰል ስዕሎቹን በግቢያችን አጥር ላይ እንደተሰቀሉ ትቷቸው ሱሱን ወደ ማጠናከሩ ተመለሰ።

ከዛ በኋላ ማታ ማታ አባታችን "የግቢው በር ታዘግቷል?" ብሎ ሲጠይቅ እማዬ "በእንበሳ እየተጠበቀ ባይዘጋስ ምኑ ይሆናለህ ብለህ ነው!" በማለት በወንድማችን

ስዕል ሙድ ትይዝ ጀመር።

****

ወንድሜ በሚቀልዳቸውም ቀልዶች ሆኑ በወንድሜ ላይ በሚቀለዱ ቀልዶች አባዬ መሳቅ አይፈልግም። አንድ ቀን ቡና ተፈልቶ አቦሉ እየተቀዳ እንዳለ ወንድሜ ተናዶ ከውጭ መጣ።

"ምነው ተናደሃልሳ! ምን ሆነሃል?" በማለት እማዬ ፊቱን አይታ ጠየቀች።

"ምን እባክሽ አርሴ በዳኛ ምክንያት ነጥብ በመጣሉ ተናድጀ ነው" በማለት መለሰ።

"አጀብ እንደው ምን አይነት ትውልድ መጣ? ራሱን ከመጣሉ በላይ የአርሴናል ነጥብ መጣል የሚያበሳጨው! አገሩ ላይ ካለ የዳኝነትና የፍትህ መጓደል በላይ የእንግሊዝ የኳስ ዳኝነት እንቅልፍ የሚነሳው ተልካሻ ዜጋ ከማየት በላይ ምን መረገም አለ?" እያለ አባዬ ሲተክን "አንተ ሰውዬ በንዴቴ ላይ ሌላ ንዴት አትጨምርብኝ! ወይ እዚህ ቤት አልምጣብህ እንዴ?" በማለት አቋረጠው።

"ያማ መች ይቀርልሃል! ይልቅ ከዛ በፊት ስራህን ብታፈላልግ ይሻልሃል" አለው አባዬ ቁርጥ ባለ አነጋገር።

"ስራ ከመፈለግ አገር መፈለግ ይቀላል!" ብሎ መለሰለት

"እንዴት ማለት?" አለው አባዬ ደሙ እየፈላ።

"ማለቴ ለስራ ፍለጋ የማባክነውን ጊዜና ጉልበት እንደ ኮሎምቦስ አገር በመፈለግ ላይ ባውለው አሜሪካንን ባላገኝ እንኳን ኢትዮጵያን የመሰለች አንዲት ተረስታ የኖረች አገር ማግኘቴ አይቀርም!" የሚል የወፈፌ መልስ ሰጠ።

"አይ አንተ ወሬ ስትፈተፍት ከምትውል አእምሮህን ለበጎ ነገር ብታውለው ይሻል ነበር! የዛሬ ዘመን ልጆች ህይዎታችሁን ማበላሸታችሁ ብቻ ሳይሆን ላበላሻችሁት ህይዎት ተጠያቂ እራሳችሁን አለማድረጋችሁ ነው የሚያሳዝነው! የራሳችሁን ችግር ወደ መንግስትና ወደ አገሪቱ መወርወር ትፈልጋላችሁ። ለነገሩ ራሱን የማያከብር ሰው ቤተሰቡንም ሆነ አገሩን ያከብራል ብሎ ማለት አይቻልም። ግን ኢትዮጵያ ባንተ ጫት ባሻገተው አፍ የምትነሳ አይደለችም! ኢትዮጵያ ማለት...." አለና የሶስት ሺ ዘመን ታሪኩን ለመተረክ ሶስት ሺ አመት ሰስለሚያስፈልግ ነገሩን በእንጥልጥል ተወው።

****

የስዕል ስራው ያልተሳካለት ወንድሜ ትኩረቱን ወደ መጽሐፍ አዙሮ ቤተሰቡን ግራ ማጋባት ቀጥሏል። አንድ ቀን እራት ለቤተሰቡ ሲቀርብ ለወንድማችንም ሰሃን ሲሰጠው ጫቱን እያመነዠከ "እያነበብኩ ነው አሁን አልበላም!" አለ ምርቃናው እንዳይታይበት ፊቱን በመጽሐፉ እየሸፈነ።

"ምን ይሆን የምታነበው?" አለ አባዬ በጥላቻ አይን እያየው።

"የአልበርት አንስታይንን ቀመር በመከተል ስኬታማ ህይዎት እንዴት መኖር እንደሚቻል የሚያስረዳ መጽሃፍ ነው"

"ቀመሩ ምን ይላል?"

"Energy=MC2" ብሎ ወደ ትንታኔ ሊገባ ሲል አባታችን አላስጨረሰውም።

"ኢነርጂው ሳይኖርህ ቀመሩ ምን ያደርግልሃል?"

"እንዴት የለኝም? ኢነርጅ እኮ የሚፈጠርም የሚጠፋም አይደለም!"

"እንዴት አይጠፋም? የምትተነፍስበት ጉልበት አጥተህ!"

"አይጠፋማ! ይሄ እኮ ሳይንስ ነው!"

"ሳይንስ ይሻሻላል! የማትሻሻል አንተ ብቻ ነህ!"

"እንዴ! ቁስ-አካል ካለ እኮ ኢነርጂ አለ!"

"በቃ አንተ ማለት ቁስ አካል ነህ! አትልፋ ምንም አይነት ኢነርጂ አንተ ውስጥ የለም!" አለና አባዬ እራቱን መብላት ጀመረ።

ወንድማችን የንቀት ሳቅ ሳቀ።

"አንተ ልጅ ስራ ብትፈልግ ይሻልሃል ብየሃለሁ። እኔ እንደሆንኩ አንተን ተሸክሜ አልኖርም። እንዲያውም በቅርቡ አባት አለመሆኔንም በፍርድ ቤት ስለማሳውጅ ችግር የለውም!" አለ አባዬ ቆንጥሮ እየጎረሰ።

"ባለፈው እኮ ስራ ተወዳድሬ ነበር!" አለ ወንድሜ ጥርሱን ብልጭ እያደረገ።

ቤተሰቡ ሁሉ በግርምት ዙረን አየነው።

"ከምሬ እኮ ነው! የጽሁፍ ፈተናውን አልፌ ኢንተርቪው ላይ ጣሉኝ!"

"ምን የሚል ጥያቄ ተጠይቀህ ነው ኢንተርቪው ላይ ልትወድቅ የቻልከው?" ብላ ታናሽ እህታችን ጠየቀችው።

"ቢሮው ውስጥ ብቻውን ሙቶ የተገኘው የአሜሪካ ፕሬዝዳንት ማነው ብለው የማላቀውን ጥያቄ ጠየቁኝ" አለን።

"ታድያ ማን ብለህ መለስከላቸው?" አለች እህቴ ለሳቅ እየተዘጋጀች።

"ምን ብቻውን ይሞታል እኔንም ይዞኝ ሞተ እንጂ ብዬ መለስኩላቸው!" አለ ከእማዬ ፊት ላይ ሳቅ እየፈለገ።

ከአባዬ ውጭ ሁላችንም የጠቀለልነውን ጉርሻ አስቀምጠን መሳቅ እንደጀመርን "አያስቅም!" አለና አባዬ አቋረጠን።

"አዎ አያስቅም! ትውልድ በራሱ ላይ ሲቀልድ ከማየት የበለጠ ውርደት የለም። ሽንፈት የማያሸማቅቀው! የቢታችነት የማያመው! እንዲያውም በሽንፈቱ ስላቅን የሚፈጥር ልጅ ቀርቶ ዜጋ ማየት ህመም ነው። ለነገሩ በትውልዱ ብቻ መፍረድ አይቻልም! መንግስትም ቢሆን መንደሩ በሙሉ የህሺሽና የሺሻ መናሃሪያ ሲሆን! አገሩ በጫትና በሲጋራ በሚኖር ትውልድ ሲወረር! አባቶቻቸውን አረቂ ቤት የሚፈረክሱ ወጣቶች ሲፈጠሩ አይቶ እንዳላየ ማለፉ ያሳዝናል!" አለና ራሱን ነቀነቀ።

"ታድያ መንግስት ቤተሰብ ጠብቆ ያላዳናቸውን ልጆች በየመንደሩ እየገባ ይጠብቅ ልትል ነው እንዴ?" አለች እማዬ።

"ብልስ? እንኳን ትውልድን በገፍ የሚገድል ሱስ ቀርቶ በየመንገዱ ትርፍ ሰው የጫኑ መኪኖችን ሲቆጣጠር ይውል የለ እንዴ? ደግሞስ አካባቢውን ሰርቶ ከመለወጥ ይልቅ ሰርቆ ለመቦዘን ምቹ እያደረገው እኛ እንዴት አድርገን እንጠብቃቸው? ከመሳሪያ ዝውውር በላይ የሱስ ዝውውሩ ተጠናክሮ ጫት ካለበት አገር ወደሌለበት አገር ሲጓጓዝ...ጪት ባህር ዳር የተቆረጠ ጫት ለምሳ አማራ ክልል ባሉ ወረዳዎች ሲደርስ እያዩ...ጉምሩኩ በህገወጥ መንገድ ሲገባ የያዘውን ሺሻ መልሶ በህገወጥ መንገድ እያሰራጨው...የእህል ማሳዎች ወደ ጫት ማሳነት እንዲቀየሩ አርሶ አደሩን እያስተማረ... አንድን ነገር ከአገልግሎቱ ይልቅ በገቢነቱ የሚመዝን መንግስት ባለበት ሁኔታ እኛ እንዴት አድርገን ልጆቻችንን ከሱስ እናድናቸው?" እያለ እራት መብላቱን አቁሞ ሲብከነከን በአረቂ እንጂ በምክር ምርቃናው እንዲጠፋበት የማይፈልገው ወንድሜ "አቦ ምርቃናዬን አታጥፉት" ብሎ ውልቅ ብሎ ወጣ።

"አይመልስህ" አለ አባታችን በሳህን የቀረበውን እንጀራ ሳይበላው ከፊቱ አንስቶ ለሰራተኛዋ እያቀበለና "ተነስማ አንተ እስኪብርቶና ወረቀት አምጣልኝ!" በማለት እያዘዘኝ። የተባልኩትን አምጥቼ ሰጠሁትና አባዬ የሳይት መነጽሩን አድርጎ መጻፍ ጀመረ። ማመልከቻውን የጻፈው ለፍርድ ቤት ሲሆን ርዕሱም "አባትነቴ በህግ እንዲወርድልኝ ስለመጠየቅ" ይል ነበር።

አዞን

ጋሼ...
በባለፈው
"አገር ምድሩ ቀዘቀዘ
መደቤ ጤዛ አረገዘ፣
በረደኝ...
ከአጥንቴ ቁርጥማን ፈለቀ
አካሌ በብርድ አለቀ
አያልኩህ....
ጋቢ መላኩ ቢያቅትህ"

ጋሼ...
ጤና ጣቢያው ሆስፒታሉ
"ብርድ ብርድ" አለን በሚሉ
ታካሚ ታጥሮ አያየህ
ሸጉጥ ከኒና ባታቀርብ
ጋቢ መላኩ ቢያቅትህ
እንዴት ባለም መድረክ ፊት
"ሙቀት ጨመረ" ትላላህ?

ተው ጋሼ!
የምድርን ጉዳይ ጨርሰው ወደ ጨረቃ ያረጉ
"የአለም ሙቀት ጨመረ ምቀን" አያሉ ሲያወጉ
ከደላው ጋራ ሰትውል የነገርንህን አትርሳ
የ'ነሱ አዞን አይደለም የኛ ገላ ነው የሳሳ።
ገንፎ ሲያጎኩ አያጄክ "ሙቀት ጨመረ" አትበለን
እኛ ነገሩን ባናውቅም ብርድ ብርድ ነው የሚለን
ባክህ ሸጉጥ ከኒኑን ከጋቢው ጋራ ላክልን።

ግሎባል ዋርሚንግ

ዘመዴ የሰጠኝ ባዶ ቦታ ላይ ቤት መስራቱ ባይሳካልኝ እንኳን ዙሪያዋን ችግኝ ለመትከል ካሰብኩ ቆይቻለሁ።

የምተከለው ዛፍ አጥር ከመሆን ባለፈ መንግስት ለሚከተለው የአረንጓዴ ልማት ኢኮኖሚ ማስረጃ የመሆን እቅድ የለውም። ያም ሆኖ ግን መንግስቴ የችግኝ ተከላ ሳምንት አውጇ..... "ዛፍን በመትከል የአዞን ንጣፍ እንደዳይሳሳ የበኩላችንን እንወጣ" አስኪለኝ ድረስ ዶማዬን አዘጋጅቼ ሰጠብቅ ነበረ።

በርግጥ መንግስትን ላለመቃረን እንጂ በመርህ ደረጃም ቢሆን ከአዞን ንጣፍ መሳሳት በላይ የደረቴ መሳሳት ያሳስበኛል።

እናንተስ?

የእውነት ግን የአፍሪካ መሪዎች በከባቢ አየር መበከል ዙሪያ ሽንጣቸውን ገትረው ሲከራከሩ አንገታችሁን አትደፉም? በአማኑ ቀን "የካርቦን ልቀት ጨመረ" ሲሉ ይከርሙና በዙፋናቸው የመጣህባቸው ቀን አናትህ ላይ የሚያጋዩት አቶሚክ ቦንብ ማፈላለግ ይጀምራሉ። በሰላሙ ቀን ዝሆኑ አንገት ላይ "ጂፒኤስ" አንጠልጥለው ሲጠብቁት ይሰነብቱና የቁርጥ ቀኑ ሲደርስ እስክ ማተቡ በፈንጅ ያንጫርሩታል።

"ኡኡቴ" አለች ዶሮ!

አሁን ማን ይሙት አፍሪካ ውስጥ የደን ዋና ጥቅም ምሽግነት መሆኑን የሚዘነጋ ሰው አለ? ችግኞቹስ ቢሆኑ "ፎቶ ሲንቴሲስ" ማካሄዳቻውን ትተው "በፎቶ ካሜራ" መኖር ከጀመሩ ሰነበቱ አይደል እንዴ! ጋዜጠኛውና ካሜራው ቀርጿቸው በሄደ

ማግስት ችግኞቹ የት እንደሚገቡ የሚታወቅ ነገር የለም።

የአፍሪካ መሪዎች "ወደ ከባቢ አየር ካርቦን የሚለቁትን ፋብሪካዎቻችሁን ቀንሱ" ብለው ያደጉትን አገሮች ሲሞግቱ እንዴት "ትን" እንደማይላቸው አይገባኝም። የእነሱ ፋብሪካዎች ስራ ያቆሙ እለት እርቃናችንን የምንቀረው እኛ አይደለንም እንዴ? ከፋብሪካዎቹ የሚወጣው ጭስ ብቻ ሳይሆን የሚፈበረከውም ምርት መራገፊያው እኛው ጋር አይደል እንዴ? ያለነሱ እኮ ምንም ነን። ከልብስና ጫማችን እንስቶ እስከ ኮስሞቲክሳችን ድረስ፣ ከቤት እቃችን እንስቶ እስከጦር መሳሪያችን ድረስ የነሱ ውጤት ነን። ኮንዶም መላከ ያቆሙ እለት በኤድስና በአባለ-ዘር እናልቃለን። መድሃኒታቸው ጋብ ያለ ቀን ትቢና ኩፍኙ ከመቃብር በታችና ከአልጋ በላይ ያውሉናል። ታድያ በዚህ ሁኔታ እነዛ ፋብሪካዎች "የኛ አይደሉም" ማለት ይቻል ይሆን?

አፍሪካ ስራ ስለፈታች ስትቀጥፍ እንጂ ከሙቀት መጨመር በላይ የጦር መሳሪያ ዋጋ መጨመር ያሳስባታል። እኔም ብሆን ከሙቀት መጨመር በላይ የቤት ኪራይና የኑሮ ውድነት መጨመር ያሳስበኛል። የእነሱ ፋብሪካዎች ስራ ያቆሙ እለት ከሰልና ወናፈን ተሸክሜ "የነጆ ኢንዱስትሪ ልመሰርት ነው" እያልኩ ገጀራዬንና ቢለዋዬን ልቀጠቅጥ እንደምንኳተትም አውቀዋለሁ። ከኒያላ ሲጋራና ከክብሪት ባክ ላይ "ሜድ ኢን ኢትዮጵያ" እያለች ጉራዋን የምትነፋ አማተር አገር ይዤ ያደጉትን አገሮች "ጭሳችሁ በከለኝ" ለማለት አንደበቴ የሚታዘዘኝ አይመስለኝም።

እኒህ መንግስታት የሚሰሩት ስራ ግርም ብሎህ "በቅርብ በጣም አንገብጋቢ የሆኑ ሆዳችንንና አይምሯችንን የሚያላሽቁ በርካታ ችግሮች እያሉ ለምን የነጮቹን አጀንዳ ታራግባላችሁ?" ብለህ ስትጠይቅ "የምንሰራው ስራ ዘላቂነት ያለውና ለመጭው ትውልድ ጠቃሚ ሊሆን ይገባዋል" በማለት ይመልሱልሃል።

መቼም ዝም ብዬ ሳሰበው እንደዚህ ትውልድ አንጀቴን የሚበላኝ የለም። ችግኝ ቢተከል ለመጭው ትውልድ፣ ስኳር ፋብሪካ ቢተከል ለመጭው ትውልድ፣ ግድብ ቢገነባ ለመጭው ትውልድ፣ ድህነትን ተረት ቢያደርግ ለመጭው ትውልድ፣ ስለ አዞን መሳሳት ቢያስብ ለመጭው ትውልድ! እንደው ለነገሩ ይሄ መጭ ትውልድ እጅና እግር ብቻ ነው ይዞ የሚፈጠረው? ወደ ፊት የሚመጣው ማረጤ መጭ ትውልድ ለራሱ አያስብም? የሚል ጥያቄ ውስጤ ይፈጠርብኛል።

የዚህን ጥያቄየን መልስ ለአፍሪካ መሪዎች ልተውና ወደ ዋናው ሃሳቤ ልመለስ።

እና ከላይ እንዳልኳችሁ በፎቶ ካሜራ ሳይሆን በፎቶ ሲንቴሲስ የሚኖር ችግኝ

ልተክል ወስኛለሁ። "ችግኝ ትከሉ" የሚለው መልዕክት ባይደርሰኝም ድፍን መቶ ብር ይዤ ችግኝ ለመግዛት ወደ አካባቢዬ ያለ "ነርሰሪ ሳይት" ሄድኩኝ። የዚህ "ነርሰሪ ሳይት" ባለቤት ሴት ስትሆን መንግስት በርካታ ሄክታር መሬት ወንዝ ዳር ስለሰጣት አካባቢውን በጉደኛ እጽዋት ሸፍናው ወደ ቅጥሩ ስትገቡ ትገረማላችሁ። ፍራፍሬው፣ ችግኙ፣ አበባው፣ ሳሩ፣ ጎጆዎቹ፣ መናፈሻው ሁሉ ነገር ገነት የሆነ ቦታ ነው።

የመትከል እንጂ የመዝናናት አላማ ስለሌለኝ ወደ ችግኝ ጣቢያው አመራሁኝና ሁለት እጆቼን ኪሴ ውስጥ ከትቼ ችግኞችን እመርጥ ጀመር። ምናልባት ያሻኝን ያህል ችግኝ ገዝቼ ከመቶ ብሩ ላይ የሚተርፈኝ ከሆነ ወደ መናፈሻው ጎራ ብዬ ኮካ ለመጎንጨት አስቤያለሁ።

ስምንት አይነት የዛፍ ዝርያዎችን መረጥኩና ከእያንዳንዳቸው ሁለት ሁለት ችግኝ ለመውሰድ ወሰንኩኝ። እንዲያውም እዚሁ መናፈሻ ላይ ከጎኔ ሲወዛወዝ የማየውን ከምክም ያለ ሾጣጣ የጽድ ዝርያ ችግኝ ጣቢያው ውስጥ ስላገኘሁ የሱን አይነት ሶስት ችግኝ ለመግዛት አቀድኩኝ።

"እነዚህ ችግኞች ስንት ስንት ብር ናቸው?" አልኩኝ መቶ ብሬን በእጄ እያፈተለተልኩ።

"አንድ ሺ ስምንት መቶ ብር" አለችኝ ቁታ የለበሰች ሴት።

ሳላሰበው "እ!" ብዬ በመጮሄ ከጎኔ የነበረው ጽድ በድንጋጤ ጎንበስ ሲል አየሁት።

"ሁሉንም እኮ አይደለም አንዱን ነው ያልኩሽ" አልኳት ድንጋጤው አለፍ ሲልልኝ።

"እኔም አንዱን ነው ያልኩህ" ብላ ገረመመችኝ።

"ጉድ ፈላ! እነዚያ የባህል ሀኪሞች ያንን ሁሉ በሽታ የሚፈውስ መደሃኒታቸውን የሚቀምሙት ከዚህ ዛፍ ይሆን እንዴ?" በማለት አሰብኩና "ለምን ለምን አገልግሎት ይውላል?" አልኳት

"አርናሜንታል (የውበት ዛፍ)" መሆኑን ነገረችኝ።

ይሄ ችግኝ ለአካባቢ ውበት ከመሆን ባለፈ የሚሰቴንም ውበት ወደነበረበት የሚመልስ ቢሆን እንኳን በዚህ ዋጋ የደን መሬት እንጂ ችግኝ የማልገዛ ቢሆንም ሰይጣን አሳስቶኝ ችግኙን ብገዛውስ እንኳን ባላንጣው ጎረቤቴ አባተ እኔን ማጥቃቱን

ትቶ ጥቃቱን ወደዚህ አትከልት እንደሚያሸጋግር እያሰብኩኝ ሰወላከፍ የሰው ችግኝ እንዳልሰብር በጥንቃቄ ሹልክ ብዬ ወጣሁኝ።

"እውነት ለመናገር እንዲህ አይነት ቅጥ ያጣ ግብይት አንድት ግሪን ኢኮኖሚ ለምትከተልና "የአካባቢ ተቆርቋሪ ነኝ" ከምትል አገር አይጠበቅም። የችግኝ ማፍላት ስራ ይሄን ያህል አዋጭ ከሆነና አንድ ችግኝ የአንድ ሙከት በግን ያህል ዋጋ ማውጣት ከቻለ ከዩኒቨርሲቲ ተመርቀው ወደ ኩብል ስቶን ጠረባ ከሚገቡት ወጣቶች ቀነስ አድርጎ በዚህ ዘርፍስ ማሰማራት ለምን አይጀመርም? እኔስ ብሆን የአንድ ችግኝ ዋጋ የኔን የወር ደሞዝ ያህል ማውጣት ከጀመረ መፅሃፌን እያነበብኩ ሀያ ችግኞችን ስንከባከብ ብከርም አይሻለኝም ወይ?" እያልኩኝ የባህር ዛፍ ችግኝ ወደሚገኝበት ገባያ አመራሁኝ።

መቼም አርናሜንታሉ ቢቀር እንኳን በቀላል ዋጋ መግዛት የምንችላቸውን ችግኞች ብንተክል ካደጉት አገሮች ተርታ በህንጻ ካብና በመሰረተ ልማት መድረስ ባይችል እንኳን በልምላሜ የተሸለ አካባቢን መፍጠር የሚያቅተን አይመስለኝም። ስለሆነም መንግስትም "ስንት ችግኝ ተተከለ?" ከሚል የቁጥር ጨዋታ ወጥቶ "ስንት ችግኝ ጸደቀ?" ወደሚል ጥያቄ ፊቱን አዙሮ መስራት ከቻልን የተሸነቆረውን አዞን ማዳን ባንችል እንኳን ዛፎቹ ጥላ ስር አረፍ እያልን የሳሳ ጭንቅላታችንን ከጠራራው ጸሃይ መከለል እንችላለን።

ጥፍርና ብእር

ሳማ እንደፈጀው ሰው ላሺኝ እንደላሰው፣
ከውሰጥም ከውጭም አሳከከኝ ምነው?
ሸረ በላኝ ንበዝ ናላዬ ፈረሰ፣
አንዳች ምናምንቴ አንሳሌ ፀነሰ፣
ልቤን አስኪነሳኝ ጸጉሬ አስከሚረግፍ፣
ቆዳዬ አስኪበልዝ ጽንሴ አስኪጨነግፍ፣
እፎከተው ዘንዳ አስኪሸር ስሜቴ፣
ጥፍርና ብእር ስጠኝ ነው ፆለቴ።

ሳቅ

የአማረኛ መዝገበ-ቃላት ሳቅን ሲተረጉም "እንደ መናጢ ፈስ ባልታሰበ ሰዓት ሊያመልጥ የሚችል፣ ከውስጥ የሚፈልቅ፣ እንደ ንጥሻ ሊቆጣጠሩትም ሆነ ሊያዙት የማይቻል ነገር" ብሎ ይተረጉመዋል።

አሁን አሁን ጥቃቅን ነገሮች ደስታችንን እየቀሙን ተቸገርን እንጂ መዝገበ-ቃላቱ እንዳለውም ውስጥህ ፈካ ያለ ጊዜ ለመሳቅ "ሳቁ" የሚል ቅስቀሳም ሆነ የኮሜዲያኖቻችን እግዣኝ አስፈላጊ አይደለም።

ሳቅ እወዳለሁ። ጓደኞቼ በሙሉ ሳቂታ ናቸው። ይህ የሆነው ያለ ምክንያት አይደለም። ጓደኞቼን የምቀርባቸው በሳቃቸው ስለሆነ ነው። ምርግ ፊት ከሆንክ የፈለገ ደግ ስብዕና ቢኖርህ እንኳን ልግባባህ አልፈልግም። በዚህ ምድር ላይ እንደ ሳቅ የሚያሸንፈኝ ነገር የለም። ከመልከኛ ሴት ይልቅ ሳቂታ ሴት በፍቅሯ ትጥለኛለች። ከኪሊዮፓትራ እና ከሄሮዳዳ ውበት ይልቅ የሳቂታ ሴት ጥርስ እግሯ ስር ይሸረኩተኛል።

ውስጤ እንደ መስከረም ሰማይ ፈገግ ያለ እለት ብቻየን ስስቅ ሰው አይቶኝ ሊገረምብኝ ይችላል። በልጅነቴም አንዳንዴ ቅዳሴ ላይ ሳይቀር ሳቄ እያመለጠኝ በመቋሚያ እስከ መዝለጥ ደርሼ አውቃለሁ። ጭራሽ ሳቄ የሚበረታው እና አስቂኝ ነገር የማገኘው ሳቅ የተከለከለባቸው ቦታዎች ላይ ነው።

እኛ አገር አጥብቀው ከፈለጉ ቀብር ላይ፣ ምርጫ ላይ፣ ችሎት ላይ፣ ሰብሰባ ላይ፣ ፓርላማ ላይ ሳቅ መሸጓል። ከኮሜዲያኖቻችን አርቲ ቡርቲ ወሬና ከጋሼ የሳቅ ትምህርት ውጭ ሁሉንም ነገር በንጹህ ልቦናና አይምሮ ልብ አድርገህ ካየኸው ውስጡ ስላቅ ታሸጓል። ለነገሩ እነዚህም ውስጥ ሳቅ የለም ብሎ መደምደም አይቻልም።

እንደሚመስለኝ በትምህርት የሚመጣ ሳቅ ከጥርስ የሚፈልቅ ነው። መቼም አንዲት ፊልም የምትሰራ ተዋናይና አንድ ልጇን ቀብራ የምትመጣ እናት የሚያፈሱት እንባ በአንድ የሚፈረጅ አይደለም። የተዋናይ እንባ ከአይን የሚፈልቅ ሲሆን የእናት ለቅሶ ግን ከልብ የሚፈልቅ ነው። ሳቅም እንደዛው ነው ከጥርስ ሳይሆን ከልብ ነው የሚፈልቀው።

ስለ ሳቅ ማብራራቱን ጋብ አናድርግና ወደ ሳቃችንማ እንመለስ።

እና እንዳልኳችሁ ሳቅ እወዳለሁ። ለምሳሌ ዛሬ እንኳን ከነጋ በስንቱ ነገር በፎጣዬ ተሸፋፍኜ ስደከም ነበር።

የተቃዋሚ ፓርቲ ሊቀመንበር የሆኑት ጋሼ አበራ እንኳን አገር ሊመሩ ቀርቶ አይናቸው ከመድከሙ የተነሳ ከአረብ አገር ልጃቸው የላከችላቸውን "ተች ስክሪን ሞባይል" አይናቸው ስር ጥደው በቅንድባቸው ሲያንሸራትቱት ስመለከት፣ አጎቴ "በወረዳችን ባለው ተቃዋሚ ፓርቲ ውስጥ አባል ሁኜ በነበር አበራን የወረዳ ሊቀመንበር ያደረገ ፓርቲ እኔን ሚኒስቴር ከማድረግ ወደ ኋላ እንደማይል" ሲነግረኝ ቆይቶ በበራችን ላይ ፖሊሶች ውርውር ማለት ሲጀምሩ ደግሞ ቅድም ያለኝን ሀሳብ ሰርዞ "የታጠቀ ያሸንፋል ብሏል ሌሊን" ሲለኝ... ይሄን አባባል አጎቴ እንጂ ሌሊን አለማለቱን ስረዳ እንደጉድ ስስቅ ነበር።

ከዛ ደግሞ ከምርጫ ጣቢያው ስወጣ ይሄው አጎቴ በስተርጅና ያገባትን ሚስቱን "በሺ ዘጠኝ መቶ ዘጠና ሁለት ዓመተ ምህረት የገዛሁትን ሸሚዝ አጥባ ላታጥብ ነገር ኮሌታውን ቀደደችብኝ" ብሎ ሲያባርራት ሳይ "ተቀደደ" በተባለው ሸሚዝ አፌን አፍኜ ስስቅ ነበር።

በዛው ልክ ደግሞ አንዳንድ ጅል አለ በማያሳቀው ነገር ሊያስቅ የሚሞክር፡-

አሁን ያ ጓደኛዬ ዳኜ በሰላም ቁጭ ብዬ ቡና የምጠጣበት ካፌ ድንገት መጥቶ "መርጬ መጣሁ" ብሎ ገጣጣ ጥርሱን በመዳፉ ሸፍኖ ይስቅና "ሳቁ ሊያባራ ነው" ብዬ ሳስብ ደግሞ "ተይህ በላይ ቀልድ ከየት ይገኛል?" ብሎ እንደገና አይን አይኔን እያዬ ሲንፈራፈርና ስቆ ሊያስቀኝ ሲሞክር ሳይ ጥርሱን ባወልቀው ደስተኛ ነበርኩኝ።

እስኪ ካላጣው ቀልድ የሀገርን ህልውና በሚወስን ምርጫ ላይ ያውም እኔን እኔን እያዩ መገልፈጥ በሰዎች ዘንድ ምን ትርጉም ያሰጣል ብሎ ማሰብ እንዴት ያቅተዋል? ያም ሁኖ ግን ቤቴ ከገባሁ በኋላ አሳሳቁን እያስታወስኩ "ቡፍ" ማለቴ አልቀረም።

አንዲህ እንደ ዛሬው በሆነ ባልሆነው ስሰቅ የምውለው ከስንት አንዴ ነው። የቤቴ አስቤዛ ሞላ ያለ እለት... የሚስቴ ፊት ወዛ ያለ እለት... ደሞዝ ያወጣሁ እለት... ባላንጣ ጎረቤቴ ጋር እርቅ የወረደ እለት ነው እንዲህ ውስጤን ሳቅ የሚሞላው። ውስጤ ሰላም የሆነ ጊዜ ለመሳቅ የሚረዱ ምክሮች የሚለው ትምህርትም ሆነ የኮሜድያኖች መናኛ ቀልድ አያስፈልገኝም። የሚያየውን ነገር ሁሉ አይምሮዬ ወደ ቧልት እየቀየረ ሲያፍነከንከኝ ይውላል።

ወደ ዋናው ሃሳቤ ልግባና ቧልት እንደ ቱልት በፈሰሰበት ሀገር ታዲያ የኛ ኮሜድያች እኛው ፈጥረን እኛው ሰቀን የጣልናቸውን ቀልዶች ሰብስበው እኛኑ ሊያስቁን ወደ መድረክ ይወጣሉ። ያም አልበቃቸው ብሎ በኮኬይን የማይወገድ ድፕረሺን ያጠቃውን ማህበረሰብ አስቃለሁ ብለው አትላንቲክን አቋርጠው ሲሄዱ ግርም ይለኛል። እዛም ደርሰው ሲመለስ ልብስ እንጂ ቀልድ አይቀይሩም።

የሚገርመው ነገር ለገና በዓል አውርተውን ያልሳቅንበትን ቀልድ ለፋሲካም ይዘውት ሚድያ ላይ ይቀርባሉ። የዘመን መለወጫ እለት በቀጫጫ በጉ ያሳቀህ ኮሜድያን ቀልዷንም፣ በጓንም ሳያወፍራት ለፋሲካም ይዞልህ ይቀርባል።

ለነገሩ እንጀራ ስለሆነባቸው ነው። ለበዓል በግ መግዣ የሚሆን ገንዘብ ሲመጣ "ቀልድ የለንም" ብለው ቀብዱን ከመመለስ ይልቅ ያችኑ ቀልድ አቅርበው ቢሳቅባቸው ይመርጣሉ። የሚያስቅ ኮሜድያን ያደረጋቸው ድህነታቸው ነው እንጂ በየመድረኩ መሳቀቅ ፈልገው አይደለም። የገንዘብ ችግራቸው ቢፈታ ማይክራፎን መስቀላቸው አይቀርም።

በህይዎቴ በጣም የሚያሳፍረኝ ነገር ኮሜድያን ኢንተርቪው ሲደረጉ ማዬት ነው። ወይ ባግባቡ ለተጠየቁት ጥያቄ መልስ አይሰጡ "እንቀልዳለን" ይሉና ጋዜጠኛው ራሱ መሳቅ ቀርቶ ማግጠጥ እያቃተው ጥያቄዎቹ ሁሉ ሲጠፉት ይስተዋላል።

ማሳቅ ታላቅ ጥበብ ነው። እንደ ዛሬው ንጉሶቻችን መሳቅ ሳይሰናቸው በፊት መድረኩን ተውትና ቤተ-መንግስቱንም የሚናጉበት ኮሜዲያኖች ነበሩ። ለምሳሌ አለቃ ገብረሃናን መጥቀስ ይቻላል።

በነገራችን ላይ የአሁን ዘመን ባለስልጣኖች ሲስቁ የማይታዩት ለምንድን ነው? ይሄን ሳስብ ባለስልጣን ለመሆን ዋናው መስፈርት ጭንቅላት ነው ኮስታራነት የሚል ጥያቄ አነሳለሁ። ነፍሳቸውን ይማረውና የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስቴራችን አሳቸው ሲስቁ ባይታዩም እኛን ግን አለቅጥ ያስቁን ነበር።

አንድ ጊዜ ወደ ሐረር ስሄድ አሳቸው ተናገሩት የተባለውን ወሬ ላውራችሁማ!

ሐረር ውስጥ የጃንሆይ አባት የራስ መኮነን ሀውልት አለ። ራስ መኮነን መቼስ ፈረሳቸው ላይ ሆነው ሲታዩ ያላቸው ግርማ ሞገስ ልዩ ነው። አደራዎች በአንድ ወቅት "የራስ መኮነን ሀውልት ይፍረስና የአሚራችን ሀውልት ይተከልልን" ብለው ሰዎች ይወከሉና ወደ ጠቅላይ ሚኒስቴሩ ይልካሉ።

ጠቅላይ ሚኒስቴሩም ከእንግዶቹ አፍ ጉዳዩን ከሰሙ በኋላ ምን ቢሉ ጥሩ ነው?

"የራስ መኮነን ሀውልት አይፈርስም። ሆኖም አሚሩ ፈረስ ይጋልቡ የምትሉ ከሆነ ሀውልታቸውን ሰርታችሁ አምጡና ከራስ መኮነን ጎላ አፈናቷቸው" አሏቸው አሉ። የተወከሉት ሰዎችም ከት ብለው ይስቁና "ባንድ ፈረስ ሁለት ንጉስ ይሉሃል ይሄ ነው" ብለው ወደ ሀገራቸው ይመላሳሉ።

የሐረር ህዝቦችም ይሄን ሲሰሙ በሳቅ ውስጥ ሆነው ጠቅላይ ሚኒስቴራችንን "ሀውልት አይውጣልህ" ብለው ተራግመው ኑሮ ይሄው ነፍሳቸውን ይማረውና አሳቸውን የሚመስል ሀውልት መቅረጽ አቅቶን ቀረ።

ለነገሩ በእሳቸው ስም የተፈበረከ ቀልድ እንጂ ሐረሬዎችም ከቡር ጠቅላይ ሚኒስቴሩም ይሄን አይሉም። ደግሞም እናንተ ሳትቀድሙኝ በፊት "የእሳቸው ሀውልት ያካናወኗቸው ልማቶች ናቸው" በማለት ላስረዳና ደስታ ካለ ሳቅን ከመፈለግ ደስተኛ ሕይወትን መፈለግ ተገቢ ይመስለኛል። ከዚያ በኋላ ሳቅ በራሱ ጊዜ የሚመጣ ይሆናል።

ማነሽ ባክሽ?

አንጀራና አዱኛ
በሚበታትኑት
በዚህ ሶስተኛ ዓለም፣
ከፈሰበከ የላቀ
መገናኛ የለም።

ገባሁ "login" ብዬ
ትኖሪያለሽ ብዬ
የለሽም ባገሩ
ሰው ሁሉ ያዛጋል፣
ባንች መጥፋት ሳቢያ
ዙከርበርግ ተከዘ
ኪሳራ ያሰላል።
አ ስ ከ ት መ ጭ ድረስ፣
ነገር በሚፈልግ በብስጩ መንፈስ፣
የተለጣጠፈ ምናምንቴ ሳስስ
አምላክ ዘግይቶበት አንድ ገጣሚ ሰው፣
"እንደምህ እግዜር ሰማይ ቤት እንዴት ነው?"
የሚል ግጥም ጽፎ አንቺን በማጣቱ፣
"አን ላይን" ይታያል ሲጨስ እንፋሎቱ፣
/ቡ.....ፍ እንደ መላቅ ቃጣኝ/
አጸብ ኮሜንትሽን

እንዲህ እንደ ዋዛ እንዲህ እንደ ቀላል፣
ያንች አኮ አንድ ላይክ
ከአስካር ሽልማት ሺ ጊዜ ያይላል!
/ ነገር ነገር አለኝ/

"በሠላሳ ድናር አንደ ጨው ልትሸጠው፣
ሊጅቹን ቸንክረህ እንጨት ላይ ልትሰቅለው፣
አግዜር አስኪመጣ አጣደፈህ ምነው?"
የሚል ኮሜንት ጽፌ፣
ሳስበው ሳስበው ሃሳቡን አግዝፌ፣
"እመጣለሁ" ብሎ "ቀረ" ያሉት አግዜር፣
ሰማይ ላይ ነው ያለ? የለም እዚች ምድር?
አይኖችሽ ላይ የለም? ልሳንሽ ላይ የለም?
ጉንጉንሽ ላይ የለም? ፈገግታሽ ላይ የለም?
አግዜር ለመኖሩ
ውቡ ከንፈርሽ ላይ
ያውና ማስረጃ ያውና ማህተም።

አሁን ወደ'ት ገባሽ? አሁን ወደ'ት ወጣሽ?
የት አለ ፈገግታሽ? የት አለ ምስልሽ?
ዙከርበርግ አራሱ ላይክ የሚቸርሽ፣
ይሄው አንችን ሳስስ
ተጥጄ ሰጠብቅ፣
አይልኝ ሰውዬው አጓጉል ሲራቀቅ፣
"በትር ሰጠን" ብሎ አግዜርን ሲጠይቅ፣
አይው የኔ አመቤት...
ይልቅ አግዜሄሩን እንደምትይልን፣
በትር ነው የበዛው ዱላ ነው የቸከን፣
አንደ'ዜ በአለንጋ አንደ በከረዛ፣
አረ ቆመጥ በዛ! አረ ዱላ በዛ!
"ኤሎሄ ኤሎሄ" አያልን አንባ ብናካፋ፣
ዱላውን ጥሎብን ሙሴ ወደት ጠፋ?
ብለዋል በይልን፣
ዱላ መመከቻ ጋሻ አንድልከለን።

ደግሞስ የኔ ልአልት ደግሞስ አመቤቴ፣
ከሁሉም ከሁሉም ዋነኛው ሲጋቴ፣
"ፀሐይ ትጥፋ" የሚል የዚህን ሰው ፆለት፣
ፈጣሪ ቢሰማው ሀልሙ ቢሳካለት፣
እግዜር ትጥፋ ብሎ የወሰነ ለታ፣
አንችን ቢያጠፋሳ በፀሐይዋ ፈንታ።
/በሰማም ሶስት ጊዜ/
አያልኩ አስባለሁ፣
አኔ ያንች ሰለባ
መግባትሽን እያየሁ፣
አስከትመጭ ድረስ
አይናቼን አቡዝዥ
ጣቶቼን ገንዥ
አጠብቅሻለሁ።

ወልዳችሁ ቅመሱት

"ምን ይምጣልሽ?" አላት።

"ምን ምን አለ አለችው?" አልጋ ብቻ የተዘረጋበትን ባዶ ክፍል ቤቱን በዐይኗ እየቃኘች።

"ሰንሴሽን ኮፊ ይሁን ኖርማል ሰንሴሽን?" አላት ሻንጣ ሙሉ ኮንዶም እየዘረገፈ።

በጣም ሳቀች።

*****

አፍታም ሳይቆዩ አንሶላ ውስጥ ሰርገው ገቡ።

"ፈነዳ!" አለችው።

ዝም አላት።

"ኮንዶሙ ፈነዳ ነው የምልህ!"

"ለምን እሳተ ገሞራ አይፈነዳም!" አላት እንደ ደራጎን በአፉ እሳት እየተፋ።

"አውጣውና ኮንዶም ቀይር እንጂ!"

በስሜት እየቃተተ ኮንዶም መጨረሱን ነገራት።

"ባረግዝስ?"" አለችው ሰውነቷ ኩምትርትር እያለ።

"ብታረግኝ?"

"አዎ ባረግዝስ?"

"ካረገሺማ?"

"እ! ካረገዝኩማ?"

"ታስወርጂዋለሽ" አለና ተርገፍግፎ ጨረሰ።

ብልቱን ሲመዘው ኮንዶሙ "ብራሰሌት" ሁኖለት ነበር።

ሀሊና በተናገረው ቃላት የተነሳ እንዲሸኛት ፍቃደኛ ባትሆንም "ካልሸኘሁሽ" ብሎ ግግም በማለቱ ወገቧን አቅፎ ሰፈሯ አደረሳት። ተመልሶ ወደ ግቢው ሲገባ የአከራዩ ህጻን ልጅ ከሰዓታት በፊት ያለቀበትን ኮንዶም በአፉ ሲነፋ አገኘው። ይሄንን ልጅ ከእድሜው በላይ የሚያስብ ብልጣ ብልጥ ስለሆነ አይወደውም። ህጻኑም ቢሆን ካሉት ተከራዮች ሁሉ እንደ እሱ የሚጠላው የለም።

"አንተ ቆሻሻ! እሱን ኮንዶም አትጥልም!" ብሎ ጮኸበት።

"ምነው መንፈያህን ነፋሁብህ እንዴ?" አለውና ሩጦ ወደ ቤቱ ገባ።

ቀኑን ሙሉ በኮንዶም የተነሳ ሲነገነግ መዋሉ ፈገግ አሰኘው።

*****

"ውሾን ያነሳ ውሻ ይሁን" ብለው ሰነበቱ።

የሆነ ቀን በእንቅልፍ እጦት የሚናውዘውን ጭንቅላቱን አባብሎ፣ አባብሎ ሸለብ ሊያደርገው ሲል ስልክ ተደወለለት።

ሀሊና ናት። እየተጨናበሰ ስልኩን አነሳው።

ስትፈራ ስትቸር "አረገዝኩ!" አለችው።

"ምን?" አላት ሞባይሉን ወደ ግራ እጁ አቀብሎ በቀኝ እጁ እስኪበቃው ድረስ እያማተበ።

"ሰው ነዋ ምን አረግዛለሁ!"

"መሲህ እንዳይሆን ብዬ ነው!"

"አትቀልድ እንጂ"

"ኧረ እየቀለድኩ አይደለም"

"እና ምን ይሻላል?" አለችው።

"አስወርጂው" አላት ጮህ ብሎ።

ሀኪሞቹ ያሏትን ነገረችው።

"እና ከማስወረድ መውለድ ቀላል ነው አሉሽ?"

"አዎ"

"በልጅሽ ህይዎት የሚወስኑት እነሱ ከሆኑ....."

"በልጅሽ አትበለኝ!"

"አኬ! በልጁ ህይወት ወሳኞቹ ሃኪሞቹ ከሆኑ እነሱ ያሳድጉት!" ሲላት ስልኩን በንደት ጆሮው ላይ ጠረቀመችበት።

"እንኳን ሰው ችግኝ ተከላም በፕሮግራም በሆነበት ዘመን አረገዝኩ ትለኛለች እንዴ?" አለና ሞባይሉን እንዳይሰበር አድርጎ ወረወረው።

ትንሽ ቆይቶ ደግሞ ወሬኛ ጓደኛው ግርማ ደወለለትና "የምስራች!" አለው።

"ምስር ልቀም" ብሎ ስልኩን ዘጋበት።

****

በተደጋጋሚ ስልክ እየደወለች ልታገኘው እንደምትፈልግ ብትነግረውም ልጁን ማስወረድ ካልቻለች እንኳን በአካል በስልክም ሊያገኛት እንደማይፈልግ ቁርጥ አድርጎ ነገራት። እንዳለውም ይሄን ማድረግ እንደማትችል ስትነግረው ስልክ ማንሳቱን ተወ። እሷ በጽንሱ ምክንያት የበላችው ምግብ አልረጋጋ እያለ ሲያስታውካት እሱም ጢንቢራው እስኪዞር ድረስ መጠጥ ሲጋፍፍ አምሽቶ ያስታውክ ነበር።

በመጨረሻ ሀሊና ስልኩን አላነሳ ሲላት ሚሴጅ ላከችለትና አነበበው። ዛሬ ልታገኘው ካልቻለች በራሷ ላይ መጥፎ ነገር ልታደርግ እንደምትችል የሚያትት መልዕክት ነበር የላከችለት።

ምንም አይነት መልስ ሊሰጣት አልፈለገም።

*****

ከቢሮ ወጥቶ ጃኬት ደርቦ ሊወጣ ሲል ግቢያቸው በር ላይ ሁለት ፖሊሶች ቁመው አየ። ዝም ብሎ ሊያልፋቸው ሲል "አቶ ተስፋ ማለት አንተ ነህ?" አሉት።

"አዎ" አላቸው።

"ለምርመራ ጉዳይ ፖሊስ ጣቢያ ትፈለጋለህ!" ብለው ይዘውት ሄዱ። የሄደበትን ምክንያት ለማዎቅ አልቸኮለም። ህሊና የከፋ ነገር ራሷ ላይ እንዳደረገች ግልጽ ሁኖለታል። አሁን ማዎቅ የፈለገው ነገር በሕይወት አለች ወይስ የለችም የሚለውን ነገር ነው።

መርማሪው ፖሊስ ወንበር ላይ እንዲቀመጥ ጋበዘው። "ህሊና በትናንትናው እለት ጽንስ ለማስወረድ ስትል በርካታ ክኒን ከኮካ ጋር ቀላቅላ በመውሰዷ ምክንያት ሕይወቷ አደጋ ውስጥ በመግባቱ ሆስፒታል ትገኛለች። ይሄን እንዲታደርግ ደግሞ ካንተ በኩል ከፍተኛ ግፊት ሲደረግ እንደነበር ተረድተናል። ስለዚህ ጉዳዩ በምርመራ እስኪጣራ ድረስ ወህኒ ቤት ትቆያለህ" ብሎ አሰናበተው።

****

ወህኒ ቤት ውስጥ በቆየባቸው ሶስት ቀናት ሲጨነቅ የነበረው ስለእሱ መታሰር ሳይሆን ስለ ህሊና ጤንነት ጉዳይ ነበር። ወደ ኋላ መለስ ብሎ ሲያስበው ሲያደርገው የነበረው ነገር የልጅ ስራ እንደነበር ተገለጸለት። "አስወርጂ" ሲላት ልጅ ካለመፈለጉ በቀር በጤንነቷ ላይ ስለሚያመጣው ጉዳት በጥልቀት ማሰብ አልቻለም ነበር። ሆኖም ፈጣሪ ሲረዳው ህሊናም ሳትጎዳ ልጁም ሳይወርድ በሃኪሞች እርዳታ መትረፍ ቻለችና ለተስፋ ካለት ፍቅር የተነሳ "ጉዳዩን የፈጸምኩት በራሴ ውሳኔ እንጂ በተስፋ ግፊት አይደለም" በማለቷ ምክንያት ከወህኒ ሊወጣ ቻለ።

*****

ከተወሰነ ወራት በኋላ ተስፋ ባላሰበው ጊዜ፣ ባልታሰበ ቦታ፣ ባልታሰበ ሁኔታ ይከሰት ጀመር። አራዳ ገባያ መሃል... አጃ፣ ዳይፐር፣ ጡጦ፣ ናን ወተት፣ ጆንሰን ሳሙና፣ እንቁላል በፔስታል ተሸክሞ ዝርክርክ ብሎ ራሱን ሲያገኘው የገዛውን አስቤዛ ገባያው መሃል በትኖ...ሚኒባስ በመሳፈር በሀረጎ በኩል "ብን" ብሎ መጥፋት አማረው።

የባለፈው ጥፋቱ አንሶት አሁንም ልጁ ከተወለደም በኋላ አባት መሆኑን ለመቀበል ማቅማማት ይታይበታል።

በቆመበት ከምኔው ከአንበሳ ወተት ወደ ናን ወተት እንደተሸጋገረ ሲያስበው ፈገግ አለ። ስሜቱን ተቆጣጥሮ ወደ ሰፈሩ ሲያመራ የብቸኝነት መዲና የነበረችው ቤቱ በሰው መዓት ተሞልታ አገኛት። ለጠፋው ብቸኝነቱ "ኡ ኡ ኡ"" ብሎ መጮህ አማረው። ጸጥታንና ኖርማል ሕይወትን አለቅጥ ፈለገ። ተስፋ "ኖርማል ሕይወት" የሚለው ነገር ለሌላው ሰው የሚጥም አይደለም።

ፔስታሉን ለሰራተኛዋ አቀብሎ መጋረጃውን ገለጥ አድርጎ በመግባት ህሊና አጠገብ ሄዶ ተቀመጠ። "የኔ ከንፈር አፈር መስሎ አንቺ በቅቤ የላሸቀ ሾርባሽን በኩባያ ትልፊያለሽ!" የሚል ስሞታ አይኑ ላይ ያነበበች መሰላት። እስከ እኩለ ቀን ድረስ ጠያቂዎች እየመጡ "እንኳን ማሪያም ማረችሽ!" ባሉ ቁጥር የመጣበትን መዓት በልቡ እያሰበ በአፉ ግን "እንኳን አብራ ማረችን" ሲል ዋለ። መቼም የሰውነቱ መጎሳቆል ሲታይ የወለደ እንጂ ያስወለደ አይመስልም። የሚገርመው ነገር ከወለደች ቀናት ያለፏት ቢሆንም የተወለደለትን ልጅ ገልጦ ለማዬት አልፈለገም። እንዲያውም ህጻኑን ጥምድ አድርጎ ይዞታል።

*****

የሆነ ምሽት ላይ "እረ ለዚህ ልጅ የአሳ ዘይት ይገዛለት!" አሉ የህሊና እናት ሾርባቸውን እያማሰሉ።

"የምን የአሳ ዘይት ነው! ኖርማሉ የኮሌስትሮል ዘይት ተገኝቷልና!" አለ ተስፋ ጮህ ብሎ። አሁን ደግሞ ኖርማል የሚለውን ቃል ከኮሌስትሮል ጋር አገናኘው።

"አይ እሱማ ግድ ነው...! ያለዚያ እኮ አይምሮው ፈጣን አይሆንም.... በትምህርቱም ደካማ ይሆናሉ!" አሉት የህሊና እናት እየተበሳጩ።

"በዚህ ፖሊሲ ተምሮ የአሳ ዘይት አልጠጣሁም በሚል ሰበብ ዩኒቨርሲቲ መግባት ካቃተው ለምን ጥፍሩን አይጠባም!" አላቸው ተስፋ የሱ ልጅ አድጎ ዩኒቨርስቲ እስኪገባ ድረስ ይሄ መንግስት ከነፖሊሲው ስልጣን ላይ እንደሚኖር እርግጠኛ ሁኖ።

"ህጻኑ ሁሉ እየጠጣ ለምን የኔ ልጅ ይቀርበታል? የአሳ ዘይቱን ጠጥቶ ጎበዝ ይሆናል እንጂ!" አለችው ህሊና ሾርባዋን በኩባያ እየጠጣች።

"አብሾ አጠጡት!" አላቸው በደም ፍላት።

"ምን ተቅባሸራለህ አንድን ሰው አባት የሚያስብለው ነገር እንቁላል መስበሩ

ሳይሆን እንቁላል አብልቶ ማሳደጉ ነው። ሰው አይኑን ባይኑ አይቶ እንደመደሰት ምንድን ነው እንዲህ አይነት አታካራ መግጠም!" በማለት የህሊና እናት ተበሳጩ።

*****

"ልጁ እንዳይታፈን ጠብቅ" ብለውት ወደ ሽንት ቤት ህሊናን አጅበው ከሄዱ በኋላ ተመልሰው "አደራህን ጥለኸው እንዳትወጣ ገና አርባ ቀን አልሞላውም" አሉት የህሊና እናት በጥላቻ አይን እያዩት።

ከመውጣታቸው ልጁ ማልቀስ ሲጀምር ሊተወው አሰበና "እንዳይታፈን!" ያሉትን አስታውሶ በድንጋጤ ለመጀመሪያ ጊዜ ቀረብ ብሎ አየው። ሰላሳ ሁለቱንም ድዱን ገልፍጦ ህጻኑ በፈገግታ ተቀበለው። ሳያስበው እሱም ፈገግ አለ።

ወደ ሰውነቱ ቀረብ ብሎ አሸተተው። ወተት ወተት የሚሸተው የህጻኑ ገላ አለቅጥ ጣፈጠው። የሚጠባውን እጁን ከአፉ ላይ አነሳና ሳም አድርጎት ወደ ቦታው ተመለሰ።

ይሄን ሁሉ ሲያደርግ መላእከት እያዘዙት ይመስል ነበር።

ገረመው።

ሌሊቱን ከእንቅልፉ በነቃ ቁጥር ልጅ የመጥላት መንፈሱን የህጻኑ ፈገግታ ፊቱ ላይ እየመጣ ሲያዳክመው አደረ።

*****

ልጁን ታቅፎ ህጻኑ ከንፈሮች ላይ የተዘረጉትን ሀረጎች ሲያስተውል በነዚያ ሀረጎች ላይ ደግሞ እንደ ኤዶም ምንጭ ውሃ ኩልል እያሉ የሚወርዱትን ከአፉ የሚፈልቁ ፈሳሾች እያዬ በዚህ ልጅ ሕይወት ላይ የሞት ውሳኔ ማስተላለፉን ሲያስብ እራሱን በጣም ይጠላዋል። ያንንም ለማካካስ የፈለገ ይመስል "ጡት ይጥባ" ካልተባለ በቀር ህጻኑ ከእቅፉ ባይወጣ ደስታው ነው።

የጨዋታ ጊዜ የነፈጋቸው ወንደላጤ ጓደኞቹ ሽንት ጨርቅ ሲያጥብ፣ ልጁን ታቅፎ ሲውል የባህሪው መለወጥ እየገረማቸው በአሽሙር ሊወጉት ይሞክራሉ።

አሱ ግን ለእነሱ ትችት ሁሌ ሲመልስ "ወልዳችሁ ቅመሱት" በማለት ነው።

መታሰቢያ

በሚገርም ዘመን- የተፈጠረ ሰው
መገረም፣ማስገረም- ይህ ነው እጣ ፈንታው።።

****

ድራማው ገራሚ- ዘፈኑ ገራሚ
የገረጣን አገር- አድማቂ፣አለምላሚ

አስኪ እንደው በሞቴ.....
ፊልሙን ዝጋውና ዙሪያ ገባህን እይ
ሁሉም ሰው ቀጣፊ- ሁሉም ሰው ተዋናይ
ሁሉም ነፍሰ በላ- ሁሉም ነፍሰ ገዳይ
አህዛቡ አስመሳይ
መንግስታቱ አስመሳይ
ቀፋይ..... መጋ ቀፋይ
/ኡ.....ይ!/
እንጀራ ጋጋሪህ-በወር ለአምሳ ዲናር- ግራ 'ምታጋባት
"አብሲቱ ቀጠነ፣ ሊጡ አልቦካም" እያልክ- አሳት ዳር የጣድካት
ዛሬ በሰው አገር ረመጥ ሲልሳት
"አህቴን፣ አህቴን" እያሉ መንኳተት
ውሸት.... ከንቱ ቅጥፈት

*****

ግራ የገባት ነፍስ "ሞንቋን" ጻፈች ብሎ
"በእገላለሁ" ዛቻ ከአገር አስኮብልሎ ፡

ዛሬ የሞተ ሰት ለቅሶ ይቃጠዋል አሱ ራሱ ገድሎ::
/አ.....ጅ.....ብ /

አሁን ብድግ ብለህ-ቲቪህን ብከፍተው
ነገ ሚሞት ህጻን-ሆስፒታል ተወልዶ- ይሄ ሁኗል ዜናው
አንድም ሰው በወሊድ እንዳይሞት ነው ጉራው

አሰኪ እንደው በሞቴ.....
በየሰው አገሩ- አሳት ለሚበላው
ያበደ ሰባኪ- ሰይፍ ለሚቀላው
ጋላቢ ማአበል- ከአለት ለሚያጋጨው
"ከጅቡ ዳንኩኝ" ሲል - አሳ ለሚልሰው
ለእንደኔ አይነት ከንቱ - ለእንዳንተ አይነቱ ሰው
የማንም ወፈፌ- ዛር አሰታጋሽ ፍጡር
ማህጸን ጨምድዶት- ሳይወለድ ቢቀር
አንዴት ያለ ምህረት- ይቅርታስ አልነበር?

ጨረርና ውሃ

የብርሃን አምላክ ፀሐይን ሲፈጥር
ዘማሞ ሰጠሸና ወቂት ላይንሽ ጨረር
ለኔም አድሎኛል...
የውቅያኖስ አምላክ ባህር ሲገነባ
ዐይንሽን እያየሁ የማፈሰው እምባ::

አመድ የሆነው ብር

ኤልሲ የመስሪያ ቤታችን ሴክሬታሪና የኔ ፍቅረኛ የነበረች ናት። ውበት እንጂ ባህሪ ላይ ብዙ ችግሮች አሉባት። ያም ሆኖ መቼም ቢሆን ልርቃት እችላለሁ ብዬ አስቤ አላውቅም። የወር ደሞዟን ሳትነካካ ባንክ ወስዳ ጣል ስለምታደርጋት ገንዘብ ይቸግራታል። ብዙ ነገሮችን ትቆጥባለች። የሞባይል ካርዱን እንተወውና የሞባይል ባትሪም ትቆጥባለች።

"call me back" እራሱ በቀን ውስጥ ከሶስት ጊዜ በላይ መላክ ስለማይቻል አሱንም እንዳያልቅ ትሳሳለታለች። እሷን ከወደድኩ ጊዜ ጀምሮ የኔ ደሞዝ የሁለታችንም ወጭ፣ የሷ ደሞዝ ግን የብቻዋ ገቢ ቢሆንም ያቀመሰችኝ ምናምንቴ ስላለ ተማርሬባት አላውቅም።

ብዙ ጊዜዬን እሷ ቤት ባሳልፍም ከእሷ ጋር ባንድ ጎጆ መኖር ስለማልፈልግ ለብቻዬ የተከራየሁት ቤት አለኝ። እሷም ብትሆን አብሬት እንዲኖር የምትፈልግ አይመስለኝም።

እብደቷና አለመረጋጋቷ አልጋ ላይ ይብሳል። ያንን የእብደት ትዕይንት ከማየት በላይ የሚመስጠኝ ነገር የለም። በዚያ ላይ ደግሞ አሳባጁ እኔ መሆኔን ስረዳ አንበሳ ከመግደል በላይ፣ የአይሲስ መሪን "አቡ በክር አልባግዳዲን" ከመማረክ በላይ የሚሰማኝ ጀግንነት የላቀ ነው።

የሴክሬታሪነቱ ተጽዕኖ ሳይሆን አልቀረም የገባትንም ያልገባትንም ጥቅስ መጻፍና መለጣጠፍ ትወዳለች። የሆነ ጊዜ "የመጀመሪያ ፍቅር በልብ ውስጥ ተዳፍኖ የሚቀር እሳት ነው" የሚል ጥቅስ ለጥፋ አገኘኋት።

"የማን ነው አልኳት?" የመጀመሪያ ፍቅረኛዬ የምትለውን አቡካዶ ጋብዞ ድንግልናዋን ወስዶ የራቃትን ወመኔ እያስታወስኩኝ።

"የማን ይመስልሃል?" አለችኝ በፈገግታ ተውጣ።

መቼም አንዲህ አይነት አባባል የእሷ እንጅ የሶቅራጠስ ሊሆን አይችልም።

"ወደድከው አይደል? ዘ-ማይንድ የሚለው መጽሄት ላይ ከታላላቅ ሰዎች አንደበት የሚለው አምድ ስር አግኝቸው ነው" አለችኝ በፈገግታ ተውጣ።

እንዲህም ያለ ታላቅ ሰው የለ! ሁለተኛስ ፍቅር ምን ውስጥ ይሆን የሚዳፈነው?

ኤልሲ ምግብ ትወዳለች።

ሌላውን ተውትና እከሌ እኮ ሞተ ሲባል "በስማም ሳይበላው ሞተ" ማለትን ታስቀድማለች። ወይም የሞተው ሰው ደግሞ የተደላደለ ኑሮ የኖረ ከሆነ "እሱስ ቅርጥፍ አድርጎ ስለበላ ቢሞትም አይቆጨው" በማለት መሞቱን ትደግፋለች።

የሰው ልጅ የመፈጠርን ሚስጥር በልቶ ከመሞት ጋር ታገናኘዋለች። ስጋ፣ ዘይት፣ በርበሬና፣ ዳቦ ገዝቼ ወደ ቤቷ እሄዳለሁ። እሷ ጨው ታዋጣና "ኑሮን ተጋግዘን ካልመራነው የሚቻል አልሆነም" ብላ ታወራኛለች።

እኔ የገዛሁት ስጋ ሲሆን በከትፎና በጥብስ መልክ ወድያውኑ ተሰርቶ ድባቅ ይመታል። እሷ ግን በራሷ ሂሳብ የገዛችው ስጋ ተዘልዝሎ ቋንጣ ከሆነ አመት ሞላው፡ ከዛሬ ነገ ይወርዳል እያልኩ ቋንጣውን አንጋጥጬ ያየሁበትን ጊዜ ማንጋጠጤን ወደ ሰማያዊው አምላኬ አድርጌው ቢሆን ኑሮ መና ይዘንብልኝ ነበር።

ሌላው ኤልሲን ቅስሟን ሰብሮ ያስቀራት ነገር ከእለታት ባንድ ቀን ያወደመችው ብር ነው። ይሄንን ነገር መቼም የምትረሳው አትመስልም።

ባለፈው ስልጠና ሄጂ ነበር። ከስልጠና ስመለስ "አምስት ሺህ ብር አጥፍቼ መጣሁ" አልኳት አልባሌ ቦታ ማጥፋቴን እያስታወስኩኝ።

"ውይ አንተ ደግሞ ብር ጠፊ አይደለ እንደ! እኔ አምና ባንድ ቀን ውስጥ አስር ሺህ ብር አመድ ማድረጌን አልነገርኩህም ለካ" አለችኝ።

"ምን አድርገሽ አጠፋሽው?" አልኳት እንደነገረችኝ እያስታወስኩ።


"በቃ በአምስት ሺህ ብር አስራ አራት ኢንች ቴሌቪዥን ከነ ዲሹ መግዛቴን

አስታውሳለሁ"

"ከዛስ?"

"ከዛማ ሶስት ግራም ወርቅ በሁለት ሺህ አምስት መቶ ብር ከመግዛቴ ውጭ፣ ሁለት ሺህ ሁለት መቶ ብር አካባቢ ባንክ ወስጄ አካውንቴ ላይ ጣል አድርጌያለሁ እንጂ፣ ሌላውን ብር ሌባ ይሰረቀኝ... መንገድ ላይ ልጣለው... መደሃኒያለም እሱ ይወቅ" ብላ ትከዝ አለች።

ኤልሲ አመድ አደረኩት የምትለውን አስር ሺህ ብር እንዴት ሁኖ እንደጠፋ እኔ ቀርቶ አዲተር እንኳን ቢመጣ የሚደርስበት ባይመስልም "አንቺ ደግሞ ከኔ የባሰ ብር አባካኝ ነሽ" በማለት አብሬ ተከዝኩ።



ሕይወት እንደ ሆሊዉድ ፊልም ፍትሃዊ እንደ ልብ-ወለድ ሚዛናዊ አይደለችም።
ሕይወት ከፍቅር እስከ መቃብር የባሰች ጨካኝ ናት። ስትበድልህና ስታስከፋህ በዋይታ እንጂ
እንደ ፊልሙ በዋሽንት አታጅብህም። ሕይወት የተጠናቀረ፣ ስርአት ያለዉ፣ በአግባቡ የተዋቀረ
ሴራ የላትም። በዛብህን ስትገድል ፊታዉራሪን ከፈረስ ላይ አትፈጠፍጥልህም።
ሕይወት ለበዳይ እንጂ ለተበዳይ አትወግንም። ተሸናፊዎች እየወደቁ ብልጦች ግን እየለመለሙ
ይሄዳሉ። በሕይወት ዉስጥ ሲበደል ኦሮ መጨረሻ ላይ በደሉን በድል የሚወጣ አክተር አይታይም።

***

አንደ እኔ አይነት የገጠር ልጅ ልጅነቱን የሚያስታዉስ አዕምሮ እንጂ ልጅነቱን የሚያስታውስ
ፎቶ የለውም። ምክንያቱም የተፈጠርኩበት አገር በወቅቱ ክርስትና እንጂ ፎቶ የሚያነሳ ሰው
አልነበረም። ለሚኒስትሪ እንኳን ፎቶ ለመነሳት ከሃምሳ ኪሎሜትር በላይ በእግር መጓዝን
ይጠይቀን ነበር።እንደዚያም ተጉዘህ እድለኛ ካልሆንክ የተነሳኸው ፎቶ "ተቃጠለ" ልትባል ትችላለህ።

ከመጽሐፉ የተወሰደ

አርሞንኤም ማተሚያ ቤት

ዋጋ ብር 50.60
15 USD